


t.me/OLDBOOKSPDF

## ውዱ አባታችን

የአባትነት ተምሳሌት፣ እጅግ ፍቅርህ የበዛ
ሳቅ ጨዋታህ ማራኪ፣ የአንደበትህ ለዛ
ምንም ብትለየንም፣ ብትቀርም እንደዋዛ
ዛሬም ሞገስ ክብራችን፣ የህይወታችን መአዛ!!

ያዳም ዘር ሆንክና፣ ረግፈህ ብትቀርም
ጥላ ባናገኝህ፣ ናፍቆትህ ቢያይልም
ብርቱ መንፈስህን፣ ጌታ አልነጠቀንም
ይኸው አብረኸ፣ አለህ አልተለየኸንም።



ለዚህ ላባታችን መኩሪያችን ለሆነው
ለንቁን ሙያ ወርዶ ሰው ላደረገን ሰው
ላካፈለን ፍቅሩ ለታላቅ ውለታው
ምንም ቢታገዝበት ትሁን መታሰቢያው።

መጽሐፉ ለውድ አባቴ ለሻለቃ ሞገስ ሰጌ መታሰቢያ ትሁንልኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ክፍል ፩

# ሴቺንቶ

## በአሜሪካ የአበሻ ታክሲ ነጂዎች እውነተኛ ገጠመኝ

ክፍል ፪

# የሩሲያ ቀልዶች

ከብርሃኔ ሞገስ ፅጌ

t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ 1

በዚች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ በአሜሪካን ከተሞች ታክሲ የሚነዱ የሀገራችን ልጆች በሥራ ላይ ያጋጠሟቸው አሳዛኝ፣ አስቂኝና አደገኛ የሆኑ እውነተኛ አጫጭር ታሪኮች ተቀምጠዋል:: መጽሐፏ በጣም መጠነኛ የሆነ ልበወለድነት ብትላበስም ባብዛኛው የታሪኮቿ እውነተኛነት ሃዲዱን ሳለመልቀቁ ቀዳሚ ትኩረት ሰጥታለች:: በውስጧ የያዘቻቸው አጫጭር እውነተኛ ፃጠመኞች በራሳቸው አንባቢውን በጉጉት እያስጋለቡ መጨረሻቸው ድረስ ያደርሱታል እንጂ ፀሃፊው አንዳንድ ለዛና ቀልዳቀልዶችን ከማካተት በስተቀር የአንባቢውን ልብ ለማንጠልጠል ሲል ዋነኛ ይዘታቸውን በሀሊና ፈጠር ታሪኮች አልበረዘም::

በተለይ የሀገር ቤት አንባቢው በታሪኮቹ ውስጥ ለሚጠቀሱ ቃላትና ሁኔታዎች ባዕድ እንዳይሆን «እዚህም እዚያም ስለታክሲ» የተሰኘ ከሀገር ቤት ታክሲ ጀምሮ ወደ ውጭው ዓለም የታክሲ ህይወት የሚያስገባ መንደርደሪያ ኮሪደር መጽሐፏ እንዲኖራት ተደርጓል::

በዚህም ኮሪደር ተዘልቆ ወደ ውስጥ በተገባ ቁጥር መጽሐፏ ታሪኮቿን በወሬነታቸው እያስነበበች የወገኖቻችንን የዕለት ተዕለት ኑሮ በማስቃኘት እግረ መንገዷንም የውጭውን ኗሪ እውነተኛ ህይወት ሹክ ትላለች::

ሀገር ቤት ያለው ህዝባችን ስለ ውጭው ዓለም ኑሮ ምቹነት ሳያየው እንደሚያምነው ሁሉ «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልንም እንደዛው አምኖ ቢከተል ኖሮ ሃገራችን የፃድቃኖች ደሴት በሆነች ነበርና በዚች መጽሐፍ ሹክታ የሰውን አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ ለመለወጥ የማይቻል ብቻ ሳይሆን የሚከጀልም አይደለም:: ይሁንና አንባቢው ያለውን የውጭ ህይወት ግንዛቤ በመጠኑም ቢሆን ማሳደግ እንደሚቻል ግን ይታመናል::

የሰው ልጅ የመኖሪያ ቦታውን ቀይሮ በሌላ ሃገር መኖር ሲጀምር ቋጥሮት በመጣው የሃገሩ ባህልና ወግ እንዲሁም ልማድና የአኗኗር ዘዬ አዲሱ መኖሪያውን መመዘን እንደማይችል መረዳት ብቻ ሳይሆን በፍጥነት ካለበት ሃገር ሁኔታ ጋር ራሱን ማላመድና ማዋሃድ እንዳለበት ካላበለዚያ ለስህተቱ የሚከፍለው ክፍያ አንዳንዴ የነፍስ ዋጋም ሊሆን እንደሚችል መፅሃፏ በተግባር



t.me/OLDBOOKSPDF

እያሳየች ለአዲስ መጪ ፍሪዎች በተለይም ለጀማሪ ታክሲ ነጂዎች ጠቃሚ ልምድ ታካፍላለች::

ታሪኮቹ በሙሉ በፀሃፊው አካባቢ የሚታወቁ ገጠመኞች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ቁንፅል ቢያደርጋቸውም በአብዛኛው የአሜሪካ ከተሞች የአበሻው ታክሲ ነጂ ህይወትና ገጠመኞች በእጅጉ የሚመሳሰል ስለሆነ ታሪኮቹ የሁሉንም የአሜሪካ ግዛት ህይወት ይዳስሳሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም::

መልካም ንባብ



t.me/OLDBOOKSPDF

# እዚህም እዚያም ስለ ታክሲ

መንገደኞችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በክፍያ ለሚያመላልሰው መኪና የተሰጠው «ታክሲ» የሚለው መጠሪያ አመጣጡ Taxoic ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም ጉዞ ማለት ነው።

በ1835 እ. ኤ. አ በእንግሊዝ ሀገር ጆሴፍ ሃንስም የተባለ ታዋቂ ግለሰብ የመጀመሪያውን «ታክሲ» ጋሪ አውጥቶ በመስራት በሂንክሊይ ከተማ እንዳሽከረከረ በታሪክነት ተዘግቧል።

ታክሲ አለም በስልጣኔ እየተመነደገች ስትሄድ በተለያየ ዓይነት እንስሳ የሚጎተቱ ጋሪዎችንና ሰረገላዎችን ተክቶ ለመምጣቱ አዲስ አበባችን ሳትቀር አንዷ ምስክር ናትና ማስረጃ ፍለጋ ባህር ማዶ መሻገር የለብንም።

በመዲናችን የጋሪን ግልጋሎት ቀስ በቀስ በመተካት በመጀመሪያ ብቅ ያሉት ታክሲዎች «ኩርኩር» በመባል የሚታወቁት ባለ 3 ጎማ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ መጠሪያቸውን ያገኙት ሞተራቸው ከሚያወጣው ድምጽ እንደሆነ ይገመታል።

ከዛም በመቀጠል ከእነዚህ «ኩርኩሮች» ላይ የዋና ከተማችንን መንገዶች የተረከቡት የጣሊያን ስሪት የሆኑት ፊያት 600 መኪናዎች ሲሆኑ «ሴቼንቶ» በመባል ይታወቃሉ። ይህንን ስያሜ ያገኙት ስድስት መቶ (በጣልያንኛ ሴቼንቶ) ከሚለው የሞዴል ቁጥራቸው ነው።

«ሴቼንቶ» የሚለው ቃል ከዛ በኋላ በታክሲነት ሊያገለግሉ ለመጡ ሌላ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ሳይቀር መጠሪያ በመሆን «ታክሲ» እንደማለት ሆኖ ለረዥም ጊዜ አገልግሏል። በመጨረሻ ግን ፊያት 600ዎቹን ሌሎች ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሀገር በብዛት እየገቡ ስለዋጧቸው «ሴቼንቶ» የሚለውም አጠራር በዛው መጠን እየደበዘዘ መጥቶ የብዙ አገር ስሪት የሆኑ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች «ታክሲ» በሚለው «አለምአቀፋዊ መጠሪያ» እየተጠሩ ግልጋሎት የሚሰጡበት ደረጃ ደረስን።

በሀገራችንና መኪና ማምረት በማይችሉ ሀገሮች የተለያዩ ሀገሮች የሰሯቸውን መኪናዎች በታክሲነት ይጠቀሙ እንጂ በስልጣኔ የቀደሙ ሀገሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

ታክሲ የሚያደርጉት ቤት ያፈራቸውን ተሽከርካሪዎች ነው:: አሜሪካ ውስጥ ፎርድና ሼቭሮሌት፣ ጃፓን ቶዮታ፣ ፈረንሳይ ሬኖልት ራሺያ ቮልጋ እንግሊዝ ብላክ ካብ ጀርመን ደግሞ በመላው ዓለም በቅንጦት የሚታወቁትን ቢ.ኤም.ደብልዩና መርሰዲስ መኪናዎች በብዛት በታክሲነት ትጠቀምባቸዋለች::

እነዚህ ያደጉ ሃገሮች የተሳፋሪዎችን ምቾት ለመጠበቅ፣ የሹፌሮችንም ስራ ለማቅለልና ደህንነታቸውንም ለመጠበቅ የቴክኒዎሎጂ ግኝታቸውን ታክሲ ላይ ያውላሉ::

ጃፓንን የተመለከትን እንደሆን በእያንዳንዱ ታክሲ ውስጥ «መንገድ መሪ» (Navigator) ስለተገጠመለት ሹፌሩ የሚሄድበትን መንገድ የግድ ማወቅ የለበትም::

ይሄ «መንገድ መሪ» መሳሪያ በትላልቅ ከተሞች ከአንድ ነጥብ ወደ ሌላ ነጥብ ለመድረስ የነበረውን አስቸጋሪነት በማቃለል መንገድ በመሳትና ባለማወቅ በሹፌሮችና በተሳፋሪዎች መካከል የሚፈጠረውን ጭቅጭቅ አስቀርቷል:: መሳሪያው በለንደን ውስጥ እያንዳንዱን ጉራንጉር መንገድ እንዲያውቁ ከ 2-3 ዓመት ሹፌሮች የሚያስለጥነው «የታክሲ ኮሌጅ» ለወደፊቱ ፋይዳ ቢስ እንደሚያደርገው መገመት አያዳግትም::

የጃፓን ሹፌሮች በአውቶማቲክ (ግብረ ርዕስ) የሚከፈትና የሚዘጋ በር ያላቸው ታክሲዎች ስለሚነዱ ከሌላው ዓለም ሹፌሮች ጋር ሲነፃፀሩ ደህንነታቸው የተጠበቀ ስራቸውም የቀለለ ነው:: በእኛ ሀገር የበር መክፈቻ እጀታቸውን ከደበቁበት መኪና ኪስ ውስጥ በማውጣት ለወጪ ገቢው ወገባቸው እስኪበጠስ እየተንጠራሩ በር ከሚከፍቱትና ከሚዘጉት አንዳንድ ታክሲ ሹፌሮች ጋርማ በምን ያነፃጸሯቸዋል?

በ21ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ኒውዮርክ ውስጥ አካለ ስንኩላን በእኩልነት የታክሲ ግልጋሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታክሲዎች በሙሉ ለተሽከርካሪ ወንበር (Wheel Chair) መጫኛ የሚሆን ተንሸራታች መወጣጫ እንዲኖራቸው በህግ ተደንግጎ ስራው በተግባር ተጀምሯል:: በአንፃሩ ኬንያ ናይሮቢ ውስጥ «ማታቱ» የሚባለው ታክሲ ደግሞ ተሳፋሪ ለማውረድም ሆነ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጫን ፍጥነቱን ከማብረድ በቀር ጨርሶ ስለማይቆም እንኳንስ ለአካለ ስንኩላን ቀርቶ ጤነኛውም ሰው ለመሳፈር መጠነኛ የአየር ወለድ ስልጠና ያስፈልገዋል::

በሰለጠነው ዓለም ትላልቅ ከተሞች ውስጥ የታክሲ ክፍያ የከተማው አስተዳደር ወይንም የታክሲ ኮሚሽን በሚያወጣው ደንብ መሠረት በኤሌክትሮኒክ ሂሳብ መቁጠሪያ ማሽን (ሜትር) ወይም በቀጠና (ዞን) አንዳንዴም ሜትርና ዞንን በማጣመር አሰራር ይከናወናል::

ለምሳሌ የኒውዮርኩ «ቢጫ ታክሲ» በርቀትና በጊዜ ፕሮግራም በተደረገ ሜትር ሲጠቀም ዋሽንግተን ዲሲ ከተማውን በ5 ዞን በመከፈል ከአንዱ ዞን ወደ ሌላው ዞን ለመሄድ በተወሰነው ታሪፍ መሠረት ክፍያ ይካሄዳል:: ፓሪስ ደግሞ ከተማዋን በ3 ቀለበታማ ዞን በመከፈልና በሜትሩ ላይ ለየዞኑ የተለያየ የአከፋፈል ዋጋ ፕሮግራም በማድረግ ክፍያ ይፈፀማል::

የክፍያ አፈፃፀሙ ላይ አንዳንድ ታክሲዎች ክሬዲት ካርድና ትራቭለርስ ቼክ ሲቀበሉ ጥሬ ገንዘብ የማይቀበል አንድም ታክሲ የለም::

የታክሲ ክፍያ እንደ ከተማው ሁኔታ የሚለያይ ሲሆን ልዩነቱም የየከተማውን የኑሮ ውድነት ማሳያ መስታወት ነው ማለት ይቻላል:: በአሁኑ ጊዜ በኑሮ ውድነት የመጀመሪያውን ስፍራ የያዘው የቶኪዮ ከተማ ታክሲ ውስጥ እግርዎ ከመግባቱ ሜትሩ 6.60 የን የመነሻ ሂሳብ ያሳይዎታል:: ይህም ክፍያ የጃፓኑን ታክሲ በውድነት በአለም ተወዳዳሪ የለሽ ያደርገዋል:: ፓሪስና ኒውዮርክ የመነሻ ሂሳባቸው $2.00 ሲሆን የኒውዮርኩ በየማይሉ 2 ዶላር ሲጨምር የፓሪሱ እንደዞኑ ከ62 ሳንቲም እስከ 1.24 ዶላር በኪሎ ሜትር ይቆጥራል:: አውሮፓ ውስጥ በዋጋው አነስተኛነት የሚጠቀሰው የግሪኩ (የአቴንስ) ታክሲ በ73 ሳንቲም ጀምሮ በየኪሎ ሜትሩ 23 ሳንቲም ይደምራል:: የለንደኑ ታክሲ በክፍያው ከውዶቹ ተርታ የሚመደብ ሲሆን ታክሲውን ከሥራ መስመሩ ሊያስወጣ የሚችል ማቆሸሽ ላደረገ ተሳፋሪ ሹፌሩ እስከ 40 ፓውንድ ተጨማሪ ለማስከፈል መብት ስላለው ከአቅምዎ በላይ ጠጥተው ከሆነ በቂ ገንዘብ ኪስዎ መኖሩን ማረጋገጥ ያሻዎታል::



t.me/OLDBOOKSPDF

በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ታክሲ በህዝብ ግልጋሎት ሰጪነት ከሚመደቡት የሥራ መስኮች ውስጥ ዋነኛው ከመሆኑም በላይ በቢሊየን የሚቆጠር ካፒታል የሚንቀሳቀስበት ራሱን የቻለ ግዙፍ ኢንዱስትሪ ነው።

ቱሪስቶችን፣ ለስራ የሚመጡትንና ኗሪዎቿን ጨምሮ 10 ሚሊየን ህዝብ የሚገኝባት ፓሪስ 15000 ታክሲዎችና 745 የታክሲ ተራ መጠበቂያና ማስሚሪያ ቦታዎች ሲኖሯት ከነዚህም የታክሲ ተራዎች ውስጥ 300 የሚሆኑት የስልክ ግልጋሎትም የሚሰጡ ናቸው። ለንደን ደግሞ የ20000 ታክሲ (ብላክ ካብ) መናኸሪያ ነች።

የታክሲ ሁኔታ ባብዛኛው ከተሞች ውስጥ ተመሳሳይነት ያለው ስለሆነ ለአብነት ያህል ኒውዮርክ ላይ ብናተኩር:-

ኒውዮርክ ውስጥ «ጆፕሲ» እና «ብላክ ካር» የሚባሉ ብዙ ሺህ ታክሲዎችን ሳይጨምር መንሃተን በተባለችው ደሴት (የኒውዮርክ ዋነኛ ክፍለ ከተማ) ብቻ ከ12000 በላይ ባለ ሜዳሊያ (የታክሲ መስሪያ ፈቃድ) የጫኑ ብጫ ታክሲዎች ሲተረማመሱ የእያንዳንዱ ሜዳሊያ ዋጋ ከ250000 ዶላር በላይ ነው።

ከእነዚህ 12000 ታክሲዎች ውስጥ ከ75% በላይ የሚሆኑት በተለያዩ ካምፓኒዎች በሹፌርነት የሚከራዩ ሲሆን ከ3 ዓመት ግልጋሎት በኋላ ከመንገድ ይገለሉና በአዳዲስ መኪናዎች ይተካሉ።

በግል ወይም በ2 ሰው በወረፋ የሚነዱ ታክሲዎች ግን መቀየር ያለባቸው በየ5 ዓመቱ ነው።

ኒውዮርክ ውስጥ በአሜሪካኑ ጀነራል ሞተርስ የመኪና ፋብሪካ ተሰርተው የሚወጡት አዳዲስ መኪናዎች በታክሲነት መንገድ ላይ ከመውጣታቸው በፊት ብዙ ለውጦችና ማስተካከሎች ይደረግላቸዋል። ከሚደረጉት ለውጦች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፣ ሜትር ይገባል፣ የሜዳሊያ ቁጥርና OFF-DUTY የሚል ፅሁፍ (ሹፌሩ ስራ ላይ ካልሆነ የሚያበራው) ጣራ ላይ ይገጠማል፣ ጥይት የማይበሳውና ገንዘብ መቀበያ ያለው የመስታወት ግድግዳ (Partition) አለበለዚያም የገባውን ተሳፋሪ በሞላ ፎቶግራፍ የሚያነሳ ድብቅ ካሜራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታክሲ ነጂዎች ታክሲውን ተከራይተው ለመንዳት የሚከፍሉት ክፍያ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በ12 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ከወጪ ቀሪ ለራሳቸው ገንዘብ ለመስራት ከትራፊክ መጨናነቁ ጋር ግብግብ ገጥመው በተገኘው ቀዳዳ እየተሹለከለኩ ለመንዳት ያልተቋረጠ ንቃትና ትኩረት ስለሚጠይቅ አይምሮን ይወጥራል::

ተሳፋሪው ሹፌሩን ጭንቀት ውስጥ የሚከትበት ጊዜም የበዛ ነው:: አይሮፕላንና ባቡር ሊያመልጠው የተቃረበው፣ ለስብሰባ የዘገየው፣ ስራ መግቢያው የደረሰበት፣ ለስራ ኢንተርቪው የቸኮለው፣ ልጁን ከትምህርት ቤት ማንሻ ሰዓት የደረሰበት ብቻ ሳይሆን እራት ለመብላት ሬስቶራንት የሚሄደው ሳይቀር «እባክህ በጣም ቸኩያለሁ ፍጠንልኝ!» ባይ ነው :: ሹፌሩም በጊዜው አድርሶ የተሻለ «ጉርሻ» ለማግኘት ሲል በራሱ ጥድፊያ ላይ የሌላውን ጥድፊያ ጨምሮ ይከንፋል:: እናም ይጨነቃል!:: አንዳንዴም እንደዛ ተጨንቆ ያደረሰው ተሳፋሪ ጉርሻ ቀርቶ የእግዜር ምስጋና ሳይሰጥ ተጣድፎ ውልቅ ይላል!:: ንዴቱ አይምሮው ላይ ጫና ያመጣል:: ሹፌሩ ተናዶ ሳይጨርስ ሌላው ተጣዳፊ ይገባል ሌላው ጥድፊያ ይቀጥላል!::

በዚህ ዓይነት 12000 ታክሲ በጥድፊያ ላይ ይሆንና ከተማዋ በጥድፊያ ትግላለች::

ከቢሮ ወደ ቢሮ ፖስታ ለማድረስ በመኪኖች መካከል የሚሽሎከለከውና ሲያሻው በእግረኛው መንገድ ላይ የሚበረው ብስክሌተኛ በበዛበት፣ በተንሸራታች ባለጎማ ጣውላ (Scater) ላይ የሚከንፈውና ሲደክመው የመኪና ጭራ ይዞ አብሮ የሚነጉደው ደብደኛ ተው በማይባልበት፣ አውቶቢሱ ፊትና ኋላ ተገጣጥሞ ሲበር የባቡር ፉርጎ በሚመስልበት፣ ፖሊስ፣ አምቡላንስና እሳት አደጋ ጩኸታቸውን እያቀለጡ በሚነጉዱበት፣ ከባድ መኪና ሸቀጥ በማውረድና በመጫን መንገድ በሚያጠብበት ወዘተ በዚህ 24 ሰዓት በሚቅበዘበዝ ከተማ ውስጥ 12 ሰዓት ሙሉ ታክሲ መንዳት እጅግ ጥንቃቄን የሚጠይቅና አይምሮ ላይ ጫናን የሚያሳድር ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ቋንቋውን በደንብ ያልተረዳው ሹፌር ገንዘቡን አውጥቶ ለማስረከብ ለሴኮንዶች በመዘግየቱ «የተበሳጨው ተሳፋሪ» ከጀርባው ላይ ያስደገፈውን ሽጉጥ ምላጭ በመሳብ ያቆስለዋል።

ሹፌሩም ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን ነፍሱንም ለመንጠቅ ከጀርባው ከተቀመጠው አውሬ ጋር ደሙ እየተንዠረዠረ ግብግብ ገጠመ። ይሄ ተመልካች የሌለው ትንቅንቅ ለደቂቃዎች ቀጥሎ ቁስለኛው ካቆሰለው እጅ ላይ ሽጉጡን በመንጠቅ የኃይል የበላይነት ብቻ ሳይሆን በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመግደል መብትም ጭምር በእጁ ገባች!

የሰውን ሕይወት ለማጥፋት ደንታም ያልነበረው ነፍሰገዳይ «እባክህ! ... እባክህ! አትግደለኝ» እያለ ለነፍሱ መማፀን ጀመረ። የቆሰለው ሹፌር ምርኮኛው እንዳይንቀሳቀስ ወንበር ላይ አንጋልሎ፣ በአንድ በኩል ደሙን ለማቆም እየታገለ ወደ ካምፓኒው የሬድዮ ጥሪ አድርጎ በተንተባተበ ቋንቋ እርዳታን ጠራ። ካምፓኒው ከ911 (የአደጋ ጊዜ ኦፕሬተር) ጋር መስመሩን አገናኘው ህይወቱ በአደጋ ላይ ሆና እንኳ ሰብአዊነቱ ያልተለወጠው ሹፌር ደሙ እየፈሰሰ ስለመሆኑና ፖሊስ ቶሎ ካልደረሰለት ህሊናውን ሊስት ስለሚችል ጨካኙ ተሳፋሪ ተመልሶ ሽጉጡን በማግኘት ከመግደሉ በፊት ሊገለው እንደሚገደድ አሳወቀ።

ያ ገንዘብና ህይወት ለመንጠቅ ሲደነፋና ሲተኩስ የነበረ አንበሳ ሱሬው ረጠበ። በወንጀለኛነቱ ሲሸሻቸው የነበረው ፖሊሶች በአስቸኳይ እንዲደርሱለት በልቡ መማፀኑን ከአትግደለኝ ውትወታው ማወቅ አያዳግትም።

አሁን የሹፌሩ የደም አፈሳሰስ ፍጥነትና የፖሊሶች የመድረስ ፍጥነት እሽቅድምድም ይዘዋል። የሚቀድመው የሹፌሩ ደም ከሆነ ሁለት ነፍስ ይጠፋል። ፖሊስና አምቡላንስ ከቀደመ ሁለት ነፍስ ይድናል። የዛም አውሬ ነፍስ ከሰው ነፍስ ከተቆጠረ።

.... የአምቡላንስና የፖሊስ ሳይረን መስማት ሲጀምር ሹፌሩ ብርታቱ በተስፋ ታደሰለት። የኒውዮርክ ፖሊስ ከነ አምቡላሱ እንደደረሰ ምርኮኛውን አስረከቦ አምቡላንስ ውስጥ ተንጋለለ። ታሪኩ በብዙኀን መገናኛ ተናኘ ። ሹፌሩ



t.me/OLDBOOKSPDF

## NEW YORK/ MANHATTAN







t.me/OLDBOOKSPDF




t.me/OLDBOOKSPDF



t.me/OLDBOOKSPDF

# ጉትሻ

ስርዝ ድልዝ የሌለው አራዳ ነው፡፡ 100!

ጠቆር፣ ጉርድርድ ያለው መልኩና አጠር፣ ደንደን ያለው ሰውነቱ «ጉትሻ!» የሚባል ቅፅል ስም አሰጥቶታል፡፡

እምላክ ለመልኩ ማካካሻ ነው መሰል ቀልድና ጨዋታ አድሎታል፡፡ ለዛ ያለው ጨዋታው ያፈዛል፡፡ ቀልዱ ጥርስ የማያስከድን እንባ እስጨራሽ! ከመሆኑ የተነሳ እናቱ ሞታ ሃዘን የተቀመጠን ሰው ሳይቀር በሳቅ ሊያንከተክት የሚያስችል ድንቅ ችሎታ ነው ፈጣሪ ያሸከመው ፡፡ ለጉትሻ !

ፍጥረት ሁሉ ነፍሱን ይወዳታል ቢባል እንኳን የሱ ፍጹም የተለየ ነው፡፡ በተፈጥሮው ሲበዛ ጠርጣሪ ቆቅ!

ሰው በተጣባበትና በተረበሸ አካባቢ ካጠገባችሁ እንደ ምትሃት ቢሰወር አትጨነቁ! እሱ ሰላም ቦታ ነው ያለው፡፡ ለምስክርነትም አትፈልጉት በዛን ግዜ አይኑም የሚያየው ሆነ አይምሮው የሚያሰላስለው ስለ ማምለጫው ነውና፡፡

ቆቅየው ሃገር ቤት እያለ «ብሄራዊ ውትድርና » ሊከቱት ያዘጋጁለትን መረብ በራሱው ዘዴና ጥበብ ሲያመልጥ ቆይቶ በመጨረሻም በቀድሞው ሶቭየት ህብረት ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝቶ አገሩን ለቀቀ፡፡ ከዛም በሶስት አመቱ ትምህርቱን አቋርጦ በጀርመን በኩል ክልጅነቱ ጀምሮ የራዕይ ግቡ ለነበረችው ለአሜሪካ በቃ፡፡ ከዛስ?

ከዛ በኋላ በአሜሪካ የገጠመውን ህይወት እንደዚህ ጨልፎ ያቃምሰናል ፡-

ዋሽንግተን የተቀበሉኝ ጓደኞቼ ዙሪያዋን ካስጎበኙኝ በኋላ «እጹብ ድንቅ!» ብዬ የተደላደለ ኑሮዬን ለመመስረት ቸኮልኩ፡፡

ጓደኞቼ ምን አይነት ስራ እንደሚሰሩ የማቀው ነገር አልነበረም፡፡ ብቻ ሁሉም ጥሩ ይለብሳሉ፣ ጥሩ መኪና ይነዳሉ፡፡ ቤታቸውም ሁሉነገሩ የተሟላ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በፖሊስና በኋላም በጓደኞቼ እዚህ አገር ወንጀለኞቹ የሚሉኝን መፈፀም እንዳለብኝና ያለበለዚያ ራሴንና አከባቢዬ ያሉትን ሰዎች ህይወት አደጋ ላይ እንደምጥል ሌላ ሌላም ተነገረኝ:: ይህንን ስሰማ ሰደፍ ያቀመሰኝን ሰው ስለ ርህራሄው አመሰገንኩ! በጥይት ስላላነደደኝ! ::

ስራዬን በነጋታው ቀጠልኩ:: ዘራፊዎቹ በሳምንትም ይሁን በሁለት ሳምንት አለዛም በወር አርብ ቀን ብቅ እያሉ እንደጎበኙን ነው:: እኔም ተላመድኳቸው መሰል አርብ በመጣ ቁጥር ይናፍቁኝ ጀመር::

የአርብ ደምበኞቻችን ገና ብቅ ሲሉ የሂሳብ መኪናውን ተረክ አርጌ ከፍቼ ልክ «ለታወቀ መፅሃፍ አንባቢ » እንደቆመ ሃውልት ፊቴን በጋዜጣ ሸፍኜ እቆይና «ጉብኝታቸውን» ሲጨርሱ «ቀጥል ተረኛ!» ብዬ መሸጥ እጀምራለሁ:: በዚህ ቀልጣፋ ትብብሬ እነሱም ሳይደሰቱ የቀሩ አይመስለኝም::

ዝርፊያው ሲደጋገም አርብ ቀን እረፍቱ የሆነ አብሮን የሚሰራ ነጭ አሜሪካዊ «እናንተ ስደተኞች እንደሆናችሁና እንደፈራችሁ አውቀውባችሁ ነው፣ ለዚህ ነው በኔ እረፍት ቀን የሚመጡት፤ እኔ ብኖር አሳያቸው ነበር! » ብሎ ይፎክራል:: ፉከራውንም በተግባር ለማሳየት አርብን ለመስራት ቀን የሚቀይረው ሲጠይቅ ፈጥኜ ስለለመንኩት እየሳቀብኝ ቀየረኝ:: አርብ እለትን ከስራ ቀረሁ:: «አርብአውያን» ግን አልቀሩም መጡ!::

የስራ ባልደረባችንም እንዝራግራሁ ብሎ የኔን ሰደፍ አቀማምሰውት በረዶ ቤት(ክፍል) ቆልፈውበት ሄዱ:: ቁልፉም እኔ ጋር ስለነበር ባሳር ተፈልጌ ተገኘሁና ከሰአታት በኋላ ተከፍቶለት ሲወጣ ነጭ ይሁን ጥቁር መለየት በሚቸግርበት ሁኔታ የጠወለገ ጎመን መስሎ ወጣ :: «ፈረንጁን የአበሻ ጎመን ያስመሰለው በረዶ ቤት እኔን አበሻውን ቢያገኝኝ ምን ሊያስመስለኝ ነበር?» ብዬ አሰብኩና በጭንቅላቴ «እንደውም እንደው ነህ አሻሮ ያስመስልህ ነበራ!» የሚል መልስ ሲመጣብኝ እንደሞኝ ሳቄን ለቀቅኩት::

ያም ሆነ ይህ የዛች ዕለት ፖሊሶቹና ጓደኞቼ የነገሩኝን ምክር በተግባር አየኋት:: አሜሪካ ውስጥ በዘዴና በጥንቃቄ መኖር እንዳለብኝ በፍጥነት ተማርኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይቅርታ ጌታዬ!  ልጆቼን ከትምህርት ቤት በማንሳት ዶክተር ጋር ስለምወስድ እዛ ድረስ ለመሄድ ጊዜ የለኝም »

«ስማ! ሹፌር ብትወስደኝ ይሻልሃል!»

«ጌታዬ! ነገርኩህ እኮ ጊዜ የለኝም»

ሰውነቱ ይበልጥ አበጠ:: አተነፋፈሱ ተቀየረ:: ከመኪና ውስጥ ጎትቶ አውጥቶኝ ነጭ ካኒቴራው ላይ ስዕል እንዳያደርገኝ ስለፈራሁ በሬን ከፍቼ ልሮጥ ዝግጁ ሆኛለሁ::

መኪናዬ መንገድ ዘግቶ ስለቆመ ጡሩንባው ተንጣጣ:: ወደፊት እንቀሳቅሼ ጥግ ላይ አቆምኩና በልመና መልክ « ጌታዬ! እመነኝ ጊዜ ስለሌለኝ ብቻ ነው አልሄድም ያልኩህ:: እባክህ ውረድልኝ » አልኩት::

«ጉዳዬ አይደለም! ይልቅ በራስህ ላይ ...ችግር ሳታመጣ ብታደርሰኝ ይሻልሃል! እናንተ ... መጤዎች ጥቁር መጫን አትፈልጉም ይሄን ...ፊልም ድሮ ነው የማቀው! እኔጋ አይሰራም!» እያለ እያንዳንዷን ቃል በፀያፍ ስድብ እያጀበ አወረደብኝ::

ሲደነፋ የስለት ሻማ የሚያክለውን «እመልካች ጣቱን» አፍንጫዬ ስር እያደረሰ ይመልሰዋል::

አምላክ ለመተንፈሻ ያህል የለጠፈልኝን አፍንጫዬን በድጅና እጁ ከፊቱ ጋር ሊሾ ሲያረገው ታየኝ::

ደግነቱ ሁኔታችንን ያስተዋለ ፖሊስ ደርሶ «እዚህ ምን እየተካሄደ ነው?» ብሎ ሲጠይቅ ተረጋጋሁ::

ሰውየው ቀድሞ አስረዳ:: ድንፋታው ጠፍቶ አነጋገሩ ተቀይሮ ትልቅ ሴት ወይዘሮ መሰለ::

እኔም በተራዬ «ልጆቼ የዶክተር ቀጠሮ ስላለባቸው ከትምህርት ቤት ለማምጣት  መሄድ ስላሰብኩ ጊዜ የለኝም» በማለት ምክንያቴን አቀረብኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ለካስ ፖሊሱ የዋዛ አልነበረም «የትኛው ትምህርት ቤት?» «የት ነው የሚገኘው?» ብሎ ጥያቄ አከታተለብኝ::

ጉድ ፈላ! ዝም ብዬ «ትምህርት ቤቱ የሚገኘው ሲልቨር ስፕሪንግ ነው» አልኩት የምኖርበትን አካባቢ በመጥራት::

ፖሊሱም «እውነትክን ነው? እኔም እዛው ነው የምኖረው የትኛው ትምህርት ቤት ነው ልጆችህ የሚሄዱት?» አለኝ:: ካገራረሙ እውነቱን እንደሆነ ያስታውቃል:: አጋጣሚው ገረመኝ::

ፖሊሱ የሲልቨር ስፕሪንግ ኗሪ ባይሆን ኖሮ ሃገሬ የማቀውን የፈረንጅ ስም ያለውን «ሴንት ጆሴፍ ትምህርት ቤት» ልጠራለት ተዘጋጅቼ ነበር:: አሁን ግን ያውቅብኛል ብዬ ሃሳቤን ቀየርኩና «ብቅርብ ስለሆነ እዛ ሰፈር የገባሁት ስሙ በደንብ አልተያዘልኝም» ብዬ ምንም የማላወቅ ለመምሰል ድሮ የምሰባብረውን እንግሊዝኛ አውቄ ይበልጥ አነካክተው ገባሁ:: የባጥ የቋጡን ለፈለፍኩ::

አጅሬ ነቅቶብኛል! «ተሳፋሪ ታክሲህ ውስጥ ከገባ በኋላ አልወስድም ማለት አትችልምና ሰውየውን አድርሰው» አለኝ::

እኔም መከራከር ልጀምር ስል «ጨርሻለሁ! ምርጫህ ሁለት ነው ተሳፋሪውን መውሰድ ወይም ቲኬትህን... !» ብሎ ቁርጥ ያለውን ነገረኝ::

«እኬ» ብዬ ልሄድ ካልኩ ወዲያ ሳስበው ይሄ ሰውዬ ከዚህ ሁሉ ፀብ በኋላ ባይዘርፈኝ እንኳ እንደማይከፍለኝ፣ እዛም ነፍስ በላ ሰፈር ገብቼ መውጣት ለአደጋ እንደሚያጋልጠኝ፣ በህልሜ ያየሁትም ነገር ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ገመትኩና ሊሄድ የተዘጋጀውን ፖሊስ ጠርቼ፣

« ኦፊሰር ! ስንት ብር ነው የቲኬቱ መቀጮ?» ብዬ ጠየቅኩት

«150» አለኝ ጠበቅ አርጎ

«ታዲያ ጉቲሻ! ነፍሴን በ150 ብር ቢገዛት አይሻልም እንዴ?» አልኩና

«አልሄድም! ቲኬቱን ስጠኝ!» አልኩት



t.me/OLDBOOKSPDF

«እርግጠኛ ነህ? አለ ፖሊሱ ተገርሞ

«አዎ!» አልኩ አስረግጬ

ምርጫ ያጣው ፖሊስ ቲኬቱን እየፃፈ ለተሳፋሪው «ጌታዬ! ላንተ ሌላ ታክሲ አገኝልሃለሁ ውረድ» አለው::

«ታዋቂ ስድባቸውን» መርቆልኝ ለመውጣት ሲታገል እኔም በአማርኛ:- «ሂድ ውጣ ጉማሬ!» ብዬ በስድብ ሸኘሁት::

ፖሊሱ ቲኬቱን ከሰጠኝ በኋላ ከአይታው እስከርቅ አንድ ሁለት መንገድ አጠፍ አጠፍ ብዬ ሽቀላዬን ጀመርኩ::

የቲኬቷን 150 ብር ለማግኘት ተጨማሪ ሰዓት አምሽቼ ለመስራት ወስኜ ስሰራ አመሸሁ::

ከምሽቱ 5 ሰዓት አካባቢ ሁለት የስፓኒሽ ዝርያ ያላቸው ውርጋጦች ሁለቱን በር በአንድ ጊዜ በርግደው ገብተው «ኬፓሳ!» አሉኝ:: «ወዴት ነው?» ጠየቅኩ::

«ሳውዝ ኢስት» ሲሉኝ «የባሰው መጣ!» ብዬ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳስብ «መብራቱ አረንጓዴ ነው እንሂድ!» አለኝ አንደኛው:: ምርጫ የለም ካለዛ ሌላ ቲኬት ማግኘት ሊመጣ ነው:: ዝም ብዬ መንዳቴን ቀጠልኩ::

እራሱ ገጠመኙ «የዚህ አገሩ ኑሮ ተሸሽቶ የሚዘለቅ አይደለም» አለኝ :: ተቀበልኩት! ::

የጫንኳቸው ሰዎች የሚሄዱበት አካባቢ ወንጀል የሚበዛበት ነው:: እንዳውም «የወንጀል ማዕከል» ቢባል ይቀላል:: ግዛቱ የአደንዛዥ እጽና ንጥረ ነገሮች ሻጮቹ ከመሆኑም በላይ በቀጠና ድንበርና በጥቅም ተጋጭተው በጥይት ሲታኮሱ በተባራሪ ጥይት የመመታት ዕድሉ ከፍተኛ ነው::

በዛ አካባቢ የሚታዩ የጉርምስና ዕድሜያቸው ጠላት የሆናቸው ለጋ ወጣቶች የማይሆን አደገኛ ህይወት ውስጥ ገብተው የሚያደርጉት ሁሉ በአጉል ጀብድ የተሞላ ነው:: ገንዘብ አስከሯቸዋል! የሚያስቡት ሆነ የሚናገሩት



t.me/OLDBOOKSPDF

በሽጉጣቸው ነው:: በተለይ በዛን ግዜ ፖሊስ በአካባቢው በብዛት ስለማይደርስ ሰዎቹ ህግ አይገዛቸውም:: በአጠቃላይ አካባቢው በ«ጋንጎች» ቁጥጥር ስር ነው:: የአዲስ አበባውን «አሪ በከንቱ» ከዚህ አካበቢ ጋር ካወዳደሩ ስሙ ተቀይሮ «ሰላም ሰፈር» መባል ነው ያለበት::

ከጥቂት ወራት በፊት እዚችው ታክሲዬ ውስጥ እያዳመጥኩት በነበረው «ኤን.ፒ.አር.» ሬዲዮ ጣቢያ ላይ የተላለፈው የዚህ አካባቢ የወንጀል ዜና ታወሰኝ:: አዎ! ከዛን ጊዜ ጀምሮ የዚህ አደገኛ ሰፈር ስም በተነሳ ቁጥር ቀድሞ የሚታወሰኝ ነገር ያ ዜና ነው :-

«አንዱን ሰጋ ወጣት ከአደንዛዥ ዕፅ ጋር በተያያዘ ፀብ በጠራራ ፀሃይ ጥይት አርከፍክፈውበት ይሄዳሉ:: አምቡላንስ መጥቶ የተመታውን ሰው አንስቶ ወደ ሆስፒታል ሲበር፣ ገድለነዋል ብለው የሄዱት ጋንጎች አካባቢው ከነበሩ አባሎቻቸው አለመሞቱ ስለተላለፈላቸው እንደገና አምቡላንሱን አስገድደው በማስቆም ሰውየውን ጨርሰውት አመለጡ »

እንግዲህ ይለይለት ብዬ በመሄድ ላይ ያለሁት ወደ እንደዚህ አይነቱ ሰፈር ነው:: ከጀርባዬ የተቀመጡትም የአንዱ ጋንግ ቡድን አባል ሲሆኑ እንደሚችሉ ተጠራጥሬያለሁ:: ስለዚህም ጆሮዬ «የናሳ» አንቴና ሆኗል::

ጎረምሶቹ የሚያወሩት ስለ ሴት ጓደኞቻቸውና ስላሳለፉት ምሽት ነው:: ጥሩ መንፈስ ላይ ነው ያሉት:: ሬዲዮኔን የሚፈልጉት ጣቢያ ላይ እንድቀይርላቸው ካዘዙኝ በኋላ ከእኔ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም:: ከትንሿ ልምዴና ከሰማሁት የሌሎች ገጠመኞች ስመዝነው ይሄ ጥሩ ምልክት እንደሆነ ገምቻለሁ::

ሊዘርፍ የመጣ እራሱ የተረበሸ ነው፣.... ስለ ሹፌሩ ለማወቅ ይጣደፋል ስለዚህም እንደብዙዎቹ ተሳፋሪዎች ጥያቄው « እዚህ ሃገር ከመጣህ ቆየህ ? ..ወደድከው?» አይነት ሳይሆን ቀጥታ «ለምን ያህል ጊዜ ነዳህ?» ነው :: የሹፌሩን ልምድ ለመገምገም::... ብር ይዞ እንደሆነም ለማወቅ ስራ እንዴት ነው? ወይም አካባቢው ከደረሰ በኋላ 100 ብር ነው የያዝኩት መልስ ይኖርሃል?



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዘተ አይነት ጥያቄዎች እንደሚያበዛና አንድ ቦታ አርፎ እንደማይቀመጥ ከነባር ታክሲ ነጂዎች ተነግሮኛል:: ወዘተ ...

እነዚህን ምልክቶች ስላላየሁ መንዳቴን ቀጥያለሁ ::

ያንን አረመኔ ሰፈር በፍጥነት እየሰነጠቅኩ በመሄድ ላይ ነኝ:: የፈራረሱና መስኮታቸው በጣውላ የተለበደ ወና ህንፃዎች ሰው ከሚኖርባቸው ይበዛሉ::

መንገድ ላይ ጤነኛ የሚመስል የሰው ዘር አይታይም:: በየመንገዱ ማዕዘን ላይ ሁለት፣ ሦስትና አራት እየሆኑ ቢራ የሚጠጡና ሲጋራና ዕፅ እየተቀባበሉ የሚምጉ ወጣቶች ብቻ ናቸው የሚታዩት::

በመንገድ ጠርዝ ላይ ካሉት መደብሮችና ከቆሙት መኪናዎች ፤ ሙዚቃው ሲደልቅ የአካባቢው ህይወት የሚላወሰው ማታ ማታ እንደሆነ ያስተውቃል::

በሌላው የከተማ አካባቢ በየማዕዘኑ የማይጠፋው የፖሊስ መኪና እዚህ ለወሬ ነጋሪ አይታይም ::

አለፍ አለፍ ብለው የቆሙት የተቃጠሉ መኪኖች የአካባቢውን አደገኛነት በእማኝነት እንዲመሰክሩ ሆን ተብለው የተተዉ ይመስላሉ::

ልክ ተሳፋሪዎቼ ውሰደኝ ያሉበት መንገድ ላይ ደርሼ ፍጥነቴን መቀነስ ስጀምር «ዋትስ አፕ ኒግር» አሉኝ::

ጭጭ አልኳቸው:: ያስመረጋጋቴን አውቀዋል:: «አይዞህ አትፍራ! ካንተ የምንፈልገው ግልጋሎትህን ብቻ ነው» ካሉኝ በኋላ የሚቀጥለው መጋጠሚያ መንገድ ላይ ወደ ቀኝ ታጥፌ እንድቆም አዘዙኝ:: ማዕዘኑ ጋር እንደደረስኩ መንገዱ «ሙት መንገድ እንዳልሆነ» (መውጫ እንዳለው) ወደ ቀኝ ተመልክቼ ካረጋገጥኩ በኋላ ታጥፌ አቆምኩ::

« እንመለሳለን » ብለው እንደአገባባቸው በሁለቱም በር ውልቅ ብለው እየነጠሩ ወደ አሮጌው ህንፃ ገቡ:: ሳይከፍሉ::



t.me/OLDBOOKSPDF

በሬን ቆልፌ ተፈተለኩ! የመንገድ መጋጠሚያዎችን ግራና ቀኝ እያየሁ ነፃ ከሆኑ ቀይ መብራት ሳይቀር እየጣስኩ ያን ሰፈር ለቅቄ ወጣሁ::

ህግና ስርዓት ያለው ክልል ከመግባቴ ለበራው የትራፊክ ቀይ መብራት አቆምኩ:: በተቃራኒው አቅጣጫ ሌላ አበሻ ታክሲ ነጂ ሁለት ጥቁር አሜሪካውያን ጭኖ እንደኔው ወደ ነፍስ በላው ሰፈር እየሄደ መብራት አቁሞት አየሁ::

መሪውን በሁለት እጁ ጭምድድ አድርጎታል:: አይደለም መጨምደድ በሁለት እጁ መሪ የሚይዝ ታክሲ ነጂ እናንተ ታውቃላችሁ! በዚህ አጨማመዱ አደገኛው ሰፈር ውስጥ ገብቶ መሪው ተነቅሎ እጁ ላይ እናዳይቀር ፈራሁለት :: ሰውየው በጭንቀት ከፊቱ የሚታለበውን ላብ በትከሻው ነው የሚያብሰው:: መሪውን እንዳይለቅ ::

የሚያረገውን ሁሉ ስከታተል መጨረሻ ላይ እሱም አየኝ! እየደጋገመ በአንገት ሰላም አባባሉ «ብቃ የምመለስ አይመስለኝም ደህና ሁን! » የሚል ይመስላል::

መስታወቴን ዝቅ አድርጌ «የኔ ወንድም! ወላዲት አምላክ ትከተልህ!» አልኩት:: ጮክ ብዬ:: ተሟሙቶ ፈገግ አለና ወደፊት ቀጠለ!

እኔም የእለት ፋይሌን ልዘጋ የቤቴን መንገድ ጀመርኩት::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ስከራሙ ተሳፋሪ

የኖርዝ ካሮላይና ስቴት የኢኮኖሚ እምብርት በሆነችው ሻርለት ከተማ ውስጥ ጋን ጭኜ እየሄድኩ ነው:: ያውም ከአፍ እስከ ገደፉ የሞላ የሰው ጋን!::

የዛን ጊዜ ታክሲዬ ውስጥ ገብታችሁ ቢሆን ገደል ግቡ ጠጅ ቤትን ያስጥርጥር ታስታውሳላችሁ:: ደግነቱ አገሩ አሜሪካ ሆኖ ነው እንጂ መኪናዩ በንብ ተከቦ ሳልነደፍ እቀር ብላችሁ ነው?

«የቸገረው እርጉዝ ያገባል» እንዲሉ ስራ የጠፋበት ቀን ሆነና የ60 ዶላር መንገድ እንድወስደው የጠየቀኝን ስከራም ሰው «እልጭንም» ማለቱ አቃተኝ::

«ስካራም እኮ ጥሩ ጉርሻ ይሰጣል፣ አንዳንዴ ኪሱ ውስጥ ያለውን የብር ኖት በሙሉ እንደ አንድ አንድ ብር አርጎ እየቆጠረ ትላልቅ ኖቶች ሁሉ ቀላቅሎ ይሰጣል» ብዬ እራሴን በራሴ ሸንገልኩ:: አዎ ገንዘቡ አንጉቶኝ ጫኝኩት::

ገና ሰውዬው ታክሲዬ ውስጥ ከመግባቱ የውስጡ አየር በሰኮንድ ውስጥ ተበከለ:: ሳምንቱን በሙሉ ሲገሸር ክርሞ አለዚያም በርሜል ውስጥ ከነልብሱ ተነክሮ ካልሆነ ሰው የተወሰነ ሰዓት ጠትቶ እንደዚህ መሽተቱ ለማመን የሚከብድ ነው::

ሰውየው የመጠጡ ክርፋት አነሰህ ብሎ ያለምንም ጥያቄ ሲጋራውን ለኮሰና የባጥ የቆጡን ማውራቱን ጀመረ:: ደግነቱ እኔም አጫሽ ነኝ:: መለፍለፉን ወድጄዋለሁ::

ስካራሞች ታክሲ ውስጥ ገብተው እንቅልፍ ሲወስዳቸው ነው መጥፎ:: በተለይ መድረሻቸውን በትክክል ሹፌሩ ካላወቀው አካባቢው ካደረሳቸው በኋላ የግድ እነሱ መምራት ስላለባቸው ስካራሞች ከተኙ መከራ ነው::

እነሱን ከእንቅልፍ ከማስነሳት ቀዶ ጥገና ለማድረግ ሙሉ ማደንዘዣ (አኒስቴዢያ) የወሰደን ሰው ያለ ጊዜው ማንቃት ይቀላል:: ስለዚህም ነው ልምዱ ያለው ሹፌር በአይኑ እየተቆጣጠረ ስካራም መንገደኛ አይኑን መክደን ሲጀምር



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋርም እየተሳጋ ለፖሊስ ካቴና ደምበኛ የሆነ፣ እሱነቱ የወላጅን ፍቅር ሳይቀር ሰልስሎ የሚበጥስ መጋዝ ሆኖባቸው እናቱ ፊታቸውን ያዞሩበት ግሬ የተጋባ ፍጡር አድርጌ ስላየሁት አሳዘነኝ::

መድረሻችን አካባቢ እየተቃረብን ጓ..ጓ የሚል የጥይት ድምፅ ሰማሁ:: ጆሮዬም መሰለኝ:: ከፊታችን በግምት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው መስቀልኛ መንገድ ላይ መኪኖች ቆመው ከሩቅ ስላየሁኝ ፍጥነቴን አቀዘቀዝኩና አቆምኩ:: ከኋላዬ የሚመጡትም ተሽከርካሪዎች እንደኔው አቆሙ:: ተኩሱ ቀጠለ::

ተሳፋሪዬም «ምንድነው ነገሩ የምን ተኩስ ነው?» ብሎ ለማየት ማንጋጠጥ ጀመረ:: የሆነ ፀጉሩን ሹሩባ የተሰራ አረንጓዴ ቱታ ከነጭ ስኒከር ጫማ ጋር ያደረገ ጥቁር ወጣት በቆሙት መኪኖች መካከል እየተዘዋወረ መትረየስ ይተኩሳል::

ፊልም እየተሰራም መሰለኝና ዙሪያውን ብቃኝ ነፍሱን ለማዳን ከሚፈረጥጥ መንገደኛ በስተቀር አንድም ካሜራ አይታይም::

በእኛና በተኳሹ መካከል የሰስት መኪና ርቀት ነው ያለው:: መስቀለኛው መንገድ ላይ ትራፊኩ እርስ በርስ በመተሳሰሩ ሰው ሁሉ መንዳት አልቻለምና መኪናው ውስጥ ተሸሸገ::

ተረረረረ... ተኩሱ ቀጠለ:: እኔም ወንበሬ ስር ገባሁ:: ሰካራሙ ተሳፋሪዬ ግን አንገቱን ለንፋስ ብዬ በከፈትኩት መስኮት አውጥቶ «አንተ ኒግር! መሳሪያህን አስቀምጥ!» እያለ ወደ ተኳሹ ይጮህ ጀመር:: የምሆነውን አጣሁ! ጭራሽ የመስኮቱ አልበቃ ብሎት በሩን በግማሽ ከፍቶ አንገቱን አውጥቶ «ኒግር ሄይ ኒገር! መሳሪያህን አስቀምጥ ነው የምልህ» እያለ መደንፋቱን ቀጠለ::

ሰውዬ ««እብድ ነህ ወይ? ታስጨርሰናለህ! ወደ ውስጥ ግባ! » ብዬ ከኋላው ጎተትኩት::



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደጉድ አፈጠጠብኝና «ዝም በል! አንተ ራስህ የሱ ቢጤ ኒገር ነህ!» ብሎ ገፈተረኝ::

ሲያቀብጠኝ የጫንኩት ስካራም በጥይት ሊያስነድፈኝ ነው ብዬ ጭንቅላቴን በእጄ ይገፍ እንደ ሰጎን በአፍጢሜ ተደበቅኩ::

ስካራሙ ይሳደባል:: ጥይት ተረረረ ይላል በቃ! «ይሄኔ ስከራሙን አይቶት ወደእኛ እየተኮሰ ነው» አልኩ:: ጥይት ሰውነቴን እንዳይበሳው እከላከለው ይመስል ሰውነቴን አጠነከርኩ::

መድኃኒያለምን እንደዛች ቀን ቀርቤውም አላውቅ:: ሀጢያቴን ይቅር በለኝ አልኩ ወደዛችኛዋ አለም ከመሸጋገሬ በፊት:: « ኒግር!» .... ተረረረ ... «ኒግር!» .....« አትሰማም ወይ? ኒግር!»... ጊዜው ረዘመብኝ:: ሰው ሲደነግጥ ያልበዋል ነው የሚባል? የኔ ግን አመዴ ወጥቶ «ወፍጮ አስፈጪ» መሰልኩ::

ጥይቱ ጋብ አለና ወዲያው ፀጥ አለ:: የኔው አንበሳ ግን ማጓራቱን ቀጥሏል «በዚህ አቅጣጫ ነው ኒገሩ የሄደው!» እያለ::

ወዲያው የእሱም ድምፅ በፖሊሶች መኪና ሳይረን ተዋጠ:: ተሳፋሪዬ «መጡ እነዚህ እንትኖች...» አለና ወደ ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ:: የሳይረኑ መሰማት የልቤን ሩጫ አበረደውና ከምሽጌ ወጥቼ ወደፊት ስመለከት ፖሊሶች በየአቅጣጫው ይሯሯጣሉ:: ብዙም ሳንቆይ ግማሾቹ ፖሊሶች ተሳስሮ የተቀመጠውን ትራፊክ ማስተናገድ ጀመሩ:: ዙሪያው በሰው ስለተከበበ በተፈጠረው ትርምስ ወደፊት ለመንቀሳቀስ ጊዜ ወሰደብን::

የኔው ተሳፋሪ «ምን ሆንኩ ባይ ነው? ይሄ ኒገር» ብሎ አንዱን መንገደኛ ጠየቀው :: «እኔ እንጃ! እዛ ከመንገድ ባሻገር ካለው መዝናኛ ክለብ ውስጥ የሴት ጓደኛው ከሌላ ሰው ጋር ስትገባ አይቶ ነው ሲሉ ነው የምሰማው:: እ እርግጠኛ አይደለሁም::» አለው::

«አይ ሴት! ካለ እነሱም አይኖር ከእነሱም ጋር አይኖር» አለ የአሜሪካኖችን አባባል:: ቁስሉን የተነካው ተሳፋሪዬ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ከየአቅጣጫው በየተራ ትራፊኩን የሚያንቀሳቅሰው ፖሊስ የኛም ተራ ሲደርስ «እንሂድ!» ብሎ ትዕዛዝ ሰጥቶኝ መንቀሳቀስ እንደጀመርኩ ተሳፋሪው «ኦ አምላኬ!

አገኙት! አገኙት» እያለ ጮኸ::

ቀስ እያልኩ እየነዳሁ በኋላ ማሳያ መስታወቴ ስመለከት ፖሊሶች ተኳሹን ወደኋላ አስረው እንደከብት ሲነዱት አየሁ:: ሲጀመር ፊልም የመሰለኝ ግር ግር አፈፃፀሙም እንደዛው ሆነብኝ ::

ተኳሹ ያን ሁሉ ጥይት የረጨው ያፈቀራት ሴት ስላበሳጨችውና ለሷም ሲል ያን ያህል እራሱን ለጉዳትና ለእስር እንደሚዳርግ እንድታውቅለት ይሆናል እንጂ ሰውን የሚጎዳ የወንጀለኝነት ባህሪይ ቢኖረው እሷንም ሆነ ሌላውን ለመጉዳት በቻለ ነበር ብዬ ገመትኩ:: በተለይ እንደዛ ሲሳደብ የነበረው የኔ ተሳፋሪ ጥይት መቅመሱ ጥያቄ አልነበረውም :: የሚያጠያይቀው ለሱ የተተኮሰው ጥይት ለኔም ይተርፍ ነበር ወይ ? የሚለው ጉዳይ ብቻ ነው ::

የግርግሩን አካባቢ ከጀርባችን ትተን ትንሽ እንደተጓዝን «7 - 11 » የሚባለው የሸቀጥ መደብር ያለበት ቦታ ስንደርስ አስቁሞኝ ገባና ባለ 6 ፓኮ በድዋይዘር ቢራ፣ ሁለት ፓኮ ማርልቦሮ ሲጋራና ቡና ገዝቶ መጣ:: ቡናና አንዱን ፓኮ ሲጋራ ለእኔ ሰጠኝና «ተደሰት!» አለኝ::ከልብ አመሰገንኩት::

በግምት ሁለት ማይል ርቀት የሚሆን መንገድ ግራ ቀኝ እያለ እየመራ ወሰደኝና «ዛሬ ልጄን የማይበት ቀን ነውና ከዚህ ከእናቷ ቤት ላምጣትና ከዛ እኔ ቤት ታደርሰናለህ» ብሎ በአንድ መለስተኛ ህንፃ ውስጥ ገባ አልተመለሰም::

40 ማይል «የጦርነት መንገድ» ለፓኮ ሲጋራና ለቡና! ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# የእህል ድምፅ

የሚኒሶታ የክረምት ብርድ እንደብዙዎቹ የአሜሪካ ግዛቶች ጆሮን በማኮማተር ብቻ የሚመለስ ሳይሆን እስከ አጥንት ድረስ የሚዘልቅ ስለሆነ በልብስም በምግብም ደረብረብ ካላደረጉ ለክፋት መዳረጉ አይቀሬ ነው::

ሲፈጥረኝ ወደ ፍየሉ ነኝና እንኩዋንስ ከሚኒሶታ አይነቱ ይቅርና ከሃገሬም ብርድ ጋር ለነበረኝ ግንኙነት ፍልስፍናዬ «እልዳፈርህም አትድረስብኝ» ነበር::

ስለዚህ ክረምቱ ግም ካለ ጀምሮ ሙቀት ሰጪ ባርኔጣ፣ የአንገት ልብስ፣ ሹራብ፣ ጥይት የማይበሳው ጃኬትና ስሪ የክረምት ጫማ ሳላደርግና ከመኖዬም ጎዝጎዝ ሳላደርግ ከቤቴ አልወጣም::

በዛች ዝናባምና ብርዳም እለት እንደወትሮዬ ተጀቧቡኜ በጠዋት ታክሲዬን አስነስቼ ስሰራ ዋልኩና ለምሳ አበሻ ቤት አቋሜ ክትፎዬን አስገባሁ:: ጨጓራዬ ይሄን ጥሬ ክትፎ ለመፍጨት በተያያዘው ግብግብ ነው መሰለኝ እንቅልፍ ስለተጫጫነኝ «መንገድ ላይ ከመስራት፣ እስኪለቀኝ ሆቴል ተሰልፌ ትንሽ በዛውም ልረፍ» አልኩና ማርየት ሆቴል ሄጄ ተራ ያዝኩ::

እንደጠበቅኩት ብዙም ሳላርፍ በ20 ደቂቃ ውስጥ የመስመሩ የመጀመሪያ ሰው ሆንኩና ለመጫን እንደተዘጋጀሁ ሆዱ ካንገቱ ስር የሚጀምር ቀፈታም ሰውዬ እሱኑ የሚመስል የሸራ ማሲኖዳ እየጎተተ የበር ላይ አስተናጋጆቹን አልፎ ቀጥታ ወደ እኔ መጣ::

የበር ላይ አስተናጋጆቹ ማሲኖዳውን እንዳይረዱትና ጉርሻ እንዳይሰጥ አቆጣጡ «በህግ አምላክ እንዳትጠጉኝ» የሚል ይመስላል::

እንደዚህ አይነቱ ተሳፋሪ ለታክሲ ነጂውም ደህና ጉርሻ እንደማይሰጥ ልምዴ ስላስተማረኝ «ወገቤን ስበጥስም አልገኝ» ብዬ በአንድ በኩል የመሲኖዲውን ጫፍ ያዝኩና በሌላው በኩል እራሱ እንዲይዝ ሰውየውንም ማሲኖዲውንም አመቻቸኋቸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይወድ በግዱ ከአንድ በኩል ተሸክሞ ዕቃ መጫኛ ውስጥ ልንጭን ስናነሳ ከሰውየው አካባቢ የሆነ ድምፅ ሰማሁና ሳቄን ማፈን አቃተኝ:: ይባስ ብሎ የሰማሁትን ድምፅ ድሮ ሃገር ቤት ከሰማሁት ተመሳሳይ ትዝታ ጋር አገናኘሁትና ወደ ውስጥ ተንፈቀፈቅኩ::

ከ20 ዓመት በኋላ ያስታወስኩትንና ሳቄን ያባባሰብኝን የሀገር ቤት ትዝታ ገጠመኙን ካቋደስኝ ከራሱ ከጓደኛዬ አድምጡት:-

«የ1ኛው ዙር ብሔራዊ ውትድርና ተመልምዬ ካዛንችስን ለቅቄ ሀረር ውስጥ ከሚገኘው ሁርሶ ማሰልጠኛ ጣቢያ ውስጥ በመሰልጠን ላይ ነበርኩ::

በዛ ማሰልጠኛ ውስጥ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያና ከከተሞች የተሰበሰብን ወጣቶች የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል ብቻ ሳይሆን የአነጋገርም ልዩነት የነበረን ቅይጦች ነበርን::

አሰልጣኝ መቶ አለቃው ሜዳ ላይ እያስተማሩን ነው:: «ትምህርትን በፀጥታ መማር ወታደራዊ ጨዋነት ከመሆኑም በላይ ግዴታም ነው» የሚለው የወታደራዊ ስነስርአት መርህ እንደተጠበቀ ስለነበር በሰፊነው ፀጥታ ውስጥ የሚንቦሰቦሰው የመቶ አለቃው ድምፅ ብቻ ነበር::

በዛ ፀጥታ ውስጥ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመጣ ብሔራዊ ወታደር ድንገት ሳቁን ቢለቀው ሰልጣኞች በሙሉ የሚጠብቀውን ቅጣት ስለምናውቅ ለሱ እኛ ደነገጥን::

መቶ አለቃው በመገረም ስሜት አዩትና «ተነስ!» ብለው ትዕዛዝ ሰጡ:: ተነስቶ ቆመ:: ሳቁ ግን አልቆመም:: ሁላችንም ሰልጣኞች ለምን እንደሚስቅ ለማወቅ ጓጓን!:: መቶ አለቃው ሳቁ ይውጣለት ብለው እየጠበቁት መሆኑ ያልጠበቅነው ነበርና ተገርመናል::



t.me/OLDBOOKSPDF

የልጁ ሳቅ የሚያቆም አይነት ያለመሆኑን የተረዱት አለልጣኞችን በቁጣ «ማነው ስምህ?» ብለው ሲጮሁበት «ብሄራዊ ወታደር ጫንያለው ሞት ባይኖር» አለ በተጠንቀቅ ቆሞ ሳቁንም አቁሞ::

«እኛ ወታደሮች በስራ ፀባያችን መከራንም፣ ሞትንም፣ ደስታንም ተካፍለን የምንኖር ነንና እስቲ ያሳቀህን ነገር ለኛም አካፍለና!» አሉ መቶ አለቃው::

«እረ ያሳፍራል ጌታዬ!» ጫኔ ነው:: /አንገቱን ወደ መሬት ደፍቶ/

«ብሔራዊ ወታደር ጫንያለው ግዴለም የሚያሳፍርም ነገር ቢሆን እንስማው» አሉት በማግባባት ቋንቋ ::

«እንግዲህ እርስዎ ተናገር ካሉኝ ምን ቆርጦኝ... ጌታዬ የሳቅኩት የእህል ድምፅ ሰምቼ ነው» አለና እንደገና በሳቅ ፈነዳ::

ግማሽ የሚሆነው ሰልጣኝ አብሮ በሳቅ ፈረሰ::

«ምን? ምን? ምንድነው የእህል ድምፅ?» አሉ መቶ አለቃ የሳቁን ጩኸት በሚያሸንፍ ድምፅ:: እሳቸውም እንደ ከፊሎቻችን ለቃሉ ባዕድ ኖረዋል::

ጫኔ አብሮት የሚስቅ ሰው ስላገኘ መንከትከቱን ቀጥሏል:: እኛም መልሱን ክሱ ስንጠብቅ ሌላ ጓደኛው ብድግ አለና «የእህል ድምጽ ማለት ጌታዬ! ከታች በኩል ድንገት የሚያመልጥ መጥፎ ሽታ ያለው ነገር ማለት ነው» ከማለቱ መቶ አለቃው ሳቃቸውን ለማፈን እየታገሉ «በሉ የ15 ደቂቃ እረፍት እናደርጋለን ሳቃችሁን ጨርሱ!» ብለው ወዲያው ፊታቸውን በማዞር ራቅ ብለው ሄዱ::

ምንም እንኳን መቶ አለቃው ጀርባቸውን ቢሰጡንና ከእኛ ተነጥለው ርቀው ቢሄዱም መሃረባቸውን በማውጣት አይናቸውን ሲጠራርጉ በማየታችን ነገሩ እሳቸውንም በሳቅ እንዳስነባቸው ገባን::......»



t.me/OLDBOOKSPDF

አዎ! እኔም ጓደኛዬ እንዳጫወታችሁ መቶ አለቃ «የእህል ድምፅ» ያመጣብኝን ሳቅ ላለማሳየት እየታገልኩ የዕቃ መጫኛውን ዘግቼ ቶሎ መኪናዬ ውስጥ ገባሁና ጀርባዬን ለተሳፋሪው ሰጠሁ::

ተሳፋሪዬም ገብቶ ሚኒአፖሊስ ሲንበርግ ኤርፖርት እንድወስደው ሲነግረኝ ሳቂ እንዳያመልጠኝ መልስ ሳልሰጥ ጉዞዬን ጀመርኩ:: ሰውዬው ግን እንዳወቅኩበት ገብቶታል፣ ሳቁ ሲንጠኝ ከትከሻዬ ላይ ስለሚታወቅ::

ሰውዬው የእኔ በሳቅ መታፈን ምንም ስሜት እንዳልሰጠው የገባኝ «የእህል ድምፁን» ሞቅ አድርጎ! ሲደግመው ነበር:: «እንዴ!» ብዬ ከመሳቅ ወደመገረም ተሸጋገርኩ:: «የእህል ድምፁ» ቀጠለ:: አሁን ስለ ሳቅና መገረም ሳይሆን በጭስ ስለመታፈኔ ሆነ ሃሳቤ:: መስኮቱን እንዳልከፍት ዝናብና ብርዱን ፈራሁ:: ለማንኛ ውም ሙቅ አየሩን ሽታውን አዛው ሰውዬው ጋር እንዲያስቀርልኝ ለቀቀኩት:: በተጀቦድኩት ልብስ ላይ ሙቀቱ ሲጨምር ዳቦ ቤት የገባሁ መሰለኝ:: ሙቀቱ በጣም ስለበዛ የውስጥ መስታወቶቹ በሙሉ ጉም ሰሩና እይታዬ ተከለለ:: ዘዴዬ ስላልሰራ የሙቀት አማራጭ ቁልፉን «ዲፍሮስት» ላይ በማድረግ ጉሙን አስለቀቅኩና ለአየር ማስገቢያ ታህል መስታወቴን ዝቅ አደረኩት::

አመናችሁም አላመናችሁም ሰውዬው በየመሃሉ መተኮሱን ተያያዘው:: አንዳንድ ጊዜ አንድ በአንድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ግብረ ርዕስ /አውቶማቲክ/::

ሰውዬውን በኋላ መስታወት «እረ አባክህ ይብቃህ!» አይነት አስተያየት ባየውም እሱም በመስታወቴ ውስጥ ቅጭም ብሎ ሲያፈጥብኝና «የእህል ድምፁን» ወደ «የእህል ንግግር» ብሎም ወደ «የእህል ዲስኩር» ሲያሸጋግረው «ምን አባክ ትሆን ዝም ብለህ ንዳ!» የሚል መሰለኝ::

ታክሲዬ ወደ ህዝብ መፀዳጃ ሽንት ቤትነት ተለወጠ:: አተነፋፈሴም ከእያንዳንዱ ተኩስ በኋላ አቅም እስከፈቀደ ትንፋሼን እየያዝኩ ሆነ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩ በጣም ስለበዛብኝና ጤነኛነቱም ስላጠራጠረኝ ዞር ብዬ ባየው ያሁሉ ጋዝ የወጣው ሆዱ ምንም አልጎደለም:: ደራሽ ወንዝ እንዳመጣው ውሻ ሆዱ እንደተቀበተተ ነው::

ይሄ ሰውዬ ገና ብዙ ያዘጋጀልኝ ድግስ እንዳለ ገባኝ:: በቃ የመርዛ መርዝ (ኬሚካል) ጦርነት ውስጥ ያለሁ ወታደር ሆኛለሁ:: ልክ እንደ ጫኔ::

ያለኝ አማራጭ የጨበጣ ውጊያ መቀላቀል ብቻ ሆኗል:: የበላሁት እንጀራ የጋዙ መርዝ አጥወልውሎኝ ከመውጣቱ በፊት በመሳሪያነት ልጠቀምበት ተገደድኩ:: እና እኔም ወደ ጠላቴ ተኮስኩ:: የአፀፋ ተኩስ!::

ያን ሁሉ መርዝ ሲረጭ የነበረ ሰውዬ «ወየው አምላኬ! ወየው አምላኬ! ይሄ ከባድ መርዝ ነው ሹፌር! መስኮቱን ክፈት! በደንብ ክፈት!» እያለ መጮህ ጀመረ::

የልብ ልብ ተሰምቶኝ «አንተም አቁማ! አለበለዚያ እዚሁ እንተላለቃታለን አልኩት» በኋላ ማላያ መስታወት አይኔን አፍጥጬ ከንፈሬን ነክሼ እያየሁት::

«ኦኬ ...ኦኬ» ብሎ የተኩስ ስምምነት አደረግን::

ያለማንም አደራዳሪ የፈፀምነው የተኩስ ስምምነት ሳይጣሶ ተከባብረንና ተፈራርተን በሰላም አየር ማረፊያው ደረስን::

የሚሄድበትን አየር መንገድ አሳውቆኝ የመንገደኞች መግቢያው ላይ አቆምኩለት::

ምንም ቢሆን የካዛንችስ ልጅ ነኝና ሻንጣ ከማውረዴ በፊት ጉርሻ የሚሰጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ቆጭ እንዳልኩ ጠበቅኩት:: ሳንቲም ቆጥሮ ራሷን ሂሳቧን 22.60 ዶላር ብቻ ከፈለኝ::

ምስጋና የለም ደህና ሁን የለም ብቻ የዕቃ መጫኛ የኤሌክትሪክ መክፈቻ ቁልፌን ተጫንኩና ፀጥ አልኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውየው ሻንጣ እንደማልሸከምለት ገባውና በሽቀ መሰለኝ ግማሽ ሰውነቱን ከመኪና ካወጣ በኋላ ለካስ አፋም አቦሬያም ኖሯል «የድመት ምግብ ነው የበላሽው?» በማለት አሾፈብኝ:: የብሽቀቱን ቁጭት ሊወጣብኝ::

እኔስ ማነኝ «ጥፋ ከዚህ አንተ ተነቃናቂ ሽንት ቤት!» አልኩት:: አፍንጫዬን ይገፍ እያሳየሁ::

ወዲያው የአይሮፕላኑ ማረፊያ ዕቃ ጫኞች ደርሰው መሲኖዲውን ማውረድ ሲጀምሩ ትንሽ ልመርቅለት አልኩና «እባካችሁ መጀመሪያ ሽንት ቤት አሳዩት! ሱሪው ተበላሽቷል !» አልኳቸው:: ዞር ብለው አዩት:: በድንጋጤ አይኑን አፍጥጦ እያየኝ መኪናዬን አስነስቼ ጠፋሁ:: «ክሺህ ሃምበርገር አንድ እንጀራ!» ብዬ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሙሽራው

ተሳፋሪው ማሳቹስተስ ጎዳና ላይ ከሚገኝ የግሪክ ቤተክርስቲያን እንዲያደርሰው አበሻውን ታክሲ ሹፌር ይጠይቀዋል፡፡

ሾፌሩም ዋሽንግተን ዲሲንና አካባቢውን አብጠርጥሮ የሚያውቅ ነባር ሹፌር ነበርና «ማሳቹስተስ ላይ ሁለት የግሪክ ቤተክርስቲያን እንዳለ አውቃለሁ፡፡ የትኛውን እንደምትፈልግ ለመለየት የቤት ቁጥሩን ልትነግረኝ ትችላለህ?» ይለዋል፡፡

ተሳፋሪም «ቁጥሩን አላውቀውም፣ አካባቢው ካደረስከኝ ግን የምሄደው ለሠርግ ስለሆነ ሰዎች በብዛት እናገኛለንና ልንስተው አንችልም» ይለውና መንዳቱን ይቀጥላል፡፡

ከመጀመሪያው የግሪክ ቤተክርስቲያን ሲደርሱ ሰው በብዛት ያያሉ፡፡ ሹፌሩም «እርግጠኛ ነኝ እዚህኛው መሆን አለበት» ከማለቱ ተሳፋሪው «አመሰግናለሁ! እዚሁ ጣለኝ ይለውና ተቻኩሎ ከፍሎ ይወርዳል፡፡

ሹፌሩም ተጠምዝዞ ወደ ከተማው ማዕከል ለመመለስ ከተቃራኒ የሚመጣው ተሽከርካሪ ሄዶ እስከሚያልቅ መጠበቅ ጀመረ ....

ተሳፋሪው ስላረፈደ በጥድፊያ እየተራመደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንደገባ የቄሶቹ ቅዳሴ አስደነገጠው፡፡ የሚያየውን ማመን አቃተው ፡፡

ሙሽራው መሃል ላይ ነው ... ዙሪያውን የከበቡት ሚዜዎቹ ሳቅ አይታይባቸውም፡፡ የዛሬው ሙሽራ ነጭ ሸሚዝና ጥቁር ከረባት አድርጎ ዙሪያውን የአበባ ጉንጉን ተደርጎለት በጣም አምሮበታል፡፡ ግን ምን ያደርጋል ሙሽሪት አጠገቡ የለችም ... እሱም ሳጥን ውስጥ ነው የተኛው ያውም እስከወዲያኛው አለም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# የአንድ ቀን ዕጣ

ብቻ እንዳች ነገር ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው:: የሰውነት ድካሙ ገና አለቀቀውም:: አይኑን አበስ አበስ አድርጎ ተጣሞ ወደተሰቀለው የግድግዳ ሰዓት አማተረ:: የሰዓት ቆጣሪው ከጠዋቱ 4 ሰዓት ላይ ተጋድሟል:: እንቅልፉ እንዳይጠፋበት የደቂቃ ቆጣሪውን ለመፈለግ ግዜ አላባከነም:: «ገና ልጅ ነው» አለና አይኖቹን ከድኖ በፍጥነት ክንብንብ ጥቅልል ብሎ ወደ እንቅልፍ አለሙ ተጣደፈ:: በእንቅልፍ ውስጥ በመስመጥ ላይ እያለ «ምነው ያሰወትሮዬ በጠዋት ነቃሁ?» ብሎ ራሱን ጠየቀ::ለአፍታም ሳይቆይ አይምሮው አጠንጥኖ «የታክሲው ፍርድ ቤት ቀጠሮ ነዋ!» አለው:: «አይ የመከራ ህይወት!» ብሎ ከአልጋው ላይ ተፈናጥሮ ሲነሳና የሰዓት ማንቂያው ሲንጫረር እኩል ሆነ::

እንቅልፍ ያልጠገበው አይምሮው ብስጭትጭት ስላደረገው እየተንገዳገደ ሄዶ ውለተኛ የግድግዳ ሰዓቱን በጡጫ ፀጥ አረገው!:: ተጣሞ የነበረው ተስተካከለ::

በልሁ እንቅልፉን ከሚነጥቀው ገንዘቡን የሚነጥቀውን ይመርጣል:: በየጊዜው የኮመዲኖ ላይ ማንቂያ ሰዓቶቹ ሲቀሰቅሱት በንዴት እየወረወረ መሰባበሩ ቢሰለቸው ነበር የግድግዳውን ሰዓት የገዛው::

በልሁ ተመልሶ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለና የሲጋራውን ፓኮ ከነላይተሩ ብድግ አድርጎ ቢከፍተው ሁለት ሲጋራ ብቻ ነው የቀረው:: «ትላንት ማታ የተገዛ ፓኮ አለቀ ማለት ነው?» ብሎ ራሱን ነቀነቀና አንዱን ሲጋራ አውጥቶ አቀጣጠለ:: የርቀት መቆጣጠሪያውን አንስቶ አቧራ የለበሰውን ቴሌቪዥኑን ለኮሰውና የሚወደውን አለምአቀፍ ወሬ የሚያጠግበው ሲኤንኤን ጣቢያ ላይ እስኪስተካከል ደጋግሞ ተጫነው::

ሲጋራውን እየማገ ራሱን ማነቃቃቱንም ተያያዘው:: አይኑ ቴሌቪዥን ላይ ቢሆንም ህሊናው ደግሞ የራሱን ቴሌቪዥን ከፈተ::



t.me/OLDBOOKSPDF

የቴሌቪዥኑን አጧራና የቤቱን መዝረክረክ አስተውሎ «ያቺ ልጅ ከመጣች ሰነበተች ማለት ነው?» ብሎ ራሱን ጠየቀ «ያቺ ልጅ» የሚላት የሴት ጓደኛው ልትጠይቀው ስትመጣ ነው ቤቱን የሰው ቤት አስመስላው የምትሄደው። እሱማ ነገር አለሙን ከተወው ሰነበተ።

ሁለት ከንፈሮቹን አጋጥሞ መጠጠና «ምስኪን ነች!» አለ በልቡ። ከልቡ «እንደሱ አይነቱን «የሰው ቢጤ» ሰው ለማድረግ የምትለፋ ሰው መሆኗን አስቦ «ልፊ ያላት!» ብሎ አዘነላት። እውነት አለው! እሷ ተስፋ አልቆርጥ አለች እንጂ በጊዜዋ እየተጫወተች መሆኑን ደጋግሞ ነግሯታል።

ደግሞ ወደ ቴሌቪዥኑ ተመለሰ ..... እንደገና ወደ ሃሳቡ ..... ቴሌቪዥን .... ሰዓቱን አየ..... ዘሎ መታጠቢያ ቤት.....

ሸሚዙን አነሳ ... ተጨማዷል ጣለው። ሌላ አንስቶ ለበሰ። ሱሪውን አጠለቀ፣ ከሸሚዙ ጋር አብሮ አይሄድም። ሌላ ሸሚዝ ቀየረ። የተሻለ ሱሪ አየ። በሰበሰው ቀየረው። «ይሻላል!» አለና ተጣደፈ ወደ ታክሲው ፍርድ ቤት።

ከተማው መሃል በ7ኛውና በ8ኛው ጎዳና መሃከል በ41ኛው መንገድ ላይ ከሚገኘው ግዙፍ ህንፃ አካባቢ የውጭ ሃገር ሰዎችን በብዛት ማስተዋል የተለመደ ነው። ነገር ግን እነዚህ የውጭ ሃገር ሰዎች ቱሪስቶች ህንፃውም ቱሪስት ኮሚሽን አይደለም። የታክሲ ኮሚሽን ፅህፈት ቤትና የኒውዮርክ ከተማ ታክሲ ነጂዎች ናቸው።

ከእስያ፣ ከአፍሪካና ከላቲን አሜሪካ ከሚገኙ አገሮች ተሰደው ከመጡት ከነዚህ ህዝቦች እጅግ በዝተው የሚታዩት ህንዶች ፓኪስታኖችና ባንግላዴሾች ወዘተ ሲሆኑ የፓርቶሪኮ፣ የዶሚኒካን፣ የሄይቲ፣ የጃማይካና የሩሲያ ሰዎችም ቁጥር ቀላል አይደለም። እስከዛሬ ድረስ ከታደለው ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የታክሲ መንጃ ፍቃድ በመነሳት በአሁኑ ሰአት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ግለሰቦች በታክሲ ሹፌርነት ይተዳደራሉ። ከዚህ ቁጥር ውስጥ አበሻው ከሺህ አንድ ቢሆን ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህ የተለያየ መንፈሳዊ እምነት የሚከተሉ ህዝቦች የየራሳቸው ሃይማኖት «ብቸኛው ትክክለኛ ሃይማኖት» አርገው ስለሚቆጥሩት ይኮሩበታል።

ማንነታቸውንም ለማሳየት የሲንግ አማኞች ጥምጥም፣ የእስላም ኩፍይት፣ የክርስቲያን የመስቀል ሃብል፣ የአይሁድ ቆብ ወዘተ ያደርጋሉ። ራስ ተፈሪያኖቹም እንደዛው።

ሁሉም የተለያየ አምላክን የሚያመልኩና የሚናፍቁት የየራሳቸው «ሰማያዊ ገነት» ቢኖራቸውም ቅሉ የሁሉም «አለማዊ የተስፋ ምድራቸው» ግን ኒውዮርክ ነች።

ኒውዮርክ ትመቻቸው አትመቻቸው ግን ሌላ ጥያቄ ነው።

የታክሲው ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት በር ላይ ጥቁር ሰማያዊ ዩኒፎርማቸው ላይ የኮሚሽኑ አርማ ያለበት መለዮና የደረት ምልክት አድርገው የሚኮለኮሉ የጥበቃ ሰራተኞች እነዚህን «መጤዎች» በማንጓጠጥና በንቀት ያስተናግዷሉ። ለነገሩ በእንግሊዝኛ ችሎታቸው ስለሚፈርጇቸው እንጂ በትምህርትማ የት ተደራርሰው።

ከእነዚህ ታክሲ ነጂዎች ውስጥ ዶክትሬት፣ ማስተርስ፣ ባችለር ድግሪ ያላቸው ቁጥራቸው የትየለሌ ነው። በነበሩበት ሀገርም የኮሌጅ አስተማሪ፣የፖለቲካ መሪዎች ፣ የጦር መኮንን፣ ሚኒስትር፣ ኢንጂነር፣ዶክተር ፣ ጠበቃ... ወዘተ የነበሩ አሉባቸው።

ይሄ ማለት ግን ሁሉም የተማሩ ናቸው ማለት አይደለም። እርሻቸውን ጥለው የመጡ ገበሬዎች፣ ግመል ጠባቂዎች፣ ሱቅ በደረቴዎች፣ ጋሪ ነጂዎች፣ መርከብ ላይ ተሸካሚዎች ... ወዘተ የነበሩም ይገኙባቸዋል።

ኒውዮርክ ግን ሁሉንም የምታስተናግዳቸው በታክሲ ነጂነታቸው ነው። እሷጋ «እንዲህ ነበርኩ» አይሰራም፣ ሆኖ መገኘት ብቻ! እንጂ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በልሁ በሶሻሊስት ሃንጋሪ ለ4 ዓመታት የህክምና ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶ ከዳር ሳያደርሰው በኢጣሊያ አድርጎ ኒውዮርክ ገባና ትምህርቱን ለመቀጠል ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ታክሲ መንዳት ጀመረ:: ነገር ግን የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥንካሬና ትዕግስት ስላጣና የሚያገኘውን ገንዘብ በአግባቡ መጠቀም ስላልቻለ አላማው ደበዘዘ:: ቀን ቀንን እየወለደ ሲመጣ ከነአካቴው ፕሮፌሽናል ታክሲ ነጂ ሆኖ ቀረ::

በራሱ አፈረና ራሱን እየሸሸ ኗሪ ሆነ:: ራሱን ሸሽቶ የተደበቀባቸውም ሲጋራ፣ መጠጥ፣ ጫት፣ ቁማር ከእለት መሸሸጊያነት አልፈው ከአባራረው አላስጣሉትም:: ይልቁንም ወደ ሱስነት ተቀይረው ህይወቱን ገድበው አቆሙት እንጂ::

አዎ! ጊዜው ይሮጣል የሱ ህይወት ግን ቆሟል:: የደመ ነፍስ ኗሪ በመሆኑ በዚች አለም ላይ መገኘቱ እንጂ መኖሩ እያከተመ መጥቷል::

«ነጋ ጠባ ሩጫ! ፋቀቅ ላይል ኑሮ!» እያለ ተስፋ ቆርጦ ለህይወት ጣጣ ተሸናፊነቱን አምኖ እጅ ሰጥቷል::

ህሊናው በምሬት ታምቆና ከራሱ ጋር መታረቅ ተስኖት የራሱ አጥፊ ጠላት ሆኖ በየቀኑ የሚኖረው ተመሳሳይ ለዛ ቢስ ኑሮው አንገፍግፎት ከልቡ ከሳቀ ዘመን ተቀያይሯል:: መኖር ዳገት ሆኖ እስቃስቶታል....

በልሁ ከእንቅልፉ በነቃ ቁጥር እሱነቱን የሚጠላበት ዋናው ምክንያቱ ያን ሁሉ ዕውቀት ተሸክሞ ያን ሁሉ እድሉን አበላሽቶ ባላሰበው የህይወት መስመር ውስጥ ተዘፍቆ በመቅረቱ ነው ለዛውም ስማቸውን እንኳ አስተካክለው በማይጽፉ ሰዎች ተበልጦ....::

ለዚህ ሰው ዛሬም ሌላው መራራ ቀኑ ነው:: «የታክሲ ኢንስፔክተር» የሚባሉ በሆነው ባልሆነው ቲኬት እየሰጡ እልፍ አዕላፍ ታክሲ ነጂዎችን የገንዘብ ማግኛ ያደረጉ ርህራሄ ቢስ ፍጡሮች እሱንም አግኝተውት በይስሙላ ፍርድ ቤታቸው የሚቀርብበት ቀን ቀጠሮው ዛሬ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመቶ ውስጥ ዘጠና ዘጠኙ ሹፌር ጥፋተኛ እየተባለ የሚፈረድበት እንደዚህ አይነት ፍርድቤት አሜሪካ ውስጥ ይኖራል ብሎ ላላየ ሰው ማሳመን ይከብዳል:: ብቻ በአጠቃላይ ህጋዊ የገፈፋ ቦታ ነው:: ለስሙ ያህል የቀጠሮው ሰዓት ቲኬቱ ላይ የተፃፈ ቢሆንም ዳኛው ጋር ለመቅረብ ከ2-3 ሰዓት በላይ ተራ መጠበቅ የግድ ነው::

እዛ ህንፃ ውስጥ አይደለም ተከሶ እግር ጥሎት የተገኘ ከተላላኪው ጀምሮ ፖሊሱን ጨምሮ እስከዳኛው ድረስ የሚፈፅሙትን እኩይ ተግባርና የሚከተሉትን አሰልቺ አሰራር ሲመለከት ሰብዓዊ ፍጡር የማይከበርበት ኋላ ቀር ሃገር ውስጥ የገባ ይመስለዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም::

ለዚህም ነው ከህንፃው ክሳቸውን ሆነ ጉዳያቸውን ጨርሰው የሚወጡ ሹፌሮች ፊት ላይ መብገን ብቻ የሚታየው:: አንዳንዶቹ ንዴታቸውን መቆጣጠር ስለማይችሉ በሃገራቸው ቋንቋ ሳይቀር እየተሳደቡ የሚወጡት ከሃገራቸው ሸሽተውት የመጡትን ግፍ የህንፃው ውስጥ ድርጊት ስለሚያስታውሳቸው ጭምር ነው:: የታክሲ ኮሚሽኑ ፅህፈት ቤት::

በልሁ የቀጠሮ ወረቀቱን በር ላይ ለተገተረው ፈርሳም የጥበቃ ሰራተኛ አሳይቶ በጣቱ ያሳየውን አቅጣጫ ተከትሎ ከሄደ በኋላ እንደ ከብት እየቆጠረ አስራ ሁለት - አስራ ሁለት ሰው ኢሊቬተር ውስጥ ከሚሞጅረው አስተናጋጅ ጋር ደርሶ በተራው እሱም ተስተናገደ::

ፍርዱ የሚታይበት 3ኛ ፎቅ ላይ ወርዶ፣ ስሙን ከባህር መዝገብ ላይ አስፍሮ፣ የተራ መጠበቂያ ቲኬቱን ተቀብሎ፣ ታክሲ ሹፌሮች ከሚንጫጩበት መጠበቂያ አዳራሽ ውስጥ ከዳር ፈንጠር ብሎ ተቀመጠ:: ቀና ብሎ የተስተናጋጁን ቁጥር ግድግዳ ላይ ሲመለከት C089 ይላል:: የእርሱ ቁጥር C398 ነውና ገና ከ200 ሰው በላይ ከሱ በፊት እንዳለ ተረድቶ በያዘው ኒውዮርክ ታይምስ ላይ ጊዜውን ለመግደል ማገለባበጡን ጀመረ:: እንቅልፍ ያልጠገቡት አይኖቹ ግን ብዙም ሳያስነብቡት ከዱት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋዜጣውን አጣጥፎ እጆቹን አጣምሮ ወደ ኋላው ወንበሩ ላይ ተለጠጠና ዙሪያውን በአይኑ መቃኘት ጀመረ:: የህዝቡ ጨኸት ያደነቁራል:: ግርግሩ ያዞራል::

አረብኛው፣ ህንድኛው፣ ጀማይከኛ፣ ሩሲያውኛ፣ ስፓኒሽ፣ ሄይትኛው ወዘተ መላቅጡ ሁሉም በቋንቋው ይለፈልፋል::

በልሁ ፈዞ ያያቸዋል:: ሶስት ሆነው ከሚያወሩ ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ በአንድ ጊዜ ያወራሉ:: ሰሚውን እግዚአብሄር ይወቀው:: በተለይ ሃይቲዎቹ ሲያወሩ ወፍጮ ቤት ያደጉ ነው የሚመስሉት:: ላንቃ የሚባል ነገር ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያውቀው የፈጠራቸው ብቻ ነው:: ሳቅ ሲሉ የሚታየው የፊታቸው ገፅታ ባይኖር ሊደባደቡ የሚጋበዙ ነው የሚመስሉት::

በልሁ አይኑን ከአንዱ ማዕዘን ወደ ሌላው እየወረወረ ይህንን የተለያየ ድራማ ይኮመኩማል::

ከሩቁ አንድ አበሻነቱ በመልኩና በአቀማመጡ መኮራመት የሚለይ ወደ ሰላሳ አምስት አካባቢ የሚገመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ ቁጭ ብሏል:: ድንገት ከበልሁ ጋር አይናቸው ተገጣጠመ:: ወዲያው ሁለቱም አይናቸውን ሰብረው እንዳልተያዩ ሰው መሆን ጀመሩ:: ሰላም ሳለመባባል::

በልሁ «አይ እኛ! የምንገርም ህዝቦች ነን እኮ» ብሎ ራሱንም ጭምር ወቀሰ:: ራሱንና የሃገሩን ልጆች ከሌላው የሚለዩበት ነጥቦችና ምክንያቶች እያብጠለጠለ በሃሳብ ባህር በመዋዠት ላይ እንዳለ ከፍ ያለና የሚያማልል «ይቅርታ!» የሚል የእንዕስታይ ድምጽ ወደ አዳራሹ መለሰው::

ዞር ብሎ ሲመለከት የአበሻ ገጽታ ያላት ነገር ግን አይናፋር ያልሆነች ጥቁር አሜሪካዊት ህዝቡ መሃል ቆማ ትኩረት ለማግኘትና ጫጫታውን ለማስቆም ደጋግማ «እባካችሁ ፀጥታ!» ትላለች:: በመከራ ጫጫታውን ጋብ አረገችው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ካምፓኒው እንደደረሰም ብዙም ሳይቆይ ከቀኑ 10 ሰዓት አካባቢ ጥሩ መኪና ተሰጥቶት አስፈላጊውን ፎርም ሞልቶ ሜትሩን አስተካክሎ የታክሲ መንጃ ፈቃዱን ሰቅሎ ግቢውን ለቆ ወጣ::

በልሁ ኒውዮርክን ከተወለደበት መንደር የበለጠ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: በዚህ «በማይተኛ ከተማ» ውስጥ ለብዙ አመታት ብዙ ሺህ ሰዓቶች ታክሲውን ዘውሮበታል:: ትራፊኩ በምን ሰዓት የት ቦታ እንደሚበረታ እንዴትም በአጭር ጊዜ ተፈላጊው ቦታ እንደሚደረስ ተክኖታል:: የከተማዋን ድልድዮችና ታናሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ፊልም ቤቶች፣ ሆቴሎች፣ መስሪያ ቤቶች፣ የምሽት ክለቦች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ ኮሌጆች፣ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች፣ሙዚየሞች ሆስፒታሎች ወዘተ ከእንቅልፉ አስነስተው ቢጠይቁት እንኳን የት የት እንዳሉ ለመተንተን ለሰከንድ ማሰብ አያስፈልገውም::

የታክሲ ስራው በምን ሰዓት የት ቦታ እንደሚደራ፣ እንደ ተሳፋሪው ሁኔታና አይነት ጥሩ ገርሻ ለማግኘት የሹፌሩ አቀራረብ ምን አይነት መሆን እንዳለበት ተጠብቦበታል::

በአጠቃላይ የታክሲ ስራ በሚጠይቀው ጥበብ ዶክትሬቱን ያገኘ ፕሮፌሽናል ነው::

እንደተለመደው የዛን ዕለት ተሳፋሪውን ወደ ቤቱ፣ ሬስቶራንት፣ ቲያትር ቤት የሙዚቃ ክለቦች በማመላለስ መንሃተንን ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ በተቃራኒው አቅጣጫ ሲሽከረከርባትና በትራፊክ ውስጥ ሲጋፋ አመሸ::

ለስ ወርቅ ቀን ነበር:: ቆንጆ ብር ሰርቷል:: እንደ ወትሮው በስራ ሰዓት አበሻ ቤት ሄዶ ጊዜም አላጠፋም:: ገንዘቡንም በግብዣ አላባከነም::

ስራውን ለማገባደድ አንድ ሰዓት ሲቀረው (ከንጋቱ 10 ሰዓት ላይ) ስራ ላይ እንዳልሆነ የሚያሳየውን የጣራ መብራቱን አብርቶ ወደ ካምፓኒው ለመሄድ



t.me/OLDBOOKSPDF

የመኪናውን አፍንጫ ወደ ሰሜን አቀና:: ከእንግዲህ ተሳፋሪዎች የሚጭነው ካምፓኒው ወደ ሚገኝበት ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚወስዱትን ብቻ ነው::

65ኛውና ብሮድዌይ መጋጠሚያ ላይ ቀይ መብራት አቁሞት እያለ ሁለት ሰዎች «ታክሲ!» ብለው የእጅ ምልክት ያሳዩታል::

«ወዴት ናችሁ?» መስታወቱን ዝቅ አርጎ

«181ኛው መንገድ»

«ግቡ!? ይላቸዋል የበሩን ቆላፊ ተጭኖ እያላቀቀላቸው::

በልሁም «ዛሬ የኔ ቀን ነው:: 15 ብር ለነዳጅም አገኘሁ ማለት ነው? ይሄ ሎተሪ ነው» እያለ ውስጡ በደስታ ረካ::

ሁለቱ ተሳፋሪዎች ምናቸውም አይመሳሰልም:: አንደኛው አጭርና ደንዳና ሰውነት ያለው ሲሆን ስፓኒሽ ይመስላል:: አለባበሱ የጅንስ ቁምጣ ሱሪና ከራሱ መሸፈኛ ያለው ጠቆር ያለ ሹራብ ነው:: ሌላኛው በግምት 1.90 ሴ.ሜ የሚሆን ቁመት ያለው፣ ሲሆን ከረባት ቀረሽ ሱፍ ልብሱ ላይ የቤዝ ቦል ኮፍያ ያደረገ ነጭ አሜሪካዊ ነው::

ሁለቱም ታክሲ ውስጥ እንደገቡ «ረኸርሙ ተሳፋሪ» ወደሚፈልጉበት ቦታ ከመሄዳቸው በፊት 71ኛው መንገድ ላይ በብሮድዌይና በዌስት ኢንድ መካከል የሴት ጓደኛውን ማንሳት እንደሚፈልግ ልመናም ትዕዛዝም በሚመስል የተምታታ አነጋገር ለሹፌሩ ለበልሁ ይነግረዋል::

በልሁም «ኦኬ» ይልና 71ኛው መንገድ ላይ ወደ ግራ እንደታጠፈ ሌላኛው ተሳፋሪ እንዲያቆም ሲነግረው ጥግ ይዞ አቆመ::

ሰዎቹ ግራና ቀኝ መገለማመጥ ጀመሩ:: በልሁም ራሱን ለማሳረፍ ወንበሩ ላይ ለጠጥ አለና ድካሙን ማዳመጥ ጀመረ::



t.me/OLDBOOKSPDF

«እስቲ ጥሩንባ ንፋ! ዴብራ ስምታ እንድትመጣ» ይላል ረኘሙ:: በዚህ ጊዜ በልሁ «ምን ነካችሁ ሰዎች? ያለነው እኮ! መኖሪያ አካባቢ ነው የተኙ ሰዎችን ከመበጥበጥ ዝም ብለን ብንጠብቃት አይሻልም?» ብሏቸው ገንዘብ እንዳይቆጥርባቸውም ሊሆን ይችላል ብሎ የሚትሩን የጊዜ ቆጣሪ አቆመላቸው::

በዚህ ጊዜ አጭሩ ቁጣ በተሞላበት ኃይለ ቃል «ምን ነካህ ሹፌር! ማነው አንተን ለተኙ ሰዎች ተቆርቋሪ ያረገህ? ጥሩንባ ንፋ እኮ ነው የምልህ» አለው::

በልሁ እግረ መንገዱን የሚያገኛትን 15 ብር ፈልጓል እንጂ ለፀብ ደንታም የለው:: ትዕግስተኛ ነው ይችላል:: ትዕግስቱ ከተሟጠጠ ግን ፀበኛውን ባየር ላይ ሲወረውረው እንጂ እንዴት አድርጎ እንዳነሳው ለማወቅ ፍጥነቱ ከአይን ይቀድማል:: ዛሬ ግን ለብሯ ብሎ የሚሉትን ሁሉ ፈፀመ::

በታዘዘው መሰረት ለአራተኛ ጊዜ ጥሩንባውን እንዳስጮኸ አንገቱ ስር የሆነ ቅዝቃዜ ተሰምቶት ዞር ሲል የሚያብለጨልጭ ሳንጃ አይሉት ጩቤ አይኑ ላይ አብረቀረቀበት::ወዲያውም «ያለህን ገንዘብ ሁሉ ቀጥል!» የሚል ሃይለኛ ድምጽ ጆሮው ላይ ባረቀበት:: ጠቅላላ ሁኔታው እንደመብረቅና ነጎድጓድ ስለሆነበት« በስመ አብ...» ከማለት በቀር ሰውየው በልሁ ነበርና አልተርበደበደም::

ጭራሽ «ረጋ በሉ! ...ያገኛችሁት ትክክለኛ ሰው ነው» ብሎ ለታክሲው ፍርድ ቤት መቀጮ አዘጋጅቶ የነበረውን 200 ዶላር፣ ሲሰራ ያደረበትን 250 ዶላር፣ ለስራ መጀመሪያ ያዘጋጀውን ዝርዝር ብር 25 ዶላር ከየኪሱ ውስጥ እያወጣ ከኋላ በጎን በኩል ተቀምጦ ጩቤውን ለደገነው አጭር ወንጀለኛ 475 ዶላር እጁ ላይ አስቀመጠለት::

ሙሉ ለሙሉ ከበልሁ ጀርባ የተቀመጠው ረኘሙ ተሳፋሪ ደግሞ ማጅራቱን በደገነው ሽጉጥ አስነክቶ «ዝርዝር ስሙኒ ሳታስቀር አውጣ! ስንፈትሽህ ሳንቲም ካገኘን ግን ጭንቅላትህን ነው በዚህ የማፈርሰው!» ብሎ ደበልጥ አፈሙዙን ማጅራቱ ላይ አሸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

በልሁም ያለኝ ይሄ ነው ብሎ ሲነግረው ዞር ሲል ከረኸርሙ ሰውዬ ጋር አይን ለአይን ተገጣጠሙ:: «አትዘር!» ብሎ በሰደፍ ጭንቅላቱን ወቃው::

«እኬ .. እኬ ያለኝ ይሄ ነው ብዬ ላስረዳህ ፈልጌ ነው እንጂ አንተን ለማየት አይደለም»

ረኸርሙ «ውሸታም! ውሸታም ነው እየኸው በዘዴ እንዳየኝ?»

አጭሩ በንዴት «እናትክንና ... ምንድነው የምታጠራው? እኔን እስካሁን በጎን አይኑ እያየኝ አይደለም እንዴ? ባለፈው እኔ እስር ቤት ስማቅቅ አንተ በነፃነት ምንም ሳይነካህ ኖርክ፣ አንተ ራስ ወዳድ ነህ! ስለኔ ደንታ የለህም» ብሉ ፀብ ፈጠረ::

በልሁም የዘራፊዎቹ መጣላት ገርሞት ሳያበቃ፣ ረኸርሙ «እኬ እኬ አታስብ! አሁን የሚያጣላን ነገር የለም:: የዚህ እንዳለፈው አይሆንም:: እጨርስልሃለሁ:: » ሲለው ፀቡ ወዲያው በረደ::

አሁን ምርኮኛው በልሁ እንደማይምሩት አረጋገጠ::

ከሱ የበለጠ ዘራፊዎቹ አይምሮአቸው የተረበሸ ነው:: አንገቱ ላይ የተደገነው ጬቤ ሲሞጫጭረው ሰውዬው እጁ እየተንቀጠቀጠ መሆኑን ለመረዳት አይምሮው አሁንም አልሳተም::

አጭሩ «ኪስህን በደንብ ፈትሽ!» ብሎ ጮኸበት:: በልሁ ትዕዛዙን ሁሉ ፈፀመ ሳንቲም ሳይቀር እጁ ላይ አስቀመጠ፣ ከፊሎቹ ሳንቲሞች በወንበር ስር ተንጠባጠቡ:: «የኪስ ቦርሳህ የታለ?»

ድጋሚ ሰደፍ እንዳይቀምስ በፍጥነት ከኋላ ኪሱ አውጥቶ ፊቱን ሳያዞር አቀበላቸው:: መዘክዘካቸውን ቀጠሉ::

የዘራፊዎቹ ትኩረት ቦርሳ ፍተሻ ላይ ሲሆን ያገኛትን ፋታ በመጠቀም «እባካችሁ! አትጉዱኝ ብቻ ያላችሁኝን እፈጽማለሁ» አለ በልሁ በማሳዘን ::



t.me/OLDBOOKSPDF

72ኛው መንገድ ላይ «ዌስት ሳይድ ሃይዌይ» ገብቶ 181ኛው መንገድ ላይ ለመውጣት ዌስት ኢንድ ጎዳና ላይ ወደ ቀኝ/ወደ ሰሜን/ መታጠፍ ሲጀምር አጭሩ «ኖኖኖ ወደ ግራ ታጠፍ!» ብሎ ጮኸበትና ትዕዛዙን ያለማወላወል እንዲቀበል ጩቤውን ጫን ብሎ አንገቱ ስር ቀረደደው::

«እኬ! እኬ!» አለ በልሁ የጩቤው ቅርደዳ እንዲቆምለት በሚማፀን ድምፅ::

«ወንድሞቼ! 72ኛው መንገድ ላይ ወደ ግራ ታጥፌ ወደ አፕታውን የሚወስደው «ዌስት ሳይድ ሃይዌይ» ልግባና 181ኛው ላይ ወጥቼ የምትፈልጉበት ላድርሳችሁ ብዬ እኮ ነው!» አላቸው::

ረዥሙ በቁጣ ቃል «ሃሳባችንን ቀይረናል! ከአሁን ጀምሮ የኔን ትዕዛዝ ተከተል» ብሎ ቁርጥ አድርጎ ነገረው::

እንደታዘዘው ወደግራ አዙሮ 70ኛው መንገድና ዌስት ኢንድ መጋጠሚያ ላይ በቀይ መብራት ቆመ::

ረዥሙ «ወደ ቀኝ ታጠፍ!» ብሎ በጩኸት አዘዘ::

በልሁ አሁን ሃሳባቸው ወለል ብሎ ታየው:: ወደ ቀኝ ሲታጠፉ «ፍሪደም ፕሌስ» ተብሎ በሚጠራው ከሰው እይታ የተከለለና የቆሻሻ መጣያ ባታ ወስደው ሊገሉት እንደሆነ አወቀ::

አሁን ካለበት ሁኔታ የማምለጥ እድሉ እየጠበበ እንደሚመጣ እርግጠኛ ሆኗል:: ሳያመነታ አንድ ነገር ማድረግ ይኖርበታል:: ጊዜ የለውም! ደግነቱ ኒውዮርክ ውስጥ በቀይ መብራት መታጠፍ ክልክል መሆኑ ጥቂት ሰከንዶች እንዲያገኝ ረዳው::

በግል ኑሮው ውሳኔ ለመወሰንና ለመፈፀም ለአመታት የማመንታት ባህሪይ የነበረው በልሁ አሁን ጥያቄው «የሞትና የህይወት» እንደሆነ ሲረዳ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ውሳኔ ላይ ደርሶ በተግባር መፈፀሙን ተያያዘው::



t.me/OLDBOOKSPDF

አይኖቹን ቀዩ የመንገድ መብራት ላይ ተክሎ ወደ አረንጓዴነት እስከሚቀየሩ የሚጠብቅ ትዕዛዝ አክባሪ መስሎ ታየ፣ በግራ እጁ የበሩን መክፈቻ እጀታ ዳስሶ አገኘው፣ ልክ ቀዩ መብራት ወደ አረንጓዴነት ሲቀየር በቀኝ እግሩ ነዳጅ ሰጥቶ በግራ እጁ በሩን ተረክ አድርጎ ወደ ውጭ ተወረወረ!

ከተቃራኒው አቅጣጫ የሚመጣው መኪና በሹፌሩ ፈጣን የመሪ አጠቃቀም ችሎታ ጎማዎቹ መንገድ ላይ በወደቀው በበልሁ ጭንቅላት ላይ ሳይወጡበት በኢንች ልዩነት ስላለፉ ሽሽቱ ከሞት ወደ ሞት ሳይሆን ቀረ::

የአንድ እግር ጫማው መኪና ውስጥ የቀረው ምስኪን አልሞትም ባይነት በሰጠው አንዳች ጉልበት ከወደቀበት ተስፈንጥሮ በመነሳት ሰው ወደማይጠፋበት ብሮድዌይ ጎዳና ጭንቅላቱን ከጥይት ቀብሮ፣ እንደ ሀገሩ የእርዳታ ጥሪ «ኡ..ኡ..ኡ» እያለ ተፈተለከ::

አላስሮጥ ያለውንም አንድ እግር ጫማ በመጣል ፍጥነቱን ይበልጥ ጨመረ:: «ብሮድዌይ» ላይ ከሚገኝ የመብራት ምሰሶ አጠገብ ቆሞ ፊቱን ወደ ኡኡታው አቅጣጫ የመለሰና በድንጋጤ አፍጥጦ አሯሯጡን ወደሚያየው ፖሊስ ጋር ሮጦ «አድካሚ ርቀቱን ጨርሶ ተዝለፍልፎ እንደሚወድቅ ሩጫ ተወዳዳሪ» እላዩ ላይ ተከመረበት::

ፖሊሱም ከላዩ ላይ በልሁን ገፍትሮ ጥሎት ራሱን በሚከላከልበት ርቀት ወደ ኋላ አፈገፈገ:: ከመቅፅበትም ሽጉጡን እንዳይነጠቅ ፈርቶም ይሁን የሚመጣው አይታወቅም ብሎ ላጥ አድርጎ በማውጣት «ምን ሆንሃል?» ... «ምን ተፈጠረ?» እያለ ይጠይቅ ጀመር::

በአካባቢው የነበሩ መንገደኞችና ሯሪዎች ለወሬው የቋመጡ ቢሆንም ፈርተው ከሩቅ ሁኔታውን እያጣሩ ከመጠጋታቸው በፊት የ«ጎዳና ተዳዳሪዎቹ» በኡኡታ ከእንቅልፋቸው ነቅተው ከሌሎች ቀድመው በመድረስ በልሁንና ፖሊሱን ከበቧቸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

በልሁ መሬት ላይ በርከክ ብሎ መኪናዋን ወደተለየበት አቅጣጫ እጁ እንደተዘረጋ ጣቱ እንደተቀሰረ ነው:: ለመናገር ትንፋሹን መሰብሰብ አልቻለም:: የልቡ ምት በልብሱ ላይ ያስታውቃል:: ህዝቡ በድንጋጤ አፍጥጦበታል፣ ከፊሉ ይስቅበታል::

በልሁ ብሮድዌይ ላይ «የብሮድዌይ ሾው» ሆነ:: ቀጥታ ከመድረክ የሚተላለፍ!

ትንፋሹን እንደምንም ከሰበሰበ በኋላ «ተዘርፌ .... ነው... አሁን.... ታክሲ ሹፌር ነኝ ዌስት... ሊንድ ላይ ... ዘረፉኝ .....» ለማለት በቃ::

ፖሊሱ በበልሁ አነጋገር ከውጭ የመጣ እንደሆነ ተገንዝቦ ዘና በማለት ሽጉጡንም ከማህደሩ መለሰ:: በልሁንም:- «ረጋ በል! ጊዜ ወስደህ ዘና በል!»

«በረጅሙ ለመተንፈስ ሞክር» እያለ ሲያረጋጋው ሞከረ በልሁም ትንፋሹን ለመመለስ እየታገለ «አኬ...አፊሰር» ...«አኬ አፊሰር» ብሎ ራሱን ለማረጋጋት ፀጥ አለ::

ፖሊሱም ሰውን ገለል እንዲል ከደረገ በኋላ «አሁን ቀስ ብለህ ንገረኝ ምን ተፈጠረ?» ብሎ እንደገና ጠየቀው:: በልሁ ሁኔታውን መግለጽ ሲጀምር የፖሊስ መኪና ሳይረን ከሩቅ ተሰማ:: ወዲያው በሁለት አቅጣጫ እያንጫጩ የተሰበሰበው ሰው ላይ ወጡበት! በሚያስብል ፍጥነት በረው በአጭር ርቀት ፍሬኑን እያስጮሁ አቆሙና ከየመኪናው እየበረገዱ ወጥተው ከአግረኛው ፖሊስ ጋር ተገናኙ::

በልሁም ትንፋሹ ተስተካከለ፣ የሞት ስጋቱ ቀርቶለት ጠላቶቹን ወደ እሚበቀል ፍጡርነት ተሸጋገረ:: «እንሂድ ላሳያችሁ አንድ ብሎክ ርቀት ላይ ነው ያሉት» እያለ ፖሊሶቹን ሊያሳምን ጣረ:: ደጋግሞ ወተወተ::

ፖሊሶቹ ግን ቃሉን እንዲሰጥ ወደ ጣቢያ ወሰዱት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳዩም ተከታታይ የምርመራ ፖሊስ ተመድቦለትና የሰነድ ቁጥር ተሰጥቶት ቃል መቀበሉ ቀጠለ: -

- የመልካቸው ቀለም
- ልዩ የፊት ምልክት
- የአይናቸው ቀለም
- የፀጉር አይነት
- ቁመት
- ግምታዊ እድሜ
- አለባበሳቸው
- የያዙት መሳሪያ
- ከየት አነሳሃቸው?
- የት ውሰደን አሉህ? ወዘተ ጥያቄው ተዥጎደጎደ::

በልሁ ለተጠየቀው ሁሉ የሚያስታውሰውን የመለሰ ቢሆንም ነገራቸው ሁሉ «ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ» ሆኖበታል:: «ወዲያው ቢሄዱ ኖሮ እንገታቸውን እናንቃቸው አልነበር !፣ ይሄ ሁሉ ምርመራ ምን ፋይዳ አለው?» ብሎ በሸቋል::

ቃል መስጠቱ እንዳለቀ አንገቱ ስር የተቀረደደውንና ሲወድቅ የተላላጠውን ለመታከም ሆስፒታል መሄድ ይፈልግ እንደሆነ ቢጠይቁት «አልፈልግም» ብሎ፣ ጉዳዩን ከያዘው መርማሪ ፖሊስ ጋር ከወንጀለኞች የፎቶ አልበም ውስጥ ዘራፊዎቹን ለመምረጥ እንዲችል ቀጠሮ ወስዶ በባዶ እግሩ ፖሊስ ጣቢያውን ለቆ ወጣ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመሃከላቸው አንደኛው ፖሊስ «ታውቀዋለህ እንዴ?» ከማለቱ «አሁን ከ30 ደቂቃ በፊት እዚህ ነበር፣ የኒውዮርክ ከተማ ታክሲ ነጂ ነው....» ብሎ ሁኔታውን ሁሉ አስረዳቸው::

በልሁ ፀጥ ብሏል:: አልኸኛነቱ ከውስጡ ይተናነቀዋል:: ምንም ሳይጠይቁት ጤነኛውን ሰው ይደበድባሉ፣ ነፍሰ ገዳይ ዘራፊውን እስኪያመልጥ ጊዜ ሰጥተው ከዛ ከፎቶ አልበም ውስጥ ይፈልጉታል:: ሊገባው ያልቻለ የፖሊስ አሰራር ነው::

ፖሊሶቹ በተፈጠረው ያለመግባባት በጣም አዘኑ ባደረጉትም ተፀፀቱ:: ወዲያውኑ ካቴናውን ፈትተው ይቅርታ ጠይቀው እቤቱ አደረሱት::

በልሁ በሩን ከፍቶ ሲገባ የግድግዳው ሰዓት በትላንቱ ጡጫ መስራቱ አላቆመም ከጠዋቱ ለ1 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል::

በልሁም «በሁለት አለም ሰዎች» ተቀጥቅጦና ተሰቃይቶ መኖሩ አላቆመም::

ኒውዮርክም ሳታንቀላፋ ነጋ::

ቴሌቪዥኑም ሲ.ኤን.ኤን ላይ እንዳለ አልጠፋም:: በማለዳው ፕሮግራሙ ለተመልካቾቹ የዜናን አለም አዳር ያስኮመኩማል::

በልሁም «ወይኔ በልሁ! ይሄን ጊዜ በቲቪ ከሚታየው ዜና ውስጥ አንዱ የኔ ይሆን ነበር» ብሎ አሰበ::

መልዕክት እንዳለው ለማሳወቅ ቀይ መብራት ብልጭ ድርግም የሚያደርገውን የስልኩን መልዕክት መቀበያ ተጭኖ ልክ እንደ ጠዋቱ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብሎ ረስቶ የሄዳትን ሲጋራ አቀጣጠለ::

«ዛሬ ማታ ከስራ ስወጣ እመጣለሁና ስራ እንዳትሄድ .... ለብርቱ ጉዳይ ነው የምፈልግህ ... እሺ! ... ቻው!» አለ የአንዕስታይ ድምፅ ከመልዕክት መቀበያው ውስጥ «ያች ልጅ» ነች አሁንም ተስፋ አልቆረጠችም::



t.me/OLDBOOKSPDF

« አንቺም ለበለጠ ብርቱ ጉዳይ ለኔ ታስፈልጊኝ ነበር ። ለህይወቴ ሳይሆን ለበድኔ አሳት» በልቡ። እሰቱ በመጥፎ ቢያልቅ ኖሮ ሁሉ ነገር በሷ ላይ እንደሚወድቅ አሰቦ።

ሲጋራውን በሰል አረገውና በጭስ ውስጥ ስለ ህይወቱ ማሰቡን ቀጠለ። ዛሬ ግን የደረሰበትን ሁሉ ሲያሰላስል ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ሰራሱ ስቅስቅ ብሉ አለቀሰ....

ነገሩን አውጥቶ አውርዶ ሌሎች ለሱ ከሚያለቅሱለት በእጅጉ ይሻላልና ፈጣሪውን አመሰገነ።

«ዳግም ፈጠርከኝ!» አለው በአንድ ቀን ውስጥ የደረሰበትን የህይወት ዕጣ በህሊናው ቃኝቶ ።

እውነት አለው! «ዛሬ ዳግማግዊ ልደቱ ነው!»

እንባቢ ሆይ!

የበልሁ ታክሲ 65ኛውና አምስተርደም ላይ ከሚገኝ «ፕሮጀክት ሀውስ» (መንግስት በድጎማ የቤት ኪራይ የሚከፍልላቸው ህዝቦች ከሚኖሩበት ህንፃ) አጠገብ ቆማ ተገኘች።

- ወንጀለኞቹ አልተያዙም።

«ያች ልጅም» ተስፋ ቆርጣ «ከበልሁ ወዲያ እርም አበሻ» ብላ ሳይሆን አይቀርም ፈረንጅ አግብታ ፤ልጆች አፍርታ «ያቺ ሴትዮ ሆናለች»

- በልሁን ታክሲውና ኒውዮርክ አሁንም አብረው ናቸው!



t.me/OLDBOOKSPDF

# ማክሰኞ

ኒውዮርክ ቀን ቀን ምን እንደምትመስል አትጠይቁኝ:: እኔ ማለት የሌሊት ወፏ ነኝ:: ፀሃይ ጠልቃ እስክትወጣ ባለው ጊዜ ውስጥ ከላይ እታች ስበርባት አድርና ወደ ጎጆዬ ጥልቅ ነው:: ከጨረቃ ተላምጄ ፀሃይን ከተለየኋት አመታት ተቆጥረዋልና እርሜን በቀን የግድ ከተማ መውጣት ካለብኝ የፀሃዩ ብርሃን አይኔን ያሳውረኛል:: ልክ እንደ ጅብ::

ፀሃይ ወደ ጎጆዋ ስትገባ እኔ ከጎጆዬ ወጥቼ ታክሲዬን መዘወሬን ጀምሬያለሁ:: ማክሰኞ ቀን::

ማክሰኞ ቀንን አልወደውም እሱም አይወደኝም:: ራሴን ቢያመኝ ማክሰኞ፣ ፖሊስ ቲኬት ቢሰጠኝ ማክሰኞ፣ ወፈር ያለ ቢል ቢመጣብኝ የግድ ቀኑ ማክሰኞ መሆን አለበት:: ታዲያ እንዴት አድርጌ ማክሰኞን ልውደደው?

ይህ ሁሉ ሆኖ የማክሰኞና የእኔ ነገር በንፁህ ገጠመኝነቱ ይገርመኛል እንጂ ሌላ እምነት ውስጥ ገብቼ በመፍራት የፈለኩትን ለማድረግ ተቆጥቤ አላውቅም:: ለዚህም ነው ዛሬም  በማክሰኞ እንደሁል ጊዜዬ ታክሲዬ ላይ ጉብ ያልኩት::

የዛሬው ማክሰኞ ግን ሲታረቀኝ ፈልጓል መሰል ያለወትሮው ዕድል ሚዛኑን ወደእኔ ደፍቷል:: መጫን፣ ማውረድ፣ ወዲያው መጫን፣ ገንዘብ መቁጠር ሆኖልኛል::

ተሳፋሪ ፈላጊ መሆኔን የሚያሳየው የጣራ መብራት ብዙም ስላልበራ እንደቀዘቀዘ ሲሆን የሂሳብ ቆጣሪ ሜትሬ ግን በስራ ብዛት እረፍት አጥቶ ግሏል::

ለአንድ 5 ሰዓት ያህል ጥሩ ጥሩ ስራ እያገኘሁ ቆንጆ ብር ከሰራሁ በኋላ ከምሽቱ 4 ሰዓት አካባቢ ተሳፋሪ ሳወርድ በተከፈተው በር ሌላው ገባ:: በጂንስ ሸሚዝና ሱሪ ላይ ቁልፉ ያልተቆለፈ ጥቁር የቢጋ ካፖርት ያደረገ ጥቁር አሜሪካዊ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚጠይቀኝ ጥያቄ ሁሉ አንጉል መልስ እየመለስኩ የውስጤን የብሽቀት ንዳድ ላራግፍበት ተዘጋጅቻለሁ::

ትንሽ ከተንዝዝን በኋላ «ሄይ ሹፌር! ዝንባሌህ ምንድነው?» አለኝ:: እንዳልሰማ ሆንኩበት::

«ሰምተኸኛል ወይ ሹፌር?» አለኝ ሞቅ ባለ ድምፅ::

«ሹፌር አይደለም ስሜ! ይሄ የምታየው ስሜ የተለጠፈው ተሳፋሪውን ከሹፌሩ ጋር ለማስተዋወቅ መሰለኝ» አልኩት

«እሱን እርሳው እኬ ዝንባሌህን ንገረኝ» አለኝ በማግባባት ቃና::

«ታክሲ መንዳት ነው» አልኩት ይለይለት ብዬ::

«ኖ..ኖ..ኖ ጥያቄዬ በምንድነው የምትተዳደረው ሳይሆን ዝንባሌህ ማለትም የተፈጥሮ ስጦታህ ሆኖ ደስ እያለህ የምታደርገው ነገር ምንድን ነው? » ማብራሪያቱ ነው በሱ ቤት «ዝንባሌህ» የሚለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ያልገባኝ መስሎት::

«ታክሲ መንዳት!» አልኩት መልሼ::

«ታክሲ የምነዳው ዝንባሌዬ ስለሆነ ነው የምትለኝ?» እንደማሾፍበት ዘግይቶ ስለገባው በመብሸቅ ስሜት::

«ትክክል! እኔ ታክሲ የምነዳው ዝንባሌዬ ስለሆነ ነው!:: ዝንባሌዬ ባይሆን ኖሮማ ሌላ ስራ ለመስራት ዕውቀቱም ገንዘቡም አለኝ» አልኩት ንቀትህን አቁም ለማለት::

አሁንም ምን ነገር እንደሚያብላላ አላውቅም ፀጥታ ሰፈነ:: መንገዳችንም ተገባዶ ከዋናው ከተማ ርቂ ጨለምለም በሚል የሰፈር መንገድ ላይ በመንዳት ላይ ነኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF

«ትሰማኛለህ» የሚለው ኃይለቃሉ ድንገት እንደ ነጎድጓድ ተሰማኝ:: «ይሄ ሰው አይተወኝም እንዴ? ሲፈልግ ሄዶ ሚስቱን ይጨቅጭቅ» ብዬ ዘግቼው መንዳቴን ቀጠልኩ::

«የኔ ዝንባሌ ምን እንደሆነ ልንገርህ?» አለኝ::

«ምንድነው?» አልኩት በማሾፍ ከቅርጫት ኳስ አያልፍም ብዬ::

«የኔ ዝንባሌማ! የሰዎችን ጭንቅላት እንደዚህ ግም! ... አድርጎ ማፍረስ ነው!...» «ግም!» ሲል በቀኝ አይኔ በኩል ያየሁትን ማመን አቅቶኛ ዞር ስል ከመላጣው የበለጠ የሚያብረቀርቅ ሽጉጥ ነው:: በ2 እጁ ሽጉጡን ደግኖ ኢላማው ላይ የሚያነጣጥር ተኳሽ በመምሰል «ብቻ አይናቸው እያየ ግም! ... ግም! አድርጎ የራስ ቅላቸውን ማፍረስ» ማለቱን ቀጠለ::

መቶ በመቶ ያልጠበኩት ነበርና የማደርገው ጠፍቶኝ ተሸበርኩ::

ሰውዬው ግም ባለ ቁጥር ጭንቅላቱ እንደዱባ ፍርስርስ የሚል እየመሰለኝ ሽምቅቅ እላለሁ:: መኪናዋም በደመነፍስ ስለምትነዳ ፍጥነቷ ወረደ:: ደግነቱ ሃይዌይ ውስጥ ያለመሆናችን ነው እንጂ አደጋ ላይ እንደምንወድቅ ምንም ጥርጥር አልነበረውም::

በደቂቃ ልዩነት ውስጥ ሁኔታዎች ተለዋውጠው «ወንድነት» የማያዋጣበት ሁኔታ ውስጥ ገባሁ::

ከመቅፅበት ወደ አሳዛኝ ፍጡርነት ተለውጬ በኮሰሰ ድምፅ «ጌታዬ!» ብዬ ተጣራሁ:: የሰማዩን ሳይሆን ከጀርባዬ የተቀመጠውን::

«ምንድነው?» አለኝ /ነብር ሆኖ ተቆጥቶ/

«ዝንባሌዬ... ምን እንደሆን ... ልንገርህ» አልኩት /በኮሰሰና በተቆራረጠ ድምጽ



t.me/OLDBOOKSPDF

«ቀጥል!» አለኝ /በእጭሩ/

«መፀለይ! የኔ ዝንባሌ ጠዋትና ማታ ተንበርክኮ ለፈጣሪ መፀለይ! 4 ልጆቼን እንዲጠብቅልኝ፣ በዚህ አለም ላይ በሰው ልጆች መካከል ያለውን ልዩነት እስወግዶ ሁሉም በእኩልነት እንዲተያዩ እንዲያደርግ! መፀለይ ነው ዝንባሌዬ» አልኩ /ለቅሶ የተቀላቀለበት በሚመስል የልመና ድምፅ/

«የምትለው አልገባኝም እስቲ ቀስ ብለህ ንገረኝ» አለኝ

ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ደገምኩት::

ሳቁን ለቀቀው!:: አሳሳቁ እራሱ አስደነገጠኝ:: ወፈፍ የሚያረገው አይነትም መሰለኝ::

«ሹፌር ተረጋጋ! እኔ ወንጀለኛ አይደለሁም! ፀረ-ወንጀለኛ የኒውዮርክ ፖሊስ ኦፊሰር ነኝ» አለና ባጁን አውጥቶ አሳየኝ::

ነፍሴ ሞትን አይታ ተመለሰች:: ሰውነቴ ውስጥ የገባው ፍርሃት ሊወጣ ባለመቻሉ ሊረጋጋ ተሳነው::

ፖሊሱ ደበልጥ ቀረበኝና እንድረጋጋ ጀርባዬን መታ መታ ካረገኝ በኋላ «የታክሲ ነጂዎችን ችግር አውቃለሁ:: ከተማ ውስጥ የተሻለ ፍራንክ ስለምትሰሩ ስራ ባለበት ሰዓት ወደ ውጭ መውጣት ጊዜያችሁን እንደሚያቃጥልባችሁ ይገባኛል:: እኔም ደግሞ ቤቴ መሄድ አለብኝ:: እኔ ቦታ ላይ ብትሆን ከእኔ የተለየ የምታደርግ አይመስለኝም:: ለዚህም ነው ያን ሁሉ ትዕቢት ስታሳየኝ ያልተናደድኩት:: ዝንባሌዬ ብዬ የነገርኩህ ዝንባሌዬ ሆኖ ሳይሆን የዋህ ስለመሰልከኝና በዚህ በኒውዮርክ ውስጥ ብዙ አይነት የማትጠብቀው ወንጀል እንደሚሰራ ለዘላለም እንዳትረሳና እራስህን እንድትረዳ ለማድረግ ነው.. .. ..

በዚህ ከተማ ውስጥ እንተንና ተሳፋሪውን የሚለየውን ጥይት የማይበግረውን የመስታወት መከለያ ሳታደርግ በፍጹም እንዳትነዳ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ግድያዎች ስላየሁና አንተም በአደጋ ላይ ያለህ ሰው ስለመሰልከኝ ነው ያን ሁሉ ያደረኩት::...... .. ህይወትህን የምታድንበት ትምህርት ይሆንሃል ብዬ ነው» ብሎኝ የደርሶ መልስ ያህል ገንዘብ ከፍሎኝ መስቀልኛ መንገድ ላይ አውርደው ተለያየን:: ያውም ደህና እደር ብሎ መልካሙን ተመኝቶልኝ::

እኔም ቀጥታ ወደ ቤቴ ነዳሁ:: በመንገድ ላይ እያለሁ ቀኑ ትዝ አለኝ:: ማክሰኞ ነው:: «ድሮስ ማክሰኞና እኔ» ከማለት በስተቀር ምን ልበል?

አንባቢ ሆይ: - ብዙ ታሪኬን ያጫወትኳቸው ሰዎች የዚህን ፖሊስ «የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ» አልተስማሙበትም:: ሰውዬው የሚገኝ አልሆነም እንጂ መክሰስ ነበረበት ያሉኝም ትንሽ አይደሉም እርስዎስ ምን ይሉ ይሆን?

ለማንኛውም የመስታወት መከታውን በነጋታው አስገባሁ:: ባሁን ሰአት ደግሞ «የኒውዮርክ የታክሲና የሊሙዚን ኮሚሽን» ሁሉም ታክሲ መከታ ወይንም ካሜራ እንዲኖረው የሚያስገድድ ህግ አውጥቶ ተግባራዊ ሆኗል::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ያልተማረው ምሁር

የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ታክሲ ነጂ ነው::ከወራት በፊት አሳፍሮት የነበረ መንገደኛ ትራፊክ በሚተላለፍበት በኩል ከፍቶ ሊወጣ ሲል በሩን አስገጭቶበት ኖሮ መኪናውን ካስጠገነ በኋላ ዳግም እንዳይጋጭበት ከውስጥ በኩል በሮቹ ላይ በእንግሊዝኛ «መውጫ» እና «መውጫ የለም» የሚል ፅሁፍ ጽፎ በመለጠፍ ሲነዳ ከረመ::

አንድ ቀን የሆነች መንገደኛ ጭኖ ሲሄድ በአብዛኛው ተሳፋሪ እንደተለመደው :-

«ከየት ሃገር ነው የመጣኸው? »

«ምን ያህል ግዜ ሆነህ?»

«የአሜሪካንን ኑሮ ትወደዋለህ ወይ?» በማለት ትጠይቀዋለች ::

ሹፌሩም መልሶቹን እንደቅደም ተከተላቸው እየመለሰ 3ኛው ጥያቄ ላይ «አሜሪካ በርግጥ ጥሩ አገር ነው... ከተጣጣርክ ያልፍልሃል» ይባላል:: ግን ይሄ አባባል አንዳንዴ አይሰራም:: ለምሳሌ ብዙ ስደተኞች ለፍተው ተምረው በተማሩት ትምህርት ስራ እያገኙም:: እኔም ከነሱ ውስጥ አንዱ ስለሆንኩ ደስተኛ አይደለሁም ቢያንስ ታክሲ ነጂ መሆን አልነበረብኝም.......» እያለ ማማረሩን ተያያዘው::

ተሳፋሪዋ አቃቂር አውጭ አይነት ሰው ኖራ፣ ብሶቱን አዳምጣ ስትጨርስ:-

«ታዲያ ኮሌጅ ከጨረስክ! እንዴት ይሄንን እንኳ አስተካክሎ መፃፍ አቃተህ?» አለችው:: በማሽሟጠጥ አነጋገር በር ላይ ወደተለጠፈው ፅሁፍ እያሳየች::



t.me/OLDBOOKSPDF

ዞር ብሎ ሲያየው በቀኝ «Exit» በግራ «Don't Exist» ይላል::

ከሁለቱ ዕሁፎች አንደኛው ስህተት እንደሆነ ቢረዳም ስህተቱ ምኑ ጋር እንደሆነ ግን ሊያውቀው አልቻለም ::

ሹፌሩ ጥሩ ጉርሻ ለማግኘት «ባለ ድግሪ ነኝ» ቢልም ተሳፋሪ ለማድረስ ካልሆነ በቀር ኮሌጅ በር ላይ ደርሶ አያውቅም:: እንደ «ኢቬሬዲ ባትሪ ድንጋይ ምልክቷ ጥቁር ድመት» 9ኛ ክፍል ወገቡን ይዞ አሳሳልፍ ሰላለው « ትምህርት ቤት በቃኝ!» ብሎ ያቆመ ሰው ነው::

ይሁንና ዕጣ ክፍሉ ሆኖ የትምህርት ቤት ነገር ባይሳካለትም «የመንገድ ላይ ቋንቋ» ልዩ ተሰጥዖው የሆነና ከመጽሃፍት የሚማር ብሩህ አይምሮ ያለው ፍጡር ስለሆነ ስህተቱ የቱ ጋር እንደሆነ ለመለየት ወዲያው ዘዴ በመቀየስ ተሳፋሪዋን: -

«ምኑ ላይ ነው ስህተቱ?» አላት

ዱ · ዓ/ተ

«S መኖር አልነበረበትማ!» አለችው አሁንም አይገባውም እንዴ? ይሄ ውሽታም ደደብ ማለቷ በግልጽ ያስታውቃል::

ቀስ ብሎ ሲያነበው የሚያወጣው ድምፅ «ኢግዚስት» የሚል ነው::

« ኢግዚስት» የሚለው ቃል ደግሞ ከዚህ በፊት ከመንገድ ላይ ለቀም ያደረገውና የሚያውቀው ቃል ነው! :: በዚህ ላይ ከሁኔታው ጋር ሊሄድ የሚችል ቃል!::

በ «ኖ ኢግዚት» ውስጥ «መውጫ» ስላገኘ ጀነን አለና: -

«በሉ በኩል ውረጂና ስህተት መሆኑን ታይዋለሽ!» አላት::

«ምን ለማለት ፈልገህ ነው? » አለች እባባሉ ግራ ያጋባት ተሳፋሪ ::

«ህልውናሽ ያከትማል!» አባባሉ በጥብጠወ ካልጋቷት አይገባትም እንዴ? እቺ ደደብ ማለቱ በግልፅ ያስታውቃል::

«አኬ! ኖ ኢግዚስት ... ዜር ኢዝ ኖ ኢግዚስተንት እንደ ማለት.. አኬ ስህተቱ የእኔ ነው ይቅርታ!» ብላ ተረታች::



t.me/OLDBOOKSPDF

አጅሬ በማሽነፉ ኩራ ፡ ሌላ ፈታኝ ጥያቄ እንዳታመጣበት ኮስተር ብሎ በመንዳት ከመድረሻዋ ጥሎ ተገላገላት ።

ይሄ «ያልተማረ ምሁር» እንደዚህ ያለ «አታቂር አውጪ» ተሳፋሪ እንዳያዋርደው የጉርሻ ማግኛ ዘዴውን እንደሁኔታው ይቀያይረዋል።

የኮሌጅ ተማሪ አድሜ ላይ ያሉ ወጣቶችን ወይም እድሜያቸው ከኮሌጅ ትዝታ ያልራቀ ተሳፋሪዎችን ሲጭን ለብዙ የኮሌጅ ህይወት ጥያቄ ስለሚያጋልጡት እዚህ ሀገር ነው የተማርኩት ለማለት አይደፍርም።

የሆነ ቀን አንድ ወጣት ተሳፋሪ ታክሲው ውስጥ ይገባና ጨዋታ ይጀምራሉ። የተለመዱት ጥያቄዎች ያን ዕለትም አልቀሩም፡ -

«ከየት ነው የመጣኸው?»

«ከኢትዮጵያ»

«እውነትክን ነው!? /በማዳነቅ አነጋገር /

«ጭጭ» /ምን የሚያስደንቅ ነገር መጣ? አሁንኑ ስለድርቅ ሊጠይቀኝ ብሎ መጠበቅ ጀመረ/

«የእሬጮኛዬ አባት ኢትዮጵያ ውስጥ የአሜሪካን ኤምባሲ ሰራተኛ ነው።»

«እዛ የቆየ ነው?» /በልቡ ለአንድ ዘመዱ ቪዛ ለማስገኘት እያሰበ/

«3 ወሩ ነው፤ ከኬንያ ተዛውሮ ገና መሄዱ ነው» አለና «አንተስ አሜሪካ ቆይተሃል?»

«15 ዓመት አደረግኩ»

«ስትመጣ ወጣት ነበርክ?» /እድሜውን ለማወቅ /

«በ23 ዓመቴ ነው የመጣሁት» /40ን ፊርቶ 38 ላይ ከቆመ አመታት ተቆጥረዋል።/

«ታዲያ ለምን ትምህርት ቤት አልሄድክም?» /ብትማር ታክሲ አትነዳም ነበር ብሎ/



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሀገር ቤት ነው ትምህርቴን የጨረስኩት» / በኮሌጅ ጥያቄ ላለመፋጠጥ/

«ምን አጥንተህ ተመረቅክ?» /የሚጠቀማቸው ቃላቶች በሙሉ «የመንገድ» ስለሆኑ ተጠራጥሯል/

«ኬሚካል ኢንጂነሪንግ» /ኬሚካል ኢንጂነሪንግ የጨረሰ የሚያውቀው ታክሲ ነጂ አለ ዛሬ እሱን ልሁን ብሎ /

«እና በተማርከው ትምህርት ለሀገርህ ምን ሰራህ?»

«ድልድይ!» /በድፍረት ሞቅ አድርጎ/

«ድልድይ!» ሳቁን አፍኖ «ማን ይባላል የድልድዩ ስም?»

ሹፌሩ እንደፈራው ጥያቄ ስለበዛበትና በመስተልኛ ጥያቄ ሊጋለጥ ነው ብሎ ስለሰጋ ቆጣ አለና:-

«ሰውዬ! ስራ ልትቀጥረኝ ፈልገህ ከሆነ እንደኛውን ስምን ሬዙሜዬን አላመጣልህም! ...ድልድይ የሚሰራ ካምፓኒ አለህ እንዴ?» አለው

ተሳፋሪወም በሳቅ እየተንከተከተ «አረ በፍጹም ካምፓኒ የለኝም! ብቻ እንደው አማቼ በዛ ድልድይ ላይ እንዳይነዳ ደውዬ ልነግረው ፈልጌ ነው» አለው::

አጅሬ ሹፌር በተሳፋሪው የሚሽሚጠጥ አሳሳት ስህተት እንደሰራ ስለተረዳ እንደ ኤግዚስቱ ጊዜ ስህተቱን ለማወቅ ቢያሰላስልም የሰውየው መ... ስለደረሰ እንደከነከነው ታክሲውን አቆመ::

ተሳፋሪውም ሃያ ዶላር ሰጠውና :-

«በህይወቴ የድልድይ ስራ ተቋራጭ ኬሚካል ኢንጂነር አንተን አየሁ! ቢሆንም ጨዋታህን ወድጄዋለሁ» አለውና ጀርባውን መታ አድርጎ «መልስ አልፈልግም !» ብሎት ወረደ::

ሹፌሩ «እሃ ለዚህ ነዋ !.... እኔ ጉርሻዬን ካገኘሁ ተሳሳትኩ አልተሳሳትኩ የት አባክ! ታገኛኛለህ» የሚለውን የራሱን ድምፅ በጆሮው ሰማው::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ስድስቱ ሱፐር ሞዴሎች

ለአዲስ አመት ዋዜማ ነው:: ያውም አለም በሙሉ አሮጌውን አመት ሸኝቶ አዲሱን ለመቀበል አይኑን ቴሌቪዥን መስኮት ላይ በሚተክልባት ኒውዮርክ!

ከተማዋ በህዝብ ተጥለቅልቃለች:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ በአሉን ለማክበር የመጡ እንግዶቿንና ኗሪዎቿን ለማስተናገድ ፖሊሶቿ ገና በጊዜ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል::

የከተማዋ 12000 ቢጫ ታክሲዎች፣ በሺህ የሚቆጠሩ «ብላክ ካር»ና «ጅፕሲ» በመባል የሚታወቁ ታክሲዎች፣ ለመዚናኞች በዚህ ዕለት ብዛታቸው ለተጠቃሚው በቂ ስላልሆነ ታክሲ ለማግኘት ሹፌሮቹን በገንዘብ ኃይል መደለልን ይጠይቃል፣ ለዛውም ባዶ ታክሲ ለማግኘት እድለኛ ከተሆነ::

ያን ዕለት ብዙ ሚሊዮን ዶላር በታክሲ ነጂዎች ኪስ ይገባል::

በእኔ ለመዚን ካምፓኒ ውስጥም ይህ ቀን እንደ «ቦነስ ቀን» ስለሚቆጠር አመቱን በሙሉ ለሰጠሁት ጥሩ ግልጋሎት ጥሩ ቦነስ እንዳገኝ ስድስት ታዋቂ ነጭ አሜሪካውያን አንዕስታይ ሱፐር ሞዴሎችን እንዳገለግል መድቦኛል::

በአዲስ አመት ዋዜማ ከእያንዳንዱ ተሳፋሪ ቢያንስ የ100 ዶላር «ጉርሻ» ይገኛልና ከ600 ዶላር በላይ የሚገኝበት ስራ በመመደቤ ሞራሌ ከፍ ብሏል::

ሞዴሎቹ ያዘዙት ነጭ ሱፐር ስትሬችድ ለመዚን ስለነበር እኔም ነጭ በነጭ ቶክሲዶ ግጥም አድርጌ ለብሼ ወጣሁ::

ደምበኞቼን የማነሳበት የዌስትቸስተሩ «ራይ ታውን ሒልተን» ሆቴል ገባሁና ለእንግዳ ተቀባዩ መምጣቴን እንዲነግርልኝ አሳውቄው ወደ ለመዚኔ ስመለስ በምድር ስገነቱ ውስጥ ባለው የግድግዳ መስታወት ውስጥ እራሴን ለመጨረሻ ግዜ አየሁት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁመት የለም እንጂ ቁመት በነበረ

እምላክ አንተን እንጂ ሌላ መች ፈጠረ:: ተብሎ የሚዘፈንልኝ አይነት ሆ
ሰሁ::

ስድስቱ ሱፐር ሞዴሎች እጅብ ብለው ከሆቴላቸው ሲወጡ ከጎጂቻቸ
የተለቀቁ ነጫጭ እርግቦች ይመስላሉ::

እነዚህን ምርጥ የሆነ « አዋቂ » ብዙ ሚሊዮን ብሮች ተከፍሎት በሙሉ
አይን እንዳይታዩ የሚገስጥ እንዳች ውበታዊ ኃይል አጎናጽፎና አሳምሮ በል
ትዕዛዝ የሰራቸው የእጅ ስራዎች የሚመስሉ ፍጡሮችን የእናት ማሕፀ
በመፍጠሩ «ፐ» ብዬ ተደነቅኩ::

እንደኛቸውን ከሌላኛቸው የመለየቱን ነገር ለወንድ ጓደኞቻቸው መተ
ይቀላል ብዬ የተውኩት በሩን ከፍቼ ለሳምታዬን እያስቀደምኩ አንድ በእን
በሀሊናዬ ፎቶግራፍ እያነሳሁ ካስገባኋቸው በኋላ ነው::

እርግቦቼን ጭኜ ወደ መንሀተን ተፈተለኩ:: በተሰጠኝ ፕሮግራም መሰረት
የመጀመሪያ መቆምያችን ወደ ሆነው «ሮክፌለር ማዕከል» ከሚገኘው በአለም
ትልቁ ከሆነው የገና ዛፍ አደረስኳቸውና በሬን ከፍቼ ከሚርመሰመሰው ቱሪስት
መሃል «እንትፍ እንትፍ .....ከአይን ያውጣችሁ» ብዬ ለቀቅኳቸው::

ህዝቡ መሃል ሲገቡ ሞዴሎቹ ይበልጥ ደመቁ:: የሰውን የአይን ትኩረት
እንደሚስቡ ስለሚያውቁት ይበልጥ ኩራ፣ ፍንድቅድቅ እያሉ ፈኩ:: አድናቂና
ተደናቂ ተገናኙ:: እነሱ ከዛፉ ጋር ህዝቡ ደግሞ ከነሱ ጋር ፎቶግራፍ ይነሱ
ጀመር:: የካሜራዎች ቅዕበታዊ ብርሃንና ጨለማው ግብግብ ገጠሙ:: መኪናዬ
ላይ ተደግፌ በማየው ትርኢት ተመስጬ ማነው? «ቁንጅና ቢራ በጨበጠ ሰው
አይን ውስጥ ነው» ያለው እልኩ:: ያባባሉ ስሁተት ቁልጭ ብሎ ስለታየኝ::

የቱሪስቶቹ ከሞዴሎቹ ጋር ፎቶግራፍ መነሳት ሽሚያ ሲገርመኝ ሁለት
ግብረሰዶማውያን ፎቶግራፍ አብሬአቸው እንድነሳ ጠየቁኝ:: ስራ ላይ ነኝ ብዬ



t.me/OLDBOOKSPDF

መለስኳቸው:: ስለግብረሰዶማውያን የነበረኝ ጥላቻ መቀነሱ ገረመኝ:: ከሣገር ቤት የመጣሁ ሰሞን ቢሆን «በሌባ ጎማ» እስተናግዳቸው ነበረ!

ለማንኛውም ብዬ መኪናዬ ውስጥ ገባሁ:: ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሞዴሎቹ መጥተውልኝ ለእራት «ፎር ሲዝን ሆቴል» ወሰድኳቸው::

ከእራት እንደወጣ ልዩ የሙዚቃ ዝግጅት ወደሚያዩበት ወደ «ሬዲዮ ሲቲ ሚዩዚክ ሆል» አመራን::

አዳራሹ ዙሪያውን ጨረቃ መስሏል:: በህንፃው ዙሪያ የሚርመሰመሰውና የሚጋፋው ለመዚን ብቻ ነው:: የግልና የየቴሌቪዥን ጣቢያው ቪዲዮና ፎቶግራፍ አንሺዎች አመቺ አመቺ በታዎች ላይ ካሜራቸውን ተክለው ከለመዚን የሚወርዱትን ታዋቂ የፊልም ተዋንያን፣ የሙዚቃ ሰዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ሞዴሎች ወዘተ ላይ ፓውዛቸውን እየለቀቁ እያንዳንዷን ነገር ይቀርጻሉ::

የፖሊሱ ብዛት በራሱ ለነዚህ ምርጥ ዜጎች ደህንነት ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጥ ይናገራል::

እኔም ቀስ በቀስ ማውረጃው ቦታ ደረስኩና በፕሮግራማቸው መሰረት ከምሽቱ 5:30 ደቂቃ እንደማነሳቸው አስታውሼ በሩን ከፈትኩ:: እያንዳንዳቸው እያመሰገኑኝ ወደ አደራሹ አመሩ:: እዚህ ግን ከነሱ የበለጡ ታዋቂ ግለሰቦች በብዛት ስላሉ ነው መሰለኝ እንደ ፎክፌለሩ ማዕከል ግቤ ኩራ አላሉም፣ ራመድ ራመድ እያሉ ወደ አዳራሹ ዘለቁ::

ወዲያው ትራፊክ ፖሊሱ «ተንቀሳቀስ» አለኝ:: በእጁ የምሄድበትን አቅጣጫ እያሳየኝ:: ተንቀሳቀስኩ:: ሴንት ፓትሪክ ቤ/ክርስቲያን አካባቢ ማቆሚያ አገኘሁና ለማቆም ሳስተካክል 4 ሰዎች ደህና ገንዘብ ከፍለው 14ኛው መንገድ እንዳደርሳቸው ለመኑኝ:: አንዳንዴ ሰዓት ሲኖረን የምናደርገው ነውና ጫንኳቸው:: ከዛም ከከተማ የማያስወጣ አንድ እራት የሚሆን ስራ አገኘሁና ሰራሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዛ በኋላ እርግቦቹን ለማንሳት ወደ ራዲዮ ሲቲ አቀናሁ:: በመንገዴ ላይ ፅጌረዳ አበባ የሚሸጥ አሂሪ አየሁና «ለሞዴሎቹ ብሰጣቸው ጉርሻዬ ይጨምራል፣ እነሱም ለእኔ ጥሩ ስለሆኑልኝ ደስ ይበላቸው» አልኩና ስድስት ፅጌረዳ እያንዳንዷን በ 4 ብር ሂሳብ ገዛቼ መውጫቸው ላይ በጊዜ ቦታ ይዤ መጠባበቅ ጀመርኩ::

ተሳፋሪዎቹ በተመለከቱት የሙዚቃ ዝግጅት ተደስተው እየተሻሙ እያወሩና እየፈነደቁ ከአዳራሹ ብቅ አሉ:: እኔም በእጅ ምልክት ያለሁበትን አሳየኋቸውና አጠገቤ ሲደርሱ አበባ ማደል ጀመርኩ:: እያቀፉና እየሳሙ ስጦታቸውን ተቀበሉኝ:: አንዳንዶቹ ጨኸታቸውን አቀለጡት:: ከልባቸውም አመሰገኑኝ ምትሃቱ ሰራ አልኩ!

አዲስ አመት ሊቀየር የቀረው ከ30 ደቂቃ ያነሰ ጊዜ ነው:: የሚቀጥለው ፕሮግራማችን በተቻለ መጠን ወደ «ታይምስ ስኩዌር» ለመቅረብና የኳሷን አወዳደቅ ከህዝቡ ጋር ለማክበር ነው:: ግፊያዬን ቀጠልኩ:: አንዳንዴም የለመዚኔን አፍንጫ ከመኪኖች ፊት እያስገባሁ በማስቆም እየቀደምኩ ወደ አደባባዩ ልቀርብ የምችልበት ድረስ ገፋሁ::

ሞዴሎቹ አካባቢውን ማየት እንዲችሉና እነርሱም እንዲታዩ የኤሌትሪክን ቁልፍ ተጭኜ የለመዚኑን ጣራ ከፈትኩላቸው ፅቱም ከወገባቸው በላይ ወጥተው ለአካባቢው ጩኸትና ውበት ተጨማሪ ኃይል ሆኑ::

ብዙም ሳይቆይ ከውስጥ እኔንና እነሱን የሚለየው ግድግዳ በጣም ተንኳኳ::

«ሰዎቹ አበዱ!» አልኩና ተንሸራታች መስኮቱን ከፍቼ «ምን ልርዳችሁ?» አልኩ::

- «እዚህ በረዶ ቤት ውስጥ ያስቀመጥነውን 6 ሻምፒኝ የት አደረከው?»
- «የምን ሻምፒኝ? »
- «ሻምፒኝ! .... በጣም ውድ ሻምፒኝ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

ኳሱ ሲወርድ እያንዳንዳቸው ሻምፒኝ ህዝብ ላይ ሲረጩ አዘጋጅተው ኖሯል:: ደነገጥኩ! የምለው ባጣ «ለኔ እኮ አላሳያችሁኝም» አልኩ::

- «ማሳየትም የለብንም! » አለች አንደኛዋ /ወዲያው ከአፌ ነጥቃ/

ወርጂ ብፈልግ እንኳን ሻምፒኝ ሽታውም የለ::

ኳሱ ሲወርድ የቀረው ጊዜ አስር ደቂቃም አይሞላ:: በዛች ጊዜ ውስጥ በዛ ትራፊክ ምን ማድረግ እችላለሁ? ዝም አልኳቸው ::

እርግቦቼ ወደ ቁራነት ተቀየሩ:: አንዳንዶቹ በጣም ስለበሸቁ ተራ ስድብ ሳይቀር መሳደብ ጀመሩ:: መስኮቴን ዘጋሁና ቁጭ አልኩ::

የኳሱ መውረድ መጀመር ትኩረታቸውን ቀየረልኝ:: ህዝቡ ከሰአቱ ጋር አብሮ ይቆጥራል:: እኔ ግን በሃሳብ ቆዘምኩ:: ዘመን ተለወጠ! ጩኸቱ ቀለጠ!

ሲያቀብጠኝ ከመንገድ አንስቻቸው ሻምፒኙን የሰረቁት ሰዎች በዛች ሰከንድ ውስጥ ከፍተው ሲራጩበት በምናቤ አየኋቸው! ::

ሞዴሎቹም ቀጥሎ የነበራቸው የክበብ ፕሮግራሞችን አጠር አጠር አደረጉና እንደተኮራረፍን ወደ ሆቴላቸው መለስኳቸው::

ያ የለፋሁበትና የአዲስ አመት ዋዜማ ምሽትና የ333ሁለት ጉርሻ ግልምጫ ሆኖ ቀረ::

የ «ቦነስ ቀኔ» «ቀነ ቢስ» ሆነ!

በመጨረሻም ካምፓኒዬ ሄጄ መኪናውን ሳስተካክልና ሳፀዳ ስድስቱ ጽጌረዳዎች በእግር ተረጋግጠው ተበታትነው አገኘኋቸው:: ልክ እኔን ያገኙኝ ይመስል የቁጭት መወጫ አድርገዋቸው! ::

……………………



t.me/OLDBOOKSPDF

# « የራፐ አቀንቃኝ »

ዘመኑ እንዲህ እንደዛሬው በመላው አሜሪካ የአበሻ ዘር ያልበዛበት፣ የአበሻ ሬስቶራንትና ግሮሰሪ በህልምም የማይታሰብበት፣ እንጀራና በርበሬ ከወላጅና ከዘመድ አዝማድ እኩል የሚናፈቅበት፣ ልምድ ያለው መካሪ የሃገር ልጅ እንደጣእት የሚመለከበት ዘመን ነበር።

እደማገኘውም ተሸኚ ሰው በሌ ላይ ሲለቀስልኝ ለእኔ የሚታየኝ ግን ዶክትሬቴን ይዤ ስመለስ ወገኖቼም እንዳለቃቀሳቸው መጠን በደስታ ሲፈነድቁ ነበር። እለቀ! ደቀቀ! በዛ ጊዜ እንዳንዶቹ በችኮላ «ዶክተር ጴጥሮስ» ብለው ቢጠሩኝም አይደንቀኝም ነበር።

ኒውዮርክ እንደደረስኩ የገጠመኝ ግን ፈፅሞ ያልጠበኩት ነበር። ትምህርት ቤትም እንዲህ እንደ ሰንበቴ ቤት ዘው ተብሎ የሚገባበት አልነበረም። ከትምህርት በፊት ራስን ችሎ መኖር፣ ለመኖር ደግሞ መፍጋት ለመፍጋት ደግሞ ከምንም የመነሳትን ሁኔታ ወዲያውኑ መቀበልን ይጠይቃል። ከዛ ነው እንግዲህ ራስን ተሸክሞ ትምህርት ቤት የሚገባው።

በዚህ የኑሮ እርከን ስሌት ዶክተርነቱ ከሰማይ መራቁን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም።

እኔም በእንግዳው ህይወቴ ውስጥ እየወደቅኩ እየተነሳሁ ከአመታት በኋላ የለመዚን ሹፌርነት ስራ አግኝቼ፣ ትምህርቴንም በተንዳኝ ጀምሬ፣ የህይወት ስሌት ሀዲዱ ላይ ተቆናጥጬ ሰው የደረሰበት ለመድረስ ጉዞዬን ተያያዝኩት።

አዲሱ ስራዬን በማክበርና በጥንቃቄ ማከናወን ጀመርኩ። ያዘዙኝን ሁሉ እየፈፀምኩ እኸረዎቼን ማስደሰቴን ያወቅኩት በጥቂት ወራት ውስጥ ምርጥ ሽንጠ ረጅም ለመዚኖች ላይ መመደብ ስጀመር ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲሆንለት መመኘትን፣ ፍቅረኛሞች የሙሽራነት ስሜት እስኪሰማቸው መንከባከብን፣ ለብቻቸው እንደሆኑ አይነት ሁኔታ እንዲሰማቸው ማድረግ ወዘተ ይጠበቅበታል::

ለአዲሱ ደምበኛዬ የተመቸሁ ለመሆንና የችሎታዬን ስጥቼ ቀንጆ ጉርሻን ለመቀበል ቋምጫለሁ:: አምሮ ፀድቶ የቆመውን ለመዚን በድጋሚ አሳጥቤ ከተባልኩት ቦታ ቀደም ብዬ ለመድረስ ተምዘገዘግኩ::

የማንሽ ነጥቤ አካባቢ በአሜሪካ የኑሮ ምደባ ውስጥ «ከፍተኛ ሃብታሞች» የሚኖሩበት ነው:: መኖሪያ ቤቶቹን ላስተዋለ እንኳን አንደዛ አምረው መሰራታቸው መታሰባቸውም ይደንቃል:: ብዙዎቹ ግዙፍ ናቸው:: የአንዳንዶቹ አገዛዘፍና ውበት በኢራቁ ጦርነት ጊዜ ባግዳድ ውስጥ ቢኖሩ ኖሮ «በሳዳም ቤተመንግስትነት ከመጠርጠር ያውጣችሁ!» የሚባልላቸው ናቸው::

በውስጣቸው የሚኖረው ቤተሰብ ቢበዛ አራት ሰው የሆነው እነዚህ ቤተመንግስት መሰል መኖሪያ ቤቶች ከቤተኛው ቁጥር እጥፍ የሆኑ የመኝታ ቤቶችና መታጠቢያ ቤቶች እንዲኖራቸው ተደርጎ መሰራታቸው የሰው ልጅ ፍላጎት ገደብ አልባ እርካታ ቢስ ስለመሆኑ ዋነኛ ምስክር ያደርጋቸዋል::

የአትክልቶቹ፣ የዛፎቹ፣ የሳሮቹ አተካከልና አከረካከም ከሰማዩ ገነት ደርሶ የተመለሰ ባድቅ መሃንዲስ ያቀደው ይመስላል:: ይሄኛውን ከገነት የሚለየው የሰማዩ ለፃድቃን ሰዎች ብቻ የተሰራ ሲሆን ይሄ የምድሩ ግን ፃድቅና ኃጢያን የሰው ልጆች ተደባልቀው የሚኖሩበት ብቻ ሳይሆን ድልብ ፈረሶች ሳይቀሩ የሚፈነጥዙበት በመሆኑ ነው::

መጠነ ኦሎምፒክ መዋኛ ቦታዎቻቸው ውብ ቅርጽ እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ እንዲመስሉ ጭምር ታስበው የተሰሩ ናቸው::

በየቤቱ ጋራዥ ውስጥ ከቆሙ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በልዩ ትዕዛዝ የሚሰሩና በዛው አመት የወጡ አዳዲስ ሞዴሎቹ በዝተው ይታያሉ::



t.me/OLDBOOKSPDF

አለም የእንገቱ ማስገቢያ ጎጃና የጎኑ ማሳረፊያ አልጋ እንድትኖረው በሚዳክርባት በዚች ምድር እነሱ ለአይናቸው ማሳረፊያና ለህሊናቸው መርኪያ ያን ያህል ተሳክቶላቸዋል::

«አይ አንች አለም!» አልኩ ገፃነምም ገነትም እዚሁ እሷው ላይ ስለመሰሉኝ::

የራሴንና የነዚህን ሰዎች ህይወት ሳነፃፅረው የምንገናኘው በምንሞቃት ፀሃይና በምንተነፍሰው አየር ብቻ ሆኖ ታየኝና «ምነው አንድዬ!» ብዬ አምላኬን ጠየቅኩ::

አንተ እንዲህ ካልክማ የሚበሉ ያጡት ምን ይበሉ? የሚል ነገር በጭንቅላቴ መጣና «እረ ተመስገን ጌታዬ ለዚህ ያደረስከኝ» ብዬ ጥያቄዬን አነሳሁ:: ፈርቼ::

በመንገዴ ላይ እያቆራረጥኩ ሳልፍ የማየው የቴጃር ከተማ ከከተተኝ የቅዠት አለም ነቅቼ የነሱን የበላይትና የተመደበልኝን ህይወት በፀጋ ተቀብዬ፣ ያለችኝን ተመስገን ብዬ በደስታ ለመኖር እራሴን አሳምኜ ለዛች ቀን የተዘጋጀልኝን እንጀራ የምጋግርበትን ቲያትር ለመስራት ለመዚኔን ከደምበኞዬ መኖሪያ ቤት በር ላይ አስተካክዬ አቆምኩና ጥበቃዬን ጀመርኩ::

ታዋቂውን የራፕ አቀንቃኝ ለማየት የልደት ስጦታ እሽጉን እንደሚከፍት ህፃን ቸኩያለሁ:: በቴሌቪዥንና በቪዲዮ ከማውቃቸው የራፕ አቀንቃኞች አንዱ ሊሆን እንደሚችልም ገምቻለሁ::

ደምበኛዬ ከንር በኩል ብቅ አለ:: ጥቁር አሜሪካዊ ነው:: ጥቁር ቢትልስ ሹራብና ጥቁር ሱሪ አድርጎ ቀይ ጃኬት ከላይ ደርቧል:: ጆሮው ላይ በሰካው ገመድና በአረማመዱ ሙዚቃ እየሰማ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የሙዚቃውንም ቃና መገመት እያዳግትም:: ትንሽ የእጅ ሻንጣ አንጠልጥሏል::



t.me/OLDBOOKSPDF

በሬን ከፍቼ፣ በንቃት ጠብቄ፣ በፈገግታ የተሞላ ሰላምታዬን አስቀድሚ ሽንጣውን ለመቀበል እጄን ስዘረጋ «ችግር የለም እኔው ጋር አደርገዋለሁ» ብሎ ወደ ውስጥ ወንበር ላይ ወረወረውና ቀልጠፍ ብሎ ገብቶ ተቀመጠ።

መኪናዬን እንዳስነሳሁ «ጌታዬን የት እንደማደርስ መጠየቅ እችላለሁ?» አልኩት።

ትንሽ ጊዜ ወስዶ ካሰበ በኋላ « ያማ ሱሺ የጃፓን ሬስቶራንት አድርሰኝ» አለኝ።

ሰመዚኔ በነዳጅ እኔ በሃሳብ መጋለብ ጀመርን!

ይሄ በግምት ከ28-30 ዓመት የሚገመት ወጣት ተፈጥሮ በለገሰችው ድምጹ እዚህ ደረጃ የመድረሱ ፍጥነት አስደንቆኛል።

«ወይ ካሰው ተወለድ ወይ ከሃብታም ተጠጋ» የሚለው የአበሻ አባባል ላይ «ወይ ሃብታም ሀገር ተፈጠር» የሚል መጨመር አለበት እልኩ እና ጥላሀን ገሠሠ ትዝ ብለውኝ። ያም እንሰ የኛዎቹ አገሬ፣ አገሬ እያሉ ሲዘፍኑ እነዚህኞቹ አገር የሚባል ነገር ከአፋቸውም አይጠሪ!

«ይገርማል! » ብሎ የለ እራሱ ዘፋኝ ገረመኝ! ሁኔታው።

«ማን ልበል ስምህን?» የሚለው የተሳፋሪዬ ጥያቄ ከሃሳቤ መለሰኝ።

«ጴጥሮስ እባላለሁ። ስራ ቦታዬ «ፒተር» በመባል ነው የምታወቀው»

«እኬ ፒተር አድምጠኝ! ጄክ እባላለሁ። እስታህ እንደነገረህ የሙዚቃ ሰው ነኝ። በቋሚት የምኖረው ካሊፎርኒያ ሲሆን እዚህ ኒውዮርክ በቋሚት ስስራ ስለምመላለስ ዌስት ቸስተር ሁለተኛዋ መኖሪያዬ ነች። አድናቂዎቼ ሰፈ... ስለሚያስቸግሩኝና ታዋቂ ግለሰብ አዳኞች (ፓፓራዚዎች) በየሚሬቸው እያሳደ... የግል ነፃነቴን ስለሚረብሹት ትኩረት ላለመሳብ ከሹፌርንትህ በስተቀር ሌ... ግልጋሎት ነገ አልፈልግም! በር መክፈት ጭምር ያንተ ስራ አይደለም ተግባባን?» አለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ግልፅ ነው ጌታዬ!» ካልኩት በኋላ « የመለያየታችን ቀን ግን እኔ ራሴ ለፊርማ ማስቸገሬ አይቀርም! » አልኩት እየሳቅኩ።

«አታስብ! በደስታ እንደምንለያይ እርግጠኛ ነኝ» ብሎ ፈገግ አለና ወደ ሙዚቃ ማዳመጡ ተመለሰ።

10 ማይል ነድተን ከሬስቶራንቱ ልንደርስ አካባቢ ከአንድ ሰዓት በላይ እንደማይቆይና እስከዛው ነፃ እንደሆንኩ ካሳወቀኝ በኋላ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እንዳነሳው አዘዘኝ።

ሬስቶራንቱ በር ላይ እንዳቆምኩ ዘልዬ በር ልከፍት ብወጣ ጃክ ቀድሞኝ ውልቅ ብሏል። ወዲያው እንግዳ ተቀባይዋ ከለመዚን የወረደ እንግዳዋን ሰላሳ ሁለት ጥርሷን እሳይታ ተቀብላው ወደ ውስጥ ይዛው ከእይታዬ ተሰወሩ። የሬስቶራንቱ ውስጥ ደብዛዛው መስታወት ስለሚሸፍነው ሻማ ቅርጽ ያላቸው መብራቶች በቀር የሚታይ ነገር የለም።

እኔም ስለውሎዬ ለሲት ጓደኛዬ ላጫውታትና በዛውም ስአቴን ለመግደል በአቅራቢያው ወዳለ የህዝብ ስልክ ሄድኩ። ደውዬም ሃሎ ከማለቷ!

«መጥፎም ጥሩም ዜና አለኝ የቱን ላስቀድም» አልኳት

«መጥፎውን» አለች

ከዛሬ ጀምሮ ለአንድ ሳምንት አንገናኝም»

«ለምን?» አለች /በቁጣ/

«ጥሩው ወሬ እሱ ነው! ከዛሬ ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ሚሊየነር ለሆነ ክከብ የራፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ እንድሰራ ተመድቤያለሁ ..........» ብዬ ሁሉንም አጫወትኳት።

«እሱስ ይሁን ትምህርት ቤትህስ?» ጠየቀች።

«ትምህርት ከገንዘብ በኋላ!» አልኳት እየቀለድኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግ አልኩ። በልቤ የመጀመሪያ ፈተናዬን በሚያስደንቅ ሁኔታ በማለፌ።

አጠገቡ ስደርስ በአንድ እጁ እቅፍ አድርጎ እየጨመቀኝ በሌላኛው መጠጡን ተቀበለኝ። ወዲያው መጠጡን ከፍቶ መጎንጨት ሲጀምር «ውጭ እጠብቅሀለሁ» ብዬ መኪናዬ ውስጥ ሽለብ ለማድረግ ወጣሁ።

«ለአንድ ሰዓት ያህል ዳንሱ ጋር ቆይቼ እመጣለሁ» ብሎኝ በመጠጡ መደሰቱን ቀጠለ።

«ከዳንስ በታ እንዷን ዕድለኛ ይዞ ይመጣ ይሆን?» ብዬ ስጠብቅ አለቃዬ ለብቻው መጣና «ወደ ቤት ንዳ» ብሎ አዘዘኝ። መንዳት ከመጀመሬ አይኖቼን ከድኖ ወደ ኋላ ተለጥጦ ተኛ። እኔም «አሹሩሩ ማሞ እሹሩሩ» እንዲሆንለት ክላሲካል ሙዚቃ አደረግኩለት። ለማንኩራፋት አፍታም አልቆየም።

በሩ ላይ ስንደርስ ሙዚቃውን አጠፋሁ። በሙዚቃ የተኛው ሰው በሙዚቃው መቋረጥ ነቃ!

«አመሰግናለሁ! ነገ የምታነሳኝ ከሰዓት በኋላ በ9 ሰዓት ከዚሁ ከቤቴ ይሆናል» ብሎኝ ዞር ዞር ብሎ ወንበሮቹ ስር ካየ በኋላ ከለቡ ጋር ከሰመዚኑ ሲወርድ የገንዘብ ቦርሳው ከኋላ ኪሱ ወንበሩ ላይ ሲወድቅ ግሬያውን ቶሎ አምልጦ ለመግባት ሲል እያወቀ ትቶት እንደሄደና አሁን ግን ስላጣው እይቼ እንደሆነ ጠየቀኝ።

ደነገጥኩና «እረ እኔ አላየሁም!» ብዬው ወርጄ ወንበር ስር መፈለግ ጀመርኩ።

«መኪናውን ከለብ ስታቆም ቆላልፈኸው ነበር?» አለኝ

«አዎን ጌታዬ!»

«ተወው በቃ አታስብ! ደግነቱ ገንዘብ ብቻ የምይገዝበት ቦርሳ ነው። ሂድ! ሂድ! ነገ እገኝዋለሁ!» አለኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሮንክስ ኒውዮርክ ከሚገኘው ቤቴ ስደርስ የሰመዚኑ ሰዓት ከንጋቱ አስር ሰዓት ይላል። በጣም ደክሞኝ ስለነበር ተጣጥቤ ድብን ብዬ ተኛሁ።

ብዙም የተኛሁ ሳይመስለኝ የቤቴ ስልክ መንጫረር ጀመረ። በመልዕክት መቀበያው «ፒተር ቢሮ ደውል» የሚል መልዕክት በተደጋጋሚ ሲያወራ ይሰማኛል። ፒጀሬም ሰብቻው ይንጫረራል። ሌላ የማይሆን ስራ ሰጥተው ይሄንን ስራዬን በደንብ እንዳልሰራ ሲያደክሙኝ ነው ብዬ የስልኩንም መልዕክት መቀበያ ፒጀሩንም አጠፋፍቼ ተኛሁ።

እኩለ ቀን ላይ ከእንቅልፌ እንደነቃሁ ቢሮ ስደውል «በአስቸኳይ እንድትመጣ!» ተባልኩ።

አለቆቼ «በአስቸኳይ ቢሮ እንድትመጣ» ያሉበት ምክንያት ተሳፋሪዬ የገንዘብ ቦርሳው እንደጠፋበት ሲነግራቸው እኔን በመጠርጠራቸው እንደሆነ ገብቶኛል።

በንጹህነት ለአመታት ያገለገልኩት ካምፓኒ እኔን በዚህ በመጠርጠሩ በጣም በሸቅኩ። ነፃ መሆኔን ካላረጋገጥኩ ብዙ የዓንሁለት ነገር መና ሆኖ መቅረቱ ነው ብዬ ሰጋሁ።

ለመዚኑን ክለቡ ጋር ሳቆም መቆለፍ አለመቆለፌን እርግጠኛ መሆን አልቻልኩም።

ተሳፋሪዬ ሲወርድ ከኪሱ የገንዘብ ቦርሳው ሲወድቅ የሆነ ሰው አስተውሏል ማለት ነው ... እድለኛውን ሌባ እኔም በር ሳልዘጋ ተውኩለት ማለት ነው .... እያልኩ በገንኩ።

«ስስገበገብ ነው ይበለኝ! »ብዬ ራሴን ወቀስኩት።

ራሴን ለመከላከል ተዘጋጅቼ ወደ ቢሮው ስገባ አለቃዬ ከፖሊስ ጋር ቆጭ ብሎ ደረስኩ።

«ልክ ነኝ አልተሳሳትኩም!» አልኩ በሆዴ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አለቃዬ «እንዴት ነህ ፒተር!» ወንበር ያዝ!» አለኝ /እንደቀድሞው ምንም ሳይለወጥብኝ::/

«ይሄ ኦፊሰር ዛገር ይባላል» ብሎ ሲያስተዋውቀኝ «ፒተር እባላለሁ» አልኩ ለፖሊሱ /አለቃዬን ቀድሜው/

አለቃዬ «ትላንት ካገለገልከው ደምበኛችን ጋር ችግር ስላለ አንዳንድ መረጃ እንድትሰጠን ነው ያስጠራሁህ» አለኝ

እኔም ተበሳጭቼ «ስለገንዘቡ ቦርሳ እንደሆነ የምትጠይቁኝ እኔ ያየሁት ነገር የለም!» ብዬ በአጭሩ ደመደምኩ::

ሁለቱም ሁለት አይናቸው ፈጠጠ!

«የምን ቦርሳ?» አለኝ ፖሊሱ ቀድሞ

«ሰውየው ለመኪን ውስጥ ተውኩት የሚለው የገንዘብ ቦርሳ!» ፖሊሱ ሳቀ አለና «ቦርሳም ጠፋብኝ ብሎሃል?»

«እምና! ሌላ ደግሞ ምን ጠፋብኝ አለ?» በመገረም መለስኩ::

«እኬ!» አለ ፖሊሱ:: አሁን ጉዳዩ የሱ ሙያ ስለሆነ እሱ ብቻ ሆነ እነጋገሪዬ:: አለቃዬ አይኖቹን እኔ ላይ ተክሎ የምለውን ለመስማት የጓ ይመስላል::

«ኦፊሰር! የእስክዛሬ ሪከርዴን ማየት ትችላለህ! እንዲህ አይነት ችግር ከእ ጋር ተፈጥሮ አያውቅም» አልኩ /በአይኔ አለቃዬን ለዚህ ቃል እንተም ምስክ ነህ እያልኩ/

ፖሊሱ «ኖ..ኖ..ኖ ስለ ቦርሳው አታስብ! እርሳው! አሁን ከእንተ የምፈልገው ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የሆነውን እንድትነግረኝ ነው» አለ አንድ ሳይቀር ከ እስከ ፐ ውሎዬን ነገርኩት::



t.me/OLDBOOKSPDF

«አመሰግናለሁ!» ብሎኝ፡፡ የተጠራሁበትን ዋና ምክንያት አስረዳኝ፡፡ ፈፅሞ ያልጠበኩት ነገር ነበርና ደነገጥኩ፡፡

የዛች እለት ፖሊስ የደረሰበትንና ከዛም በኋላ ያለውን ጠቅላላ ታሪኩን እንካችሁ!

- ተሳፋሪዬ ስልክ ደውሎ ስሙን፣ ስራውንና የመኖሪያ ቤቱን አድራሻ ካሳወቀ በኋላ የለመዚን ግልጋሎት እንደሚፈልግ ይነግራቸዋል፡፡ ስልኩን የተቀበሉት ሰምሪት ክፍሎች የተሳፋሪ የመኖሪያ አድራሻ የከፍተኛ ሃብታሞች ሰፈር መሆኑን ስለተገነዘቡ የተለየ እንክብካቤ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ያሳቸውን ቁ1 ለመዚንና ቁ1 ሹፌር እንደሚመድቡለትም ቃል ገቡ፡፡ እኔና የአለቃችን ለመዚን ለስራው ተመረጥን፡፡

- ስራዬን በጀመርኩ በነጋታው የሂሳብ ክፍሉ የደምበኛችን የብድር ካርድ አልሰራም ማለቱን ለዋናው አለቃችን ያሳውቃል፡፡

- አለቃችንም ሞክሮ አይሰራም፡፡

- እንደዛ አይነት መኖሪያ ሰፈር የሚኖር ሰው ጋር ደውሎ ካርድህ አልሰራ አለን ማለት ደምበኛችንን ማስቀየምና ማጣት ይሆናል ብለው ሌሎች ለመዚን ካምፓኒዎች ጋር ይደዋወላሉ፡፡

- በመጨረሻ የአንድ ለመዚን ካምፓኒ ስራ አስኪያጅ ከዚህ በፊት «የራፐ አቀንቃኝ» እንዴት አድርጎ እንዳታለላቸውና እስካሁንም በፖሊስ እንደሚፈለግ ዘርዝሮ ይነግራቸዋል፡፡

- ጉዳዩን ለፖሊስ ያሳውቃሉ፡፡

- ፖሊስ ተከታትሎ እሱ በሰጠው አድራሻ የሚኖሩት ሁለት ባልና ሚስት ዶክተሮችና ሁለት ልጆቻቸው እንደሆኑና እነሱም ከነልጆቻቸው ፍሎሪዳ እረፍት ላይ እንደሆኑ ይደርስበታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

- ፖሊስ አፈላልጎ የስልክ ግንኙነት አድርጎ ለዶክተሮቹ ሁኔታውን ይገልፅላቸውና ወዲያው ሲበሩ ይመጣሉ::

- ፖሊስ ጠቅላላ ያገኛቸውን መረጃ በመሰብሰብ ጉዳዩን ሲቋጨው «ታዋቂው የራፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ» የዶክተሮቹ ልጆች ሞግዚት «የከንፈር ወዳጅ» ሆና ተገኘ!

ዶክተሮቹ በጣም ተደናገጡ! ስማቸው በጋዜጣ እንዳይወጣም ለፖሊስ ቢማፀኑም ዋስት ቸስተር ጋዜጦች ለህትመት የሚመጥን ወሬ ስላገኙ:-

«ታዋቂው የራፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ» የስመዚን ሹፌሩን 50 ብር አጭበረበረ! በሚል አርዕስት አጅበው ወሬውን በአደባባይ አወጡት:: ተሳፋሪው በሚሄድባቸው ቦታዎችና ሬስቶራንቶች የሰራቸውን የረኸርም ጊዜ ማጭበርበሮች ከፖሊስ ማህደር አውጥተው ዘገቡት::

እኔም በመንደር አውደልዳይ መታለሌ አበሸቀኝ!:: የተሳልኩትም ስላልያዘ ለእንጦጦ ማርያም ምንም ሳላደርግ ቀረሁ::

ህይወቴንም ለማሳካት መታገል እንጂ አቋራጭ መንገድ እንደማያዋጣኝ ተገንዝቤ የኑሮ ውጣ ውረዴን ቀጠልኩበትና ከ3 አመት በኋላ ትምህርቴን ከዳር አድርሼ ጥሩ ስራ አገኘሁ::

ለዓመታት ሳሽከረክረው የነበረውን ለመዚኔን በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኋላ ተቀምጬ በሹፌር ሄድኩበትና ተሰያየን! :: የሰርጌ ዕለት!!

ጓደኛዬም ዛሬ ሚስቴ ብቻ ሳትሆን የልጆም እናት ሆነች! እኔም እንደ እናቴ የማርያም ወዳጅ ነኝና እሷም በዚህ ክሳኛለችና ውለታዋን ቆጥሬ የኒውዮርኳን ማርያም የአቅሟን ያህል እያገለገልኩ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ውሎዬ

‹‹ልክ ነው /right/ የሚለውን ቃል ለታክሲ ነጂ አይነግሩም›› ይላሉ አሜሪካኖች፡፡

ምክንያታቸው ታክሲ ነጂዎች እንግሊዝኛ ስለማይችሉ ወደቀኝ ይጠመዝዛሉ የሚል ነው፡፡ ስለዚህም ‹‹ልክ ነው›› ማለት ካለባቸው በብዛት ‹‹ትክክል›› /correct/ የሚለውን አማራጭ ቃል ይጠቀማሉ፡፡

ኅብረተሰቡ ይህንን የተሳሳተ ጅምላዊ ፍርድ አምኖ ስለተቀበለው ታክሲ ውስጥ ሲገባ እንግሊዝኛ በደንብ ከማይገባው ‹‹መሃይም›› ፍጡር ጋር ለመገናኘት የሀሊና ሚዛኑን አስተካክሎና ቆልፎ ነው፡፡

ብዙ ተሳፋሪዎች የሚሄዱበትን አድራሻ ካሳወቁት በኋላ ሹፌሩ በትክክል ተረድቷቸው እንደሆን ያሉትን በመድገም እንዲያረጋግጥላቸው የሚሹት ከዚህ ጅምላዊ ፍርድ የተነሳ ነው፡፡

የዚያን ዕለት መንሃተን ውስጥ ‹‹ማድሰን›› ጎዳና ለይ ከሚገኝ ውድ መደብር ውስጥ ሲወጡ አግኝቼ የጫንኳቸው ሁለት ወጣት ሴቶች ‹‹ኩይንስ›› /queens/ ከሚባለው የኒውዮርክ ክፍለ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እንዳደርሳቸው አድራሻውን ከነገሩኝ በኋላ አንደኛዋ፡-

‹‹ያልኩህ ገብቶሃል?›› መንገዱንስ እርግጠኛ ታውቀዋለህ?›› ብላ በማስጠንቀቂያ ቋንቋ ጠየቀችኝ፡፡

የሚገርመው ካነጋገሯ ራሷም እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋዋ እንዳልሆነ ለማንም ቦግ ብሎ ያስታውቃል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በልቤ ‹‹እስቲ ይሁን›› ብዬ፣ የነገረችኝ አድራሻ ግልፅ እንደሆነና መንገዱንም በትክክል እንደማውቀው አረጋገጥኩላት፡፡

አሜሪካ ከመምጣቴ በፊት በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት ለአመታት የኖርኩና ቋንቋቸውን የተማርኩ፡ ባህላቸውንና አኳኋናቸውን የምረዳ ስለሆነ ተሳፋሪዎቼ ታክሲ ውስጥ እየገቡ ሳለ በቋንቋቸው ሲነጋገሩ ሩሲያውያን እንደሆኑም አውቂያለሁና ‹‹ምን እሱ ብቻ ከየት አገር እንደመጣሽ ሳይቀር ግልጽ ሆኖልኛል›› አልኩ በልቤ ወደ ‹‹ኩይንስ›› ለመሄድ ‹‹ኢስት ሪቨር››ን የማቋርጥበትን ‹‹ሚድ ታውን ታናል››ን ለመያዝ መንዳቴን በመጀመር፡፡

‹‹እነዚህ ታክሲ ነጂዎች ቋንቋ የማይገባቸው ደደቦች ናቸውና ታክሲ ስትወስጂ በትክክል የምትሄጅበትን አድራሻ ተረድቶ እንደሆን ማረጋገጥ አለብሽ›› የሚለው የሩሲያውኛ ቋንቋ በጆሮዬ ዘልቆ ለፀብ ጋበዘኝ፡፡

‹‹በእውነት?.... እኔ እንኳን ብዙም ታክሲ አልጠቀምም፡፡ ስጠቀምም እስከዛሬ ይሄ ነው የምለው ችግር ገጥሞኝም አያውቅ፡፡›› አለች፣ ሁለተኛዋ ክብ ፊት ያላትና የጉንጮቿ ትልቅነት ከገምባሯ መፍጠጥ ጋር አይኗን ጉድጓድ የገባ ያስመሰለው ትሁት ሴት የምትመስለዋ፡፡

በዚያን ሰዓት ግማሽ አይምሮዬ የመልስ ምት ለማዘጋጀት ስራውን ሲቀጥል ሌላኛው ግማሽ ደግሞ የሚሉትን ለመስማት ጆሮ ሆነ፡፡

ሴትዬዋ ንቀት የተሞላበትን ጥላቻዋን ቀጥላለች፡-

‹‹...በዚህ ላይ የመንገድ ምልክቶችን እንዴት አንብበው እንደሚሄዱ ይደንቀኛል ...ብዙዎቹ መፃፍ ማንበብ የማይችሉ መሃይሞች ናቸው...››

‹‹እውነትሽን ነው?››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ታዲያሳ ! ይሄኔ ይሄም ኒግር አንዱ መሃይም ሊሆን ይችላል ....›› /ምንም እንኳን ቋንቋውን እንደማላውቅ ብትገምትም በሹክሹክታ/

‹‹ይሄስ አይመስለኝም.... ቋንቋውም ቢያንስ ከኔ የሚሻል ይመስለኛል...በዚህ ላይ አጠገቡ ያስቀመጠውን ጋዜጣ አታዩም? በደንብ ያነባል ማለት ነው...››

‹‹አንዱ ተሳፋሪ አንብቦ ሲጨርስ ጥሎት የሄደውም ሊሆን ይችላል መሃይምነቱን ለመደበቅ ካጠገቡ ያደረገው›› ስትል አንድ ሰው ሌላውን ሰው ለማሳነስ ያን ያህል የማያውቀውን ሰው መፈረጁ ያልጠበቅኩት ነበርና ደሜ ከመፍላት አልፎ መንተክተክ ጀመረ፡፡

እቺን እራሷን አድናቂ ሌላውን ናቂ ፍጡር በራሷ ቋንቋ በስድብ ሞልጬ ለዘላለም የማትረሳው ትምህርት ልስጣት ካልኩ በኋላ ቆይ ላስጨርሳትና መጨረሻ ላይ ሂሳቤን ተቀብዬ ያለ የሌለውን አወርድባታለሁ በማለት ከአፌ መለስኩት፡፡ ራሴንም አረጋጋሁ፡፡

ትንሽ እንደተጓዝን የዝችው የተሳዳቢዋ ሴትዮ ሞባይል ተንጫረረ፡፡

ወደ ሚድ ታውን ታናል /midtown tunnel/ የሚያስገባው ትራፊክ ተጨናንቆ የታክሲዬ የፍጥነት ማሳያ ሰሌዳ ከ10 - 15 ማይል ውስጥ ይዋዥቅ ነበርና ጆሮዬን ወደ ስልክ ምልልሱ ለመጣል ሁኔታው የተመቸ ነበር፡፡

ስልኩን ጆሮዋ ላይ ግጥም አርጋ ይዛው ነው መሰል ከዛኛው ጫፍ የሚወራው ጥርት ብሎ አይሰማም፡፡

በእንግሊዝኛ የተጀመረው ሰላምታዋ ወዲያው ወደ ሩሲያውኛ ተቀየረ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ሄሎ!››

‹‹ሁ ኢ.ዝ ዚስ?››

‹‹ሃይ ሚሻ! ሀው አር ዩ?››

‹‹ውነትክን ነው?››

‹‹ሳቅ.... እንድንገናኝ መጓጓት ካልሆን በተር ልናፍቅህ እንኳን አልችልም››

‹‹እኬ! እኬ! ይሁንልህ›› ሳቅ

‹‹.... ለመሆኑ ክቢሮ ነው የምትደውለው?››

የሞባይልህንማ ሰጥተኸኝ መዝግቤዋለሁ.. ማን እንደደወለልኝ አውቅ ነበራ!››

‹‹ቆየኝ አንድ ግዜ ያዝልኝ .... ሔሎ 7777777 ነው››

‹‹ወየው እምላኬ! የቤት ቁጥርህን ነው የሰጠኸኝ? እኔስ ብሆን የአካባቢ ኮዱን እንዴት አላስተዋልኩትም? አይገርምም?....ደውዬ ሚስትህ ብታነሳ ኖሮስ?››

‹‹ውነትም ያን ዕለት በጣም ሰክረህ ነበር ማለት ነው!››

‹‹ስታስደንሰኝ ሚስትህ ምንም ነገር እንዳልጠረጠረች እርግጠኛ ነኝ!››

‹‹ውነትም ታምንሃለች! ሳቅ... እንተም የምትታመን ነሃ! ሳቅ››

‹‹የአሜሪካን ሴቶች ሁሉ ሂሊሪ ክሊንተንን እንዳይመስሉህ ኖ! ሳቅ....ትዳርህን እንዳታፈርስ....››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ዛሬ ማታ እንኳን አይመቸኝም .. ነገ ጠዋት በ2 ሰዓቱ አውሮፕላን ከባለቤቴ ጋር ወደ ፍሎሪዳ ስለምንሄድ ማታ ጉድ ጉድ የምልበት ብዙ የዝግጅት ስራ ይጠብቀኛል››

‹‹የእውነት! … አሁን እራሱ ለጉዞ የሚያስፈልጉ አንዳንድ ነገሮች ከጓደኛዬ ጋር ገዛዝተን በታክሲ ወደቤት እየተመለስን ነው››

‹‹ለማንኛውም እንደተመቸኝ ከዛው እደውልልሃለሁ! … የሚመቸኝን ሰዓት እስከምንገርህ አደራ እንዳትደውል››

‹‹እኬ ውዴ! ታናል ውስጥ ልንገባ ስለሆነ ስልኩ ከመቋረጡ በፊት ልሰናበትህ››

‹‹እኬ! እኬ ባይ!.....››

‹‹አይ ላቭ ዩ ቱ!›› ስልኩ ተዘጋ፡፡

‹‹አይ ላቭዩ ቱ!›› የሚለው የስልክ ምልልሷ መዝጊያ ቃል ከፊቷ ነጸብራቅ ጋር አብሮ የሚሄድ በመሆኑ ወንድ ልጅን ለማንበርከክ ጥሩ አርጋ መተወን የምትችል አርቲስት መሆኗን ይመሰክራል፡፡

ታክሲዬ ውስጥ ከገባች ጀምሮ ያስተዋልኩት፤ ጋጠወጥነቷ፣ ሞጥሟጣነቷና የፀባይዋ ሃይለኛነት በማኅበራዊ ህይወቷም ውስጥ የምታንጸባርቀው ከሆነ ውበቷን ያደበዝዘው ይሆናል እንጂ፤ ይቺ ከ25-28 አመት ባለው ዕድሜ ውስጥ የምትገመተው ይቺ ጉብል ተፈጥሮ ደህና አርጋ የለገሰቻት ፍጹም ውብ ናት፡፡

የውበቷ ዘውድ የሆነው፣ ትከሻዋ ላይ ተዘለፍልፎ የወደቀው ብሎንድ ፀጉሯ፣ የጠራው ነጥብ አልባ ፊቷ፣ የሚያማልለው ሰማያዊ አይኗ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጣጣቸው አንድም ቀን ለምግብ መፍጫነት ያገለገሉ የማያስመስላቸው በቁመት የተደረደሩ ጥርሶቿ፣ በየፊናቸው ለንግድ ማስታወቂያነት የሚታጩ ናቸው፡፡

ጉብሷ አጭር ቀሚስ በመልበስ የእግሮቿን ውበት ለማሳየት ስትል ብቻ ብርዳማው የክረምት ወቅት መጥላት የሚገባት ፍጡር ናት፡፡

ስልክ ደዋዩ ባለትዳር ሚስቱን አስጥሎ ያስከነፈው ሚስጥር፣ ይሄው ተፈጥሮ ለሷ አድልቶ ያደላት ውበት መሆኑን ለመረዳት የግድ ከእሱ መስማት አያስፈልግም፡፡

‹‹ኦ ማይ ጋድ! ይሄ የታናል ትራፊክ ንቅንቅ የሚል አይደለም፡፡ ... ከፊታችን የመኪና ግጭት መኖር አለበት እንጂ ....›› እያለች በተዘዋዋሪ መልስ እንድሰጣት ስትጠብቅ ቃል አልተነፈስኩም፡፡ ዝምታዬ አብሽቋት ካሁን አሁን በቀጥታ ልትጠይቀኝና አንዳንድ የሷ ቢጤ ተሳፋሪዎች እንደሚያደርጉት የትራፊኩ ብሰጭታቸውን ሹፌሩ ላይ ለመወጣት በፊት ያልተናገሩትን ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ‹‹በዚህ በኩል ለምን መጣህ?›› እንደሚሉት ልትለኝ ነው ብዬ ስጠብቅ፡፡

‹‹ደግሞ ከማን ጋር ነው? እንደዚህ በፍቅር የምታወሪው....›› የሚለው የጓደኛዋ ጥያቄ ቀደመ፡፡

‹‹አይ የኔ ነገር .. ለካ አልነገርኩሽም .. የትላንት ወዲያው ሰርግ ላይ የሆነ ባለትዳር ሙጥኝ አይልብኝ መሰለሽ፡፡ .. የሚገርምሽ እኮ ሚስቱም እዛው ሰርግ ላይ ነች..››

‹‹እንቺስ ብትሆኚ ባልሽ አብሮሽ ከሌለ ባለትዳር አይደለሽም ማለት ነው? ... ምን እንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ አስገባሽ?››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ምን እንቺ ደግሞ! .. ሁሌም ወገ ታጠብቂያለሽ ..እኔ ያገባሁት ያባቴን እኩያ መሆኑን አጥተሽው ነው? የኔ እመቤት! ብዙ አለመጣጣም እኮ አለ! ... በዚህ ላይ ታሪኩን ያወራሁልሽ ‹‹አሌሻ››ን ከሞስኮ አስመጥቼ እስከማገባ ድረስ ውስጤ የባለትዳርነት ስሜት እንደማይሰማው ብትረጂልኝ ደስ ይለኛል፡፡›› ብላ እንደመገሰጥ የሚከጅል አነጋገሯን ማኩረፍ በቃጣው ሁኔታ ሰበሰበችው፡፡

በሁለቱ መካከል የሰፈነው አፍታ ፀጥታ ‹‹አሌሻዬን ከልቤ ውስጥ የሚፍቀው ምንም አይነት ወንድ አይመጣም!›› ለሚለው ድንገት ከረጅም የግልግል ትንፋሽ በኋላ ለተወረወረው የሴትዬዋ አባባል ጉልበት ስለ ሰጠው ይሁን አላውቅም የልብ ፍቅረኛዋን ሳታገኝ ምንም ምድራዊ ሃይል እንደማያቆማት አሳመነኝ፡፡

የ‹‹አሌሻ ታማኝ›› ለፍቅሩ ያላትን ጽናት ተንፍሳ ስታበቃ ቆዘመች፡፡ ምናባ ሩሲያ ድረስ ጋልቦ በ‹‹ፍቅረኛዋ›› ትዝታ ላይ አስፈጥጧታልና ታናሌን ጨርሰን መውጣታችንን ያጤነች አልመሰለኝም፡፡

እኔን ያሳመነኝ ሁኔታዋና አባባሏ ጓደኛዋን አሳዝኗታል መሰል እንባቷን ካወዛወዘች በኋላ፡-

‹‹ታዲያ እንደዚህ ከሆነ ‹‹ግሪን ካርድ›› ሽን እንደሆነ አግኝተሻል.. ለእንድሬ ፍቅር ከሌለሽ ለምን ቁርጡን ነግረሽ አትፈቺውም?..››

‹‹ገንዘቡስ ሊዲያ! እንደዚህ የሚያንቀባርር ባል ከየት ይገኛል? የኔን ተይው! ....ሃገር ቤት ለወላጆቼ የከፈተላቸው ቢዚነስ ስንቱን ስራ አጥ ዘመዴን ሳይቀር ከችግር ያላቀቀ ነው፤ ታናሽ ወንድሜን አሜሪካ አስመጥቶ ለኮሌጅ እየከፈለ የሚያስተምር እኮ ነው እንድሬ ...››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ታዲያ እንደዚህ አይነቱን ባል አፍቅረሽ አርፈሽ ቁጭ ማለት ነዋ!››

‹‹ስሚ ሊዲያ! እንድሬን ማፍቀር የምችል አይመስለኝም፡፡ ለሱ ያለኝ ፍቅር ሌላ አይነት ነው፡፡ የውለተኛ ፍቅር አይነት.....በቃ! ቤተሰባችንን ሁሉ የሚንከባከብ ጥሩ አባት ማለት ነው ለኔ!›› ብላ ፀጥ አለች፡፡

አለፍ አለፍ እያልኩ በኋላ ማሳያ መስታወቱ ሳያት በግራ እጅ ጣቶቿ ፀጉሯን ከፋኛ ታንገላታና መልሳ በጣቶቿ ታበጥራለች፡፡ ያበጠረችውን እንደገና መልሳ ታምሳለች፡፡

ድርጊቷ ውስጧ የገጠመውን ሙግት ያጋልጣል፡፡ ትንሽ እንደቆየች ያልተቋጨውን ሙግቷን ባትፈታውም በይደር አሳለፈችው መሰል በረዥሙ ተነፈሰች ፡፡ አፏም ለመናገር ተከፈተ፡፡

‹‹እየሽ ‹‹አሉሻዬን›› እንደምንም አሜሪካ አስመጥቼ ከሱ ጋር ህይወቴን ካላቆራኘሁ ሰላምን ላገኛት አልችልም፡፡ የራብኝን ፍቅሬንም አግኝቼ ሳልጠግበው በምንም አይነት የተሟላ ደስታ አይኖረኝም፡፡ … ያሰሱ›› ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ ጓደኛዋ:-

‹‹አይ በቃሽ! .. እንግዲህ ስለ አሉሻ ከጀመርሽ ማብቂያም የለሽ ! ስለሱ መስማት አልፈልግም... የማይሆን ነገር ነው የምታወሪው ... እንዴ!... እምላክን ብትረሺ ህሊናሽ እንዴት ላመል እንኳ አይወቅስሽም? እንድሬም እኮ አምላክ አለው! አሉሻን ለዘላለም እንዳታዩው ወይም እንድትጠይው ሊያደርግ ይችላል፡፡..

‹‹ተይ ተይ ተይ እንደሱስ አትበይ! አሉሻዬን ማግኘት ካልቻልኩማ እንዴት ህይወቴን እንደምቀይሳት እኔ ነኝ የማውቀው›› አለች ቁጭት ብላ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጓደኛዋ ከት ብላ የሚሽሚጠጥ ሳቅ እየሳቀች‹‹ ራስሽን ልታጠፊ?››

‹‹ለማን ይድላው ብዬ ነው ራሴን የማጠፋው››አለችና ትንሽ አሰብ አድርጋ፡-

‹‹ያቺ ከኛ ቤት በታች መታጠፊያው ላይ የምትኖረው ሴትዮ ምን አለችኝ መሰለሽ››

‹‹የትኛዋ ሴትዮ?››

‹‹ያቺ ቢጫ ሃመር መኪና የምትይዘው ናታ!››

‹‹እ እኬ ! ያቺ ሴትዮ ! አንቺ እንኳን ‹‹ይቺ ሴትዮ መተዳደሪያ ስራዋ ምን እንደሆን ባውቅ ደስ ይለኛል.. እጅግ ሃብታምና ደስተኛ ትመስለኛለች›› ያልሺኝ?››

‹‹አዎና! በቀደምለት ከኛ ሰፈሩ ሞቢል የመኪና ዘይት ስናስቀይር እንገናኝ መሰለሽ!››

‹‹እሺ! ››

‹‹ራሷ መጥታ ስትተዋወቀኝ ሩሲያዊት መሆኗን ስነግራት ‹‹ፍጹም አትመስይኝም ነበር››ብላ ተገረመች፡፡ እኔም ቀስ ብዬ የህይወቷን ሚስጥር አዘከዘኳት››

‹‹ስራሽ ምንድነው አልሻት?››

‹‹ራስዋው ነገረችኝ፡፡ የሆነ የሆነ ባለሙያዎች ተቋም ውስጥ ፀሃፊ ነኝ አለችኝ››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ቤቷም ሆነ መኪናዋ ግን በፀሃፊነት የሚተዳደር ሰው ሊኖረው የሚችለው አይነት አይደለም››

‹‹ቆይ ልንገርሽ አይደል! ... ምን አለችኝ መሰለሽ ‹‹የኔ የህይወት ፍልስፍና እንደዚህ ነው፡፡.... ሴት ልጅ የተሟላ ኑሮ እንድትኖር ሶስት ወንዶች ያስፈልጓታል፡፡ በየሬስቶራንቱና በየመዝናኛ ቦታው አብራ የምትታየው ቆንጆ ለግላጋ ወንድ፣ አንድ ገንዘቡ ወንድ ያደረገው ሽማግሌ፣ ሊላው ደግሞ ወሲባዊ ዕርካታ የሚያስገኝላት .... ሶስቱም አይነት ወንዶች ስላሉኝ ህይወቴ ደስተኛ ነው›› ብላ የኑሮ ስሌት ሚስጥሯን አጫወተችኝ፡፡ ውነት አላት! በዚች ምድር ላይ ሁለቴ የኖረ የለም! ... እያንዳንዷን ሰዓት በደስታ ለማሳለፍ ማቀድና መጣር አለብሽ ... እናም አሉሻቡን አስመጥቼ መኖር ካልቻልኩ ህይወቴን የምቀይሳት በሴትየዋ የህይወት ፍልስፍና መሆኑ የማይቀር ነው አልኩሽ››

ጓደኛዋ መልስ ሳትሰጥ ዝም ብላ በመገረም አፍጣ ስትመለከታት፡-

‹‹ቆይ ሊንዳ! የሴትየዋን እድሜ ስንት ትገምቻለሽ?›› ብላ ጠየቀቻት፡፡

‹‹ከ34 እስከ 37 አመት ባለው ውስጥ የምትሆን ይመስለኛል››

‹‹እየሽ እሷ ግን 49 አመቷ ነው!.. እንደኔ ግምት ግማ ከ32 አመት አላስበልጣትም ነበር››

ትሁቷ ጓደኛዋን በጎን አይኗ እያየቻት ‹‹ዕውብ ድንቅ የኑሮ ፍልስፍና ነው ያስተማረችሽ›› ካለቻት በኋላ የሽርደዳ ሳቅ እየሳቀች፡-

‹‹ባዲሱ ፍልስፍናሽ መሰረት ይሂ አዲሱ ወዳጅሽ የትኛው መሆኑ ነው? ለወሲብ ማርኪያነት ወይስ አብረው የሚታዩበት ቆንጆ?››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹አብረው የሚታዩት ቆንጆ!›› ሳቅ.....

‹‹ከምር! እሱም እኔም ባለትዳር ባንሆን በነፃነት ከነኑ ሽጉጥ የሚባልለት አይነት ሰው ነበር!...የአሌሻቤን ፎቶግራፍ አሳይቼሽ የለም? .. ምናለፋሽ? ቁርጥ እሱን ነው የሚመስለው! .. ቁመናው ሆነ መልኩ የማንንም ሴት ልጅ ልብ የሚያቀልጥ ነው›› ብላ ከመለሰች በኋላ በመስታወቱ ሳያት ከንፈር እንካከሷ ‹‹የፈለገው ይሁን እንጂ አለቀውም!›› የምትል ይመስላል፡፡

‹‹ለምን አብሮ የሚታይ ብቻ? ወሲብ የሚያረካም ከሆነ ሌላ ሶስተኛ ለምን አስፈለገ ?››

‹‹አይ አንቺ ደግሞ ባለትዳር ነው እያልኩሽ! አንድ ሰው ሁለት ሴት ሊያጠግብ እንዴት ይቻለዋል? ..›› አለች የማፈር ሳቅ እየሳቀች፡፡

‹‹ታዲያ እንድሬን የመሰለ ሃብታም ሽማግሌና አብረው የሚታዩት ቆንጆ ይዘሻል! ለወሲብ ደግሞ ጥቁሮች አይታክቱም ይባላልና ወደ ሃርለም አካባቢ ብቅ ብሎ ማፈላለግ ነዋ!›› አሁንም የማሽሟጠጥ ሳቋን ለቀቀችው፡፡

‹‹ምነው ምን አልኩሽ? ... እኔ ታንያ! ባሪያሽ አይነካካኝም፡፡... እነዚህ ነጭ አሜሪካን ጋለሞታዎች አብረዋቸው ሲሄዱ እንኳን ደሜ ይፈላል፡፡ እነሱ አብረው በመኖር ተላምደዋቸው ነው እንጂ ... ልጆች ሆነን ትዝ ይለኛል...ሞስኮ ያለው ‹‹ፓትሪስ ሉሙምባ ዩንቨርሲቲ ለትምህርት ከአፍሪካ የሚመጡትን ኒግሮች ለማየት ‹‹ዙ ፓርክ››

እንሂድ ነበር የምንባባለው›› ረጅም ሳቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ዛሬ እንደዚህ በያጋጣሚው እየተገናኘን ተላመድናቸው እንጂ የምር ዝንጀሮ ስለሚመስሉን ጭራቸውን ለማየት ሁሉ እንጓጓ ነበር….›› ሳቅ

‹‹ይሄ ኒግር ግን ትንሽ ከነጭ ተቀላቅሏል መሰለኝ ፀጉሩም ብዙ ከርዳዳ አይደለም፣ አፍንጫውም ከኛ ብዙ አይለይም.. ምናልባት አረብም ሊሆን ይችላል››

‹‹ኖ አረብ አይመስለኝም፡፡ ሰሙን አታይም የአረብ ስም አይመስልም፡፡…ከመሪው ጎን መስቀል የሰቀለውም ክርስቲያን ቢሆን ነው፡፡›› በነሱ ቤት አረብ በሙሉ እስላም ነው፡፡

‹‹ኦ አኬ! ልክ ነሽ … የስፓኒሽም ስም አይደለም›› ካለች በኋላ

‹‹ሰር ዌር ዩ ፍሮም ?›› የሚለውን ጥያቄ ድንገት ወረወረችብኝ፡፡ ታንያ፡፡

በልቤ ሰረሰርሽ ይውለቅ አልኩና የሚያወሩትን ሁሉ ትኩረት እንዳልሰጠሁት ለማስመሰል በተከላካይነት ድምፅ ‹‹እናገራችሁኝ?›› አልኳት፡፡

‹‹እም! ይሄ ስም የየት ሀገር ስም ነው?›› /ወደ ተሰተሰው መንጃ ፍቃድ እያሳየችኝ/

እኔስ ማነኝ ‹‹ምን ቢሉሽ ምን ታውቂያለሽ?›› እንደማለት፡- ‹‹የጃንሜዳ›› አልኳት፡፡

የፈራሁት አልቀረም ‹‹እውነትክን ነው? እኔም እንደዛው ነው የገመትኩት!›› ብላ ሳቁን ልታስለቅቀኝ እንደምንም መለስኩት፡፡ ሊዲያ ግን ስምታው የማታውቀው ስለሆነባት ቀስ ብላ ጓደኛዋን ጠየቀቻት፡-

‹‹ጃንሜዳ ቤርሙዳ አካባቢ ያለ ሃገር ነው?››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹አይደለም፡፡ አፍሪካ ውስጥ ነው››

እኔም በተራዬ ይበልጥ ራሴን ለመደበቅ ‹‹ስትነጋገሩ የነበረው ቋንቋ ጀርመንኛ ነው አይደል?

ታንያ ‹‹አይደለም! ሩሲያውኛ ነው›› አለችኝና ወደ ጓደኛዋ ዞር ብላ በሩሲያውኛ፡- ‹‹መሃይም ነው አላልኩሽም?›› አለቻት ሳቋን እያፈነች፡፡

ሴትዮዋ አዋቂ መስሎ የመታየት በሽታ የተጠናወታት መሆኗ በግልፅ ያስታውቃል፡፡ ለሰው የምታሳየው ዕውቀት እንደሌላት ስለምታውቅ አዋቂ መስላ ለመታየት የግድ ሌላውን መሃይም አድርጋ ማሳየት አለባትና የተፀናወታት በአካባቢዋ ያለውን ሁሉ የሚለክፍ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡

ሩሲያ በቆየሁባቸው አመታት እንደዚች አይነት ፍጡር እንዴት እንዳልገጠመኝ ገረመኝ፡፡

እኔ እስከማውቀው ሩሲያውያን ባህልና ወጋቸው፣ ማህበራዊ መመዘኛቸው ብዙም ንዋይን ያላስቀደመ፤ በሰው ልጆች ተፈጥሯዊ እኩልነት ያመነ፣ ከዘረኝነት የተላቀቀ መሆኑን ነው፡፡

ህዝቡ ለእንጎርኪ፣ ቶልስቶይ፣ ፑሽኪንና ደስቶቭስኪይ ወዘተ መጣጥፎች ልቡ መቅለጡና አንባቢ ህዝብ መሆኑ፣ ማህበራዊ ሚዛኑ ለዕውነት ያጋደለ፣ ለሃቅ ምንግዜም ከርሱ የተራቡ፣ ለእውነተኛ ፍቅር የሚዋልል ቡን ስንልቡና ስላለው ነው፡፡

ለዚህ ነው ከዛ ህዝብ አብራክ እንደዚች አይነቷ ንዋይ አነፍናፊና ዘረኛ መፈጠሯ የደነቀኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ሩሲያውያን አንድ አይነት በጎ ቀና መንፈስ ያላቸው ናቸው ለማለት ሳይሆን ሩሲያውኛ ከመናገሯ በስተቀር ከሩሲያውያን የምትጋራው ስነልቡናዊ ዘይቤ አላየሁባትም ማለቴ ነው፡፡

‹‹አሜሪካ ተመጥቶ መሰልጠኑ ይሆን?›› ብዬ ራሴን ጠየቅኩት፡፡ ለራሴው ጥያቄ መልስ ስሻ ኒውዮርክ ውስጥ እስከዛሬ ያጋጠሙኝን ሩሲያውያን በሃሳቤ ቃኘኋቸው፡፡ ቅኝቴም በቅርቡ የተዋወኳቸውን ሩሲያውያኖች አስታወሰኝ፡፡

...........ያነሳኋቸው ከጆን ኤፍ ኬኔዲ አለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ነው፡፡ ሁለት ናቸው፡፡ እደሚያቸው በ30ዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገመቱ ወይዛዝርት፡፡

ከብሩህ ገፅታ ጋር ‹‹ሰላም!›› ብለውኝ፣ ሻንጣቸው ስለሚከብድ በጥንቃቄ እንዳነሳ ነግረውኝ፣ ታክሲዬ ውስጥ ከገቡ በኋላም ውሎዬ እንዴት እንደነበር ከጠየቁኝ በኋላ ‹‹እባክህ! አፐር ኢስት ሳይድ መንሃተን 79ኛውና ዮርክ አቨንዩ ላይ ውሰደን›› ብለው የጠየቁኝ፡፡

እነኚህን እንደነታንያ ካነጋገሬቻው ብቻ ሳይሆን ከሁኔታቸውም ቀምር ሩሲያውያኖች መሆናቸውን አውቄያለሁ፡፡

ጊዜው ከሰአት በኋላ ከስራ መውጫ ሰአት አካባቢ ነበርና ትራፊክ ከመብዛቱ የተነሳ ከኤርፖርቱ ወደ መንሃተን መውጫ የሆነው ‹‹ቫን ዊክ ኤክስፕሬስዌይ›› ስሙ እንደሚያመለክተው ‹‹Express way›› ሳይሆን ረዥም የመኪና ማቆሚያ መስሏል፡፡

ተሳፋሪዎቼ በራሳቸው ቋንቋ ወሬያቸውን ቀጥለዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ሩሲያውኛ ተናጋሪዎችን ሳሳፍር ‹‹ሩሲያ ውስጥ ከየት አካባቢ ናችሁ?››



t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት በዛው አገራቸው እንደነበርኩ አሳውቃቸውና ከእየሩ ፀባይ ጀምሮ በጋራ የሚወሱ ጉዳዮች ላይ እናወራለን፡፡ በዛች ዕለት ግን በጣም በመደማመጥ የሚያወሩትን ተሳፋሪዎቼን ላለመረበሽ በዝምታ እያዳመጥኳቸው መንዳቴን ቀጠልኩ፡፡

ወይዛዝርቶቹ የጋራ ወሬያቸውን ጨርሰው በየፊናቸው በሃሳብ ነጉደው ታክሲው ፀጥታ ሲነግስበት አንድ ነገር በጭንቅላቴ መጣልኝ፡፡ ሀገራቸውን እንደማውቅ በተለየ ሁኔታ ማሳወቅ፡፡ እናም ቀጠልኩ፡፡

‹‹ይቅርታ አድርጉልኝና ስታወሩት የነበረው የምን ሃገር ቋንቋ ነው?››

‹‹ሩሲያውኛ ነው!››

‹‹አንተስ ከየት ነህ?››

‹‹ከኢትዮጵያ ነኝ››

‹‹ኒውዮርክ ከመጣህ ቆየህ ?››

‹‹አዎ ቆየሁ .. ከ10 አመት በላይ ሆኖኛል›.

‹‹በኒውዮርክ ውስጥ ታክሲ መንዳት በጣም አስቸጋሪና አደገኛም ነው፡፡ ለምን ይህንን ስራ ለመስራት መረጥክ?››

‹‹ምርጫ አልነበረኝም .... አሜሪካ ውስጥ ኮሌጅ ለመግባት የሚያስችል መሰረታዊ ትምህርት በሀገሬ ስላልተማርኩና ካልተማሩ ደግሞ ጥሩ ስራ ስለማይገኝ የነበረኝ ጥሩ አማራጭ ሙያን ከማይጠይቁ ስራዎች የተሻለ ገንዘብ የሚገኝበት ታክሲ መንዳት ስለነበረ ነው››

‹‹ በሀገርህ ለምን ት/ቤት ሳትሄድ ቀረህ?››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹በሀገሬ እያለሁ እስከ 8ኛ ክፍል ከተማርኩ በኋላ አቋርጬ ሌላ ገንዘብ ማግኛ ትምህርት ስለጀመርኩ በመደበኛ ትምህርት ሳልገፋ ቀረሁ፡፡››

‹‹ገንዘብ ማግኛ ትምህርት ስትል የቴክኒክ ትምህርት ማለትህ ነው?››

‹‹አይደለም! የተማርኩት የገንዘብ ማግኛ ትምህርት፡- የሰዎችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ከእጃቸው አሻራ ላይ በማንበብ መናገር፣ ማንኛውንም አይነት ቋንቋ ሰዎች በሚስጥርነት ቢጠቀሙበት መረዳት የሚቻልበትን ልዩ ዘዴ ወዘተ የመሳሰሉትን ነው፡፡ በዚህም ጥልቅ ስልጠና ስለተሰጠኝ ማንም ሰው ሊያማኝ አይችልም››

በመገረም አይን እርስ በርስ ተያዩ፡፡

ወዲያው አንደኛዋ ቀድማ ‹‹እሺ እኔ በሩሲያውኛ ምን እንዳልኩ ልትነግረኝ ትችላለህ?›› በማለት ጠየቀችኝ፡፡

‹‹እችላለሁ! ግን ለሁለታችሁም የመጠየቅ ዕድል የምሰጣችሁ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡... ከዛ በኋላ ግን ገንዘብ አስከፍላለሁ!›› አልኳት የቀልዴን እንደሆን በሚገልፅ አሳሳቅ፡፡

‹‹እኬ እኬ›› አለችና አንደኛዋ ቀድማ በሩሲያውኛ ተናገረች፡፡ ትንሽ እንደማሰብ አልኩና በኋላ ማሳያ መስታወት እየተመለከትኳት ‹‹የተናገርሽው 79ኛውና ዮርክ አቨንዩ አድርሰን ብለሽ ነው›› አልኳት፡፡

የጥያቄውን መልስ ማግኘቴን ለመናገር ሀሊናቸው እንደበታቸውን ማዘዝ ስለተሳነው ከዛ ይልቅ ልክ እንደበፊቱ በመገረም ተያዩ፡፡ አሁን ግን እዟዟራቸውም ፈጥኗል፣ አይናቸውም ይበልጥ ፈጥጧል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠያቂዋ ተሳፋሪ ትንሽ በመገረም ትንሽ ካሰበች በኋላ ‹‹ኖ ኖ ኖ ኖ! ሚስጥርህን አውቄዋለሁ! ምን እንዳልኩ ልታውቅ የቻልከው ‹‹ዮርክ›› የሚለው የጎዳና መጠሪያ በሩሲያውኛም ‹‹ዮርክ›› ስለሆነ በጭፍን መላምት ተጠቅመህ ነው!›› ብላ ጮኸች፡፡ አጫጨሿ ‹‹ነቃሁብህ አይደል?›› የሚል አይነት ነው፡፡

የውስጡን ሳቅ ለማፈን እየታገልኩ ‹‹ይሄማ ምክንያት ማብዛት ነው፡፡ ያልሽውን አግኝቼዋለሁ፡፡ የሰጠሁሽን አንድ ዕድል ተጠቅመሽበታል፡፡ አሁን የመጠየቅ ዕድል የምሰጠው ለጓደኛሽ ብቻ ነው፡፡›› አልኳት፡፡

‹‹እኬ! እኬ!›› አለች ጓደኛዋ ለመጠየቅ በመጣደፍ፡፡ እናም ተናገረች፡፡

ወዲያው ብመልስላት ቋንቋውን መቻሌን ስለሚጠራጠሩ ‹‹አነጋገርሽ በጣም ፈጣን ስለሆነና መኪና እየነዳሁ በኋላ መስታወት የከንፈሮችሽን ንቅናቄ ለመከታተል ትንሽ ስለሚቸግር ሳትቸኩይ በቀስታ ድገሚልኝ›› አልኳት፡፡

ሳትቸኩል ‹‹ከ6 አመት መለያየት በኋላ ሀገሬ በመሄድ እናትና አባቴን ጎብኝቼ፣ አሮጊቷን እያቴን ሳትሞትብኝ አይቼ በመመለሴ በጣም ደስ ብሎኛል›› በማለት ደገመችው፡፡

ይሄንን ውስብስብ አረፍተነገር ቃል በቃል ብተረጉም አሁንም ያለጥርጥር ቋንቋቸውን እንደማውቅ ስለሚጠረጥሩ፤ እንደሚያስብ ሰው ጊዜ ወስጄ ‹‹እንደሚመስለኝ የተናገርሽው ከብዙ አመት ናፍቆት በኋላ ሀገርሽ ሄደሽ ቤተሰቦችሽን በሙሉ በማግኘትሽ ደስተኛ እንደሆንሽ ነው.. ልክ ነኝ?›› አልኳት /መልሱ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማወቅ እንደቋመጠ ሰው/



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠያቂዬ «ዩ ራይት! ዩ ራይት!» አለች ለኔ፡፡ ለራስዋና ለጓደኞ መሆኑ ነው መሰል በሩሲያውኛ «ይህን ማመን አልችልም! የሚገርም ነው» የሚለውን ቃል መላልሳ ደገመችው፡፡

የመጀመሪያዋ ጠያቂ አፏን ይዛ በአይኗ መናገር ይዛለች፡፡

እኔ ምንም የሚያስደንቅ ነገር እንዳልሆነና በነሱ ላይ የተፈጠረውን ስሜት ማየት ለኔ የተለመደ ነገር እንደሆነ ለማሳየት ኮስተር ብዬ መንዱ ላይ አተኩሬያለሁ፡፡

እንደኛዋ ጠያቂዬ የተዘጋውን እንደበቷን ለመግፀን ከፈተችው፡፡ እኔን፡፡ «አባክህ! አባክህ! እንዴት ማወቅ እንደምትችል ንገረን» አባባሏ «እምላክ ሆይ አባክህ ተለመነን» የምትል አስመሰሏታል፡፡

የሞኝ ጥያቄ ነው የምትጠይቂኝ ለማለት የማሽሟጠጥ ሳቄን በጭንቅላቴ ውዘወዛ እያጀብኩት «ይሄ ማለትማ ለ3 አመት የተማርኩትን ትምህርት በ45 ደቂቃ የታክሲ ጉዞ እንዳስተምራችሁ መፈለግ ማለት ነው፡፡ የኔ እመቤት በዚህ ላይ ነገርየው የተፈጥሮ ስጦታን የሚጠይቅ ነገር ነውና ጥያቄሽን ለማሟላት ያዳግተኛል .... ለማንኛውም ግን ያሳየኋችሁ ሁሉ ምትሃት ሳይሆን የፊት ገፅታን፣ የአይንን፣ የከንፈርንና የአካል እንቅስቃሴን በቅፅበት ኮፒ አድርጎ ወዲያው በማገጣጠም የንግግሩን ፍሬ ነገር የመጨበጥ ጥበብ ነው፡፡ በአለማችን ያሉ ቋንቋዎች በሙሉ የጋራ የሆነው ሚስጥራቸው ይሄው ነው! ተግባባን?» በማለት ፈላስፋ መስዬ በኩራት ተራቀቅኩ፡፡

«እሺ እሱስ ይሁን የእጃችንን አሻራስ ታነብልናለህ?» የሚለውን ጥያቄዋን ከረሽም የልመና ዜማዊ ቅላጼ ጋር «አባክህ!!!» በሚለው ቃል ደመደመችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ትንሽ ኮራ በማለት በመጀንን ላይ እንዳለሁ ሁለተኛዋ ተሳፋሪ ሁለት የመቶ ብር ኖቶች ከቦርሳዋ አውጥታ «የሁለታችንንም ታሪክና የወደፊት ዕጣ ፈንታ በትክክል ከነገርከን ይሄ 200 ዶላር ያንተ ነው!» በማለት መልስ እስክሰጥ ክፍ አድርጋ ይዛው ቆየች፡፡

ደግነቱ እነሱው ሃገር እያለሁ አብረውኝ ይማሩ የነበሩ ህንዶች ዋና ዋናዎቹን የውስጥ እጅ የእሻራ መስመሮች ማለትም ዕድሜ፡ የትዳር ሁኔታ፣ የልጆች ብዛት፡ ዕድለኛነት፣ የመኖሪያ ቦታ፡ ገንዘብ እያያዘ ወዘተ የሚሏቸውን አሳይተውኝ ነበርና ምንም እንኳ ባላምንባቸውም ታክሲዬ ውስጥ ከገቡ በኋላ ሲያወሩ ከነበረው የባሎቻቸውና ልጆቻቸው ወሬ ጋር አብሬ በመቀየጥ ስላለፈው ህይወታቸው በመጠኑ ነገርኳቸውና የወደፊቱን በተመለከተ ግን ረዥም ዕድሜ፣ ጤንነትና የደስታ ህይወትን አምበሸበሽኳቸው፡፡

የነገርኳቸውን ሙሉ በሙሉ ማመናቸውን ያረጋገጥኩት ከምስጋና ጋር 200 ዶላሩ ከጎኔ ካለው የፊት መቀመጫ ላይ ሲወረወርልኝ ነው፡፡

የምገርም ሰው መሆኔ ተነገረኝ፡፡ የልብ አድናቆታቸው ተቸረኝ፡፡ ታክሲዬን ወደዚያ ወርውሬ ወደፊቸ በዚህ እስደናቂ ችሎታዬ መተዳደር እንዳለብኝና እነሱም ብዙ ደምበኛ እንደሚያስገኙልኝ ሳልጠይቅ ቃል ገቡልኝ፡፡ ለማንኛውም የስልክ አድራሻዬን መጨረሻ ላይ እንድሰጣቸው ጠየቁኝ፡፡

እንደተልደ የጀመርኩት ነገር እየሰፋ መጥቶ ሰዎቹ በቁምነገር ስለኔ የወደፊት ህይወት አሳቢና ተጨናቂ ሆነው ሲመክሩኝ የኔ ጭንቀት እንዴት አድርጌ ሁኔታውን እንደምቋጨው ሆነ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የማዴታ እውነቱን መናገርና 200 ዶላራቸውን መመለስ አሰብኩ። እውነቱን ስነግራቸው ደግሞ «ድንገት ሊበሳጩ ይችሉ ይሆን ?» ብዬ አሰብኩና በመጨረሻ «መውረጃቸው ደርሰዋልና ቢበሳጩም ወዲያው ጥያቸው ስለሚሄድ እዳው ገብስ ነው» የሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩ።

ሳቁን እንደ ሬዲዮ ዜና አቅራቢው «የመግቢያ ሙዚቃ» በመጠቀም ለቀቅኩትና « ምን መሰላችሁ!» ብዬ ቀልባቸውን ሳብኩት።

ምስኪን ተሳፋሪዎቹ «ከተአምረኛው ታክሲ ሹፌር» ሌላ የቀረ «ተአምር » ጠብቀው አፋቸውን ከፈቱ።

« እስካሁን ያወራኋችሁ ወሬ በመንገዳችን ላይ የነበረውን ትራፊክ ላለማሰብ ያመጣሁት ዘዴ ነው። ማለትም የነገርኳችሁ በሙሉ እውነት አይደለም። ካልኩ በኋላ ንግግሬን ቆም አድርጌ በመስታወት ሳያቸው፣ አፋቸው ሳይላወስ ያፈጠጠው አይናቸው «ምን !? ምንድነው የምታወራው!?» ይላል ።

በሩሲያውኛ ቋንቋ መናገር ቀጠልኩ።

« እኔ ማለት ለአመታት በሞስኮ የተማርኩ፣ ባህልና ወጋችሁን በመጠኑ የምረዳ፣ ቋንቋችሁንም መጥፎ ባልሆነ ደረጃ መናገርና መግባባት የምችል.....»

በማለት ታሪኬን ባጭሩ በመጨመር የእንቆቅልሹን ስምና ወርቅ ፈታሁላቸውና 200 ዶላሩን በመጣበት ሁኔታ ወደኋላ ወረወርኩት።

የተሳፋሪዎቹ አይምሮ ያልጠበቀውን የሩሲያውኛ ንግግሬን መስማት የጀመረው ዘግይቶ መሆኑን የተረዳሁት «የፈጣሪ ያለህ! የፈጣሪ ያለህ» ማለት የጀመሩት የተወሰኑ ሰከንዶች ከተናገርኩ በኋላ ስለነበር ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹የፈጣሪ ያለህ!›› ማለታቸውን አቁመው ሲያዳምጡኝ የነበሩትን ወይዛዝርት ንግግሬን ስጨርስ መልስ ለመስጠት ጊዜ አስፈልጓቸዋል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ያልጠበቁት ነገር በመፈጠሩ ግራ ተጋብተዋል፡፡ ባጠቃላይ መላ ቅጡ ጠፍቷቸዋል፡፡

በኔ በኩል ቲያትሬን ጨርሼ በመስታወቴ ሁኔታቸውን እየተከታተልኩ ፤ እየሳቅኩ መንዳቴን ቀጥያለሁ፡፡ ነፍሳቸው ስትመለስ ሳቁን በሳቅ አጀቡት!፡፡

ፍጹም ያልጠበቁትና መቼውንም የማይረሱት ገጠመኝ እንደሆነ ደጋግመው ተናገሩ፡፡ ‹‹ፕሮፌሽናል አክተር›› ነው የሆንክብን በማለት መታለላቸውን ሙሉ በሙሉ በደስታ ተቀበሉት ፡፡

መውረጃቸው እስኪደርሱ እንደ ‹‹የወንዝ ልጆች›› ሆነው ቀርበውኝ በጋራ ነጥቦች ላይ በሩሲያውኛ እየተቀባበልን ስናወራ ጊዜ አጥሮ ወሬያችንን ሳንጨርስ ህንፃቸው በር ላይ ደረስን፡፡

የበር ጠባቂው የታክሲውን በር በመክፈት ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ!›› ብሎ ተግባሩን ሲጀምር የእቃ መጫኛውን ቁልፍ ተጫንኩለትና ለተሳፋሪዎቼ አዲስ በወጣው ህግ መሰረት የሚጠበቅባቸው ክፍያ 30 ዶላር መሆኑን አሳወቅኩ፡፡

ሩሲያውያን ተሳፋሪዎቼ ‹‹ቆንጆ ጉዞ ነበር!›› በማለት ካመሰገኑኝ በኋላ ወዲያና ወዲህ ሲንገላታ የነበረውን 200 ዶላር የያዘችው ለመጨረሻ ግዜ እንዱን ወደኔ አንዱን ወደቦርሳዋ ወረወረችና ‹‹አመሰግናለሁ! መልስ አልፈልግም›› ከማለቷ ሁለቱም ፈጠን ብለው መውረድ ጀመሩ፡፡ እኔም እንዳያመልጡኝ በችኮላ ለ100 ዶላር የሚገባውን ምስጋና አቀረብኩላቸውና .... መኪናዬን ከማንቀሳቀሴ በፊት እጅ በማወዛወዝ ተሰነባበትን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔና ፍሊያውያን ታክሲዬ ውስጥ ስንገናኝ ሁልጊዜም ደሂንን በሚመስል ሁኔታ ነው የምንለያየው፡፡ እኔም ታክሲ የምነዳ ሳልሆን ከጓደኞቼ ጋር ያለሁ ነው የሚመስለኝ፤ እነሱም ከሌሎች ተሳፋሪዎች የተለየ ቅርበት የሚያሳዩኝ እንደኔው የጓደኝነት ስሜት ተሰምቷቸው ይመስለኛል፡፡

የዛሬዋ ተሳፋሪዬ ግን እንኳን እንደጓደኛ ቀርቶ ሰውን እንደሰው የማታይ መሆኗ ፊቷም ያልጠበቅኩት ነው፡፡ የዛሬው ገጠመኜ ‹‹ለካስ እንደዚህም አይነት አለ?›› ብዬ ከፍሊያውያኖች ጋር ወደፊት የሚኖረኝን ግንኙነት እንደሚያስቀይረኝና የተቆጠበ እንደሚያደርገው ነሁኑ ታውቆኛል፡፡

ከታንያ ጋር እጅ በማወዛወዝ ሰላምታ ሳይሆን አዕምሮ በሚጠዘጥዝ እንደምንለያይ ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚህም ቤታቸው አካባቢ እየተቃረብን ስለሆነ የስድብ ውርጅብኝ ላወርድባት ተዘጋጅቻለሁ፡፡

ደህና እኔን ለቀቅ አድርጋ ስለ ፍሎሪዳ ፍቅሯ፣ ስለሄደችባቸው የመንሃተን ምርጥ ሬስቶራንቶች፣ ስለ የምትሄድባቸው የታወቁ የቁንጅና ሳሎኖች ገጠመኞቿ ወዘተ ያለማቋረጥ ስትለፈልፍ የነበረችው ሴትዮ አርዕስቷን ቀይራ ወደኔ ተመለሰች፡፡

‹‹ሜትሩን አየኸው? 35 ዶላር ይላል! እዚህ ከኛ ቤት መታጠፊያ ላይ ስንደርስ ከ33 ዶላር መብለጥ አልነበረበትም!››

‹‹ምንም አይደለም በቃ! በጣም ትራፊክ ውስጥ ስለተቀመጥን የ2 ዶላ ለውጥ ሊመጣ ይችላል››

‹‹ኖ ኖ ኖ በፍፁም ሊመጣ አይችልም››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹በቃ ተይው አሁን ለ2 ዶላር ምን እንዲህ ያበሸቅሻል? ለዛውም ስንሄድ አንቺ ስለከፈልሽ አሁን የመክፈል ተራው የኔ ነው፤ በቃ ለኔ ተይው እንዳትናገሪው!››

‹‹አንቺ ደግሞ ለ2 ዶላሩ መስሎሽ ነው እንዴ? እኔን የሚያበሽቀኝ የማንም መሀይም ከአፍሪካ ሜካዎች ይመጣና ሰርቶ የሚያልፍለት አንስ ሰውን ለማታለል ሲሞክር ነው እንጂ!›› ስትል ከቁጥጥር ውጭ ሆንኩኝ፡፡ ቤቷ እንደደረሰች ገንዘቤን ከተቀበልኳት በኋላ ሙሉዋ አድርጌ ልለድባት የተዘጋጀሁት ሰውዬ ባላሰብኩበት ጊዜና ቦታ ጦርነት አስጀመረችኝ፡፡ በራሷ ቋንቋ፡፡

‹‹ምን አልሽ? አንቺ ደደብ! መሃየሟ አንቺ ነሽ!.. የሰውን ማንነት ቀርቶ እራስሽን ሳታውቂ አፍሽን የምትከፍቺ!›› ሁለቱም አይናቸው ፈጠጠ፡፡

‹‹ከሜካ እየመጡ የሚያልፍላቸው አንስ የምትይው አንቺ እራስሽ ስደተኛ ሆነሽ እንዲያልፍልሽ አይደለም አሜሪካ የመጣሽው? እንዳንቺ አይነት ጨለማ ሩሲያ ውስጥ ያለ አይመስለኝም ነበር!

ተሳዳቢዋ ፊቷን በእጇ ከልላ ‹‹አንተ ጥሩ ሰው አይደለህም! እንዴት ሚስጥራችንን ቋንቋ እንደማያውቅ ሆነህ ትሰማለህ? ተንኮለኛ ነህ!›› እያለች ስትለፈልፍ፥ ሊላኛዋ ‹‹ፊቷን ጉልበቷ ውስጥ ቀብራ ‹‹ወየው እምላኬ! ወየው እምላኬ!›› ትላለች፡፡ እንደሙዚቃ አጃቢ በመደጋገም፡፡

እኔ በንዴት እየተንበገበኩ የጆሯቸው ታንቡር እስኪበጠስ በጩኸት እንዴ በሩሲያውኛ እንዴ በእንግሊዝኛ ሲትዬዋን ማዋረዴን ቀጥያለሁ ፦

‹‹..... ዝምበይ አንቺ ደደብ ዘረኛ! የተሳደብሽውን የዘረኛነት መርዛም ስድብ በቴፕ ቀድቼልሻለሁ ፍርድ ቤት ስትቀርቢ ትሰሚዋለሽ!....›› /አሁን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለቱም ወየው አምላኬ! ከማለት በስተቀር ሌላ ቃል ለማውጣ ድንጋጤያቸው የሚያስችላቸው አልሆነም/

‹‹......በስልክ ከፍቅረኛሽ ጋር ያወራሽውንና የእሉሻን ታሪክ ጨምሮ ጠቅላላ ያወራሽውን የቴፕ ቅጂ ኮፒ በውሽት እታለሽ ላገባሽው ባሌ እስረክብልሻለሁ!››

ተሳዳቢዋ ሴት ሳንባ መሰለች፡፡ ለዘላለም ሰው የማማትና የመናቁ በሽታዋን የነቀልኩላት ይመስለኛል፡፡ ፍፁም ያልጠበቀችው ሁኔታ ስለገጠማት ከእንግዲህ ወዲህ የማታውቀው ሰው ባለበት ፀያፍ ሩሲያውኛ ቃል እንደማይወጣት አልጠራጠርም፡፡

ከቢታቸው መድረሴ ከስድብ ውርጅብኝ ገላገላቸውና መኪናው ከመቆሙ ተሳዳቢዋ በሩን በርግዳ ስትሮጥ ሊድያ ድፍን 50 ዶላር ወርውራ መልስም ሳትጠይቅ በሩጫ ተከተለቻት፡፡ ሁለቱም በድንጋጤ በሩን እንኳን ሳይዘጉ፡፡

በአይኔ ስከተላቸው ከግዙፉ የሃብታም ቪላ በጓሮ በኩል እየተጣጣሁ ገቡ፡፡ ወዲያው እነሱ ከገቡበት ጓሮ በኩል እሳር የሚያሀል ዥንጉርጉር እዳኝ ውሻ እያጓራ ወደኔ መጣ፡፡ መኪናዋን በፍጥነት መንዌቄ በማስነሳት የተበረገዱትን በሮች በራሳቸው ዘጋኋቸውና መንገዴን ቀጠልኩ፡፡

ውሻው ትንሽ መንገድ ሸኝቶኝ ሲመለስ ‹‹ለጊታህ ታማኝ ነህና ከሚስት ተብየዋ አንተ ትሻላለህ›› ብዬው ወደ መንሃተኔ አቀናሁ ፡፡

በመጣሁበት ‹‹ሚድ ታውን ታናል›› ብመለስ ክፍያ ስለሚጠብቀኝ በማያስከፍለው ‹‹ኩይንስ ቦሮ›› ድልድይ /Queens borough bridge/ ለመሻገር ወሰንኩና ወደሱም የሚያደርሰኝን ‹‹ኩይንስ ቡልቫርን›› /Queens boulvard/ ይዤ ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በምናቤ የሲትዬዋን ባል እየቃኘሁ ከራሴው ጋር ማውራትና መሟገቴም እንደዛው ቀጥሏል፡፡

ሰውዬው የአሜሪካንን ከፍተኛ የህይወት ውጣ ውረድ ሩጫ ተቋቁሞና አሸንፎ በምንም ይሁን በምን ከፍተኛ ሃብታሞች የደረሱበት ቦታ የደረሰ ነው፡፡ መቼም አንድ ሰው እዚህ ቦታ ላይ የመድረሱ ሚስጥር ባብዛኛው በህይወቱ ሂደት ውስጥ ለሚገጥመው ሁኔታ ትክክለኛ የውሳኔ ምላሽ በመስጠቱ ከዛም በላይ የየጊዜውን የህይወቱን ዕቅድ በሚገባ በማቀዱና በመተግበሩም ነው ብዬ ገመትኩ፡፡

ምናልባትም ቤሳ ቤስቲን ከሀገሩ ይዞ ያልመጣው ስደተኛ በአዲስ ሀገር ውስጥ የሚገጥመውን ባዕድ ሁኔታ ሁሉ አጢኖና ተላምዶ፡ ዋነኛው የኑሮ ስርዐት ውስጥ ዘልቆ በመግባት ውጤታማ መሆን መቻሉ መለኛ ሀሊናና ጠንካራ ሰብዕና ቢኖረው ነው፡፡ ያም ባይሆንና በወንጀል የከበረ ቢሆን እንኳን የዘመኑን የተራቀቀ ፀረ ወንጀል ክትትል ለመቋቋም ጥበብንና ወሳኝነትን ይጠይቃልና በዚህም በዚያም ግለሰቡ ተራ ሰው እንዳልሆነ አሰብኩ፡፡

‹‹ታዲያ ይሄ የህይወትን መሪ ጨብጦ የማሽከርከርን ዘዴ የተካነ ፍጡር በትዳር ምርጫው ላይ የወሰነው ውሳኔ የታወረ የመሆኑ ሚስጥር ምንድነው?›› ብዬ እራሴን ጠየቅኩት፡፡ ‹‹በስሜት መመራት ነዋ!›› ብዬ ስመልስ አፍታም አልወሰደብኝ፡፡

‹‹ልክ ነኝ ስሜት ትክክለኛ ውሳኔን የሚጋርድ ግድግዳ ነውና በስሜት ተነድቶ ተሳሳተ›› ካልኩ በኋላ ኖ ኖ ኖ በስሜት ተነድቶ ሳይሆን በሃብቱ ተማምኖ ነው!.... በሃብቱ ጡንቻ እንደሚገዛት ተማምኖ ስለመሆኑ ሲትዬዋ አረገልኝ ከምትለው መረዳት ይቻል የለም እንዴ? በማለት ሃሳቤን ለወጥኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ እንደገና ተመልሼ ወጣትነቷና ውበቷ አሸንፎት.... ወዘተ በሚል የሃሳብ ባህሮች ውስጥ ስደፈቅ ስወጣ ቆየሁ።

በመጨረሻ «ትክክለኛ ሁኔታውን ለመገመት እንደምን ይቻላል፤ ከራሱ ከባለቤቱ በስተቀር ማንስ ሊያውቀው ይችላል?» በሚሉት ጥያቄዎች የራሴኑ ጥያቄ በራሴው ጥያቄ በመመለስ ሃሳቤን ቆረጥኩት።

የሚስት ተብየዋን ውስጠ ማንነት ግን በተፈጠረው አጋጣሚ ለማወቅ ስለቻልኩና ለባሏም ምን እንደደገሰችለት ከራሷ እንደበት ስለሰማሁ አዘንኩለት። «ድብቅ አላማዋንና ፍላጎቷን ተፈጥሮ በለገሰቻት ውበት ሸፍናና ደባብቃ ከጓዳው የገባችው ህጋዊ ቀማኛ ምናልባት እድሜ ልክ የለፋበትን ንብረቱን እኩል ለእኩል ለመካፈል ከፍርድ ቤት ስታቆመው ምን ይሰማው ይሆን» ብዬ አሰብኩና ለሱ እኔ በገንኩ።

ኩይንስ ቡልቫርድ ላይ እንዲህ ከራሴ ጋር እያወራሁ በመንዳት ላይ እንዳለሁ በኋላ ማሳያ መስታወቴ የኔ ቢጤ ባለ ታክሲ የግራ መስመሩን ይዞ «እንደ ጀት» ሲምዘገዘግ አየሁት። በስራ ፀባያችን ምክንያት «ምን አይቶ ነው?» ብዬ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ነቅቼ ወደፊት ስመለከት ከሩቅ ርቀት ላይ ታክሲ ለማስቆም እጃቸውን የሚያወዛውዙ ሴትዮ አየሁ።

ኩይንስ ውስጥ ያውም ወደ መንሃተን አቅጣጫ በሚወስድ መንገድ ላይ ተሳፋሪ ማግኘት ብዙም የማይገኝ እድል ነውና ሳልቀድም ለማንሳት ነዳጅ መስጫውን እስከመጨረሻው ረገጥኩት። ከእነዳዴ ተሳፋሪዋን እንዳላየሁ በመረዳት ቀድሞኝ ሊያነሳ ሲከንፍ የነበረውን አሞራ አበሳጨሁት መሰል ልክ ሴትዬዋን ለማንሳት እንዳቆምኩ የመኪናውን ጡሩንባ እንባርቆት በመጣበት ፍጥነት ባጠገቤ ያለመጠን ተጠግቶ አለፈ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሳፋሪዬ ከ70 አመት በላይ ይገመታሉ፡፡ ባጭር የተሰተካከሉት ነጭ ፀጉራቸው ብን እስኪል ተበጥሯል፡፡ ደንደን ያለው ሰውነታቸው ከአቅማቸው በላይ መከበዱን የመንገድ ጠርዙን ደረጃ /ኮርዶን/ ወርዶ ታክሲ ውስጥ ለመግባት የነበራቸው በጥንቃቄ የተሞላና ጊዜን የሚወስድ እርምጃቸው ይመሰክራል፡፡ በቀኝ እጃቸው የእጅ ቦርሳ አንጠልጥለዋል፡፡ በግራ እጃቸው የታቀፉትን በሰማያዊ ወረቀት የተጠቀለለ አበባ አጨማመዳቸው ከፍተኛ እንክብካቤ እንደሚያደርጉለት ያስታውቃል፡፡

ጊዜያቸውን ወስደው ወደ ታክሲዬ እንደገቡ ሰላምታ ተለዋወጥንና መንሃተን 102ኛው መንገድና 2ኛው ጎዳና ከሚገኘው ‹‹ሜትሮፖሊታን›› ሆስፒታል እንዳደርሳቸው ነገሩኝ፡፡ ባደዬን ወደመንሃተን የምሄደው ሰውዬ ተከፍሎኝ ልሄድ ነውና ደስ አለኝ፡፡

የያዙት አበባ ለህመምተኛ የሚሰጥ መሆኑን በመገመት ለወሬ መክፈቻ አደረግኩት፡፡

‹‹ቆንጆ አበባ ይዘዋል! የቅርብ ዘመድ ታሞብዎ ነው?››

‹‹እመሰግናለሁ የኔ ልጅ !.... አዎ ባለቤቴን ልጠይቅ ነው የምሄደው››

‹‹ሆስፒታል ከገቡ ቆዩ?›› /እሳቸው ባይገባቸውም በለመደብኝ የከንፈር መምጠጥ እጅቤ/

‹‹ዛሬ 29ኛ ቀኑ ነው›› /በረዥሙ ተነፈሱ/

ቀኑን በትክክል መቁጠራቸውና አተነፋፈሳቸው እያንዳንዷን ቀን በጭንቅ እንደሚቆጥሯት ለመገንዘብ ያስችላል ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ውይይታችን ቀጠለና ባለቤታቸው የ76 አመት አዛውንት እንደሆኑና ሀመማቸው ከአመት በፊትም ሆስፒታል አስገብቷቸው እንደነበር፣ ባለቤታቸውን የያዛቸው የደንዳኔ ካንሰር በሰውነታቸው እንደተሰራጨና ከ3ወር በላይ እድሜ እንደሌላቸው ዶክተራቸው እንዳሳወቃቸው፣ አሁን እነደገና እንዳገረሸባቸው ወዘተ ካጫወቱኝ በኋላ፡-

‹‹ባሌ በዶክተሮቹ ስሌት ትርፍ ህይወት ነው እየኖረ ያለው፣ ነፍሱ በእግዚአብሄር እጅ ነች›› አሉና ከራሳቸው ጋር ማውራት ጀመሩ፡፡

የሴትዮዋ ሁኔታ አሳዘነኝና ‹‹እግዚአብሄር ያውቃል! ዶክተሮች የሚሉት ሁሉ ይሆናል ማለት አይቻልም›› በማለት ማፅናናቴን ከመጀመሬ ‹‹እንደዚህ ስለሰው ነገር የሚያሳስበው የየት ሀገር ሰው ይሆን?›› ብለው በመገረም ይመስለኛል ሀገሬን፣ ሀይማኖቴን፣ መቼ እንደመጣሁ፣ የኒውዮርክ ኑሮዬ ተስማምቶኝ እንደሆን ወዘተ እየጠየቁኝ በየተራ መልስ ሰጠኋቸው፡፡ ስለኔ መጠነኛ ግንዛቤ እንዳገኙ፡-

‹‹ሲያዩህ ጥሩ ሰው ትመስላለህ ... በፀሎትህ ባሌን እንደምታስብልኝ እርግጠኛ ነኝ›› አሉኝ፡፡ በፀሎት የተጋሁ ሰው ባልሆንም አስታውሼ ለመፀለይ ለራሴ ቃል ገባሁና ‹‹እፀልይላችኋለሁ!.. ሁሉን ለአምላክ አሳልፈው ይሰጡ! ጌታ ከዚህ ችግር የሚወጡበትን ብርታት እንደሚሰጣቸው ተስፋ አለኝ›› አልኳቸው፡፡

ለመልካም ምኞቱ ካመሰገኑኝ በኋላ ‹‹እንዳልከው የኔም ተስፋ በእግዚአብሄር ቢሆንም አሁን ግን የ51 አመት የትዳር ጓደኛዬን ሊወስድብኝ ነው ብዬ በጣም ፈርቻለሁ›› አሉና ተከዙ ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይችን ትንሽ ቆይተው በእጃቸው የያዟት አበባ ላይ አይናቸውን ተክለው ‹‹ይች አበባ ለባሌ የምሰጣት የመጨረሻ ስጦታ እንዳትሆን ነው ስጋቴ!›› ብለው ሲሉ የሆድ ብሶታቸው በፊታቸው ላይ መነበብ ጀመረና እንባቸው በአይናቸው ግጥም አለ፡፡ተጣድፈው ከቦርሳቸው ውስጥ ናፕኪን አወጡና የአይናቸው ኩል እንዳይበላሽ በጥንቃቄ እንባቸውን አበሱት፡፡

ሁኔታቸው ከንፈር ከማስመጠጥ አልፎ በሃዘን ስሜት የሚያስወርር ነበርና ለማፅናናት ቃል ልወረውር የምችልበት ሁኔታ ላይ አልነበርኩም፡፡ በዝምታ መንዳቴን ቀጠልኩ፡፡

ተሳፋሪዬ ትንሽ ጊዜ ወስደው ውስጣቸውን ካረጋጉ በኋላ፡- ‹‹ከእንግዲህ አምላኬን እድሜ ስጠኝ ብዬ አልለምነውም፡፡ ባሌን የሚወስደው ከሆነ ግን በዛች የመጨረሻ ትንፋሹ ሰአት ካጠገቡ አርገኝ፣ ስሜውና እንደማፈቅረው ነግሬው የምሰናበትበትን ሁኔታ እንዳይነፍገኝ ብቻ ነው ፀሎቴ!›› አሉና ቆዘሙ፡፡

እኝህን ምስኪን ሴት የባሰ ሃዘን ውስጥ ከተትኳቸው ብዬ ተፀፀትኩና ትኩረታቸውን ለማስቀየር አርዕስት ለውጬ ‹‹ልጆች አላችሁ?›› አልኳቸው፡፡

‹‹እግዚሃብሄር ይመስገን ሁለት ሴቶችና አንድ ወንድ ልጅ እንዲሁም ስድስት የልጅ ልጆች አሉን፡፡ .....ልጆቻችን ከኔ ጋር ሆነው አባታቸውን ያስታምማሉ፡፡ የልጅ ልጆቻችንም እንዲሁ ካጠገቡ አልተለዩም››

‹‹ይሄ እድለኛነት ነው! የልጆቻችሁ ደጋፊነትና ጥሩነት የእናንተ በፍቅር ላይና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተው የንጹህ ትዳር ውጤት ይመስለኛል››



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ይሆን ይሆናል፡፡ ዋናው ግን እምላክ ትዳራችንና ልጆቻችንን ስለባረከልን ነው!......›› ካሉኝ በኋላ ትውስ ያላቸው ነገር ሲያስፈልጋቸው እኔም አርዕስት በማስለውጤ ደስ አለኝ፡፡ ያስፈልጋቸውንም ነገር ለመስማት ጓጓሁ፡፡ እሳቸውም ሊያሜውቴኝ አልሰሰቱም፡፡ ‹‹ምን መሰለህ ! ...›› ብለው ጀመሩ፡፡

‹‹.... ልጆቻችን ገና በለጋ እድሜ እያሉ ሁኔታቸውን ያስተዋሉ ሰዎች ከራሳቸው ልጆች ያነፃፅሯቸውና ስለሚገረሙባቸው ‹‹እንደዚህ የተባረኩ ልጆች የማሳደግ ጥበባችሁ ምንድነው? የትኛውን የልጅ የማሳደግ መመሪያ መፅሀፍ ነው የምትከተሉት?›› በማለት ባሌን ሲጠይቁት የሁልጊዜም መልሱ ‹‹ብዬና ሚስቴ ጉልበት!›› የሚል ነበር፡፡ ታዲያ አንዳንዶቹ ምን ማለቱ እንደሆነ ስለማይገባቸው እኔ መሃል እገባና ‹‹እኔና ሚስቴ በጉልበታችን ተንበርክከን እምላካችንን በመለመን ማለቱ ነው እሳቸው ነበር›› በማለት በድጋሚ ፈገጉ፡፡

‹‹የሚደንቅ ነው!›› የሚል ነበር የተሰማኝን ስሜት የገለፅኩበት አጭር ቃል፡፡

ሴትየዋ ተመልሰው የወሬያቸውን አርዕስት ስለባለቤታቸው አደረጉት፡፡ ‹‹ከባለቤቴ ጋር በትዳር ተሳስረን በኖርንባቸው ዘመናት ቤታችን በፍቅር የሞቀችና ደስተኞችም ነበርን፡፡ ይሄ ነው የምለው ባሌ ያስቀየመኝ ነገር ትዝ አይለኝም፡፡ እኔም ባሌን ቅር አሰኘቸው አላውቅም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ብዙ ብዙ የህይወት ውጣውረድ አብረን ስላሳለፍን ያለእሱ የኔ ህይወት ጣዕም የለሽና ትረጉም አልባ እንደሚሆን ነው፡፡ ከእንግዲህ መፅናኛዎቼ ልጆቼና ልጅ ልጆቼ ብቻ ናቸው፡፡ ባሌ የሌለበት የኔ ህይወት ሳጥን እንደሚቀመጥ አብስ ነው፤ ከልጆቼ ጋር ስሆን የምለብሰው እንሱ የሌሉበት ደግሞ እውልቁ



t.me/OLDBOOKSPDF

የማስቀምጠው፡፡.....›› በማለት ያንን አስፈሪ ባዶ ህይወት እንጂ ሞትን እንደማይፈሩት ገለፁልኝና ዝምታ ዋጣቸው ፡፡

በሃሳብ እንጓጎዳቸው ወሬያቸውን በጥሞና የሚያዳምጣቸው ሰው እንደነበር ሳይቀር ያስረሳቸው መሰለኝ፡፡ ምናልባትም ከባላቸው ሞት በኋላ የሚጠብቃቸው ‹‹ባዶ ህይወትን›› በምናባቸው እየኖሩት ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩ፡፡

ካሳፈርኳቸው ጊዜ ጀምሮ ያጫወቱኝ ታሪካቸው፣ አኳኋንና አባባላቸው ሁሉ በውስጤ የመሰረጽ ሀይል ነበረውና ታክሲዬን የማሽከረክረው በደመነፍስ ነው፡፡

የሰው ሀሊና መዝገብ ቤቱ ውስጥ ያኖረውን የቆየ ገጠመኝ ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ ሲገጥመው፣ አዲሱ ለአሮጌው ‹‹የይለፍ ቃል›› በመሆን ፋይሉን ከተቀመጠበት ያወጣዋልና የኒህ ተሳፋሪዬ ታሪክ ሌላዋን ሞት አይፈሬ ተሳፋሪዬን ትውስታ ከፊቴ ደቀነው፡፡ በህይወቴ እንደዚህ አይነት ሰዎች ሲያጋጥሙኝ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑንም ሀሊናዬ መዘገበው፡፡

እኛኛዋ ወይዘሮ ከእኚህኛዋ የሚለዩት በዚያን ጊዜ ባለቤታቸው ከሶስት ዓመት በፊት የተለዩዋቸው መሆኑና በአሜሪካ የኑሮ ልኬት በዝቅተኛ ገቢ ህይወትን የገፉ መሆናቸው ነው፡፡

ሴትዮዋን የወሰድኳቸው እዛው ከከተማ ከተማ ስለነበር ብዙም ጊዜ ስላልነበረን ስለልጆቻቸው ሁኔታ ያጫወቱኝ ታሪክ አልነበረም እንጂ የትዳር ዘመናቸው ርዝመት፣ የፍቅር ጎጆቻው፣ የመዋሃዳቸው ሁኔታ ወዘተ ከዛሬዋ ተሳፋሪዬ ጋር በእጅጉ አምሳያ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያዋ ወይዘሮ የኢኮኖሚ ችግር ያነሱልኝ ቢሆንም ያወጉኝ ትዳራቸው የገንዘብ ችግር ከሌለባቸው ያሁኗ ተሳፋሪዬ ጋር መመሳሰሉ ገንዘብ የትዳር መሰረት እንደማይሆን ይመሰክራል፡፡

መበለቷ (ባላቸው የሞቱባቸው ሴት) ታሪካቸውን በማጠቃለል ላይ፡-

‹‹ከባለቤቴ ጋር በጡረታ በምናገኘው ገቢ ስንተዳደር ቆይተን የኑሮ ውድነት እየናረ ስለመጣ በወር አንድ ቀን እንኳ ቲያትርና ፊልም ቤት ለመግባት ባጀታችን አቅም አነሰው፡፡ በዚህም ምክንያት ድሮ በሰበሰብናቸው ፊልሞችና ሙዚቃዎች እቤታችን በመዝናናት ተወሰንን፡፡ እንደበፊቱ አዘውትሮ ለእራት ሬስቶራንት መሄድ ቀረና እራት እቤታችን ማብሰል ጀመርን፡፡ ቀስ በቀስ ከአለም ተገልለን አንዳችን ላንዳችን አለም ሆነን ኖርን፡፡.... ይሄው ባሌ ከሞተ በኋላ ሶስት አመት ሙሉ በህልሜ የማላየው ቀን ያንሳል፡፡ ራሴን ለመርዳት ከላይ እታች ደፋ ቀና የምልበት የፃተኑ ውሎዬ ሁሉ እሱን ስለሚያስታውሰኝ ናፍቆቴን ያበዛዋል....›› ሲሉኝ

‹‹እዚህ ኒውዮርክ የኑሮ ውድነቱም ከፍተኛ ነው፤ አካባቢው ደግሞ ባለቤትዎን እያስታወሰዎት ህይወትዎን ይበልጥ ሃዘን ውስጥ ከሚፈጥርዎት ለምን ለቀው ሌላ አካባቢ አይኖሩም? ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡

ትንሽ ቆጣ ብለው ‹‹ባሌንማ ጥዬው አልሄድም! መቃብሩን በየጊዜው በመጎብኘት አብሬው ጊዜ አሳልፋለሁ፤ ለልጆቴና ለጎብኛ እመቤታችን እበባ አኖርለታለሁ፤ እኔም ከሬሚ ሰው እይደለሁምና ስሞት አጠገቡ መቀበር እፈልጋለሁ›› ሲሉኝ ያንን ባለማገናዘቤ ራሴን ወቀስኩት፡፡

በብቸኛዋ ተሳፍሪዬ ታሪክና ሁኔታ ልቤ ስለተነካ እቤታቸው ሳደርሳቸው ‹‹እሜቴ! የዛሬውን የታክሲ ክፍያ ለኔ ይተዉት!›› ከማለቴ ‹‹የለም! የለም!



t.me/OLDBOOKSPDF

እንተ መከፈል የለብህም! ስለሃሳብህ ግን አመሰግናለሁ!›› ብለው፣ ጭራሽ ሞቅ ያለ ጉርሻ ከጻግም ምስጋና ጋር ወርውረውልኝ ቶሎ ሊያመልጡ በራቸውን ከፈቱ፡፡

ምንም ማድረግ ስላልቻልኩ ለማለት ያህል ሳይሆን ከልቤ ፡-

‹‹በጣም አመሰግናለሁ እሜቴ! ረዥም ዕድሜም እመኝልዎታለሁ!›› አልኳቸው ድምጼን ከፍ አድርጌ፡፡

በር ከፍተው በመውረድ ላይ የነበሩት ተሳፋሪዬ አንገታቸውን መለሱና እንባ በተናነቀው ድምፅ ‹‹የኔ ልጅ! እድሜንስ አልፈልገውም! ከባሌ ለመገናኘትን በጣም ቸኩያለሁ!›› አሉኝና ከታክሲዬ ያቅማቸውን ያህል ፈጥነው በመውረድ በሩን ዘግተው ወደ ሆንፃቸው መግቢያ አመሩ፡፡

የኚህ ምስኪን ሴት አባባል ከሀሊናዬ ዘልቆ በሃዘን ስሜት ቢረብሸኝ፡እርምጃቸውን ሲከተል የነበረው አይኔ ግጥም ያለበትን ደራሽ ዕንባ መሸከም አቃተው፡፡

እነዚህ ሁለት ሴቶች ከባላቸው ጋር ሞት ብቻ በእካል የሚነጥላቸው አይነት ፍጡሮች መሆናቸውና፣ ሞትን የሚፈሩት ሳይሆን መልሶ እንዲያገናኛቸው የሚናፍቁት መሆናቸው አስደነቀኝ ፡፡

‹‹ሁለት የማይተዋወቁ ሰዎች ስለአንድ ነገር የሚያወሩት አንድ አይነት ነገር እውነት ነው›› የሚለው ብሂል ደምቆ ታየኝና አከበርኳቸው፡፡

የሰው ልጅ ተቀራርቦና በትዳር ተሳስሮ ከመኖር አልፎ ነፍሱ ተዋህዶ አንድ ነፍስ መሆን እንደሚችልና የአንዱ አካል ሲረግፍ ሌላው መኖሩ እንደሚያቆም እነዚህ ድንቅ ፍጡሮች አሳወቁኝ፡፡ ከሞት ወዲያ ማዶ ያለን



t.me/OLDBOOKSPDF

የማይበጠስ የልብ መተሳሰር አሳዩኝ፡፡ «ለካስ ፍቅር ከመቃብር ባሻገርም ይቀጥላል» አልኩ፡፡

ላፍታ ከጋለብኩበት የመበለቷ ታሪክ ትዝታ ተመልሼ በመስታወት ተሳፋሪዬን ስቃኛቸው በመቆነጃጃ ዱቄትና ቅባት የእርጅናቸውን አሻራ ለመደበቅ ቢሞክሩም «አሻፈረኝ» እያለ መሽብሸቡ የሚያስታውቀው የፊታቸው ገፅ የውስጥ ስሜታቸውንም በማጋለጥ የሃሳብ ውጣ ውረዳቸውን ቁልጭ አድርጎ በማሳየት ላይ ነው፡፡

ዳግም ከዚህ ከገቡበት የሃሳብ ማጥ ላላርፋቸው አሰብኩና፡-

«እሜቴ! መቼም የሚገርም የትዳር ጉዞ ነው ያሳችሁ! ብዙ ሰው እንደዚህ አይነቱን የፍቅር ህይወት እንደተራብ ሳያገኘው ይሞታልና እርስዎና ቤተሰብዎ እድለኞች ናችሁ!» ብዬ ንግግሬን ሳላሳርግ «ልክ ነህ የምትለው እውነት ነው!» በማለት አቋረጡኝ ፡፡

የሊዲያንና የእንድሬን የትዳር ሁኔታ በማጫወት እርስስት አስቀይሬ ከገቡበት የሃሳብ ማጥ ላወጣቸው የጀመርኩትን የመንደርደሪያ ወሬ ሳልጨርሰው ሲያቋርጡኝ ተመልሰው ወደባላቸው ወሬ በመግባት እንዳይቀድሙኝ በመስጋት ቶሎ ማውራቴን ቀጠልኩ፡፡

«አዩ እሜቴ! ታክሲ መንዳት መቼም የማያገናኘው አይነት ሰው የለም፡፡ ይሄው ከርስዎ አይነት ሰው ሞት እንኳን የማያደበዝዘው የሰው ልጆች የትዳር ትስስር አደመጥኩ፡፡

ይገርምዎታል!.. ከእርስዎ በፊት ያነሳኋቸው ተሳፋሪዎች ደግሞ በተቃራኒው...» በማለት ጀመርኩና ጠቅላላ ሁኔታውን አጫወትኳቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በወሬዬ መካከል ስለኔ ሩሲያ ውስጥ መኖር በመገረም ካቀረቡልኝ ጥያቄዎች በስተቀር ያደመጡኝ ፍፁም ከነበሩበት ሃሳብ ተላቀው በጥሞናና በመገረም ስሜት ነበር፡፡

ጨዋታቄን ማነው ጥፋተኛ እኔ ነኝ ወይስ እሱ? የጥሩ ትዳር ምርጫስ ሚስጥሩ ምንድነው? በሚሉት ጥያቄዎች የውይይት አጀንዳ በማስያዝ ቋጨሁት፡፡

‹‹እ እ እ እ እ›› አሉና ጀመሩ የሀሊናቸውን የትኩረት ነጥብ በማሰባሰብ ጥያቄዬን ለመመለስ፡፡

‹‹ከባድ የፍልስፍና ጥያቄ ነው የጠየቅከኝ.... በኔ አስተሳሰብ ትዳር ማለት ...›› ብለው መልሳቸውን ከመጨረሻው ጥያቄ ጀመሩት፡፡

‹‹ትዳር ማለት በምድራችን ከሚፈፀሙ መጣመሮች /Partnership/ ታላቅ፣ ክቡርና ቅዱስም ይመስለኛል፡፡ ትዳር በተስፋ ተኮትኩቶ፣ በእምነት ላይ ተገንብቶ፣ በቃል ኪዳን ተሳስሮ፣ ደስታና ችግር ተካፍሎ፣ የኑሮ ማቃኛ ዘዴን በጋራ መክሮ ልጆች አፍርቶ አሳድጎና አስተምሮ ለቁምነገር የማብቃት ,ወዘተ በብዙ ዘርፍ የተቆላለፈ የዕድሜ ልክ ጉዞ ነው ባይ ነኝ››

‹‹እሺ!›› በማለት በዕሞና መከታተሌን አሳወቅኳቸው፡፡

‹‹እንግዲህ እኔ የነገርኩህና የምነግረህ ሁሉ የራሴን ፍልስፍና ነው፡፡ የኔ የትዳር ፍልስፍና ወደ ወግ አጥባቂዎቹ ያደላ ቢሆንም፣ ቢሆን ይመረጣል ባይ ነኝ እንጂ እንደነሱ ሁሉም እንደዚህ ማድረግ አለበት ብዬ የምሰብክ ሰው አይደለሁም፡፡ አደራህን በተሳሳተ መልክ እንዳትወስድብኝ ››

‹‹ይገባኛል›› አልኳቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሉውን የጥያቄ መልስ ለመመለስ እንደሚቸገሩ ሊያሳውቁኝ፡-

‹‹በአለማችን ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ግለሰቦች ሳይቀሩ በትዳር መጣመር የጀመሩበት ዘመን እንደመጣና ‹‹ትዳር›› የሚለው ቃል ፍቺ ብዙ ክርክር ያስነሳ መሆኑን የምታውቅ ይመስለኛል፡፡›› አሉኝ፡፡

ሁኔታውን በሚገባ እንደምረዳና የምጠብቀውም የግል አስተያየታቸውን ብቻ እንደሆነ በመግለፅ እንዲቀጥሉ ጠየቅኳቸው፡፡ ቀጠሉ፡፡

‹‹በትዳር ሂደት ውስጥ ሳይነጣጠል የሚጓዝንና በአንድ ገፅ ውስጥ አብሮ የሚገኝን ተጣማሪ ነፍስ ሲያስቡ እንደ ማግኔት የሚያሳስቡ መስፈርቶችን መቃኘት ያሻል፡፡

እንግዲህ የሁሉም ሰው መስፈርታዊ ቅደም ተከተል ቢለያይም አብዛኛው ሰው የሚስማማባቸው ነጥቦች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ ከፍቅር ጀምረው፡ ቁንጅና፣ ወሲባዊ መጣጣም፣ ሃብት፣ ተመሳሳይ ቀለም፣ የወንዝ ልጅነት፣ እድሜ፣ መንፈሳዊ እምነት፣ ፀባይ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ዝንባሌ፣ ሙያ፣ በልጆች ብዛትና አስተዳደግ ላይ ያለ አስተሳሰብ፣ የጤንነት ሁኔታ..ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከነዚህ መስፈርቶች አንዱን ብቻ ነጥሎ በመውሰድ የተመሰረተ ትዳር የትም እንደማይደርስ በሙሉ እምነት ልነግርህ እችላለሁ፡፡ ብዙ ሰው የመጀመሪያ መስፈርቱ የሚያደርገውን ‹‹ፍቅር›› እንኳን ብቻውን ጥሩ ትዳር ሊያጎናፅፈን አይችልም፡፡

በሌላ ማዕዘን ስንመለከት ደግሞ የአንዱ መስፈርት መጉደል ትዳርን ባያፈርስ እንኳን የሆነ እንከን ይጥልበታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምሳሌ የትምህርት ደረጃን እንውሰድ፡፡ ልብ በል! ሰው ይበልጥ በተማረ ቁጥር እየተቀየረ ይሄዳልና ዶክትሬቱን ያገኘ ሰው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ያለው አስተሳሰብ ምን ያህል ጮርቃ እንደሚሆንበት አስብ!፡፡ ስለዚህ በሌሎች መስፈርቶች ተውጦ ብዙ የተማረው በትምህርት ብዙ ያልገፉት ቢያገባ በትዳር ውስጥ ለሚከሰቱ መፍትሄዎች የኔ አስተሳሰብ ይደመጥ ማለቱ አይቀሬ ነውና ትዳሩ እንከን እንደሚያገኘው አያጠያይቅም፡፡

እድሜንም ብንወስድ ያው በአካል ፍላጎትና በአስተሳሰብ ላይ ልዩነት ስለሚያመጣ በግሌ ‹‹ዕድሜ ቁጥር ነው›› ከሚሉት ወገኖች የምቃረን ብቻ ሳልሆን፣ እድሜ ከቁጥር መግባት አለበት ባይ ነኝ፡፡

ሁልጊዜም የተለዩ /Exceptionals/ ሰዎችና ሁኔታዎች እንደሚኖሩና የምናወራው ‹‹በአብዛኛው ህዝብ ላይ›› ተመርኩዘን መሆኑን ሳንረሳ ማለቴ ነው፡፡ ያለዚያማ የ25 አመት እድሜ ልዩነት ያላቸው የኮሌጅ ፕሮፌሰርና ተማሪው የነበረች ወጣት ተጋብተው ልጆች አፍርተው በጥሩ ትዳር የሚኖሩ ሰዎች እንደማውቅ እራሴው ልነግርህ እችላለሁ›› ካሉ በኋላ ‹‹ግልጽ ነኝ?›› የሚለውን የማረጋገጫ ጥያቄ በሳቅ አጅበው አቀበሉኝ፡፡

ሴትየዋን በዕጥና ባዳምጥም የሚያስተላልፉት መልዕክቶች በተንዳኝ የራሴን የትዳር ህይወት ጨምሮ በግል የማቃቸውን ትዳር የተሳካላቸውንም ሆነ ያልተሳካላቸውን ሰዎች በህሊናዬ እያስጎበኙም ነበርና ከወሰደኝ ሩብ ሰመመን ነቅቼ መልሳቸው እንዳረከኝም ጭምር ለማሳወቅ ምላሼ፡-

‹‹ግልፅም ልክም ነዎት!›› የሚል ነበር ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እሳቸው ግን በሰጡኝ መልስ ብዙ አልረኩም መሰለኝ አሁንም በአንደኛው ጥያቄ ላይ ተጨማሪ ትንተና ቀጠሉ፡፡

‹‹ምን መሰለህ ወዳጄ! ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ኩይንስ ቦሮ ድልድይ ላይ ሆነን የቃኘነው የመንሃተን ከተማ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር መኖሪያ ቤት ውስጥ ትዳር እንዳለ አስብ፡፡ ይሄን ሁሉ ጥንድ ያስተሳሰረው የየራሱ ምክንያት አለውና ትዳር ብቸኛ ስሌት የለውም፡፡

ሁሉም ትዳር እንዲሟሉለት የሚጠይቃቸው ሁኔታዎች ባብዛኛው ቢመሳሰሉም ትዳሩ በሁለቱ ነፍሶች ሁኔታና ድርጊት ነውና የሚቀረፀው፣ እንደሰዉ አይነትና ብዛት ትዳርም ይለያያል፡፡ እናም በዚች ከተማ ውስጥ ሚሊዮን አይነት ትዳር አለ፡፡

አንተ የምትፈልገውን አይነት ትዳር ለመመስረት የምትፈልጋት ነፍስ እሷ ግን የምትፈልገው ያንተ አይነቱን ላይሆን ይችላልና ‹‹ትክክለኛ›› ነፍሶችን የማጣመር ኬሚስትሪ የአምላክን እርዳታ የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ነው የብዙ ሰው ትዳር ገጠመኝ የሆነው፡፡

ትዳር እንደ ተክል ነው! በሂደት ውስጥ መኮትኮትን፣ የሚያስፈልገውን መመገብን፣ ሟሟላትን፣ መከለልን፣ ማሳመርን ወዘተ ይጠይቃል፡፡ የጋብቻ እለት ሁሉ ነገሩ ተሟልቶ አይገኝምና ትዳር ብዙ መልፋትን ይጠይቃል፡፡ ከአያያዝ ጥሩ ትዳር ሲፈርስ መጥፎው ደግሞ ወደ ጥሩነት ሊለወጥ ይችላል፡፡

ትዳር ህይወት ያለው ነገር ነውና ህይወት እንዳለው ፍጡር ይታመማል፡፡ ባብዛኛው የህመሙ መንስኤ ህይወቱ የተገነባባቸው ከሁለቱ ወይም ከሁለት አንዱ ሲሎች ላይ ነው፡፡ ስለዚህም ህመሙን አክሞ ለማዳን



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹የትዳር ክሊኒኮች›› መሄድ ያስፈልጋል፡፡ የሚድነው ይድናል የማይድነው ይሞታል፡፡

አሁን ያጫወትከኝ ሩሲያውያን ግለሰቦች ግን ‹‹ትዳር ክሊኒክ›› መሄድ ያለባቸው አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ሲጀመርም ትዳር አልነበራቸውም፡፡ ትዳር ማለት የግድ የሁለት ሰዎችን ፈቃደኝነት ይጠይቃል፡፡ ልጅቷ ለጊዜው አሜሪካ መምጫነትና የወደፊት እቅዷን ለሟሟላት ሃብታሙን ሰውዬ ድልድይ አደረገችው እንጂ አላገባችውም፡፡ በማለት አስረግጠው ተናገሩ፡፡፡፡

ይሄን ሲናገሩ ‹‹ሀገር ቤት ድረስ በመሄድ ቢጤውን ሳይሆን በእድሜም የሚወልዳትን ‹‹በማግባቱ››› እያመጣ፤ ልጅቷ ይዛ የመጣችው አገልግል እንኳ ተበልቶ ሳያልቅ ትታው ሄደች፤ ሊላዋ ባሏ እንዲህ የሚባለው አውሮፕላን ማረፊያ ሲጠብቃት እሷ ቲኬቱን አስቀይራ በሌላ አይሮፕላን ወደሌላ...ወዘተ የሚባል ወሬ እየሰማሁ ስገረም የነበረው አባገባብ ነዋ! ለካስ ድሮም አልተጋቡም›› ብዬ ለተሳፋሪዬ የትዳር ሎጂክ እጄን ሰጠሁ፡፡

ምነው እንዱን ቅስም የሚሰብር ገጠመኝ ለሌላው ትምህርት አልሆነው? የሚለው ምላሽ የሌለው ጥያቄ ግን ከአይምሮዬ ተንጠልጥሎ ቀረ፡፡

ምንም እንኳ እኔ ከራሴ ጋር ውይይት ብከፍትም ተሳፋሪዬ ግን ጥያቄዬን መመለሳቸውን ቀጥለዋል፡፡

‹‹እናም ማነው ጥፋተኛ ላልከኝ ጥያቄ ጥፋተኛውን የሚያውቀው እግዚአብሄር ነው፡፡ እሷ ናት ወይ እሱ? ላልከው ሁለቱም እኮ ጥፋተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አየህ ልጄ ዘመን ተቀይሯል! የሰው ልጅ ሞራሉ ዘቅጧል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የውስጥ ሰላምና ደስታ የለውም፤ እናም ውስጡ የጎደለውን በሙሉ በገንዘብ ሃይል ሊያሟላ ይጥራል፡፡ ገንዘብ እስካስገኘለት ድረስ ምንም ነገር ከማድረግ የሚያቆመው ሞራላዊ ድንበር የለም፡፡ ልጅቷ ሃብታሙ ቤት የገባችው ገንዘብንና አሜሪካንን ብላ በዛም ላይ ተረማምዳ የኋላ ኋላ የምትወደውን በማግኘት ለማግባትና የተሟላ ህይወት ለመኖር ነው፡፡ ዛሬ በሷ ቦታ ላይ ቢሆን ስንቱ ከሷ የተለየ ያደርጋል? ብለህ ራስህን ብትጠይቅ መልሱን የምታጣው አይመስለኝም፡፡

ፉሲያ ያለው ወዳጇም ለሷ እውነተኛ ፍቅር ቢኖረው ኖሮ ሃብታሙን ማግባቷን በተቃወመ ነበር፡፡ እሱም ሌላ አጀንዳ ስለሚኖረው ሁሉ ነገር ተሳክቶላቸው ቢመጣ እንኳ ሰላም ኑሮ እንደማይጠብቃቸው መገመት አይከብድም፡፡

ሃብታሙም ቢሆን ገንዘብ ካገኘ በኋላ እድሜው ያሳጣውን ወጣት ቆንጆ በገንዘቡ ገዛ እንጂ እውነት ያን ሁሉ ውለታ ለሰው የሚውል ደግ ፍጡር ሆኖ መሰለህ? ይሄኔ ስንት የስጋ ዘመዶቹ እርጥባን የሚሹ ይሆናሉ! ከዛ በፊት ሚስት የነበረችው ሊሆንም ይችላል ልጆችም ጭምር፡፡..... በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ምን እናውቃለን? እናም የዛሬዋ አለም እንደዚህ ነች በጥቅም! በገንዘብ አዙሪት የጠዘች!... እናም ለዚህ ነው ፍርዱን ሳምላክ መተው ነው ያልኩህ›› ብለው ደመደሙ ፡፡

ሲትየዋ ብዙ የሚደመጡ ስለነበሩ ብዙ ጥያቄዎች እያነሳሁ ባዳምጣቸው ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ጉዞችንን ፈፅመን ሆስፒታሉ ግቢ በመግባት ላይ ስለነበር ጥያቄዬን አንስቼ ስለሰጡኝ የህይወት ተሞክሮ አመሰገንኳቸው፡፡

እሳቸውም በጥሩ ስሜት መንገዱ ሳይታወቃቸው ስላመጣኋቸው ካመሰገኑኝ በኋላ ሆስፒታሉ ዋናው መግቢያ ላይ እንድጥላቸው ነገሩኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ባሉኝ መሰረት ታክሲዬን ወደበሩ አስጠግቼ አቆምኩላቸው፡፡ ልክ እንደዛኛዋ መበለት ተሳፋሪዬ እኚህኛዋም ሜትሩ የቆጠረው ላይ ጥሩ ጉርሻ ጨምረው ሲከፍሉኝ፡-

‹‹በጣም ጥሩ የሆነ ትምህርታዊ ጉርሻ ሰጥተውኛል ተጨማሪ ጉርሻ እኮ አያስፈልግም ነበር!›› ስላቸው ‹‹ይሁን ግድየለም! በጥሩ ሁኔታ እንዳመጣኸኝ መግለጫ ይሁንልህ ብዬ ነው! አመሰግናለሁ! ራስህን ጠብቅ!›› ብለው ለመውረድ ቦርሳና አበባቸውን ሲያዘገጃጁ በር በመክፈት ልረዳቸው ዘልዬ ወጣሁ፡፡

በሩን ከፍቼላቸው እንደወጡ ከጀርባዬ በኩል ‹‹አያትዬ! አያትዬ!›› የሚል ድምፅ ሰሰማ ዞር ስል ከ16-18 አመት እድሜ የምትገመት በሰማያዊ ጂንስ ሱሪ ላይ ነጭ ሹራብ ያደረገች ወጣት ቡና አይነት ረዥም ፀጉሯን እያስተካከለች ከመግቢያው ኮሪደር አቅጣጫ በሰው መሃል እየሮጠች ስትመጣ አየኋት፡፡

አሮጊቷ ተደናግጠው እንደ ሃውልት ቆመው፡- ‹‹ምን ተፈጠረ!? ምን ተፈጠረ!? ደህና አይደለም ወይ?›› ቢሏትም መልስ ሳትሰጥ እቅፍ አደረገቻቸው፡፡ በእንባ ሲቃ እየተንሰቀሰቀች መሆኗ ለአያቷ ጥያቄ በቂ መልስ ቢሆንም በባዶ ተስፋ ደረታቸው ስር ልጥፍ አድርገው እንዳቀፏት ነበሩ፡፡ የተናነቃት ሲቃ ፋታ ሲሰጣት እንገታቸው ስር ገብታ ‹‹አያቴ ደህና ሁኚ! ብሎሻል!›› አለቻቸው፡፡

የልጅ ልጃቸውን እቅፎ የነበረው እጃቸው የያዘውን አበባ ለቀቀው፡፡ የፈሩት ደረሰ! አበባውን በለቀቀው እጃቸው አፋቸውን ሸፍነው አንዴ ወደ ውስጥ አንዴ ወደ ውጭ ተንሰቀሰቁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እይምሮዬ አጠንጥና ‹‹ባዶ ህይወታቸው›› እነሆ በዚህ ሁኔታ ጀመረ ብሎ ሹክ ሲለኝና በእንባ የሚያሰፈንቅል የሃዘን ስሜት ሰውነቴን ሲወረው ያችን የወደቀች አበባ እንስቼ ለበር ላይ ጠባቂው ‹‹ስጣቸው›› ብዬ በማሰረከብ መኪናዬን እስነስቼ ሆስፒታሉን ለቀቅኩ፡፡

ምንም እንኳ የተወሰነ የስራ ሰዐታት ቢቀረኝም በጣም ስለተረበሸኩ መኪናውን ለማቃው ሹፌር ታክሲ ማቆሚያ ላይ በመተው ወደቤቴ ለመሄድ በመወሰን በቀጥታ ወደ ነዳጅ ማደያ ነዳሁ፡፡

ነዳጄን እየሞላሁ መኪናዬን ሳፀዳዳ ወንበር እግር ስር ትንሽ የእጅ ቦርሳ ወድቃ አገኘሁ፡፡ ‹‹አይ ዕዳዬ! እኚህ ሴትዮ ቦርሳቸውን ጥለው ሄደዋል መመለሴና እሳቸውን ማየቴ አልቀረልኝም›› ብዬ ካነሳሁት በኋላ ስከፍተው እንድሪናና ታንያ የሞስኮው ‹‹ቀይ አደባባይ›› ላይ ከሚገኘው ቤተ መቅደስ ፊትለፊት የተነሱት ፎቶግራፍ ተቀምጧል፡፡ ፎቶግራፉ የሙሽሮች ባይሆን ከእባቷ ጋር የተነሳችው ነው ማለቴ አይቀርም ነበር፡፡ ፎቶዋ ላይ ዛሬ ካየኋት የበለጠ ታምራለች፡፡ ፊቷ እንዳለ እየሳቀ ነው፡፡ ከ‹‹ባሏ›› ጎን እሸንጎቧ እንደአሮጊቷ ተሳፋሪዬ ሞት የማይለያት ትመስላለች፡፡ እንድሪ ምንም ቢኳኳል በዚች ምድር ላይ ከግማሽ ምእተ አመት በላይ መኖሩ ያስታውቃል፡፡ ደረቴን ነፍቶ ኩራ ብሏል፡፡ ምናልባትም ‹‹እቺን የመሰለች ሚስት አግኝቻለሁ›› ብሎ!

ጉደኛውን ቦርሳ ማገለባበጤን ቀጥዬ ሰውር የሆነ ዚፕ አግኝቼ ስከፍተው ተሳዳቢዋ ተሳፋሪዬ ምናልባት ለፍሎሪዳ ጉዞዋ ያዘጋጀችው ባለሃምሳውና ባለመቶው ኖት ተጋድሟል፡፡ እኔ ግን የጠጣሁት የስድብ ዋጋ ነው በማለት ስቆጥረው ..ስቆጥረው.... ስቆጥረው.....



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዲጄው

ወጣቱ ታክሲ ነጂ ኒዉዮርክ ዉስጥ ብዙ ሞክሼዎች ስላሉት እሱነቱን ለመለየት ህብረተሰቡ ‹‹ዲጄው›› የሚለውን የቅፅል ስም ከዋና ስሙ በማስከተል ይጠራዋል፡፡

ኒዉዮርክ ዉስጥ በትላልቅ አዳራሾችና በእበሻ ምግብ ቤቶች ዉስጥ በሚዘጋጁ የመዝናኛ ምሽቶች ላይ ምርጥ ሙዚቃዎችን ደርድሮ በማጫወት ህዝብ ከሚያዝናኑ የተዋጣላቸው ዲጄዎች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ተቀጥያ ስሙ በእርግጥም እሱንቱን የሚገልጽና ጥሩ መለያውም ነው፡፡

"ዲጄው" ለሙዚቃ ያለው ፍቅር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ባጋጣሚ ስሙ በሌለበት እንኳን ሲነሳ፤ ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቹ፤ ጥያሜው፤ ቁንጮዉ ዞማ ፀጉሩ፤ ምንግዜም ዕድት ብሎ የቀለም ቅንጅቱ የተጠበቀው አለባበሱ ብቻ ሳይሆን ከጆሮዉ ላይ የማይለየው ሙዚቃ ማዳመጫው በሰው ህሊና ውስጥ ድቅን ማለቱ የማይቀር ነው፡፡

ከሙዚቃ ጋር ያለው ግንኙነት የእሳና የባህር አይነት በመሆኑም ሙዚቃ በሌለበት ተንከላዋሽ በድን ማለት ነው እሱ፡፡ በሙዚቃ እንደ አበባ ትፈካለች ህይወቱ፡፡ የሰው መለኪያ ሚዛኑ ሳይቀር ሙዚቃ ነው፡፡ ሙዚቃ አፍቃሪ ሁሉ ለሱ ቢጤው ነው፡፡ ሊቀርበው ሰከንድ አያቅማማም፡፡

ይሄን ወጣት ከሩቅ ለሚያውቁት፤ ዲጄነቱ፤ አለባበሱ፤ ቁንጮው፤ የጆሮው ሎቲ የዘመኑ ፋሽን አሳዳጅ የሚል ታርጋ የሚያሰጠው ቢሆንም፤ ቀረብ ብለው ሲያዩት ደግሞ ቁጥብነቱ፤ ሰው አክባሪነቱ፤ ኢትዮጵያዊ ይሉኝታው፤ እነጋገሩ ወዘተ ዘመናዊ ገጽታውን አደብዝዘው የተገላቢጦሽ ‹‹ይሄ ልጅ የጥንት



t.me/OLDBOOKSPDF

አባቶቻችን ባህላዊ ፈለግ ተከታይ ሳይሆን አይቀርም›› የሚያሰብል ጥርጣሬ ውስጥ ይከታሉ፡፡ እናም ጥልቅ ውስጠ ማንነቱ ግራ ያጋባል፡፡

ከእኳኋኑ ገጽታውና ከድርጊቱ ግን፣ በራሱ ላይ ከፍተኛ መተማመን ያለው፣ ትክክሻው የህይወትን ውጣ ውረድ መሸከም የሚችል የተረጋጋ ሰው መሆኑና ሙዚቃ አፍቃሪነቱ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ በግልፅ የሚታይ ማንነቱ ነው፡፡

‹‹ዲጄው›› ለሙዚቃ ሲኖር መተዳደሪያው ታክሲ መንዳት ነው፡፡ ኒውዮርክ ውስጥ ታክሲ ከሚያሽከረክሩ አበሾች መካከል በእድሜ ልጅ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የሆነው ‹‹ዲጄው›› የማታው ክፍለ ግዜ ሹፌር ነው፡፡ የቀኑን ክፍለ ጊዜ ደግሞ ሌላ ጓደኛው ይነዳል፡፡ መኪናውን የሚቀያየሩት መንሃተን ውስጥ ለታክሲ ማቆሚያ ከተመደቡ የመንገዶች ጠርዝ ላይ ሲሆን ይሄ ቦታ ለሁለቱም ሹፌሮች የስራ መጀመሪያና መጨረሻ ነጥብ ነው፡፡ ተረኛው ስራውን ሲጨርስ በዚህ ቦታ ላይ አቁሞት ይሄዳል፡፡ የሚቀጥለው ተረኛ አስነስቶ ስራ ይጀምራል፡፡ የስራ ዑደቱ በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡

‹‹ዲጄው›› ዛሬም እንደተለመደው ከሰዐት በኋላ 11 ሰዓት ላይ ታክሲውን ጓደኛው ካቆመለት ቦታ አንስቶ መስራቱን ጀመረ፡፡ እንደ[illegible] ኑ ሁኔታና እንደሞራሉ በሚቀጥሉት 12 ሰዓት ውስጥ የኒውዮርክ ነዋሪዎችና ቱሪስቶቿ ለታክሲ ከሚያወጡት ገንዘብ ውስጥ ዕድሉ ያስገኘለትን ለመቀራመት መከንፉን ተያያዘው፡፡ ሙዚቃውን እያስደመመ ግርግሩ ውስጥ በመስመጥ ራሱም የግርግሩ አካል ሆነ! ተዋሃደ፡፡

በዛች ጉደኛ ከተማ ተሳፋሪ ከላይ እታች፣ ደግሞም ወደ ጎን እየወሰደው የሹፌርነት ተግባሩን በሚገባ ሲያከናውን አመሸ፡፡ በሰላምታ ተቀብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

በሙዚቃ አስተናግዶ፡ ከፈለጉበት ቦታ አድርሶ ክፍያውን ከምስጋና ጋር በመቀበል ድግግሞሽ ተጋግሏል ዲጂው!፡፡

ታክሲ ነጂዎች የዚህ አይነቱን ቀን ‹‹ቢዚ ቀን›› ይሉታል፡፡ ሙዚቃውን እየከሰከሰ ስራውን ሲያጣድፍ ‹‹ሙዚቃውን አጥፋልኝ›› የሚል ቀርቶ ‹‹እባክህ የሙዚቃውን ድምፅ ትቀንሰው?›› በማለት‹‹ የሚነጅሰው›› ተሳፋሪ ሳልገጠመው ለ‹‹ዲጂው›› ደግሞ ምሽቱ ከ‹‹ቢዚ ቀን›› በላይ ነው፡፡ ሞራሉም ሰማይ ደርሷል!

በዚሁ ሁኔታ ሲንጉድ ሰዓቱም በዛው መጠን ነጉዶ ምሽቱ ወደ ሌሊት ከዚያም ወደ ንጋት ተሸጋገረ፡፡ በእለቱ የስራ ገጠመኞቹ እድለኛም ስለነበረ በከተማዋ ውስጥ ለታክሲ መንጓገርነት ተገሊጋዩ ህዝብ ካወጣቸው ገንዘቦች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ድርሻውን አግኝቷል፤ የቀኗ የተሰፋ እቁማዳው ከጠበቀው በላይ ተወጣጥራለች፡፡

አሁን የሚቀረው ታክሲውን ነዳጅ ሞልቶና አጸዳድቶ ለባለ ተራው በማቆም በወትር ከስራ በኋላ እዛው ታክሲ ማቆሚያው ጋ ተገናኝተው በአንደኛው የቤት መኪና ወደ መኖሪያው የሚያደርሱትን ጓደኞቹን በማግኘት ቤቱ ገብቶ የደከመ ሰውነቱን ማሳረፍ ነው፡፡ ስለዚህም ከስራ ውጭ /off duty/ የሚለውን የጣራ መብራት አብርቶ ወደ ነዳጅ ማደያ መንዳት ጀመረ፡፡

ብዙም ሳይነዳ ከመንገድ ዳር የፖስታ ማጠራቀሚያ ሳጥን ስላየ፤ታክሲውን አቁሞ ወደ ሀገር ቤት ሊልክ ያዘጋጀውን ደብዳቤ በመክተት ወደ ታክሲው ሲመለስ ሁለት ሰዎች ‹‹እባክህ ግሪንዊች ቪሌጅ ልታደርሰን ትችላለህ?›› በማለት ይጠይቁታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ዲጄው›› ሰአቱን ሲመለከት ወደ ቤት ከሚወስዱት ጓደኞቹ ጋር ያለው የቀጠሮ ሰአት 30 ደቂቃ ይቀረዋል፡፡ በ30 ደቂቃ ውስጥ አድርሷቸው፣ ነዳጅ ሞልቶ ከታክሲ ማቆሚያው እንደሚደርስ በመገመት ‹‹እኬ ግቡ!›› ይላቸውና አሳፍሯቸው ይነጉዳል፡፡

እንዳሰበውም ትራፊክ የሌለበት ሰአት ስለሆነ ባጭር ጊዜ ውስጥ አድርሷቸው ተሳፋሪዎቹም አመስግነው ከተሩ ጉርሻ ጋር ሂሳባቸውን ከፍለው ሲወጡ እነሱ በከፈቱት በር ሁለት ጎረምሶች ዘው ይላሉ፡፡

ወጣቱ ታክሲ ነጂ ፈጽሞ ያልጠበቀው ነበርና፡-

‹‹ይቅርታ ልጆች! የስራ ሰአቴን ጨርሻለሁና ሌላ ታክሲ ውሰዱ›› ከማለቱ

አንደኛው ‹‹ኖ ኖ ኖ እንደዛማ አትበል! ሩቅ አንወስድህም.. እዚሁ መንሃተን ነው.....15 ደቂቃችን ታክሲ አጥተን ከተንተርን!›› በማለት ተንጫረረ፡፡/ ራስ መሸፈኛ ያለው ቡናማ ሹራብ ያደረገው ጎረምሮ ድልዘ አይኑን ጎልጉሎ/

"ዲጄው" እነዚህ ሰዎች ያን ያህል ጠብተው ከሆነ አይለቁኝም ብሎ በማሰብ፡-

‹‹መኪናውን የምመልሰው ‹‹አፐር ዌስት ሳይድ›› /upper west side/ አካባቢ ነው፤ እናንተስ በዛ አቅጣጫ ናችሁ?›› በማለት ማንገራገሪያውን አቀረበ፡፡

‹‹ስማ ሰውዬ እኛ የምንሄደው በተቃራኒ አቅጣጫ ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት /south street seaport/ አካባቢ ነው፡፡ ..... በጭቅጭቅ ጊዜያችንን



t.me/OLDBOOKSPDF

ባታጠፋብን ይሻላል በጣም እንቸኩላለን፡፡›› በማለት የሚወርዱ አይነት እንዳልሆኑ እቅጩን አስረግጦ መለሰለት፡፡ /ድልህ አይኑ/

‹‹ስማ ! የማትወስደን ከሆነ ቁጥርህን ለታክሲ ኮሚሽን ለጥቼልህ ችግር ውስጥ መግባትህ ነው!›› አለ፡፡ ረዥም ጸጉሩ የተንጨበረረውና ግማሽ ፊቱን የከለለው ስፓኒሽ ይሁን ነጭ መለየት የሚያዳግተው ሌላኛው ተሳፋሪ /ጣቱን ወደተሰቀለው የዲጂ የታክሲ መንጃ ፈቃድ ቀስሮ፡፡/

‹‹ዲጂው›› በቀጠሮው ሰአት ለመድረስ ባለመቻሉ ጓደኞቹ ጥለውት ሲሄዱ ታየው፡፡

በዛ ጭር ባለ ጭለማና የአደንዛዥ ዕጾች ትራፊክ መዘዋወሪያ በሆነበት ሰአት የምድር ውስጥ ባቡር /ሜትሮ/ ጠብቆ ወደ ቤቱ የመሄድ አደገኛነትና በድካሙ ላይ የሚጠብቀው ተጨማሪ መንከራተት ሲታየው በጣም በሸቀ፡፡

አልወስድም እንዳይላቸው ደግሞ ቢያንስ 4 ቀን የለፋበትን ገንዘብ በመቀጮ ለታክሲ ኮሚሽኑ ማስረከቡ ነው፡፡ ሁኔታው የሁለት ጨለማ ምርጫ ሆኖበት ለሰኮንዶች ካሰበ በኋላ ይዟቸው መሄዱን መርጦ የመኪናው ማርሽ ላይ እልሁን በመወጣት በመዳፉ በሃይል ገጭቶ አስገባውና ቁልቁል መንዳት ጀመረ፡፡ ወደ ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት፡፡

ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት ወርልድ ፋይናንሺያል ዲስትሪክት/ world financial district/ ከሚባለው የመንሃተን ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚጠቃለል ሲሆን በ1993 የሃገራችን ዘመን መለወጫ ዕለት ባሸባሪዎች ከወደሙት መንትያ ሰማይ ገብ ህንጻዎች ደቡብ አቅጣጫ 2 ኪ.ሜ በማይሞላ ርቀት ውስጥ የሚገኝ ስፍራ ነው፡፡

ወርልድ ፋይናንሺያል ዲስትሪክት የአለም ገበያ ውጣ ውረድ የልብ ትርታ የሚለካበትና የአያሌ የንግድ ማዕከሎች መናኸሪያ በመሆኑ እጅግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብለው የተገነቡት ያካባቢው ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ባብዛኛው ለዚሁ ተግባር የዋሉ ቢሮዎች ናቸው፡፡

ይሄ በስራ ቀን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰራተኞችን የሚያስተናግደው አካባቢ ማታ ከስራ ውጪና ቅዳሜና እሁድ ከህንጻዎቹ ጥበቃና ግልጋሎት ሰጪ ሰራተኞች በስተቀር ባዶ ወና ይሆናል፡፡

ብሮድዌይና ወተር ስትሪት /broadway & water st./ የተባሉት መንገዶች ለፋይናንሺያል ዲስትሪክቱ ዋነኛ መግቢ በመሆን ከሰሜን ወደ ደቡብና ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ሰንጥቀው ያልፋታል፡፡

የፋየናንሺያል ዲስትሪክት ደቡባዊ አካል የሆነው ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት ደግሞ ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው የመንሃተንን ደቡባዊ ጠርዝና ኢስት ሪቨርን/east river/ በመከተል በተዘረጋውና የከተማዋ የመጨረሻ መንገድ በሆነው በሳውዝ ስትሪት/ south st./ ስም የተሰየመውን ወደባዊ አካባቢ ያካትታል፡፡

የሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት ምስራቁ ክፍል የአሳ ምርት ማራገፊያ ወደብ ሲሆን ምዕራቡ ክፍል ደግሞ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች፣ ምግብ ቤቶች፣ የሙዚቃና ልዩ ልዩ ትዕይንቶች ማቅረቢያ መድረኮች፣ ባለ ምቹ መቀመጫና መንጋለያ ያላቸው የወንዝ ዳር ሰገነቶች ወዘተ እንዲኖሩት ተደርጎ በመጠነ ግዙፍ መርከብ ላይ የተሰራ የቱሪስት መስህብ ይገኛል፡፡

ከኢስት ሪቨር ባሻገር ከሚገኘው የብሩክሊን ከተማ ጋር መንሃተንን የሚያገናኙት ‹‹ብሩክሊን›› ና ‹‹መንሃተን›› የሚባሉት ድልድዮች እንደ እግራቸው የቆመው በዚሁ በሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት አካባቢ ውስጥ በመሆኑ በወንዙ ላይ የተንጣለለውን ሸንጣቸውን ለመመልከት

እመቺ ስፍራነቱን ለተመለከተ ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሉቀን መለሰ ‹‹የኔ ዓለም ! እንሂድ አባይ

ድልድዩን ልናይ›› ብሎ ከመዝፈኑ በፊት ይህንን ቦታ ቢያየው ኖሮ

‹‹የኔ ዓለም እንሂድ መንሃተን ልናይ ድልድዩን›› ብሎ ይዘፍን ነበር የሚያሰኝ ነው፡፡

ይሁንና ማታ ማታ የቱሪስት መስኅቡ ከተዘጋ በኋላ የድልድዮቹ አገዛዘፍ ከጭለማና ከጭርታው ጋር በማበር የአካባቢውን ቅፈት ያከብደዋል፡፡

በዚህ ላይ በሳውዝ ስትሪት እናት ላይ የተዘረጋውን ‹‹የፍራንክሊን ሮዘቬልት ሃይዌይ›› ከተሸከሙት ብዛት ካላቸው ትላልቅ የብረትና የሲሚንቶ ምሰሶዎች ጋር አካባቢውን ጉራንጉራም ከማድረጉም በላይ ሰማዩን በከፊል በመጋረድ ይበልጥ ያጨፈግገዋል፡፡

ወደዚህ ወደ ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት ቁልቁል መንዳት የጀመረው ‹ዲጂው› የሚሄዱበትን ነጥብ አድራሻ ለማረጋገጥ ፡-

‹‹ሳውዝ ስትሪት ሲ ፖርት ምኑጋ? ››በማለት ከመጠየቁ፡-

ጨበሬያሙ ‹‹ዎተር ስትሪት!›› አለ ከመቅፅበት ፡፡

‹‹ዲጂው›› ንዴቱን ወደሚያበርድበት ሙዚቃው ተመልሶ እያዳመጠ ማሽከረርከሩን ቀጠለ፡፡

ብዙም ሳይሄዱ ተሳፋሪዎቹ እንደ አይናፋር ፍቅረኛሞች መንሾካሾክ ጀመሩ፡፡ ትንሽ ቆይተው ዙሪያቸውን በመቃኘት አይናቸው መቅበዝበዝ ቀጠለ፡፡ የተረጋጉ አይደሉም፡፡ መንሾካሾክ እንደገና ግራና ቀኝ መንገዱን መገላመጥ ተደጋገመ፡፡ ትንፋሽ እተነፋፈሳቸው ሳይቀር ተቀይሯል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣቱ ሹፌር ሁኔታቸው ከተለምዶ ተሳፋሪ የተለየ ስለሆነበት የሙዚቃውን ድምፅ ቀንሶ መንገዱ ላይ ከነበረው ትኩረት የእነሱን ሁኔታ በኋላ መስታወቱና በጆሮው መከታተሉ በልጧል፡፡

"ዲጄው" ወደ ደቡብ ሲከድ 7ተኛው ጎዳና፣ ፓሪክ ስትሪት፣ ዌስት ብሮድዌይ እየተባለ ስሙ የሚቀየረውን መንገድ ሔርሶ ቪሲ ስትሪት ላይ ወደ ግራ ብሮድዌይ ላይ ወደቀኝ ታጥፎ ቁልቁል ነዳ፡፡

ብሮድዌይ ወደ ፎተር ስትሪትነት ሲቀየር ሳይከፍሉ ለመሮጥ እንደተዘጋጁ ጠርጥሮ ሳይቀደም የመሳሪያውን ምላጭ ለመሳብ እንደተዘጋጀ ዘብ ወታደር የኤሌትሪክ በር መቆለፊያው ቁልፍ ላይ ጣቱን ካስተካከለ በኋላ ድምፁን ጎርነንና ሞቅ አድርጎ፦

<<ፎተር ስትሪት ደርሰናል ! መውረጃችሁ የት ላይ ነው?>>

<<ፎተር ስትሪትን ይዘህ ቀጥል መቼ እንደምታቆም እነግርሃለሁ!››
/አለ እሱም እንደ ዲጄው ድምፁን ከፍ አድርጎ/

<<የምትሄዱበትን ትክክለኛ አድራሻ አታውቁትም? ወይስ ምንድነው?>> አለ ዲጄው ልትሮጥ አስበህ ከሆነ ትችለሁ በሚል አይነት ፡፡

ድልህ አይኑም ‹‹ሄይ! ሄይ! ሹፌር ተረጋጋ .... ይታይሃል ክፍት ያለው ሰማያዊ ሀንዛ ? እሱጋ ስትደርስ አቁምና ብሎ ተቆጣ ፡፡ አባባሉና አቆጣጡ ቷዳፈርከ፡ ወጥ ረገጥክ .....ዝም ብለህ የምንልህን ፈጽም የሚል ነው፡፡

ፎተር ስትሪት የፎቅ ደን በሚመስሉት ሰማይ ጠቀስ ፎቆቿ ውስጥ በሚስተናገዱና በሚዋከቡ ሰራተኞቿና ባለጉዳዮቿ እንደማትጨናነቀው ሁሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ሰዓት ረጭ ብላለች፡፡ አልፎ አልፎ ከሚንቀሳቀሱ መኪናዎች በስተቀር የእግረኛ ዘር አይታይም፡፡

ወጣቱ ሹፌር ከእነዚህ አጠራጣሪ ሰዎች ለመገላገል በመቻኮል እስከ መጨረሻው የሰጠውን ነዳጅ በመከልከል የተንገረው ሀንጻ ፊት ለፊት ለማቆም ፍጥነቱን ሲያበርድ፣ ድልህ አይኑ፡-

‹‹ኖ ኖ ይቅርታ ሹፌር! የምንፈልገው አድራሻ ይሄ አይደለም ...የጓደኞችን ቢሮ ጠፍቶብን ነው፡፡ ........ ለማንኛውም እስቲ ወደቀኝ ታጠፍ›› እያለ ሲናገር ‹‹ዲጂው›› በኋላ መስታወት ሊመለከተው አይኑን ሲወረውር ከሩቅ የሚመጣ የፖሊስ መኪና ያያል፡፡ ይሄን ጊዜ የልብ ልብ ይሰማውና፡-

‹‹ስሙኝ! ከበፊቱም ጊዜ እንደሊለኝ ነግሬያችኋለሁ ... አካባቢው ደርሳችኋል ስትፈልጉ ውጡና በእግራችሁ ፈልጉት›› ይላል፡፡

በዚህ ጊዜ ጨበሪያሙ ‹‹ስማ! ይሄ ያንተ ችግር ነው፡፡ የኔ አይደለም ....... የምንፈልገው ቦታ የማድረስ ግዴታ አለብህ! .... ተጠምዘዝና ሳውዝ ስትሪት ላይ ካጣነው ያኔ እንወርድልሃለን›› በማለት ትዕዛዝና ልመና በተቀላቀለበት ሁኔታ ወተወተ፡፡

በዚህ መሃል የፖሊስ መኪናዋ ፆተር ስትሪትን ይዛ ቀጥታ ወደ ቻይና ታውን ስትበር ታክሲዋ ወደቀኝ ታጥፋ የበለጠ ፀጥ ካለውና ዕይታው ከደበዘዘው ‹‹ሳውዝ ስትሪት›› ላይ ስትወጣ የተሳፋሪዎቹ መቅበዝበዝ አይጎ አወጣ፡፡

ግራና ቀኝ፣ ኋላና ፊት አገለማመጣቸው አድራሻ ጠፍቶበት ከሚፈልግ ሰው የተለየ እንደነበር የሚያረጋግጠው የተሳፋሪዎቹ ትርኢት ተጀመረ!



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹ዲጄው›› ባልጠበቀው ሁኔታ ጨበሪያሙ ተሳፍሮ በመሄድ ላይ ያለውን መኪና በር በመበርገድ ‹‹እዚህጋ አቁም!›› ብሎ ሲጮህበት ቆሊው ተገፈፈ፡፡ እንደታዘዘውም ታክሲውን ወደ መንገዱ ቀኝ ጠርዝ ሰቦ ከማቆሙ ጨበሪያሙ ዘሎ በመውጣት በሹፌር መስኮት በኩል በመሄድ ከውጭ እንደሚከፍል ሰው መስታወቱን በሃይለኛ ኩርኩም አንኳኳ፡፡ ‹‹ዲጄው›› ፊቱን ወደሱ ሲያዞር ከውስጥ የቀረው ድልህ አይን ደግሞ፡-

‹‹ገንዘብህ የታለ? ያለህን ጠቅላላ አምጣ! .. አሁኑኑ!›› ብሎ አምባረቀ፡፡ የተዋከበው ምስኪን ወደ ጓለኛው ከመዞሩ ‹‹አምጣ እኮ ነው እምልህ!›› ብሎ ሲጮህበትና በያዘው ሽጉጥ አንገቱ ስር ሲያጮህበት አንድ ሆነ፡፡

‹‹ዲጄው›› በጥይት ጩኸት ጆሮው ሲደነቁርና አንገቱ ስር የሆነ ቅዝቃዜ ሲሰማው ‹‹እዚህማ አልሞትም›› ብሎ የነዳጅ መስጫውን እስከመጨረሻ ረገጠው፡፡

ታክሲዋ ሲጢጢጥ ብላ ተመንጭቃ በመነሳት በፍጥነት በረረች፡፡ አንድ ወንጀለኛ ከቆመበት ትታ፣ አንድ ነፍሰ ገዳይ፣ አንድ ሽጉጥ፣ አንድ ተገዳይ ይዛ!፡፡

ወጣቱ ለታክሲ ስራም ልምድ ወጣት በመሆኑና የሃገሩ ይሉኝተኛነትም ታክሎበት ለነፍሰ ገዳይ ዘራፊዎቹ ብዙ እድል ሰጣቸው፡፡ ይሄ ነው የሚባል መድረሻ ነጥብ የሌላቸውና ያሉትን የሚተያዩና መሆናቸው በራሱ ትልቅ ምልክት ነበር፡፡ መቅበጥበጣቸውና ሽክሹክታቸው ነገር እንዳለ ጮኸ የሚናገር ነበር፡፡ የፖሊስ መኪና ሲያዩ እንወርዳለን ያሉበትን ቦታ ብቻ ሳይሆን አቅጣጫም ጭምር መቀየራቸው በየዋህነት የሚታለፍ ሳይሆን ጥሩ ማንቂያ ደውል ነበር፡፡ ሰዓቱና አካባቢው በራሱ የመኪች መስታወት ግድግዳው መስኮት ተዘግቶ የሚሰራበት ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይሄ ሁሉ ሆኖ የወጣቱ ጥርጣሬ «ሳይከፍሉ ሊሮጡ ነው» ከሚል አላለፈም፡፡

እነሱ ግን እስከ ንጋቱ ድረስ ታክሲ የሚያንቀሳቅሱበትንና 24 ሰዓት ሙሉ የማያሸልበውን የኒውዮርክ አካል «ግሪንዊች ቪሌጅ»ን በማጥመጃነት ተጠቅመው ቀንቷቸዋል፤ ታክሲ ነጂዎች ደህና ገንዘብ የሚይዙበትን ሰዓትና መግደያ የሚሆናቸውን ጭር ያለ አካባቢ መርጠዋል፡፡

ወንጀለኞቹ ሹፌሩን ከሁለት አቅጣጫ በማዋከብ፡ ከኋላ የተቀመጠው በጥይት መትቶ ሲጥለው ከውጭ ገንዘብ ከፋይ የመሰለው ፊሳውን ገፋ አድርጎ መኪናውን በማስነሳት ጓደኛውን ተሳፋሪ አስመስሎ ምናልባትም እዛው አጠገባቸው ካሉት ድልድዮች ባንዱ በመጠቀም የግድያውን ቦታና ከተማውን በቶሎ ለቀው በመውጣት ሹፌሩንና መኪናውን እንዳሰቡት አድርገው ገንዘቧን ለመቀራመት እንዳቀዱ ድርጊታቸው አፍ አውጥቶ ይናገራል፡፡

ያም ሆነ ይህ «ዲጂው» ነጻጅ መስጠቱን ቀጥሏል፤ ታክሲዋም መሄዷን ፡፡

በቀላሉ ሊታረድ በይሉኝታ ገመድ ሲጎተትና ትዕዛዝ ሲፈጽም የነበረው በሬ ከመቅጽበት ተለውጦ ኃይለኛ ተፈራጋጭ ስለሆነበት ነፍሰገዳዩን አስደንግጦታል፡፡

«አቁም! አቁም!» ብሎ ጮኸ፡፡ የመኪናው በኃይል ወደፊት መመንጨቅ ሚዛኑን አሳጥቶት ኋላው ወንበር መደገፊያ ላይ ተጋጭቶ እየተመለሰ፡፡

«ዲጂው» ግን ያለመሞት ወኔውን አሰባስቦ መኪናዋን የተሻለ ብርሃንና ዕርዳታ ወደሚያገኝበት አቅጣጫ ረገጣት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

2ኛው የተኩስ ጩኸት አምባረቀ፡፡ አሁንም አንገቱና ትከሻው መካከል ደገመው፡፡ ደሙ እንደጉድ እየወረደ ቢሆንም ቆራጡ ወጣት እግሩን ከነዳጅ መስጫው አላወረደም፡፡ መኪናውም አልቆመም፡፡

ሁለት ጊዜ በጥይት የተመታው ልጅ እራሱን ተቆጣጥሮ ህይወቱን ለማትረፍ አስፈላጊውን ሁሉ በትክክል ሲፈጽም መቺው ከመደናገጡና ከመርበትበቱ የተነሳ በትክክል ስለማያስብ ለ3ኛ ጊዜ የተኮሰው ነዳጅ እየሰጠ ያስቸገረው የወጣቱ የቀኝ እግር ላይ መሆኑ ነው፡፡

ኢላማውን በትክክል አግኝቶ ቢመታም ዋነኛ ኢላማ ባለመሆኑ ወኔው የማይሞተው አንበሳ በቆሰለ እግሩ ጥርሱን ነክሶ ነዳጅ እየሰጠ የመኪናዋን አቅጣጫ ወደ ዎተር ስትሪት ሲያስይዝ፡ ሙከራው ሁሉ ዋጋ ቢስ የሆነበት ነፍሰ ገዳይ የራሱን ነፍስ ለማዳን በሩን በርግዶ በመዝለል ፈረጠጠ፡፡

ሁለት በሯ የተበረገደው ታክሲ በግምት 15 ሜትር ያህል ሄዳ ዎተር ስትሪት ላይ እንደወጣች ደም በብዛት የፈሰሰውና እግሩ የዛለው አሽከርካሪዋ በቂ ነዳጅ ሊሰጣት ባለመቻሉ ፍሬኗ ሳይያዝ በገዛ እጇ ቆመች፡፡ የተዝለፈለፈውን ሹፌሯንም በመሪዋ ተቀበለችውና ደጋግፋ ያዘችው፡፡

ሁለት በሯ ተበርግዶ የማይሆን አቋቋም መቆሟ የማንንም ትኩረት ሊስብ የሚችል ነበርና በዎተር ስትሪት ላይ የሚያልፍ ‹‹ብላክ ካር›› የሚባለው ታክሲ ሹፌርም ተጠራጥሮ በማቆም ፖሊስ በሬዲዮ በማስጠራት ያየውን ሁኔታ አስረድቶ ሳይጨርስ ሳይረናቸው ከአነስ፡ አነስ ከአምቡላንስ ቀድመው ደርሱ፡፡ የኒውዮርክ ፖሊሶች!፡፡

ፖሊሶቹ መሪው ላይ የተዝለፈለፈውን ቁስለኛ በጥንቃቄ ወንበር ላይ ካንጋለሉት በኋላ ስለ አቁሳዩቹ ሁኔታ መልክ፡ አለባበስ፡ የቀለም አይነት፡ ክብደት፡ ዕድሜ፡ የያዙት መሳሪያ አይነት ወዘተ በጥያቄ ያዋክቡት ጀመር.



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁስለኛው ግን «እባካችሁ እሱን ትታችሁ ሃኪም ቤት አድርሱኝ» በማለት ተማጸነ፡፡

ፖሊሶቹም አምቡላንስ እየደረሰ እንደሆነ በመንገር ጥያቄያቸውን እንዲመልስ ማግባባታቸውን ቀጠሉ፡፡

አቅም እያነሰው፣ ትንፋሹም እየደከመ ያለው የ3 ጥይት ቁስለኛ «እባካችሁ እርዳታ» እያለ ሲያቃስት አይኑም አብሮ ይለምናል፡፡

የፖሊሶቹ ጥያቄ ያለማቆም፣ ቃለ ምልልሱ በዚያች ሰዓት በስምሪት ላይ ለሚገኙ የፖሊስ ሮንዶች በሙሉ ስለሚተላለፍ በተለይ ወንጀሉ በተፈጸመበት አካባቢ ያሉት ፖሊሶች ወንጀለኞቹ ርቀው ሳይሄዱ ለመያዝ የሚያስችል አጋጣሚ ስላለ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት የወንጀል ጉዳተኛው ህይወት የማትተርፍ ከሆነ፣ ያለ ምንም ጭብጥ መረጃ /ኢንፎርሜሽን/ ወንጀሉ ከሟቹ ጋር እንዳይቀበር በመፍራትም ይመስላል፡፡

ለዲጂው ግን ቅድሚያው ህይወቱን ለማትረፍ ብቻ እንዲረባረቡለት ነውና ብዙም አልተባበራቸውም፡፡

ጭቅጭቁ ሲበዛበት በተቆራረጠ ድምፅና በብዛት በምልክት መልስ እየሰጠ ቁስሉን ሲያዳምጥ ቀስበቀስ ህሊናውን መቆጣጠር እየተሳነው አቅሙም እየደከመ መጣ፡፡ አይኑም ተከደነ፡፡

ደሙ እየፈሰሰ፣ አቅሙ እየደከመ፣ ራሱን እየሳተ በመሄድ ላይ ያለው ቁስለኛ፣ እንደዛ የደከመ ህሊናው አትላንቲክን አቋርጦ፣ የብሱን ተጉዞ ትውልድ ሃገሩ በመግባት ወላጅ ዘመዶቹን ለመሰናበት አቅምም ጊዜም ነበረው፡፡ «የኔ ነገር እንደዚህ ሆኗልና ደህና ሁኑ» አላቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በለጋ እድሜው ስንቱን ጉድና የጉሮ መሰናክል ተቋቁሞ፣ የተሻለ ሀይወት ሊኖርባት ተስፋ ሰንቆ የመጣባትን አሜሪካንን ‹‹ተስፋዬን በላሽው?›› ብሎ ወቀሳት፡፡

በጥይት ውርጅብኝ ደሙን አፍስሰው መኖሩን የነፈጉትንና እንደወጣ መንገድ ላይ ያስቀሩትን ወሮበሎች ረግሞ ሳይጨርስ ሀሊናው በዝብርቅርቅ የጨኸት አለም ተጠልፎ ወደ ታላቅ የቅዠት ባህር ሰጠመ፡፡

‹‹ዲጂው›› ከብዙ ቀናት ህክምና በኋላ ተሽሎት ከ‹‹ኒውዮርክ ዩንቨርሲቲ ሆስፒታል›› /ኤን ዋይ ዩ/ በክዘራ እየተረዳ ሲወጣ የድሮው ዲጂ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡

እምላክ ትረፍ ብሎት ጥይቶቹ አጥንቱን ስላልነኩ አካሉ ሙሉ በሙሉ የተመለሰ ቢሆንም ማንነቱ ግን እስከወዲያኛው ተቀይሯል፡፡

ሙዚቃን ከሚያደምጥባቸው ጆሮዎቹና በሙዚቃ ከሚረካው ሀሊናው የነዛ እውሬዎች የማቀከብ ትዕይንትና የጥይት ጨኸት ተፍቆ ወጥቷል ለማለት ይከብዳል፡፡

ሶስቱ ጥይቶች በአካሉ ላይ ካስቀሩት ጠባሳ ይልቅ ፈጽሞ ባልጠበቀው ሁኔታ ድንጋጤ ውስጥ በመግባት የተጎዳው እይምሮው ከደረሰበት ጠባሳ ለመንፃት ጊዜንና የባለሙያን ክትትል የሚጠይቅ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

‹‹ዲጂው›› ከሆስፒታል በወጣበት ሰሞን ዳግም ቆሞ ሊመሄድ በመብቃቱ ‹‹ከሞት ወደ ህይወት›› ብሎ የሰየመውን ፓርቲ በመደገስ ደስታውን ከወዳጆቹና ከሚቀርቡት ጋር ተካፈለ፡፡ ያውም እራሱ ዲጂ ሆኖ!፡፡

ያች ቀን የዲጂነት ህይወቱ የመጨረሻ ቀን ሆነች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይሄ ወጣት በሚያስደንቅ ሁኔታ ፍርሃቱን ተቆጣጥሮ ለብዙ ሰው ማድረግ የሚከብደውን በማድረግ ህይወቱን ቢያተርፍም የድሮው ዲጀንቱ፥ቀልጣፋነቱና፥ ራዕዩ ‹‹ሳውዝ ስትሪት›› ላይ ተገድለው ፈዘዝ ቀርዘዝ ያለ ፍጡር ሆኗል፡፡

አንዳንዴ ሰዎች ተሰብስበው በሆነ አርዕስት ላይ ሲያወጉ በጥሞና ፈዝዞ የሚያዳምጥ የሚመስለው ልጅ በመሃል ወሬያቸው ውስጥ ገብቶ ከቶም የማይገናኝ ነገር ማውራት ሲጀምር ለተመለከተው በቁጭት ሀዘን ውስጥ ይወረውራል፡፡

ከደረሰበት ሁኔታ አንጻር ሲታይ በህይወት መትረፉም እጅግ እድለኛ ነው፥ የሚያስብል ቢሆንም ይሄ ህይወትን ገና ማጣጣም የጀመረ ወጣት ሰርቶም ሆነ ተምሮ ትልቅ ቦታ መድረስ ሲችል መንግስት ‹‹ለወንጀል ጉዳተኞች›› በሚሰጠው ዕርዳታ ተገድቦ ሲቀር አንጀት ያሳርራል፥

የወጣቱን ደም ያፈሰሱት ወንጀለኞችን ለመያዝ የተመደበው ዲክቴክቲቭ እስካሁን እንቅቅልሹን አልፈታም፡፡

‹‹ዲጀው›› እንካ ጸባየ ሸጋነቱ፥ ሰው አክባሪነቱ፥ ካለባበስ ጥራቱ ጋር እንዳለ አለ፡፡

ለከርሞ ጤና የመሆኑ ትልቅ የተስፋ ምልክት ሆነው!



t.me/OLDBOOKSPDF

# የቀይ መብራት መዘዝ

ሌሊቱን ስሰራ አድሬ በማግስት ከንጋቱ 10 ሰዓት አካባቢ በ2ኛው ጎዳና ላይ ተሳፋሪ ይዤ ወደ ዳውን ታውን (ደቡብ) እየሄድኩኝ ነው፡፡

በዚህ በኒውዮርኩ 2ኛው ጎዳና ላይ የሚገኙት የትራፊክ መብራቶች ቀለም አቀያየር ስርዓት በየ1/20ኛ ማይሉ ርቀት ላይ በተዘረጉት መንገዶች መካከል የ6 ሰኮንድ ልዩነት እንዲኖረው ተደርጎ የተቀመረ ሲሆን የአበራሩም ቅደም ተከተል (አፈሳሰስ) ከሰሜን ወደ ደቡብ ነው፡፡ ይህም ቀመር በ30 ማይል ፍጥነት የሚነዱ ተሽከርካሪዎች በየመብራቱ ላይ ሲደርሱ ወደ አረንጓዴነት እየተቀየረላቸው እስከመጨረሻው ሳይቆሙ እንዲሄዱ ተደርጎ የተስተካከለ ነው፡፡

እኔም 2ኛው ጎዳናና 54ኛው መንገድ መገናኛ ላይ ልደርስ ስል አረንጓዴው መብራት ወደ ቢጫ ተቀየረ፡፡ ፊት ለፊት ከርቀት የማያቸው አረንጓዴ መብራቶች ላይ ደርሼ ከመብራቱ አቀያየር ጋር ፍጥነቴን በማስተካከል ሳልቆም ወለል ብሎ በሚታየው ትራፊክ አልባ መንገድ ላይ ለመንዳት ፍጥነቴን ጨመርኩ፡፡ መንገዱን አቋርጬ ሳልጨርስ ቀይ መብራት ቢበራም ጥሼው መብረሬን ቀጠልኩ፡፡

ለካስ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በሚወስደው 54ኛው መንገድ ላይ ስኩተር (ባለ 3 እግር ኩርኩር) የሚነዳ ፖሊስ ቆሞ ኖሮ በቀይ መብራት መጣስ ሊያስቆመኝ ሳይረኑን እያስጮኸ መብራቱን እያምቦለቦለ እስራ ገባ፡፡

እኔም በየጊዜው ለቲኬት መቀጮ የምገብረው ገንዘብ ያንገሸገሸኝ ከመሆኑም ሌላ «ለዚችስ ኩርኩር አላቆምም» ብዬ ለማምለጥ ፍጥነቴን ጨመርኩ፡፡ የየመንገዶቹን አረንጓዴ መብራት ልደርስባቸው አቃተኝ፡፡ በየመገጣጠሚያው ከቢጫ ወደ ቀይ ሲቀየር ሆነ የምደርሰው፡፡ ቀይ መብራት መጣስ ስራዬ ሆነ፡፡ ፖሊሱ ያሳድደኛል እኔም እከንፋለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሳፋሪዬ በጎን በኩል ጣራ ላይ የተንጠለጠለውን የእጅ መያዣ በሁለት እጁ ጨምድዶ ይዞ «ማይ ጋድ!»፣ ‹‹ ማይ ጋድ!›› ይላል::

42ኛው ባለ 2 ተሳላፊ ሰፊ መንገድ ላይ ብታጠፍ የቆመ መኪና እንዳያግደኝ ይጠቅመኛል በማለት ታጠፍኩ::

ፖሊሱ በሬድዮ ለሌሎች ፖሊሶች እስተላልፎኖሮ ብዙም ሳልሄድ ከተቃራኒው አቅጣጫ ሳይረናቸውን እያጯጯሁ መንገድ ዘግተው አስቆሙኝ:: ሽጉጥ በደገኑ ፖሊሶች ተከበብኩ::

ተሳፋሪዬ በሩን በርግዶ ከወጥመድ እንዳመለጠ ወፍ ቱር አለ:: ሁለት እጄን ወደ ላይ ሰቅዬ ተማረኩ::

ከፖሊሶቹ ጩኸት ውስጥ ‹‹እጅ ወደ ላይ!! እንዳትንቀሳቀስ!» የሚለውን ቃል ስለሰማሁ እንዳሉኝ አደረኩ::

አንዱ ፖሊስ በሬን ሲበረግደው ሌላኛው ምኔን ይዞ እንዴት ከመኪናዬ ውስጥ እንዳወጣኝ እስካሁንም ግልፅ የሆነልኝ ነገር የለም::

ደረቴን ከመኪናዬ የኋላ ዕቃ መጫኛ ላይ አጣብቀው እግሮቼን በኋላ ጎማዎች ልክ ሲያንፈረክኳቸው ለድብዳብ የሚወጠር የበግ ቆዳ መሰልኩ:: ቁመቴ አጠረ::

የፖሊሶቹም እጆች ከጫማዬ እስከ ማጅራቴ ደሞ እንደገና ወደ ታች ለፍተሻ ተሯሯጡ:: በስውር ጎሸምሸም አደረጉኝ:: ቀበቶዬ ተፈቶ ውስጥ ሱሪዬ ተበረበረ:: ኪሴ ውስጥ ያለ ነገር በሙሉ ተዘከዘከ ወጣ:: የቀራቸው ነገር ቢኖር እግሮቼን ወደ ላይ አንስተው እንደ ጆንያ ማራገፍ ብቻ ነው:: ምንም ነገር አጡ::

ያ ባለ ኩርኩር ፖሊስ የመንጃ ፍቃዴን ወስዶ ሪከርዴን ሲያጣራ ግማሾቹ ፖሊሶች ወደ መኪና ብርበራ ተሸጋግረው ጠቅላላ መኪናው በባትሪ ተፈተሸ:: አሁንም ምንም ነገር ሊያገኙብኝ አልቻሉም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ቲኬቱ ላይ ከ1 ወር በኋላ ትራፊክ ፅህፈት ቤት እንድቀርብ ታዝዣለሁ:: ለማውቀው ሰው ሁሉ ባማክርም እንዲህ አይነት የ13 ቲኬት ልምድ ያለው ሰው ስላልነበረ ታሪኩን በመገረም ከመስማት በቀር ምክር ሊመክሩኝ ማናቸውም አልደፈሩም:: ብዙዎቹ ይሄንን ክስ ከማሽነፍ «ሎተሪ ማሽነፍ» የሚቀል ነው የሆነባቸው:: ጭንቄ ያስጨነቃቸው ዘመዶቼና የቅርብ ጓደኞቼ የተለያየ ጠበቆች ጠቁመውኝ ሁሉንም ባነጋግርም የሁሉም መልስ ተስፋ አስቆራጭ ሆነብኝ:: ሁሉም በአንድ ቃል የሚነግሩኝ የቲኬቱን መቀጮ መክፈሌ አጠያያቂ እንዳልሆነ ሲሆን የሚለያዩት መንጃ ፈቃዱ ላይ ነጥብ እንዳይያዝብኝ ሊረዱኝ እንደሚችሉ በሚሰጡኝ ተስፋ ነው:: ለዛውም እርግጠኝነታቸው ከ40 - 70% ብቻ ነው:: የነሱ እርግጠኝነት በፍርድ ቤት ለ10 ደቂቃ እኔን ለመወከል የጠየቁኝ ክፍያ ላይ ነው:: ከ300-500 ዶላር ቅድሚያ ክፍያ! :: ይሄ ክፍያ ለቲኬቱ መቀጮ የምከፍለው 13 ሲባዛ በ 65 ዶላር ላይ የሚጨመር ነው::

በሰኮንድ ክፍልፋይ ውስጥ ያለማመዛዘን የወሰንኩት ስህተተኛ ውሳኔ አባዜው መች በዚህ አብቅቶ!

የኒውዮርኩ የታክሲና ሊመዚን ኮሚሽን ማንኛውም በትራፊክ ጽህፈት ቤት የተከሰሰ ታክሲ ሹፌር ለተመሳሳይ ጥፋት በድጋሚ በታክሲ ኮሚሽን ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ እንዲታይ በአሜሪካ ግዛት ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ኢ-ፍትሃዊ ህግ አውጥቶ ስለነበር ከ2 ወር በኋላ እንድቀርብ በደብዳቤ አሳወቀኝ::

እንግዲህ በ3 ጅቦች ልበላ የተዘጋጀሁ ፍጡር ሆኛለሁ! በትራፊክ፣ በጠበቃና በታክሲ ኮሚሽን::

ነገሮችን ሁሉ አውጥቼ አውርጄ ከሴን ራሴው ልሞግተው ወሰንኩ:: አዎ! «የትራፊክ ፅህፈት ቤቱ የሚቀጣኝን ይቅጣኝ እቀበላለሁ፣ የታክሲ ፍርድ ቤት ቀርቤ ለሚነጥቁኝ የታክሲ መንጃ ፈቃድ ተጨማሪ ገንዘቤን የማስረክብበት ምክንያት የለም፣ ሌላ ስቴት ሄጄ ታክሲዬን እነዳለሁ፣ ከጅብ የማያስጥል አህያ ባል እንደሚባለው ለሆነብኝ ጠበቃም ሳንቲም አላወጣም» ብዬ ወሰንኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ውሳኔ ካደረግኩበት ቀን ጀምሮ ስበላም ስጠጣም ታክሲዬን ስነዳ ሃሳቤና ትኩረቴ ሁሉ እንዴት አድርጌ መከራከሪያ ምክንያት እንደምፈጥር ሆኗ ብዙ ሃሳቦችን አወጣሁ አወረድኩ:: ነገር ግን እንኳን ማሳመኛ ቅጣት ማቅለያም አላገኘሁም::

የሆነ ቀን « ጆሮዬ ስለማይሰማ ሳይረኑን አልሰማሁም ልበል » ብዬ ውሳኔ ላይ ከደረስኩ በኋላ፣ በደንቆሮ ጆሮ መንዳቴ መንጃ ፈቃዴን ሊያስነጥቀኝ እንደሚችል የገባኝ በነጋታው ነበር::

እራሴን ወቀስኩ:: «እውነትም ደንቆሮ ነኝ» አልኩ:: እንዴት ይሄን ማመዛዘን አቃተኝ ብዬ:: እንዲህ ግራ የገባው ሰው እንደሆንኩ ቀን ቀጠሮው ወደኔ እየሮጠ ነው::

በየጊዜው እራሴው ያወጣኋቸውን አቅዶች እራሴው እያፈረስኩ አንድም ነገር ሳልጨብጥ ቀን ቀንን እየወለደ ፍርድ ቤት መቅረቢያዬ የቀረው ጊዜ በሰአታት መቆጠር ጀመረ::

በፍርድ ቀኔ ዋዜማ ማታ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ስለ ነገዬ ሳውጠነጥን «ትራፊክ ፖሊሱ በጣም ትንሽ መኪና ይዞ አለቅጥ ተጠግቶኝና እስሬ ገብቶ ስለሚነዳ ሳቆም ተጋጭቶ ቢጎዳ መከራ ውስጥ ሊከተኝ ይችላል ብዬ የፈራሁ የዋህ ሆኜ ብታይስ ?» ብዬ አሰብኩ::

በተጨማሪነትም «ትምህርት የሌለኝ መሃይም ስለሆንኩ የታክሲ መንጃ ፈቃዴን በማጣቴ ምክንያት ብነጠቅ ብዙት ያለውን ቤተሰቤን ሊያስተዳድርልኝ የሚችል ሌላ ስራ ስለማላገኝ አስከፊ የኑሮ ችግር ውስጥ እንደምዘፈቅ ስለታየኝ ነው» ብዬ ባማሳዘን ዳኛውን ልማፀነው የሚል ሃሳብ መጣልኝ:: ቢቃ ከምንም የሚሻል ሃሳብ ነው ብዬ ደመደምኩ::

በነጋታው ይህንኑ መከራከሪያዬን ይዤ ፍርድ ቤት በመሄድ ከቀጠሮው ሰሌዳ ላይ የተመደበልኝን ክፍል ካረጋገጥኩ በኋላ ከቀጠሮው ሰዓቴ 10 ደቂቃ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ብዬ ገባሁና ኮምፒዩተሯ ላይ ለተጣደችው የችሎቱ ፀሐፊ አስራ ስሰቱን ቲኬት ሰጠኋት፡፡ ቀና ብላ በመገረም አይን እየቸኘና ወንበር እንድይዝ ነገረችኝ፡፡

የዳኛው መሰየሚያ በሚያብረቀርቁ ቀጫጭን ጣውላዎች ተገጣጥሞ በተሰራ ባልኮኒ የተከበበ ሲሆን በግራና በቀኝ በኩል መወጣጫ ደረጃዎችና በሮች እንዲኖሩት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

ግራና ቀኝ የቆሙት የአሜሪካ ባንዲራዎች ችሎቱን ክብር አጎናፅፈውታል፡፡ በባልኮኒው አናት ላይ ዳኛውና ፀሃፊዋ የሚጠቀሙባቸው ኮምፒዩተሮች፣ የድምፅ መቅረጫ ቴፕ፣ ወደ አራት የሚደርሱ ተሰጣጭ ማይክራፎኖች፣ የእንጨት መዶሻ፣ ተሰኪ ብዕሮች፣ ማስታወሻ መፃፊያ ወረቀቶች፣ ማህተሞች ከነመርገጫቸው ወዘተ ለመጠቀም በሚያመቹበት ቦታ ተቀምጠዋል፡፡

ከችሎቱ በቀኝ በኩል «ለፖሊስ ብቻ» የሚል ፅሑፍ መደገፊያው ላይ የተለጠፈበት አግዳሚ ወንበር ፊቱን ወደ ተከሳሽ መቀመጫዎች አድርጎ የተቀመጠ ሲሆን የተቀረው ክፍል ለተከሳሾች በተዘጋጁ ከ35-40 በሚደርሱ ምቹ ወንበሮች ተሞልቷል፡፡

ተከሳሾች ቀስ በቀስ እየተንጠባጠብን በመምጣት በክፍሉ ውስጥ ከተደረደሩት ወንበሮች ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን ያዝናቸው፡፡

ኒውዮርክ ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ሕዝብ የስደተኛው ሕዝብ ቁጥር 5% ባይሞላም በዚህ ክፍል ውስጥ ግን በግምት 80% የሚሆነው ተከሳሽ ስደተኛ ነው፡፡

ከዚህ ስደተኛ ተከሳሽ ውስጥ አብዛኛው የህግ የበላይነት በሌለበት ሃገር ውስጥ ተወልዶ ያደገ በመሆኑም ከፖሊስና ከፍርድ ቤት ጋር ያለው በፍርሃት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በደመ ተዋህዶ ለትንሿ የትራፊክ ፍርድ ቤት እንኳን ያለው ፍራቻና መሸማቀቅ ከፍሉ ውስጥ እግሩ ከረገጠበት ሰዓት ጀምሮ ከፊቱና ከአኳኋኑ ይነበባል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚች ክፍል ውስጥ ጠበቆችና ተከሳሾች አልፎ አልፎ ከሚያንሾካሹኩት ድምፅና ከወረቀት መንክሻከሽ በቀር ፀጥታው በራሱ ለፍርሃት የሚጋብዝ ነው:: አብዛኛው ተከሳሽ ለራሱ ወደ ውስጥ በማውራትና እራሱን በማዳመጥ ተጠምዷል::

ጺሙን የሚያሽው፣ ራሱን የሚቋጨው፣ አፍንጫውን የሚሰረስረው፣ በጆሮው የሚጫወተው፣ አይኑን አንድ ቦታ ላይ ተክሎ የጎስጎሰው ወዘተ ተከሳሽ በሙሉ ሃሳቡን አሰባስቦ ራሱን ለመከላከል እንዲችል ህሲናውን በከባድ ማርሽ በመጠቀም ላይ መሆኑን በግልፅ ያስታውቅበታል::

እኔም አንድ ወር ሙሉ ያስመቋረጥ ፀጉሬን ስፈትል የከረምኩት ያለ ምክንያት አልነበረም::

ከሳሽ ፖሊሶች በተመደበላቸው ቦታ ላይ አንድ በአንድ እየገቡ ቁጭ ካሉ በኋላ የቲኬት ማስታወሻቸውን እያገላበጡ በማየት፣ ለማነፃፀሪያ ተከሳሻቸውን በአይናቸው በመፈለግ፣ ትውስታቸውን ለማደስ አይምሯቸው ከባድ ስራ ላይ ነው:: ልክ እንደ እኛ!::

አንዱ ለማምለጥ አንዱ ለመያዝ በዚች ክፍል ውስጥ የሚገኝ ፍጡር ህሲና በሙሉ መከራ ፍዳውን እያየ ነው:: በስራ ብዛት!::

በዚህ ሁኔታ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ በጎሪጥ መተያየታቸው ሲጨመርበት አይጥና ድመት አስመስሏቸዋል::

የኔውም ድመት መጨረሻ ላይ መጣ:: እሱም እንደጓደኞቹ ቲኬቶቹን እያገላበጠ የከሰሳቸውን ሰዎች በአይኑ እየቃኘ ማስታወሻ ይፅፋል:: እኔ እሱን፣ እሱም እኔን ለማስታወስ ችግር አልነበረብንም:: ድንገት አይን ለአይን ስንጋጭ «ሰላም» ማለቱ ነው መሰል ፈገግ አለ:: እኔ ግን ሳላውቀው «መጥፎ የአማርኛ ስድብ» ከአፌ ተፈተለከ:: ሁኔታው እየሳቁ መግደል ስለሆነብኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙም ሳይቆይ ዳኛዋ በቀልጣፋ አረማመድ ወደ ክፍሉ ሲገቡ የሁሉም አይን እሳቸው ላይ አነጣጠረ:: የፖሊሶችም ጭምር::

ሴትዮዋ ያማረ እግራቸውን ለማሳየት ያደረጉት ቀሚስ እጥረቱ ህግ ባይኖር ኖሮ በዋና ሙታንታ ከመምጣት የማይመስሉ መሆናቸውን ይመሰክራል::

እድሜያቸው ወደ 60 የሚገመተው ሴትዮ ፊታቸውና ሰውነታቸው ፈጽሞ አይገናኝም:: በ20 ዓመት ለጋ ወጣት ሰውነት ላይ የተሰካ የ60 ዓመት ሴት ይመስላሉ::

ዳኛዋ ገና ከመሰየማቸው ስማቸውን አስተዋወቁና ስለ ፍርድ ቤቱ የፍርድ አፈፃፀም ገለፃቸውን ቀጠሉ::

እኔም በየጊዜው እየተከሰሰኩ ስቀርብ መስማቱ የሰለቸኝ ነገር ነበርና እልፍ አልፎ ጆሮዬ ውስጥ ከሚገባው ቃላቸው በቀር አላዳመጥኳቸውም:: ይልቁንም የራሴን «ቲያትር» ለማቅረብ ሃሳቦቼን ማጠንጠኔን ተያይዤዋለሁ::

ፖሊሱን ባቆምለት ተጋጭቶ ሊሞት ... ሊጎዳ ይችላል... ፈራሁኝና ... ሳላቆም ቀረሁ? ታምነኝ ይሆን? ... ኖ ... በፍርሃት ብቻ! ሌላ ነገርስ? ነገር ከማብዛት .... ፍርሃት ብቻ! ... ሌላው እንዳይጎዳ ፍርሃት? በአሜሪካ? ኖ ... አታምነኝም! ለራሴ ቢሆን አኬ! ... ለራሴ ፍርሃት .... የምን ፍርሃት? ... በቃ! ተሳፋሪው ..... ::

የሆነ ነገር ብልጭ አለልኝ:: ሃሳብ! ግሩም ሃሳብ! አካልና አይምሮዬ ባንድ ላይ ተቀበለው::

‹ሕገባህበት አዘቅት መውጫው ብቸኛ መንገድ ይኸው ነው! ሳታወላውል ግባበት!›› አለኝ የሆነ ነገር:: በህሊናዬ የሚወራጨው ጭንቀቴ እየተረጋጋ እምነቴና ድፍረቴ በሰውነቴ እየጨመረ መጣ:: ወዲያው የመጣልኝን ድርሰት እንዴት እንደምተገብረው ማዘጋጀቱን ቀጠልኩ:: እንደገና ወደ ከያኒነት ተሸጋግሬ ልምምዱን ተያያዝኩት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ተራዬ ደርሶ ወደ መድረክ ስጠራ እንደ ኀበዝ ቲያትረኛ በሙሉ ልብ ቀረብኩ:: ዳኛዋ 13 ቲኬት ከፊታቸው ሲቀርብ የማንበቢያ መነፅራቸውን ዝቅ አድርገው ከእግር እስከራሴ አዩኝና ወዲያው የተዘጋጀው ፎርም ላይ እየሞላሉ

«አቶ ---------- ------------------ ማለት አንተ ነህ?»

«ክቡርነትዎ! አዎ እኔ ነኝ:: »

«አድራሻህ ------- ---------- --------- ----- ነው?»

«ትክክል! »

«መንጃ ፈቃድህን ለማረጋገጫ ማየት እችላለሁ?»

እውጥቼ አስቀመጥኩ

«እነዚህን 13 ቲኬቶች ማግኘትህን ታረጋግጣለህ? »

«አዎ ክቡርነትዎ! የኔ ናቸው::»

«ተከላካይ ምስክር አለህ?»

«ክቡርነትዎ! የለኝም::»

«ለተከሰስክበት 13 ቲኬት ጥፋተኛ ነህ አይደለህም? »

«ክቡርነትዎ! ጥፋተኛ አይደለሁም! » /ፍጥጥ ብዬ ዳኛውን እያየሁ/

ዳኛዋ አስፈላጊውን ፎርም ሞልተው ከጨረሱ በኋላ ፖሊሱን መሃላ አስምለው ቀጥል! አሉት::

ፖሊሱ እንደፈጠነ ካሴት ተረረረረ እያለ ሃጢያቱን አንድ ሳይቀር ሲዘከዝክ ዳኛዋ ራሳቸውን እየነቀነቁ ቲኬቶቹን እያገላበጡ ያያሉ:: አልፎ አልፎም በነጭ ወረቀት ላይ ፖሊሱ የሚያወራቸውን መንገዶች ይስላሉ:: ከጎኔ ቆሞ የሚለፈልፈውን ፖሊስ ስህተት ድንገት ባገኝበት ብዬ በጥሞና አዳመጥኩት:: ምንም ነገር ሳይጨምር ሳይቀንስ ክሱን አስረድቶ አበቃ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ዳኛዋ ከእኔ በፊት ተከሰው በቀረቡ ሰዎች ላይ ፖሊሶች የክስ ማስረጃቸውን ሲያቀርቡ የነበረው አደማመጣቸው ተቀይሮ ከሳሽ ፖሊስ በኔ ላይ ማስረጃውን ሲደረድር አይናቸውን ኳልኩለው ጆሮአቸውን አቅንተው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የመከታተል ሁኔታቸው የኔን ክስ በተለየ ሁኔታ ማየታቸውን እንኳንስ ለኔ ለባለጉዳዩ ለማንኛውም ተመልካች ይመስክራል ፡፡

ፖሊሱ በጥንቃቄ ክሱን ከነማስረጃው አቅርቧል:: ዳኛዋም በጥንቃቄ ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት ተዘጋጅተዋል:: ከእንግዲህ የቀረው ጥንቃቄ በኔ በኩል ያለው ነው::

ሰውነቴን ለማረጋጋት በረዥሙ ትንፋሽ ከሳብኩ በኋላ ለኑሮዬና ለህልውናዬ ስል ቆራጥ ጠበቃ መሆን እንዳለብኝ ራሴን አሳመንኩት:: ጉሮሮዬን አጥርቼ፣ አንገቴን አንቅቼ፣ ደረቴን ነፍቼና፣ አይኖቼን ዳኛዋ አይን ላይ ተክዬ ትዕዛዛቸውን መጠባበቅ ጀመርኩ::

ዳኛዋ በድጋሚ ከእግር እስከ ራሴ ከቃኙኝ በኋላ ቁጣና ግልምጫ በተቀላቀለውና ረጋጥ ባለ አነጋገር: -

«መከላከያ ነጥብህን ከማቅረብህ በፊት ቀጥዬ ለምጠይቅህ ጥያቄዎች «ነው! ወይንም አይደለም!» የሚል መልስ ብቻ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ» በማለት ሲያሳውቁኝ:-

«እሺ ክብርት ሆይ!» ነበር መልሴ ቆፍጠን ብዬ፡፡

«የመጀመሪያውን ቀይ መብራት ጥሰሃል?»

«አዎ»

«ሁለተኛውን መብራት ጥሰሃል?»

«አዎ ክብርት ሆይ!»

..........«አስራ ሰስቱንም ቀይ መብራቶች ጥሰሃል ማለት ነው?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ ክብርት ሆይ!»

«ፖሊሱ ከተናገረው ውስጥ ተቃውሞ አለህ?»

«ፖሊሱ ከተናገረው ውስጥ ተቃውሞ የለኝም»

ዳኛዋ ፊታቸው ላይ መነበብ የጀመረውን ግራ የመጋባት ሁኔታ «ታዲያ ጥፋተኛ አይደለሁም ያልክበት ምክንያት ምንድነው?» በሚለው ጥያቄያቸው አጎሉትና መልሴን ለመስማት አፈጠጡብኝ::

እኔም ከነበርኩበት ሁኔታ ምንም ሳልተየር በተረጋጋ ሁኔታ «ክብርት ሆይ! ሁኔታው ባጭሩ እንደዚህ ነው ...» በማለት ጀመርኩ::

«ተሳፋሪዬ ከንጋቱ 10 ሰዓት አካባቢ ዳውን ታውን እንዳደርሰው ነግሮኝ ጥቂት እንደተጓዝኩ ሽጉጥ ደግኖ ወደ መንገድ ዳር ወጥቼ እንዳቆምና ያለኝን ገንዘብ ሁሉ እንዳስረክበው በጩኸት አዘዘኝ:: እኔም ያለኝን ለመፈፀም የመኪናዬን ፍጥነት አብርጄ ከመሃል መንገድ ወደ ዳር በመውጣት ላይ እያለሁ 54ኛውና 2ኛው ጎዳና ላይ የፖሊስ ተሽከርካሪ ቆሞ ስላየሁ የእሱን ትኩረት ለመሳብ ከፊት ለፊቱ ላይ ቀይ መብራት ጥሼ አለፍኩ::

እኔ እንደፈለኩት ፖሊሱ ሊያስቆመኝ ሳይረኑን ማስጮህ ሲጀምር ለማቆም ፍጥነቴን ሳበርድ አጋቹ «እንዳታቆም! ጭንቅላትህን ሳላፈርሰው በፍጥነት አምልጠው!» የሚል ትዕዛዝ ሰጠኝ:: .... ምርጫዬ ህይወቴ በእጁ ላይ ያለችውን አጋቹን ትዕዛዝ መፈፀም ብቻ ነበር! ስለዚህም ቀይ መብራቶቹን ለመጣስ ተገደድኩ!.....

ፖሊስ ኦፊሰሩ እንደተናገረው 42ኛው መንገድ ላይ እንደታጠፍኩ ከተቃራኒ አቅጣጫ የመጡ ፖሊሶች በመኪናቸው መንገድ ዘግተው አስቆሙኝ:: .... ከየአቅጣጫው ሽጉጥ በደገኑ ፖሊሶች ተከበብኩ ....» በማለት የነበረውን ሁኔታ አነበነብኩና «ይሄው ነው! ክብርት ሆይ!» በማለት ንግግሬን ደመደምኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመስራት ምክሬ ተሳፋሪዬ ሁሉ የሚዘርፈኝ፣ ሽጉጥ የሚያወጣብኝ እየመሰለኝ ሁኔታው ከአይምሮዬ እስኪወጣ ድረስ ስራዬን ለማቆም ተገድጃለሁ:: ለረዥም ጊዜም ባለመስራቴም ኢኮኖሚዬ ተቃውሷል:: የኑሮ አቅዴ ተዛብቷል:: ችግሬ በዚሁ ከቀጠለ ከነቤተሰቤ ለችግር መዳረጌ አይቀሬ ነው» አልኩ::

እዛው የመጣልኝ ሃሳብ ለራሴው እስኪገርመኝ ድረስ ውስጤን አስደሰተው:: በተዘዋዋሪ ዳኛዋ ጥፋተኛ ብለው ቢወስኑብኝ ለዛ ሁሉ ቲኬት የምከፍለው ገንዘብ እንደሌለኝ የማሳውቅበት ሁኔታ ስለተከሰተልኝ ጥሩ እርጌ ለራሴ ጠበቃነት እንደቆምኩ ታውቆኛልና ድምጼን ከፍ አድርጌ ዳኛዋ አይን ላይ አይኔን ተክዬ «መልሴ ይሄው ነው!» አልኳቸው::

ዳኛዋ ከመቅጸበት የክሱ ቅጽ ላይ መቸከቸኩን ተያያዙትና ሲጨርሱ «ተከሳሹ ያቀረበው የመከላከያ ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ስላገኘሁት ጥፋተኛ አይደለም! ብዬ ወስኛለሁ!» በማለት 13ቱን ቲኬት በማህተም መደብደብ ሲጀምሩ ልቤም አብሮ ከበሮ ይደልቅ ገባ በደስታ!

እኔም የውስጥ ደስታዬን ከፊቴ ላይ መደበቅ አልቻልኩም:: ሳላቀው በዘገሬ ባህል ለዳኛዋ ያልተለመደ እጅ ነስቼ «አመሰግናለሁ» አልኩና ወደ ዳኛዋ ረዳት /መዝጋቢ/ ተጠግቼ የፍርዱን ፎቶ ኮፒ ተቀብዬ እንደተሳፋሪዬ ውልቅ አልኩ። ቢያንስ በግማሽ ሩጫ!::

በትራፊክ ፍርድ ቤት ማሸነፌ ከታክሲው ኮሚሽን ክስ ነፃ ስለሚያደርገኝና ለጠበቃም ሳንቲም ስላላወጣሁ «ሲስቲም ድቦች» «አጨበጨቢ» እንዳሉ ቀሩ:: የሃሳብ ሸክሜ ተራግፎ በምትኩ በደስታና በኩራት ተሞላሁ!

መቀጮ ለመክፈል በኪሴ አጭቄ የነበረውን ብር ይዤ አበሻ ምግብ ቤት ሄድኩና የማቀውንም የማላቀውንም በግብዣ ብቻ ሳይሆን በወሬዬ ወሬም አምበሸበሽኩት!::



t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ 2

በዚች እነስተኛ መጽሐፍ ግማሽ አካል ውስጥ ከተለያዩ ሩሲያውኛ መጻሕፍትና ጋዜጦች የለቀምኳቸውን ቀልዶች ወደ አማርኛ በመመለስ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ::

ሰው ቀልድ ሲነገረው የአቅሙን ነው የሚስቀ:: ነገሩ የተገለጸለትን ያህል!

የራሱን ባህል፣ ወግና ልምዱን፣ አኗኗሩንና ስነልቦናዊ አመለካከቱን አማካይ መለኪያው አድርጎ ያደመጠው ቀልድ ከተለምዶው ውጭ የተለየና ያልጠበቀው መልዕክት ወይም ድምዳሜ ሲኖረው ስሜቱን ይኮረኩረውና ሰው ይስቃል::

እንደየሃገሩ ሁኔታ አማካይ መለኪያው ሊለያይ ስለሚችል አንዱን ህዝብ በሳቅ እንባውን የሚያስጨርሰው ቀልድ ሌላውን ህዝብ ጉንጩን አሸሽቶ ከንፈሩን ላያስገልጠው ይችላል:: ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚከሰተው ቀልዱ የተመረኮዛቸው ሁኔታዎች ለሌላው ህብረተሰብ ባዕድ ስለሚሆኑ ነው::

በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ የቀረቡት የሩሲያ ቀልዶችም በብዛት የሚያጠነጥኑት በህይወታቸው ዙሪያ ስለሆነ ለእኛ ሰው ባዕድ ሆነው ስሜት የማይሰጡ ሊሆኑ የሚችሉት ጥቂት አልነበሩም::

እንደዚህ ዓይነቶቹ ቀልዶች «በቀዶ ጥገና» ለውጥ ካልተደረገላቸው አለዚያም በቅድመ ማብራሪያ ካልታጀቡ በቀር ከሀገር ውስጥ ቀልድነት አልፈው ለውጭ የሚበቁ መሆን አይችሉም::

እኔም በትርጉም ስራዬ ወቅት ይህንኑ ነው ያደረግኩት::

ለእኛ ሀገር አንባቢያን ግልጽ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸውን ቀልዶች እንደወረዱ ተርጉሜ አቅርቤያቸዋለሁ:: ከፊሎቹ በእኛ ሀገር ሁኔታ ካልተቀየሩ ስሜት አልባ ስለሚሆኑ «የቀዶ ጥገና» ለውጥ አድርጌላቸዋለሁ:: ለአንዳንዶቹ የሚያስፈልጋቸውን ማብራሪያ አስከትያለሁ::

ቀልዶቹ የሩሲያውያንን የተለያየ ዘመን ህይወት የሚያመላክቱ፣ በተለያየ ህብረተሰብና በቤተሰብ ግንኙነት ላይ የሚያተኩሩ፣ ልማዳዊ ፀባዮችን ወዘተ የሚዳስሱ እንደመሆናቸው መጠን ሁሉም አንባቢ ቀልዶቹን ይረዳ ዘንድ የተወሰነ ጠቃሚ መረጃ (Information) መስጠቱ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ነው: -

እንዳንዶቹ ቀልዶች በዘመነ ሶቭየት ህብረት ከሃገሪቱ ህዝብ ውስጥ አይሁዳውያን የነበሩት ላይ ምን አይነት አድልዎና ጭቆና ይደረግባቸው እንደነበር ለማሳየት የተፈጠሩ ናቸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

## ነብር ካየሁ ቆየሁ

- አባቴ ሰርከስ አትወስደኝም?
- በፍጹም ልጄ በፍጹም
- የሆኑ ልጆች ሰርከስ ውስጥ ሴትየዋ ራቁቷን በነብር ላይ ስትጋልብ ይታያል ብለው ሲያወሩ ሰምቼ...
- ራቁቷን?! እንግዲውማ እንሂዳ! እኔም ነብር ካየሁ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል ለካ!

*　　　　*　　　　*　　　　*

## እንዴት አታነብም?

- ስማ እንጂ! አሰፋ! ቴሌፎን እንዳስገባሁ አወቅክ አይደል?
- አላወቅኩም
- እንዴት? የስልክ ማውጫ አታነብም ማለት ነው?

*　　　　*　　　　*　　　　*

## ስለአባትህ ስህተት

አስተማሪዋ ለተማሪው፡ -

- ነገ አያትህን ትምህርት ቤት ይዘህ እንድትመጣ!
- አባቴን ማለትዎ ነው?
- አይደለም! አያትህን እንድታመጣ ነው የምፈልገው። ልጃቸው በአንተ የቤት ስራ ደብተር ላይ በየቀኑ ምን አይነት ስህተት እንደሚሰራ ላሳያቸው እፈልጋለሁ!

*　　　　*　　　　*　　　　*

## ቁጠባ

ሰውየው ቢጋብሮሽ አረማመድ ተገርሞ፡ -



t.me/OLDBOOKSPDF

- ለምንድነው እግርህ እስኪሰነጠቅ በረኸሙ የምትራመደው?
- ጫማዬን እየቆጠብኩ ነዋ!

* * * *

## መስላሌ ተርፏል?

ጋብሮሽ ከመስላል ወድቆ ህሊናውን ከሳተ በኋላ ነፍስ እንደዘራ፡ -

- መስላሌ ተርፏል ?

* * * *

## ሽክም ለማቅለል

ጠጪ ሽማግሌው የመጠጥ መደብር /ግሮሰሪ/ ገብተው፡ -

- 8 ፋሽኮ ቪኖ ስጠኝ!
- አባት 8 ቪኖ ለብቻዎ አይከብድዎትም?
- እውነትክን ነው! ግማሹን እዚሁ ቁጭ ብዬ ብጠጣው ይሻላል!

* * * *

## ማሞቂያውን ላጠፋው....

መስኮብ ውስጥ ባልየው መጠጥ ቤት ለመሄድ እንደተነሳ ለሚ፤ -

- ለባብሺ!
- ሚስት በደስታ፡-
- አብረን እንድንሄድ ነው?
- ባል በቁጣ :-
- ኖ..ኖ..ኖ! የቤት ማሞቂያውን ላጠፋው ስለሆነ ......

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## <u>እንዳይሸጥለት</u>

ሁለት ህፃናት የኔ አባት ከአንተ አባት በሃብት ይበልጣል እየተባባሉ ክርክር ላይ ናቸው:: በመጨረሻም ክርክሩ እየጦፈ ሲመጣ አንደኛው: -

- ንገረኝ ካልከኝ የእኔ አባት ድፍን አዲስ አበባን መግዛት ይችላል!
- እኔ ደግሞ አዲስ አበባን እንዳይሸጥለት ለአባቴ እነግረዋለኋ!

*　　　　*　　　　*　　　　*

## <u>ከፊውሱ አድርሰኝ</u>

ፍቅረኛሞች በባቡር እየሄዱ እያለ: - ልጅቷ: -

- ወየው! ትከሻዬን ይጨመድደኛል
- ልጁም ትከሻዋን ሳም ያደርግና: -
- አሁንስ እንዴት ነው?
- በቃ ለቀኛል!
- ከተወሰነ ደቂቃዎች በኋላ :-
- እንገቴን በጣም ነው ያመመኝ
- ልጁም አንገቷን ሳም ያደርግና :-
- አሁንስ እንዴት ነሽ?
- አሁን አያመኝም ትቶኛል
- ከተወሰነ ደቂቃዎች በኋላ
- እረ ምንድነው ነገሩ? አይኔን ይቆጠቁጠኛል!
- ልጁም አይኗን ሳም ያደርግና
- አሁንስ እንዴት ነሽ?
- ወዲያው ነው መቆጥቆጡን የተወኝ!
- ሁኔታቸውን ካጠገባቸው ቁጭ ብሎ ሲያስተውል የነበረ ሰውዬ: -

የእኔ ወንድም! ሰማ የኔ ወንድም! እንደው እባክህ ሄሞሪይድ መፈወስ ትችላለህ?



t.me/OLDBOOKSPDF

## ቆራጥ ውሳኔ

ቢራ መጠጣት የሚወድ ሰውዬ ደርዘን ቢራ አዞ ከቡና ቤቱ ሽንት ቤት ይሄድና: -

- «ኡፍ! አሁንስ በእናንተ መሃል መሆን ሰለቸኝ!» እያለ ቢራውን ሽንት ቤት ውስጥ እንቆረቆረው!

* * * *

## ሲያቀብጠኝ ዕዳ ልግባ!

ሩሲያዊው ቤተሰቡ በሙሉ ከባህር ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ እሱ ግን ከዳር ተቀምጦ መጽሄፍ ያነባል:: ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ድንገት ከመቀመጫው ተፈናጥሮ በመነሳት መጽሄፉን ወርውሮ እየጮኸ: -

ኡኡ እባካችሁ እርዳታ! ሚስቴ ባህር ውስጥ ሰመጠች! እባካችሁ እኔ ዋና አልችልም! እርዱኝ ጎበዝ! ላወጣልኝ ሰው 1000 ዶላር እሰጣለሁ! ሚስቴን አትርፉልኝ! 1000 ዶላር.....

በመስመጥ ላይ ካለችው ሴት 10 ሜትር ርቀት ላይ የነበረ ጎበዝ ዋናተኛ ነበርና ወዲያውኑ በዋና ደርሶ ተሸክሞ ከዳር አወጣትና ወደሰውየው እጁን ዘርግቶ:-

ታዲያ የታለ 1000 ዶላሬ?

ታውቃለህ! ውሃ ውስጥ ሆና ከሩቁ ሳያት ሚስቴ መስላኝ ነበር ለካስ እማቴን ነው ያወጣሃት

እዬ ጉድ! በገዛ እጄ እዳ ልግባ? አሁን ስንት ነው መክፈል ያለብኝ?

* * * *

## ብሄራዊ ደሃው

ሰውየው ከታወቀ ብሄራዊ አርቲስት ጋር እንደተተዋወቀ: -



t.me/OLDBOOKSPDF

- አርቲስት ነህ? ... እኔ የባንክ ሰራተኛ ነኝ:: ላለፉት 10 ዓመታት ቲያትር ቤት ገብቼ ያለማወቄን ሳስበው በጣም ያሳፍረኛል!
- እረ ይሄ የሚያሳፍር ነገር አይደለም! እኔ በህይወት ዘመኔ ባንክ ቤት ገብቼ አላውቅም

* * * *

## የፀሃፊዋ ስም

ባለ ከምፓኒው«አዲሱ ሩሲያዊ» ከእንቅልፉ ሲነቃ ሚስቱ: -

- አንተ ሰው! ካምፓኒህ ውስጥ ይሄን ያህል ስራ በዝቶብሃል ማለት ነው?
- እንዴት ጠየቅሽኝ?
- ሌሊቱን በሙሉ የፀሐፊዋን ስም ስትጠራ ነዋ! የሚነጋው

* * * *

## በጣም ፈጣን

ሌላው ባለግል ካምፓኒ «አዲሱ ሩሲያዊ» ከሚስቱ ጋር እራት በመመገብ ላይ እንዳለ: -

- አዲስ ፀሐፊ ቀጠርክ እንዴ?
- አዎ ቀጠርኩ::
- እና እንዴት ነች?
- ምንም አትል::
- ቆንጆ ነች?
- ያው እንደማንኛውም አይነት ሴት ነች ::
- አለባበሷስ ?
- በጣም ፈጣን!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፈጣኑ «ተማሪ»

ጋብሮቮ ለልጁ: -

- ስማ እንጂ ልጄ! እራት በነፃ የመብላት ዘዴን ደረስኩበት!
- እንዴት? አባባ!
- የማያውቁህ ሬስቶራንት ሊዘጉ አካባቢ ትገባና ቆንጆ የሆነ ተከታይ ምግብ ያለው እራት ታዛለህ! ..ቃኛክህን ደጋግመህ ትጠጣለህ:: ከዛም ቡናህን ትይዝና ሲጋራህን ለኩሰህ ትዝናናለህ:: አስተናጋጆቹ ወደ ቤታቸው መሄድ ሲጀምሩ የመጨረሻው ገንዘብ ሊቀበል ሲመጣ «ለወጣው ጓደኛህ ከፈልኩኝ እኮ!» ትለዋለህ....
- አባባ! መቼም ግሩም ዘዴ ነው! ነገ ብንሞክረውስ?
- ጥሩ አብረን እንሞክራለን

ት - ቀ

በበነጋታው አንድ ሬስቶራንት ይገቡና እንደተባባሉት ያደርጋሉ:: በመጨረሻም ምግብ ቤቱን የሚዘጋው የመጨረሻ አስተናጋጅ ይመጣና: -

ይቅርታ! ሬስቶራንቱ ሊዘጋ ነው:: እኔም መሸብኝ ሂሳብ እንተሳሰብ!

አባት - ሂሳቡንማ ለጓደኛህ ቅድም ሰጠነው እኮ!

ልጅ - በነገራችን ላይ መልሳችን እየጠበቅን ነው!

* * * *

## ድብቅ መልስ

በቢሮው ስራ ላይ የተሰራው ስህተት ብዙ ኪሳራን በማስከተሉ የተናደደው የቢሮው ኃላፊ የበታቹ ጋ ይሄድና: -

- አንተ ነህ ወይስ እኔ ነኝ ደደቡ? ወይስ ሁለታችንም?
- አለቃዬ ባለዎት ልምድና ተሞክሮዎ ቢያንስ ደደብ ሰው መቅጠር ይቻልዎታል?

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የከፋ አይመጣም

አባሷ ቢሮ ሄዳ ፎቶግራፉ በሚያምር ፍሬም ውስጥ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ ያየች ሚስት በመገረምና በመደሰት:-

- ሁልጊዜም ፎቶግራፌን እንደዚህ ከፊት ለፊትህ አርገህ ነው የምትሰራው ማለት ነው?
- አዎ ውዴ! ስራ ላይ ችግርና ጭቅጭቅ ባጋጠመኝ ቁጥር የአንቺን ፎቶግራፍ ስመለከት ሁሉ ነገር ይቀልልኛል...
- (ሚስት በደስታ አፏ ተከፍቶ ፊቷ በርቶ እያዳመጠች ነው)
- ምክንያቱም ምንም አይነት ከዛ የከፋ ችግር እንደሌለ ምስልሽ ስለሚያስታውሰኝ....

*  *  *  *

## ህይወት ሲዘቅጥ

ስነባብተው የተገናኙ ጓደኛሞች ሰላምታ በመለዋወጥ ላይ ናቸው: -

- እሺ ተከልሽ! ኑሮ እንዴት ነው?
- ትዝ ይልሃል? እምና ስትጠይቀኝ «ኑሮ ፋንዶ ነው» ብዬህ አልነበረም? ለካስ ማር ነበር!

*  *  *  *

## እንግሊዝኛን ከ «እንግሊዛዊ»

ሃብታም የራሺያ ባልና ሚስቶች እንግሊዝ ሃገር ለጉብኝት ከሄዱ በኋላ እግረ መንገዳቸውን «የማደጎ ጉዳይ ጽ/ቤት» ይሄዱና: -

እባክዎ! እንግሊዛዊ የሆነ ከ3 ወር ያልበለጠው ህፃን በማደጎነት ፈልገን ነበር

ለምን በማደጎ እንግሊዛዊ ማሳደግ መረጣችሁ?

ሲያድግ እንግሊዝኛ እንዲያስተምረን

*  *  *  *



t.me/OLDBOOKSPDF

## በአንድ እግሬስ

ጋብሮሽ መጠጥ ቤት ይገባና አንድ ብርጭቆ ውስኪ ያዛል:: ባሬስታውም: -

- ባለ 5 ብሩን ነው ባለ 10 ብሩን?
- ልዩነቱ ምንድ ነው?
- ምርጫም ቁጭ ብሎ ለመጠጣት ከሆነ ቦታ ይይዛሉና 10 ብር ነው:: ቆመው ከጠጡ ግን 5 ብር ብቻ ነው
- በአንድ እግር ቆሜ ብጠጣስ?

* * * *

## ዶሮ ብታልም

ጋብሮሽ ቀዶ ጥገና ሊደረግለት ማደንዘዣ ከተሰጠው በኋላ ዶክተሩ: -

- ከ1 ጀምረህ ቁጠር
- 1 2 3 .... 95 96 97 98 99 ብር ....

* * * *

## በጊዜ እንድትከፍል

የግል ክሊኒክ ዶክተሩ ምርመራውን ከጨረሰ በኋላ ለታካሚው: -

- ከአሁን ወዲያ እንዲች ብለህ መጠጥ እንዳትቀምስ!
- ምነው ዶክተር! ይሄን ያህል በሽታዬ ጠንከር ያለ ነው ማለት ነው
- በሽታህ እንኳን ቀላል ነው! የታከምክበትን እንድትከፍል ገንዘብ መቆጠብ ስላለብህ ....

* * * *

## የጦርነት መንስኤ

የ 10 አመቱ ልጅ ለአባቱ: -

- አባቴ! ጦርነት የሚነሳው እንዴት ነው?



t.me/OLDBOOKSPDF

- ልጄ ሆይ! ጦርነት የሚነሳው እንዴት መሰለህ ... እንዘል እንግሊዝና አሜሪካ ቢጣሉ
- እናት አባትየው ሳይጨርስ በመሃል ጣልቃ ገብታ:-
- አሜሪካና እንግሊዝ በፍጹም ሊጣሉ አይችሉም !
- አሁን ይጣላሉ የሚል ከአፌ ወጣኝ? /በመበሳጨት/ እኔ ያልኩት ለምሳሌ ያህል ነው
- የሚገርም እኮ ነው! ይሄን አንድ ፍሬ ልጅ ጭንቅላቱ ውስጥ ዝም ብለህ የማይሆንና መጥፎ ነገር ትከትብታለህ? /በቁጣ /
- አባት እየተንጨረጨረ:-
- ምን አይነት መጥፎ ነገር ጭንቅላቱ ውስጥ ስከት አየሽኝ?
- ይሄ ልጅ አንተ የምትለውን ዝባዝንኬ ሁሉ ከሰማ በምንም አይነት አይምሮው ውስጥ ቁም ነገር ያለው ነገር አይኖርም! /ካለች በኋላ ወደ ስድብ አመራች/
- ሁኔታቸው ያስጨነቀው ህፃን: -
- አመሰግናለሁ እናቴ ... አመሰግናለሁ አባቴ! ጦርነት እንዴት እንደሚጀመር ግልፅ ሆኖልኛል::

* * * *

<u>የተንጓገለውን...</u>

በሆነ የምሽት ግብዣ ላይ ሁለት ዶክተሮች እያወሩ እያለ አንደኛው: -

- ያ ሰውዬ ምንድነው በግልምጫ አይን የሚያይህ?
- ሚስቱ ከፉኛ ጉሮሮዋን ታማ እንደበቷ ሁሉ ተዘግቶ የነበረውን እክሚ በማዳን እንደገና መናገር ስለጀመረች!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምክር

እንዴት ነው ጥሩ ጓደኛ ማግኘት የምችለው?

ውሻ አሳድግ!

*　　　*　　　*　　　*

## ቮቫችካ

የቮቫችካ እናት ለአባትየው: -

- እባክህ! ይሄ የቤት ውስጥ ስራ አላልቅ ብሎኛልና ቮቫችካን ዛሬ እንኳን ከመዋዕለ ህፃናት ሄደህ አምጣው
- እኔ የመዋዕለ ህፃናቱን ህንፃውን እንጂ የሚማርበትን ክፍሉን ስለማላውቀው ራስሽ ሄደሽ አምጭው!
- ይሄ ምንም ምክንያት አይሆንም ክፍሉ ላይ የተለጠፈውን አንብበህ ታገኘዋለህ
- አባት እየተነጫነጨ መዋዕለ ህፃናት ይሄዳል:: 1ኛ ፎቅ ላይ ሲገባ በሩ ላይ «ህፃናት» የሚል ሲያነብ እዚህ መሆን አለበት ይልና አንኳኩቶ ሲከፈትለት: -
- «የእኔን ልጅ ቮቫችካን ልወስድ ነበር የመጣሁት »
- «ወደ ላይ ፎቅ ይውጡ !»
- 2ኛው ፎቅ ሲወጣ «ባለጌ ልጆች» የሚል ተፅፏል አባትየው ይገረምና አንኳኩቶ ሲከፈትለት: -
- « የእኔ ልጅ ቮቫችካ በአጋጣሚ እዚህ ይሆን? »
- «እዚህ የለም ወደ ላይ ፎቅ ይውጡ ! »
- 3ኛ ፎቅ ሲወጣ «አደገኛ ልጆች» የሚል ተለጥፏል:: ያንኳኳና፣
- «ቮቫችካ እዚህ ይሆን ?» /በመሳቀቅ/
- «እዚህ የለም ወደ ላይ ፎቅ ይውጡ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

- 4ኛ ፎቅ ላይ ሲወጣ «ከሰው የተፈጠሩ የሰይጣን ግልገሎች» ይላል:: በሩን እንኳኩቶ ሲከፈትለት: -
- «ሾጣጥካ የሚባል ልጅ እዚህ ይሆን ያለው? »
- «እዚህ የለም ወደ ላይ ፎቅ ይውጡ!»
- 5ኛ ፎቅ ላይ ሲወጣ በሩ ላይ «ሾጣጥካ» የሚል ተጽፏል!

ሾጣጥካ በመላው ሶቭየት ህብረት የሚታወቅ ከሌሎች ህፃናት ለየት ያለ ተማሪ ሲሆን በህዝቡ «የቀልድ አለም» ውስጥ በፈጣን አሳቢነቱ፣ በተንኮሉ፣ በአደገኛነቱ ወዘተ የሚነገርለት ገፀ ባህርይ ነው::

* * * *

## ምስጋና

ሾጣጥካ ከትምህርት ቤት ሲመለስ ለአባቱ: -

- አባቴ ዛሬ ዳይሬክተራችን ወንድምና እህት እንዳለኝ ጠየቀችኝና እኔም የወላጆቼ ብቸኛ ልጅ እንደሆንኩ ነገርኳት
- እና ዳይሬክተሯ ምን አለች?
- እግዚአብሄር ይመስገን!

* * * *

## እኔ ሳልሆን...

የ3ኛ ክፍል ውስጥ በማስተማር ላይ ያለችው አስተማሪ: -

- ተማሪዎች! ከመሃከላችሁ ደደብነቱን የሚያምን ተማሪ ካለ ተነስቶ ይቁም! ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሾጣጥካ ተነስቶ ይቆማል
- ሾጣጥካ ለምንድነው ደደብ ነኝ ብለህ ያሰብከው?
- አይ! እኔ ደደብ ሆኜ ሳይሆን እርስዎ ለብቻዎ ከሚቆሙ ብዬ ነው::

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## አል ራይት!

አስተማሪዋ የተማሪዎችን አይምሮ ለመፈተን የግራ ጆሮ፣ የግራ አይን፣ የግራ እጅና እግር የሌለው ሰው በእንግሊዘኛ ምን ይባላል?

- አንደኛው ተማሪ - ዲዝኤብል
- አስተማሪው - ሌላስ
- ሁለተኛው ተማሪ - ሃፍ ማን
- አስተማሪው - ሌላስ
- ሾጣችካ - አል ራይት!

*     *     *     *

## ስንት መስኮት?...........

የሾጣችካ እናት ለአባቱ: -

- ውዴ! ሾጣችካ የትምህርት ቤት መስኮት ስለሰበረ ዳይሬክተሩ እንደሚፈልግህ ሳልነግርህ ዘነጋሁ
- አሁንስ አላበዙትም እንዴ!? ይሄ ትምህርት ቤት ስንት መስኮት ቢኖረው ነው?

*     *     *     *

## ለዚህ ነዋ!

ለመሞት በማጣጣር ላይ ካለው ሰውዬ ጎን የተቀመጡት የነፍስ አባቱ በወዲያኛው አለም ስለሚጠብቀው አስደሳች ህይወት ደጋግመው እየነገሩት ነው:: ሟቹ ነገሩ አልጥም ስላለው: -

- የነፍስ አባቴ! በሚነግሩኝ ነገር ላይ እንዴት እንደዚህ እርግጠኛ ሊ... ቻሉ? ከሞት በኋላ ስላለው ቆንጆ ህይወት ከሞት ተመልሶ የተናገረ ሰው የለ!
- ይሄውልሃ! ለዚህ ነው እኮ እንድም ሰው የማይመለሰው!



t.me/OLDBOOKSPDF

## አሳምሬ ቀለጥኩኝ

ሁለት ጓደኛሞች ተገናኝተው:-

- ምነው አዘነሃል? ህይወት እያስጨነቀችህ ነው መሰለኝ
- በጣም! አንድ የማውቀው ሰው በፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ፊቴን ለማሳመር 10000 ብር ተበድሮኝ አሁን ምን እንደሚመስል ስለማላውቅ ብሬ ቀልጦ መቅረቱ ነው።

## ይሄውልህ!

ባለተደራራቢ አልጋና የሬስቶራንት ፉርጎ ባለው ባቡር አንድ አይሁድና አንድ ሩሲያዊ አንድ ክፍል ደርሷቸው እየተጓዙ ነው። አይሁዱ የአሳ ጭንቅላት አውጥቶ ሲቆረጣጥም ሩሲያዊው ያየውና በመገረም: -

- የአሳ ጭንቅላት ለምንድነው የምትበላው?
- የኔ ወንድም! የአሳ ጭንቅላት ብዙ ፎስፎረስ ስላለው አይምሮን ለማሳደግ እንዴት ጥሩ መሰለህ!
- ውነትክን ነው? እስቲ ለኔም አካፍለኝ?
- ለምንድነው የማካፍልህ? የቀረውን ለአራቱ አደርገዋለሁ። ከፈለክ አንዱን በ3 ሩብል ልሸጥልህ!
- እንካ 15 ሩብል 5 ስጠኝ!

ሩሲያዊው 5ቱን የአሳ ጭንቅላት ቆረጣጠመና ማወራረጃ ሊገዛ ወደ ሬስቶራንት ሄዶ ሲመለስ:-

- ምን አይነት ደደብ ብሆን ነው? ሬስቶራንት ውስጥ በ1 ሩብል እየተሸጠ ካንተ በ3 ሩብል ሂሳብ የገዛሁት!
- ይሄውልህ! ባንድ ግዜ አይምሮህ ማደግ ጀመረ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ከጀመርክ በኋላ ያው ነው

ከስራ እንደወጡ እንደወትሮአቸው ፋት ሊሉ እየሄዱ ነው: -

- ውስኪ በጣም እየተወደደ አልመጣብህም?
- ነፍስ! ውድ የሆነው የመጀመሪያው ብርጭቆ እንጂ ከዛ በኋላ ያለው ያው እንደድሮው ነው!

* * * *

## የሰው ህይወት ሚስጥር

እግዚአብሔር አህያን ከፈጠረ በኋላ እንዲህ አለው: -

- ከጠዋት እስከማታ ትሰራለህ፣ ሸክምም ይበዛብሃል፣ ምግብህም ሳር ይሆናል በተረፈ ጭንቅላትህ ነፈዝ እንዲሆን 50 ዓመት ትኖራለህ::

አህያም መለሰ:-

- ጌታ ሆይ! 50 ዓመት እንደዚህ በስቃይ ልኖር? እባክህ እምላኬ ከ30 ዓመት በላይስ አታኑረኝ!

እግዚአብሄርም የአህያውን ጥያቄ አፀደቀለት ቀጥሎም ውሻን ፈጠረ እንዲህም አለው:-

- ለሰው ልጅ ጓደኛ ትሆናለህ፣ ከክፉ ትጠብቀዋለህም፣ ምግብህም የሰው ትራፊ ይሆናል፣ በዚህ ሁኔታ 25 ዓመት ትኖራለህ:: ውሻም መለሰ: -

ጌታ ሆይ! የምለምንህ ነገር ቢኖር በዚህ ሁኔታ ከ10 ዓመት በላይ እንዳታኖረኝ ነው:: እግዚአብሄርም የውሻውን ጥያቄ አፀደቀለት ቀጥሎም ዝንጀሮን ፈጠረ:: እንዲህም አለው: -

- ኑሮህ ከዛፍ እዛፍ በመዝለል እንደ ቀውስ ይሆናል፣ ለሰው ልጅ መዝናኛ አስቂኝ ፍጡር ሆነህ 20 ዓመት ትኖራለህ:: ዝንጀሮውም መለሰ: -

ፈጣሪዬ! እንደዚህ ሆኜ 20 ዓመት መኖር ምን ያደርግልኛል:: እባክህ እድሜዬን ከ10 ዓመት አታስበልጠው! እግዚአብሄርም ያለውን አደረገለትና በመጨረሻ ሰውን ፈጠረ: - እንዲህም አለው:-



t.me/OLDBOOKSPDF

- አንተ ሰው ነህ! በምድር ላይ ያለው ነገር ሁሉ የአንተ ነው፣ አለምን በሙሉ መቆጣጠር የሚያስችልህ ህሊና ላንተ ብቻ ሰጥቻለሁ፣ የ20 ዓመት እድሜም ይኖርሃል:: ሰውም መለሰ: -

ጌታ ሆይ! 20 ዓመትማ ያንሰኛል:: ባይሆን አህያው የመለሰውን 20 ዓመት፣ የውሻውን 15 ዓመት፣ የዝንጀሮውን 10 ዓመት ለእኔ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ!

- እግዚአብሄርም የሰውን ጥያቄ ስለፈቀደ ሰው ለ20 ዓመት እንደ ሰው ይኖራል:: ከዛም እንደ አህያው ከጠዋት እስከ ማታ በስራ ይፈጋል:: በመቀጠልም ልጆች ይወልድና እንደ ውሻ ልጆቹን ከክፉ ነገር እየጠበቀ፣ እየደከመና ከቤተሰቡ የተረፈችውን እየተመገበ ይኖራል:: በመጨረሻም እንደ ዝንጀሮው የልጅ ልጆቹ መዝናኛና መጫወቻ ይሆንና ህይወቱ ያከትማል::

*　　　*　　　*　　　*

## ኮታ

የአልኮል ሱሰኛው ሊታከም ዶክተር ጋር ገብቷል: -

- እንዴት ነው? ብዙ መጠጥ ትወስዳለህ?
- አይ! ብዙም አይባልም እንደው ብቻ በየቀኑ 2 ሊትር አረቄ ብቻ ነው የምጠጣው
- እረግ እረግ! ... ለመሆኑ መጠጥ ከጀመርክ ቆይተሃል?
- ሩቅም ባይባል ... ከልጅነት ጀምሮ ነው
- በስመአብ! ... ታዲያ አንተን ምን ማከም ያስፈልጋል:: ያለን አማራጭ ቃል_መገባት ብቻ ነው!
- መልካም ዶክተር! እርስዎ እንዳሉ ..
- በቀን ሁለት ብርጭቆ ብቻ ለመጠጣት ሞክራ!
- ሁለት ብርጭቆ ብቻ? መልካም ይሁን! እስማማለሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተወሰነ ቀን በኋላ ሰውየው በእግሩ መቆም እስኪያቅተው ጠጥቶ ሲንገዳገድ ዶክተሩ ያገኘዋል፡-

- ምነው ወንድሜ! ከሁለት ብርጭቆ በላይ እንዳትጠጣ ተስማምተን አልነበረም?
- እረ ባክህ! /በማሽሟጠጥ/ በቃ እኔ ካላንተ በስተቀር ሌላ ዶክተር ጋ አልታከምም ማለት ነው? /የዶክተሮች ብዛት ሲባዛ በ2 ብርጭቆ/

* * * *

## በእግራቸው መሀል

የግብረገብ አስተማሪው በማስተማር ላይ እያሉ ተማሪው ለጥያቄ እጁን አወጣና ሲፈቀድለት፡-

- መምህር ሆይ! በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ሰማህ ወይ ተማሪ! የአባትህ የጫማ ቁጥር ስንት ነው?
- 41
- የእናትህሳ
- 38
- ልዩነታቸው ታየህ!? በእግራቸው መካከል መሆኑን!

* * * *

## አንባራዊነት

አስቂኝ ቀልዶች በብዛት በሚነገርባት የዩክሬይኗ አዴሳ ከተማ በሚጓዘው ባቡር ላይ ሁለት አይሁዳውያን ተሳፍረው እየሄዱ ነው፡፡

- አየኸው ያንን ሰውዬ? አልበርት አንስታይን እኮ ነው!
- እና ምን ይጠበስ?
- እንዴት ምን ይጠበስ? እሱ እኮ ነው የአንጻራዊነትን ንድፈ ሃሳብ ያገኘው!
- የምን ንድፈ ሃሳብ ነው የምታወራው?



t.me/OLDBOOKSPDF

- ይሄውልህ ሳስረዳህ! በራስ ቅል ላይ 3 ፀጉር ብዙ ነው ወይስ ትንሽ?
- ትንሽ!
- በሾርባ ውስጥ ያለ 3 ፀጉርስ?
- እሱማ ብዙ ነው!
- ይውልህ! አንፃራዊነት የሚባለው ይሄ ነው
- አይይ! አሁን ይሄንንም አስቴን ቀልድ አርጎ ነው? አይሳ ይዞት የሚሄደው ...

• • • •

**ሲስቀብህ ታየኝ**

- ሕፃኑ ልጅ ከአያቱ ጋር እየተጫወተ ነው: -
- አያቴ! ትንሽ ልጅ ነበርክ?
- ነበርኩ ልጅ ነበርኩ!
- እቤት! መቼም ህፃናት በሙሉ በመሳጣህና በፂምህ ሲስቀብህ ታየኝ!

• • • •

**የፎቶዋ ክብደት...**

- ለምን ጓደኛህን ተውካት?
- ባክህ እንዴት እንደወፈረች ብታይ! አብሮ መታየቱም አሳፈረኝ
- እንዴ! ይህን ያህል ወፍራለች ማለት ነው?
- እጅግ በጣም! ፎቶግራፏ ብቻ 2 ኪሎ ይመዝናል።

• • • •

**3 ነገሮች: -**

- የአይንን ትኩረት የሚስቡ 3 ነገሮች:-
- የእሳት ነበልባል አንቦጋቦግ፣ የውሃ ፏፏቴ አወራረድና የደሞዝ አከፋፈል!



t.me/OLDBOOKSPDF

## እሷ ትቅር እንጂ

- እማቼን ከእውቶቡስ ተራ ብትቀበልልኝ 5 ብር እሰጥሃለሁ
- ድንገት ከቀሩስ
- እጥፍ እሰጥሃለሁ!

* * * *

## ለእንደሱ አይነት

ሁለት የልጃገረድ ጓደኛሞች ውይይት ይዘዋል: -

- ስሚ እስቲ! ከበደን ላግባው? ወይስ ይቅርብኝ:: ምን ይመስልሻል?
- ምን ጥያቄ አለው? አግቢው እንጂ! የተማረ ምሁር ነው! በዚህ ላይ መኪና አለው! ቤት አለው! ...
- ምናልባት ንብረቱ ከጓደኛቹ ተበድሮ የገዛውና ያልተከፈለ ዕዳ ቢሆንስ?
- አንቺ ደግሞ ዝም ብለሽ ነው! አሁን ለእንደሱ አይነት እምነተ ቢስ፣ ራሱን ብቻ ወዳድ ስግብግብ ሰው ያበደ ነው ገንዘብ የሚያበድረው?

* * * *

## ልዩነት

- በፑቲንና በቡሽ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ፑቲን ፕሬዚዳንት ለመሆን ጦርነት ጀመረ:: ቡሽ ግን ጦርነት ለመጀመር ፕሬዚዳት ሆነ::

* * * *

## ጥሮ-ግሮ ከላይ

ሁለት የልጅነት ጓደኛሞች ከብዙ ዓመታት መጠፋፋት በኋላ በአጋጣሚ ተገናኝተው ስለ ራሳቸው ትዝታና አሁን ስለደረሱበት ማውራቱን ጨርሰው ስለ አብሮ አደጎቻቸው መጠያየቅ ጀምረዋል:-



t.me/OLDBOOKSPDF

| | |
|---|---|
| መከተ | «ስማ እንጂ ያ ሳህሉስ እንዴት ነው? ትገናኛላችሁ?» |
| አጥላው | «አዎ አንዳንዴ እገኘዋለሁ:: ጤንነቱም በጣም ደህና ነው» |
| መከተ | «ህይወቱስ እንዴት ነው ከምን ደረሰ?» |
| አጥላው | «ሳህሉ ማለት ብርቱ ሰራተኛ ነው ከስር የጀመረ ጥሮ ግሮ ዛሬ ከላይ ደርሷል» |
| መከተ | «ጎሽ ያርግለት! ሚሊየነር ሆኗል በለኛ!» |
| አጥላው | «እንደሱ ሳይሆን ከሊስትሮነት የጀመረ አሁን ፀጉር አስተካካይነት ደርሷል ማለቴ ነው» |

* * * *

## ደርሶ መልስ

ሰውየው ጓደኛው አዲስ ከተከራየው ቤት በእንግድነት አርፎአል፡-

- አካባቢያችሁ መጠጥ ቤት ይኖራል?
- እንዴታ!
- ምን ያህል ያስኬዳል?
- እንደ ሰውየው ይለያያል:: እኔ የሚፈጅብኝ ስሄድ 3 ደቂቃ ስመለስ 30 ደቂቃ ነው::

* * * *

## ካርታ መጫወት አያውቁም

ሁለት ባለትዳር የሆኑ ሴቶች ጓደኝነት እንደጀመሩ፡-

- እንዴት ነው በባልሽ ደስተኛ ነሽ?
- ታውቂያለሽ! የኔ ባል ካርታ መጫወት እንኳን አያውቅም
- ካርታ መጫወት የማያውቅ ከሆነማ ታድለሽ! የኔው እኮ ካርታውን ካገኘ እቤቱም አይገባ!



t.me/OLDBOOKSPDF

- የኔም እኮ እንደዛው ነው!! በዛ ላይ ካርታ መጫወት አያውቅም ሁሌም ገንዘቡን ይበላል ማለቴ ነው ::

* * * * 

## አጉል ግምት

የባልና ሚስት ፍቺ የሚታይበት ፍርድ ላይ:-

ዳኛ - ይህንን ሰው ለምን ልታገቢው ቻልሽ?

ሴትየዋ - ለምን እንዳገባሁት ነው የጠየቁኝ... /ትንሽ ካሰቡች በኋላ/ ይሄ ሰው በየቀኑ የሚጠጣበት ገንዘብ ካለው ብዙ ብር የሚያገኝ ደሞዝተኛ መሆን አለበት ብዬ በመገመት ነው::

* * * *

## መፍትሄ

ፀጉር አስተካካዩ የቆየ ደምበኛውን እያስተካከለ ነው: -

- አሁንስ ፀጉርህ በጣም እየሳሳ መጣ:: እንደኛውን በራ ሆነህ ሳትቀር መርገፉን ለማቆም ያሰብከው ነገር የለም?
- ያሰብኩት ነገር አለ ሚስቴን ልፈታ ነው! /በቁጭት ከንፈሩን ነከሰ/

* * * *

## የአመት አቆጣጠር

- ዛሬ እንዴት ነው? ዘንጠሃል!
- የጋብቻዬን 50ኛ አመት የወርቅ ኢዮቤልዩ እያከበርኩ ነው
- ተው እንጂ! ገና ካገባህ 5 ዓመትህ አይደለም እንዴ?
- የኔ ወንድም? ለኔ እያንዳንዱ ዓመት እንዴት እንደ 10 ዓመት እንደረዘመብኝ እኔ ነኝ የማውቀው::

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ውርስ

ህፃናት ስለራሳቸው ያላቸውን ስውቀት እየተሻሙ በማውራት ላይ ናቸው

- የኔ አይን ልክ እንደ አባቴ ነው ...ጆሮዬ የእናቴ ነው
- የኔ ፀጉሬ የእናቴ ነው..... አፍንጫዬ ያባቴ ነው
- የኔ ጥርሴ የአያቴ ነው .....አገጬ የእናቴ ነው
- የኔ ሱሪዬ የወንድሜ ነው ....

* * * *

## ቁጭት

25ኛ የጋብቻ ኢዮቤልዩ በማክበር ላይ ያሉ ባልና ተጋብዞ የመጣ ጓደኛው ጨዋታ ይዘዋል፡፡

| | |
|---|---|
| ባል | «ስማ እስቲ! ሰው የገደለ ሰው ምን ያህል ጊዜ ነው የሚታሰረው?» |
| እንግዳ | «25 ዓመት» |
| ባል | «ሲቆጭ! ይሄኔ ነፃ ሰው የምሆነውን? /በልቡ/ |

* * * *

## ታይታኒክ

ሰውየው መደብር ገብቶ ለልጁ ልደት ስጦታ የሚሆን ትልቅ የአሻንጉሊት መርከብ በ100 ብር ይገዛና ውሃ መታጠቢያ ቤት ገንዳ ውስጥ ሞልቶ ከልጁ ጋር ሆነው ቢሞክሩት የአሻንጉሊት መርከቡ ትንሽ ይንሳፈፍና ይሰምጣል፡፡ እንደገና ደጋግመው ቢሞክሩትም ያው ሆነ፡፡

አባትየው በጣም ይናደድና ስልክ አንስቶ ....

- የአሻንጉሊት መደብር ነው?
- አዎን ጌታዬ የአሻንጉሊት መደብር ነው !
- ስማ አሁን ከ1 ሰዓት በፊት ድፍን 100 ብር ኖት ከፍዬ «የመርከብ አሻንጉሊት» የገዛሁት ሰውዬ ነኝ!



t.me/OLDBOOKSPDF

- አስታውሳለሁ ጌታዬ! ምን ልርዳዎት?
- የሚሰምጥ መርከብ ነው በ100 ብር የምትሸጡልኝ? /በንዴት/
- ልክ ነው ጌታዬ ይሰምጣል! የመረጡት መርከብ እኮ «የታይታኒክ» ሞዴል ነው፡፡

* * * *

## ኮንዶም ገዥው

አንድ ጨዋነት የሚነበብበት ሰውዬ ፋርማሲ ይገባና ተራውን ጠብቆ ወደ ሻጯ ከተጠጋ በኋላ በጆሮዋ አንሾካሾከ ፡-

ሴትየዋ ለካ ሞጥሟጣ ኖራ እየጮኸች

«ምን ምን ዓይነት የመከላከያ መሳሪያ አላችሁ?» የምትለኝ የምፈራ መስሎህ ነው?

የኔ ወንድም ይሄ መከላከያ ሚኒስቴር አይደለም ፋርማሲ ነው!»

* * * *

## ልዩነት

አበሻውና ፈረንሳዊው ጭውውት ይዘዋል

| | | |
|---|---|---|
| አበሻ | - | በእናንተ ሃገር ጥሩ ሴት የምትባለው ምን ዓይነት ነች |
| ፈረንሳዊ | - | ባልና አንድ ፍቅረኛ ብቻ ያላት |
| አበሻ | - | እንደዚች አይነቷማ በኛ ሃገር «ሰራቂ» ነው የምትባለው |
| ፈረንሳዊ | - | እኛ ሃገር «ሰራቂ» የምንለው ባልና ብዙ ፍቅረኛ ያላትን ነው |
| አበሻ | - | ባልና ብዙ ፍቅረኛ ያላትማ በኛ ሃገር «ዘመ-ተኛ» ነው የምትባለው |
| ፈረንሳዊ | - | እኛ ሃገር «ዘመ-ተኛ» የምንላት ባልም ፍቅረኛም የሌላትን ነው |
| አበሻ | - | ባልም ፍቅረኛም የሌላት በኛ ሃገር «ብቸኛ» ነው የምትባለው |
| ፈረንሳዊ | - | እኛ ሃገር «ብቸኛ» የምንላት ባል ብቻ ያላትን ነው |

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ትዝታ

ሁለት በፍቅር ኖረው ያረጁ ባልና ሚስቶች የድሮ ትዝታቸውን ሲያወሩ ቆይተው በጣም ስለተመሰጡ ድሮ በልጅነት የሚያሳልፉትን ጊዜ በተግባር ለመድገም እንደዚህ ይስማማሉ ፡-

ሽማግሌው - «ቀጠሯችንን ከግማሽ ሰዓት በኋላ ልጅ ሆነን እምንቀጣጠርባት መናፈሻ ውስጥ ካለችው ቦታችንጋ እናድርግና ልክ ድሮ ስንገናኝ የምናሳልፈውን ጊዜ ብናሳልፍስ?»

አሮጊቷ - «በጣም ጥሩ ደስ ይለኛል!»

ሽማግሌው - ከዘራቸውን ይዘው ደንቀፍ ደንቀፍ እያሉ ከቤታቸው በመውጣት እያዘገሙ ከቀጠሮው ቦታ ደርሰው «የልጃገረድ ጓደኛቸውን» መጠበቅ ጀመሩ፡፡ ሴትየዋ ግን ከቀጠሮው ሰዓት አረፈዱ፡፡

ሽማግሌው - «እች የኔ ሚስት እኮ የምትገርም ነች! ከ60 ዓመት በኋላ እንኳን ከቀጠሮ ሰዓታችን አርፍዳ እየመጣች ታስጠብቀኝ እንደነበር አልረሳችም» ብለው እየተገረሙ መጠበቅ ቀጠሉ፡፡ ብርዱ እየጨመረ መጣ፡፡ ሴትየዋ ግን አይመጡም፡፡ ሽማግሌው በብርድ መርገፍገፋቸው ቢያናድዳቸውም «ትንሽ ልጠብቅ» እያሉ የቀጠሮው ጊዜያቸው 1 ሰዓት አለፈው፡፡ በዚህ ግዜ ሽማግሌው ተስፋ ቆርጠውና በጣም ተበሳጭተው በብርድ እየተንቀጠቀጡ ወደ ቤት ተመልሰው ንዴት በተሞላበት ኃይለ ቃል፡-

«ስሚ አንቺ አሮጊት! ምን ነኩቶሽ ነው? እንደዚህ ብርድ ላይ የምታቆሚኝ! ካልፈለግሽ በፊቱኑ አልፈልግም አትይኝም ነበር?» ቢሏቸው አሮጊቷ ልክ እንደ ልጅነታቸው እየተቅለሰለሱ፡-

«የኔ ፍቅር! ... መምጣት ሳልፈልግ ቀርቼ ሳይሆን እማዬ! ከዚህ ቤት ትወጭና እግርሽን ነው የምሰብረው ስላለችኝ ነው ....

*  *  *  *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የህይወት ታሪክ

ሬስቶራንት ውስጥ ተመጋቢው የዶሮ አሮስቶ እየበላ ነው::

ተመጋቢ «ስማ እስቲ አስተናጋጅ! ለመሆኑ የዚህ ዶሮ እድሜው ምን ያህል ነበረ?»

አስተናጋጅ «ጌታዬ! በኛ ሬስቶራንት ከዶሮ አሮስቶ ጋር ድንች ጥብስ፣ ሰላጣና ቲማቲም እንጂ የህይወት ታሪኩን አብረን አናቀርብም»

* * * *

## ለጥያቄው መልስ

እናት ልጇን ምሳ እያበላችው ሳለ ልጅ ጥያቄ መጠየቅ ጀመረ :-

ልጅ - «ለምንድነው የአባቴ ፀጉር ትንሽ የሆነው?»

እናት - «ጭንቅላቱን ብዙ ስለሚያስብበትና ስለሚሰራበት!»

ልጅ - «ያንቺ ፀጉር ለምን እንዲህ በዛ?»

እናት - «እርፊህ ምሳህን ብላ! /በቁጣ/»

* * * *

## ራስ ላይ ምስክር

ሰውየው ከፊልም ቤት እየወጣ:-

ሰው ሁሉ ይሄን ፊልም «የደደቦች ፊልም ነው» «የደደቦች ፊልም ነው» ይላል እኔ ግን ወድጄዋለሁ!

* * * *

## በአንድ ቀን አናገባም

ጓደኞቿ - ስሚ እንጂ! የዛሬ ዓመት ያስተዋወቅሽን ፍቅረኛሽ እንዴት ነው? መቼ ነው የምትጋቡት?

ልጅቷ - በቅርብ ይመስለኛል፣ ግን በአንድ ቀን አናገባም::



t.me/OLDBOOKSPDF

## የፍቅር አቅጣጫ

ያ ሁልግዜ አበባ የሚያመጣልሽ ፍቅረኛሽ ምነው ጠፋ?
አበባ ሻጯን አገባ::

* * * *

## የወርቅ ጥርስ

ሴትየዋ መሃል መርካቶ የቆመው ፖሊስ ጋር እየሮጠች ሄዳ:-

ሴትየዋ - «ፖሊስ! ፖሊስ! አንተ እዚህ ቆመህ 10 ሜትር ርቀት ላይ የወርቅ ሰዓቴን ነጠቁኝ..

ፖሊስ - «ታዲያ ምን አፍሽን ዘጋው? ኡኡ ብለሽ ብትጮሂ እደርስልሽ አልነበር!»

ሴትየዋ - «ምነው ፖሊስ! ይሄ ሁሉ የወርቅ ጥርሴ አይታይህም ማለት ነው?»

* * * *

## ስውር አጥር

ኢንስፔክተሩ የወህኒ ቤት የግምገማ ጉብኝቱን ከፈፀመ በኋላ ወደ ወህኒ አዛዡ ቢሮ ገብቶ:-

ኢንስፔክተር - «የዚህ ወህኒ ቤት አጥር በጣም የላላ በመሆኑ እስረኞች ያመልጣሉ የሚል ስጋት የለባችሁም?»

የወህኒ አዛዥ - «በፍጹም! በፍጹም የለብንም!» በእርግጠኝነት

ኢንስፔክተር - «እንዴት እንደዚህ እርግጠኛ ልትሆን ቻልክ?»

የወህኒ አዛዥ - «ጠዋት ጠዋት ስራዬን የምጀምረው እስረኞቹን በሙሉ ሰብስቤ በሃገሪቱ ውስጥ የኑሮ ውድነት እንዴት እየናረ እንደሄደ ገለፃ በማድረግ ስለሆነ.....

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ውበት እንደ ጤዛ

ትልቅ መደብር ውስጥ በገንዘብ ተቀባይነት የምትሰራ ሴትና እህቷ ስለ ትዳር መያዝ በመወያየት ላይ ናቸው:-

እህትየዋ - «ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው እንደዛ ወንድ ላይ ስትከሪ የኖርሽ ልጅ «ባል የማገኝ አይመስለኝም» ብለሽ ተስፋ የቆረጥሽው?»

ገንዘብ ተቀባይዋ - ወንዶች ሂሳብ ሲከፍሉ መልሳቸውን እየረሱ መሄድ ካቆሙ ጀምሮ::

* * * *

## ሳይናገሩ መናገር

የመሃል ዳኛ:- «ጎረቤትህን «ደደብ» ብለህ መሳደብህን ፍርድ ቤቱ አምኖ ተቀብሎታልና 5000 ብር ተቀጥቼሃለሁ! ከዚህ በተረፈ ለፍርድ ቤቱ የምትናገረው ነገር ካለህ መናገር ተፈቅዶልሃል!?»

ተከሳሽ:- «ለክቡርነትዎ የምናገረውስ ነገር ነበረኝ በዚህ ዓይነት አቀጣጥ ግን ዋጋውን ስለማልችለው አለመናገሬን መርጫለሁ!»

* * * *

## በፖለቲካ መርካት

የስነ አዕምሮው ሃኪምና ታካሚው በምርመራ ክፍል : -

ሃኪም:- «መቼ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ በፖለቲካ መርካት የጀመረህ?»

* * * *

## የወንድ ትምክህተኛው

ሰውየው ሊታከም ዶክተር ጋር ሄዷል::

ታካሚ- «አይምሮዬ ላይ የሆነ ችግር ተፈጥሮብኛል»

ዶክተር- «ለምን እንደዚህ ልትል ቻልክ?»

ታካሚ- «ሚስቴ የምትናገረው የምሁር አነጋገር ሆኖ ይሰማኝ ጀምሯል»



t.me/OLDBOOKSPDF

## የዶክተር ጽሑፍ

ሁለት የሴት ጓደኞሞች ለብርቱ ጉዳይ ተቀጣጥረው ተገናኝተዋል፡፡

አንደኛዋ - «የተከበረ ዶክተር ባሏ ለስራ ጉዳይ ከፍለሃገር ሄዶ በለነበተ ቀጥር ጎረቤቷ ከሆነው ፋርማሲስት ጋር በፍቅር ትንጎዳጎዳለች» እያለ ሰፈሩ በሙሉ እያማሽ ነውና ይሄን ነገር ባልሽ ሰምቶ ችግር ከመፈጠሩ በፊት ብታቆሚው አይሻልም?»

የዶክተር ሚስት - «ቲ ቲ ቲ ቲ ... ይሄንንማ መቼ ባሌ ከስራ መጥቶልኝ በነገርኩት ቲ ቲ ቲ ቲ... እኔ ፋርማሲስቱ ቤት የምሄደው ባሌ የሚልክልኝን ደብዳቤ እንዲያነብልኝ ነው»

*   *   *   *

## ገንዘብ ሳትቀበል

- ዶክተር! ምን ሆነህ ነው እንደዚህ ያዘንከው?
- አከመው የነበረው ሰው ስለሞተ ነው ያዘንኩት
- በቃ ምን ታደርገዋለህ? ለሌላ ጊዜ ግን ይሄ ትምህርት ሆኖህ በቅድሚያ ገንዘብ ሳትቀበል ማንንም አታክም፡፡

*   *   *   *

## ውሻ በቀደደው.....

ዶክተር «ስትተኚ መስኮትሽን ከፈት አድርገሽ ተኚ ያልኩሽን አደረግሽ?»

ህመምተኛ «እዎ ዶክተር እንዳሉኝ አድርጌአለሁ»

ዶክተር «እንደዛ የሚያስቃይሽ አስም ወዲያው ጠፋ! አይደል?» /በእርግጠኝነት/

ህመምተኛ «አስሜ እንኳን አልጠፋም፡፡ የጠፋው የወርቅ ሃብሌ ... ቦርሳዬ ቴሌቪዥኔ...

*   *   *   *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ያንተ ሚስት ትሻላለች

### ሁለት ፓይለቶች

አንደኛው - «በል! አንተ አብርር እኔ እስቲ አዲሷን አስተናጋጅ ላዋራት» በማለት ወዳስተናጋጆች ክፍል ሄደ:: ከ30 ደቂቃ በኋላ ይመለስና:-

«ዝም ብላ ነገር ነች የኔ ሚስት ትሻላለች»

በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ፓይለት «እስቲ እኔም ልያት!» ብሉ ይሄድና በ3 ደቂቃ ውስጥ ወዲያው ተመልሶ:-

ሁለተኛው - «ልክ ነህ! ያንተ ሚስት ትሻላለች::»

* * * *

## ዶክተር አይደለሁም

- ዶክተር! ሚስትዎን ይደበድባሉ የሚባለው ወሬ እውነት ነው?
- ውሸት ነው! ዶክተር አይደለሁም! /በቁጣ/

* * * *

## የሆነ ጸጉር አስተካካይ

ተዋንያኑ መድረክ ላይ እየተጫወተ እያለ ያደረገው አርቲፊሻል ጺም ስለተላቀቀበት ፈጣን ዘዴ ፈጠረና አብራው መድረክ ላይ ለምትጫወተው ተዋንያን «የኔ ቆንጆ! የሆነ ሰው ኮቴ ይሰማኛል» ብሎ ከመድረክ ጀርባ ወጥቶ ጺሙን ሊያስተካክል ቢሞክር የሚሆን ስላልሆነ ገንጥሎ ጥሎት ወደ መድረክ ተመለሰ::

አብራው የምትሰራው «የኔ ጌታ ማን ነበር የመጣው?» ብትለው:-

«አይ ዝም ብሎ ነገር ነው የሆነ ፀጉር አስተካካይ» ብሎ ወደ ጥና ቲያትር ...

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## መስቀለኛ ጥያቄ

ከሚስትህና ከፊልም የሴት አክተሮች ምረጥ ብትባል ከፊልም የሴት አክተሮች ውስጥ ማንን ትመርጣለህ?

* * * *

## አዲስ አስተዳደር

ሰውየው አዘውትሮ ከሚመገብበት ሆቴል ምሳውን ሊበላ ሲገባ «ሆቴላችን በአዲስ አስተዳደር ሊያገለግላችሁ ተዘጋጅቷል» የሚል ተለጥፎ ስለየ:-

ደምበኛ - ባለቤቷ ሆቴሉን ሸጠች እንዴ? /ወደተለጠፈው እያሳየ/

አስተናጋጅ - አልሸጠችም:: ባል አገባ!

* * * *

## አንቺስ መቼ ነው

አንቺ! ለምንድነው ቀብር ላይ እንጂ ሰርግ ላይ የማትታይው?

ቀብር ላይ «አንቺስ መቼ ነው?.. .. .. .. ...» የሚለኝ የለማ

* * * *

## የጋብቻ በዓል አከባበር

ሚስት - የጋብቻችንን 10ኛ ዓመት እንዴት ነው የምናከብረው?

ባል - በ 1 ደቂቃ የህሊና ፀሎት

* * * *

## ክብደት የመቀነስ ዘዴ

- «እንዴት እንዲህ ሸንቀጥሽ ባክሽ?»
- «ባሌ ሌላ ሴት ጋር እየሄደ ሲያበግነኝ ሲያበግነኝ...»
- «ውንትሽን ነው? በቃ ተፋታችሁ ማለት ነው?»
- «አልተፋታንም:: ገና የምቀንሰው አንድ 3 ኪሎ ይቀረኛል»



t.me/OLDBOOKSPDF

## ማን መስሎሽ ነው

ነፍሷ ልትወጣ ያለች ሴት ለሚሊየነር ባሏ በደከመ ድምፅ ሃጢያቷን በመናዘዝ ላይ ነች:-

ሚስት - «አንተ ለኔ ሁሌም ጥሩ ነበርክ እኔ ግን አንተ እንደሆንክልኝ ልሆን ቀርቶ ጭራሽ ብዙ በደልኩህ:: አንተን በመስለ ባሌ ላይ ከቀኝም ከግራም ከሌሎች እገናኝ ነበር...»

ባል - «በቃ! መፀፀት አቁሚ:: ማን መስሎሽ ነው ቡናሽ ውስጥ መርዝ የጨመረልሽ?»

• • • •

## ድርሻህን ውሰድ

ሁለት ጓደኛሞች ገና እንደተገናኙ:-

«ሰማ! ኒኒ መንታ እንደወለደች ሰማህ?»

«ሂድ» ወደዛ! /ማመን አቅቶት/

«የኔ ወንድም አንተው ሂድ! እኔማ ሄጄ የድርሻ ልጄን ወስጃለሁ::»

• • • •

## አጋላጭ መብራት

- «ትላንትና የሆነውን መገመት አትችይም ፊልም ቤት ገብተን በማየት ላይ እያለን»
- «የፊልሙ ክር ተበጥሶ 30 ደቂቃ ሙሉ ጭለማ ሆነ::»
- «ታየኝ እኮ! ሁሉም ሰው በፍርሃት ሲደነግጥ»
- «ታዲያሳ! ድንገት ሳይታሰብ መብራቱ ስለበራ ...»

• • • •



t.me/OLDBOOKSPDF

## ባል ተብዬው

ማሚስት - «እራት አሁን እየደረሰ ነው፤ ቀጥዬ ልጆቼን አጣጥቤ አስተኛ ለሁ፤ የሽሚዝ ቁልፎችህን ተካክዬ እተኩስልሆና ቤቱን ካስተካከልኩ በኋላ ፊልም ቤት መሄድ እንችላለን!»

ባል - «በጣም ጥሩ! ግን ቲኬቶቹን መቼ ሄደሽ ልትገኚ ነው?»

* * * *

## ጥያቄና መልስ

ትንሹ ልጅ አባቱን በጥያቄ፡-

ልጅ - «አባቴ! ገንዘብ ማለት ምን ማለት ነው?»

አባት - «ልጄ! ገንዘብ ማለት መኪና! ውስኪ! ቆንጆ ቤት! ማለት ነው»

ልጅ - «ገንዘብ ከሌለስ?»

አባት - «እውቶቡስ፤ ሻይ፤ ያንተ እናት ....»

* * * *

## ውል

ሰውዬው ሸራተን ሆቴል አጠገብ «የበቆሎ እሸት ጥብስ» በመሸጥ ላይ እንዳለ ድሮ በብድር ያሰለቸው ጓደኛው ያገኘውና ፡-

ጓደኛው «እስቲ እባክህ አንድ 20 ብር አበድረኝ»

በቆሎ ሻጭ «ባበድርህ ደስ ይለኝ ነበር ነገር ግን እዚህ ቦታ ላይ እኔና ሼህ አላሙዲ ቢዝነስ ስናካሂድ እኔም ለሰው ገንዘብ እንዳላበድርና እንዳልሰጥ፤ እሳቸውም የበቆሎ እሸት ጠብሰው እንዳይሸጡ ውል በመፈራረም ነውና ልረዳህ ባለመቻሌ ይቅርታ!»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

### ተሳስተሃል እየወጣ ነው

ዋሽንግተን ዲሲ አበሻ ሬስቶራንት ውስጥ ነው። ሰውየው ጠረጴዛ ይዞ ውስኪ ያዛል አስተናጋጇ አቀረበችለት። 2ኛ ውስኪ አዘዘ ጠጣ 3ኛ ... 4ኛ... 7ኛ ውስኪውን ሲያዝ አፉ እስርስር ብሏል። አሜሪካን አገር ለሰከረ ሰው መጠጥ መቅዳት በህግ የተከለከለ ስለሆነ፡-

| | |
|---|---|
| አስተናጋጇ | «ይቅርታ የሚበቃህን ያህል ጠጥተሃልና መታዘዝ አልችልም» |
| ጠጪ | «በፍ..ጹ..ም ማ..ስ..ተዋል እችላለሁ» እየተኮላተፈ |
| አስተናጋጇ | «እሺ አሁን ምን እያየህ ነው?»/ ወደ ጓሮው በር እያሳየች/ |
| ጠጪ | «በተ..ከፈተው በር ሁ..ለት ያበጠ አ..ይን ያለው ድ..መት እየገባ ነው» |
| አስተናጋጅ | «የኔ ወንድም ተሳስተሃል እየወጣ ነው» |

* * * *

### እሃ! ለዚህ ነዋ!

ሰውየው አሳ እያጠመደ እያለ፡-

| | |
|---|---|
| ፖሊስ | «የኔ ወንድም እዚህ ቦታ ላይ አሳ ማጥመድ ክልክል ነው!» |
| አሳ አጥማጅ | «እሃ! ለዚህ ነዋ 3 ሰዓት ሙሉ አንድ እንኳን አሳ ያላጠመድኩት» |

* * * *

### ከዚያ ወዲህ

እጮኛሞች ውይይት ላይ ናቸው፡ -

- «የኔ ህይወት! ከመጋባታችን በፊት ስላወጣኋቸው ሴቶች ልናዘዝልሽ እፈልጋለሁ።»
- «በቃ አትጨነቅ የኔ ቆንጆ እሱን እኮ የዛሬ ሁለት ሳምንት ነግረኸኛል»
- «እሱማ ቆየ አይደለም እንዴ! ከዛ ወዲህ ያለውን ማለቴ ነው።»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## በየቀኑ....

በቅርብ የተጋቡ ባልና ሚስቶች ናቸው። ሚስት አራት አቅርባለች ባልየው ሹካውን ሳህኑ ላይ እያቃጨለ በመተከዝ ላይ ነው፡-

ሚስት - «የኔ ቆንጆ ትወደኛለህ?»

ባል - «እሱንማ ከጋብቻችን በፊት ነገርኩሽ አይደል እንዴ? ይልቁንስ አሁን በየቀኑ የምትቀቅይውን መኮረኒ እወደው አልወደው እንደሆን ብትጠይቂኝ ነበር ጥሩ።»

* * * *

## ስልክ ማውጫ ቢኖረኝማ..

ገበያው የደራ ትልቅ መደብር ውስጥ ይገባና

- «የሽንት ቤት ወረቀት ምን ያህል ነው የምትሸጡት?»
- «5 ብር»
- «ረከስ የሚልበትን ቦታ ልትነግረኝ ትችላለህ?»
- «ስልክ ማውጫ ላይ ይፈልጉ ጌታዬ ስራ እያስፈቱኝ ነው! /በንዴት/»
- «ስልክ ማውጫ ቢኖረኝ ኖሮማ ምን የሽንት ቤት ወረቀት አስፈለገኝ! /በማጉረምረም/»

* * *

## ለቀብር ፈቃድ

ስራ አስኪያጅ - «ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ አመንኩኝ»

ሰራተኛ - «ምን አዲስ ነገር ተገኘ?»

ስራ አስኪያጅ - «ከትላንት ወዲያ ሞታ ለቀብር ፈቃድ የወሰድክባት አክስትህ በስልክ እየፈለገችህ ነው።»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ቬንትሌተሩ ሲያዘንብብን.........

ቴክሳስ ውስጥ ከሚገኝ የገጠር ቢራ ቤት በመዝናናት ላይ ያለ «ካው ቦይ» ሆዱን ይቆራርጠውና ሽንት ቤት ቢሄድ ተይዟል:: ነገርየው ጊዜ የማይሰጥ ነበርና ከመጠበቅ ብሎ 2ኛ ፎቅ ሲሮጥ ይሄድና በሩን ሲከፍተው ወና ቤት ነው:: ከወናው ክፍል መሃል ላይ ቀዳዳ ነገር ሲያገኝ ጊዜም ምርጫም ስላልነበረው ይፀዳዳበትና ሰው ሳያገኘው ፈጠን ብሎ ወደ ቢራው ቤት ሲወርድ፤ ሰው ሁሉ ጠረጴዛ ስር ተደብቋል:: ካው ቦዩም ወዲያው ሽታጡን መዘዝ ያደርግና:-

ካውቦይ - «ምን ሆናችሁ ነው ጠረጴዛ ስር የገባችሁት?»

ጠጪዎች - «ቬንትሌተሩ ጭቃ ሽንት እንደ ጉድ ሲያዘንብብን የት ነበርክ /ባንድ ላይ/»

* * * *

## እንኳንስ ፒያኖ

ልጁ መናፈሻ ውስጥ ባለ አግዳሚ ወንበር ላይ የተቀመጠች ልጅ አጠገብ ሄዶ ይቀመጥና ወሬ ለመጀመር ሲጨነቅ ሲጠብብ ከቆየ በኋላ:-

ልጅ - «እንትናዬ .. ..ፒያኖ መጫወት ትችያለሽ? » /በፍርሃት ድምፅ/

ልጅቷ - ከእግር እስከ ራስ በግምገማ እይታ ካየችው በኋላ በማሽሟጠጥ አነጋገር -

«ለመሆኑ ሙዚቃስ የምትሰማ ሰው ነህ?»

* * * *

## ሌላ ማግባቴ አይቀርምና.......

ሰውየው ወጣትና ቆንጆ የሆነች ሚስቱ ብትሞትበትም ቀብር ላይ ሃዘኑን ውጦ ጠንክሮ እንዳለ ነው:: የሚስቱ የድሮ ጓደኛዋ የነበረው ግን እዬዬውን ያስነካው ጀመር:: ምን ዓይነት ጥሩ ሰው እንደነበረችና መሞቷ እንደሚያንገበግብ እየተናገረ እንባውን እየዘራ አብሬ ጉድጓድ ካልገባሁ ብሎ አስቸገረ::

ይሄንን ሁኔታውን የተመለከተው ባል ጠጋ ይለውና:-



t.me/OLDBOOKSPDF

- በቃህ በቃህ! የኔ ወንድም ራስህን አትጉዳ:: እኔም በቅርብ ሌላ ሚስት ማግባቴ አይቀርም ተፅናና!

• • • •

## ሃያ ዘጠኝ

ደምበኛው ከሆነበት መደብር ሄዶ

- እስቲ በሚስቴ ልደት ኬክ ላይ የሚሆኑ ሻማዎች አምጣ
- ስንት ልስጥህ?
- ያው እንደተለመደው ነዋ! 29

• • • •

## ሂልተን ሆቴል

ባልና ሚስት በቅናት እየተጨቃጨቁ ነው:-

«እመነኝ ነው እኮ የምልህ! ያንተ ጓደኛ እዚህ ቤት እግሩ ረግጦ አያቅም!»

«እንደዛ ከሆነ ትልቁን ፎጣችንን አንቺ በሌለሽበት ሰርቆናል ማለት ነው!»

«የምን ፎጣ ነው የምታወራው፣ ለሰርጋችን በስጦታ ያገኘነውን?»

«እሱን ሳይሆን «ሂልተን ሆቴል» የሚለውን»

• • • •

## የቀለበት ሚስጥር

ሁለት የወንድና የሴት ሾርከዱዎች ጨዋታ ይዘዋል

| | | |
|---|---|---|
| ወንድየው | - | «ሴቶች ጣታቸው ላይ ማንኛውንም አይነት ቀለበት ሲያደርጉ ምን ማለት ነው?» |
| ሴቷ | - | «ምንም ማለት አይደለም!» |
| ወንድየው | - | «የቃል ኪዳን ቀለበት ሲያስሩስ?» |
| ሴቷ | - | «ባለ ትዳር ነን ማለታቸው ነው» |



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድየው - «ሁለቱንም ሲያስሩስ?»
ሴቷ - «ትዳራችን ምንም ማለት አይደለም ማለታቸው ነው።»

* * * *

## ራሷን የማትጠግብ

እሁን ስለኔ ማውራት እናቁምና ስላንተ እናውራ:: ለምንድነው ልትወደኝ የቻልከው?

* * * *

## አስተሚጨት

- ሲገርም! ቁርጥ 3ኛ ባሌን ነው የምትመስለው
- እስካሁን ስንት ብታገቢ ነው?
- ሁለት!

* * * *

## ምናለ ተኩሰሽ ብትለብሽ

ሰካራሙ ወደ ቤቱ በማዝገም ላይ እያለ 2 የመንገድ ላይ ሴተኛ አዳሪዎች እርቃነ ስጋቸውን ቆመው ያገኛቸዋል

ሰካራም - «ለምንድነው ራቁትሽን መንገድ ላይ የቆምሽው?»
ወጣቷ - «ጋሽዬ! ልብሴ ስስ ስለሆነ እያስታውቅም እንጂ ለብሻለሁ እኮ»
ሰካራም - «አንቺስ? /ጠና ያለችውን/»
ጠና ያለችው - «የኔ ወንድም ስስ ልብስ አርገናል አልንህ እኮ!»
ሰካራም - «እሱስ ይሁን አንቺስ እንደ ጓደኛሽ ምናለ ተኩሰሽ ብትለብሺ»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የመጀመሪያውና የመጨረሻው.....

ሰውየው መጠጥ ቤት ይገባና

- «በዘጠኝ መለኪያ ውስኪ ታመጪልኝ?»
- «እሺ ጌታዬ! /ብላ አስተናጋጇ መሄድ ስትጀምር/»
- «የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን አታምጭው ይቅርብኝ»
- «ለምን? /በመገረም/»
- «የመጀመሪዋው እሺ ብሎ በጉሮሮዬ አይወርድልኝም! የመጨረሻው ደግሞ የመሃከለኞቹን ይዞብኝ እየሄደ ስለተቸገርኩ ....»

* * * *

## ካገዙና ነበር.....

ሁለት ጓደኛሞች መንገድ ላይ ቆመው በማውራት ላይ እያሉ አንድ መርሰዲስ የያዘ ግለሰብ ቀይ መብራት ይዞት ከፊት ለፊታቸው ያቆማል።

አበበ «ከበ! ይሄን ሰውዬ አታቀውም?» መርሰዲስ ወደያዘው እየጠቆመ

ከበደ «አላውቀውም»

አበበ «ከ 2 ዓመት በፊት «የዕዳት ሰራተኛ» የነበረና ዛሬ ግን ሚሊየነር የሆን ሰው ነው።»

ከበደ «ካገዙና! ነበር የሚያፀዳው?»

* * * *

## ትለምጅዋለሽ

ወደ 40 ዓመት ዕድሜ የተጠጋች ሴት «የእጅ መዳፍ እያነበበ የወደፊት እጣ ፈንታን ከሚናገር «ሳይኪክ» ጋር ሄዳ መዳፏን ካስነበበች በኋላ፦

ሳይኪክ «40 ዓመት እስኪሞላሽ በገንዘብ እጦት ታለቅሺያለሽ»

ሴትየዋ «ከዛስ?» /ሰፍ ብላ! /

ሳይኪክ «ከዛ በኋላ ግን ስቃዩን ትለምጂዋለሽ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

## ይሄ ባለቤቴ አይደለም

ሬስቶራንት ውስጥ ነው፡-

አስተናጋጅ - «ምነው ባለቤትዎ ጠረጴዛ ስር ገቡ?»
ተስተናጋጇ - «ይሄ ባለቤቴ አይደለም ባለቤቴ አሁን ገብቶ እዛ በሩጋ የቆመው ነው»

* * * *

## የመጨረሻው ጥርስ

ትምህርት ቤት ውስጥ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች ጥያቄና መልስ ላይ ናቸው፡-

አስተማሪ «በመጨረሻ ላይ የሚበቅለው የሰው ጥርስ የትኛው ነው?»
ተማሪ «የወርቅ ጥርስ!»

* * * *

## የውበት ሳሎን ማስታወቂያ

ፓሪስ ውስጥ ከሚገኝ አንድ የቁንጅና ሳሎን መግቢያ ላይ እንደዚህ ተፅፏል፡-

«ፓስፖርትዎ ላይ ያለውን የልደት ቀንዎን ለመለወጥ እርስዎ ካወቁበት ሌላውን ነገር ለኛ ይተዉት!»

* * * *

## ሲያስፕኝ

ስላምታ ሰጥቷት ስሟን ጠይቆ ገና እንደተዋወቁ ፀጥታ ሰፈነ

- እና ምነው ዝም አልክ አውራ እንጂ
- እንዲሁ ነኝ ሲያስፕኝ ዝም ያደርገኛል

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

ደደብ ዳኛ

- ለምን ሚሊዮን ብር ሰረቅክ?
- እርቦኝ ! /በማሽሟጠጥ/

• • • •

## የቀብር ፈቃድ

በስንት መከራ ስራ ያገኘና ከልቡ ሲለፋ ከርሞ የ3 ወር የሙከራ ጊዜውን ሊጨርስ 1 ቀን ሲቀረው ስራ አስኪያጅ ቢሮው ያስጠራውና:-

- ለመደብንህ ስራ ብቁ ሆነህ ስላላገኘንህ ከነገ ጀምሮ ስራ እንዳትመጣ
- እንደዛማ ከሆነ ከዛሬ ጀምረህ እስናብተኝ ቀብር መሄድ አለብኝ
- የምን ቀብር? /በመገረም/
- ያንተ ቀብር! /በንዴት/

• • • •

## የጥያቄው መልስ

- ለምንድነው ሴቶች ሲባሉ አይምሯቸውን በእውቀት ከማዳበር ይልቅ ውጪአቸውን ለማሳመርና ለመኳኳል ብዙ የሚጨነቁት?
- በዚች አለም ላይ እውር ወንዶች ከደንቆሮ ወንዶች በብዙ ሚሊዮን የሚያንሱ ስለሆነ

• • • •

## አስደንግጠኸው ነበር

ግጥሚያው እንዳለቀ ተዘርሮ የተሸነፈው ቦክሰኛና አሰልጣኙ መልበሻ ክፍል ውስጥ እያወሩ ነው: -

አሰልጣኝ - «3ኛው ዙር ላይ ባላጋራህን በጣም አስደንግጠኸው ነበር»
ቦክሰኛ - በመገረም «ውነትክን ነው? ምኑ ላይ ስመታው?»



t.me/OLDBOOKSPDF

አሰልጣኝ - «ህይወትህ በእጁ ላይ ያለፈች መስሎት»

* * * *

**በመጀመሪያ....**

የስነ አዕምሮ ዶክተሩና ታካሚው ህመምተኛ በምርመራ ክፍል ውስጥ ናቸው:-

ዶክተር «ያለብህን ችግር በትክክል ተረድተን አስፈላጊውን ህክምና እንድናደርግልህ፣ የግድ ታ አንተነትህን ማወቅ ያስፈልገኛልና አንተው ራስህ ስለራስህ ምንም ሳትደብቅ ማንነትህን ከመጀመሪያው ጀምረህ ንገረኝ»

ታካሚው ጥቂት ካሰበ በኋላ:-

«እንግዲህ እንደዚህ ነው:: በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠርኩ.. ..

* * * *

**አሁን ይሞክራ!**

ማደንዘዣ በሌለው የገጠር የጥርስ ህክምና ክሊኒክ ውስጥ ተራውን በመጠበቅ ላይ ያለ ታካሚ በፍርሃት እየተንቆራጠጠ ነው:: ዶክተሩ የእይታ ምርመራ አድርጎ ሁለት ጥርሶችህ መነቀል አለባቸው ካለው በኋላማ ጭራሽ በፍርሃት ይንቀጠቀጥ ጀመር::

ሁኔታውን ያስተዋለው የጥርስ ሃኪም «እንኳ እስቲ ለድፍረት እንዲሆንህ እችን ጠጣ» ብሎ ካቲካላ በብርጭቆ ሞልቶ ሰጠው::

ታካሚው ካቲካላውን በአንድ ትንፋሽ እንደውሃ ግጥም አደረገው:: ከ5 ደቂቃ በኋላ:-

ዶክተሩ «እሺ እንዴት ነው ድፍረት አገኘህ?»

ታካሚው «እንዴታ! .. አሁን እናቱ የወለደችው ጥርሴን ለማውለቅ ይሞክር!»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## 31ኛው ተረኛ

ጋዜጣ አዟሪው «30 ሰዎች በድምፅ የለሽ ጥይት ተረሸኑ!» ጋዜጣ ፈላጊ ጋዜጣ! ... 30 ሰዎች በድምፅ የለሽ ጥይት ተረሸኑ!.. .. ጋዜጣ!» እያለ ይጮሃል።

መንገደኛው ወሬው አንጉቶት ገዛውና ቢያገላብጥ ቢያገላብጥ ጋዜጣ አዟሪው የሚያወራውን እልቂት ሊያገኘው ስላልቻለ የቴጋ ነው ሊለው መለስ ሲል ጋዜጣ አዟሪው «31 ሰዎች በድምፅ የለሽ ጥይት ተረሸኑ.. .. ጋዜጣ ፈላጊ ጋዜጣ» ሲል ሰማው!

* * * *

## ጆሮዎቼን ያዝ

ልጅ፣ በቅርብ የተዋወቀችው ጓደኛዋ ሁኔታ ገርሟት: -
ለምንድነው በተሳሳምን ቁጥር «ጆሮዎቼን ያዥ» እያልክ የምታስቸግረኝ?
ምክንያቱም ከዚህ በፊት በእንደዛ አይነት ሁኔታ ላይ እያለሁ ነው ቤሳ ቤስቲን ሳይቀር ኪሴ የተራገፈው። /በቁጭት/

* * * *

## ምዕራፍ 17

የእሑቱን መንፈሳዊ ትምህርት እንዳጠቃለሉ ሰባኪው መነኩሴ «በሚቀጥለው እሁድ የምንማረው ስለ ውሸት ይሆናል ስለዚህ ሁላችሁም የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 17ን አንብባችሁ እንድትመጡ» ብለው አሳሰቡ።

በሳምንቱ እሁድ እለት «ስንቶቻችሁ አንብቡ ያልኳችሁን አነበባችሁ?» ብለው ሲጠይቁ ከምዕመናን ውስጥ የተወሰኑት እጃቸውን አወጡ።

መነኩሴው «እንግዲህ ምዕመናን የዛሬ ትምህርታችን ከዚሁ ነው የሚጀምረው የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 17» ካሉ በኋላ እጃቸውን አውጥተው የነበሩትን ሰዎች በአይናቸው እየገረመሙ ቆዩና «የለውም!» አሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## እሷም እንዳንቺ

የካምፓኒው ስራ አስኪያጅ ቢሮ ገብታ:-

- «ለምንድነው ሚስትህ በመጣች ቁጥር የምትገላምጠኝ?»
- «ድሮ እሷም እንዳንቺው ፀሃፊዬ ስለነበረች::»

* * * *

## «የመኖሪያ» ለውጥ

ሰውዬው ለሚስቱ ወሬ ይዞ መጥቶ

ባል - «ከወህኒ ቤቱ ፊት ለፊት የሚኖረውን አብርሃምን ታውቂዋለሽ?»

ሚስት - «አውቀዋለሁ! ምነው ጠየከኝ?»

ባል - «ከትላንትና ጀምሮ ከቤቱ ፊት ለፊት መኖር መጀመሩን ጓደኞቼ ነገሩኝ::»

* * * *

## የመንግስት ጋዜጦች

ደርቤ - «የመንግስት ጋዜጦችን ታነባለህ?»

አየለ - «በደንብ ነዋ! ያለዚያማ እንዴት አድርጌ ጥሩ ህይወት እንዳለኝ ማወቅ እችላለሁ?»

* * * *

## <u>ይሄም መኖር ይባላል!</u>

የጎጆ መዝጊያ ተንኳኳ:-

- «እስቻለው እዚህ ነው የሚኖረው?»
- «የለም? እዚህ አይኖርም»

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ እንደገና ተንኳኳ

- «እስቻለው እዚህ ነው የሚኖረው?»
- «የለም! እዚህ አይኖርም»



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደገና ከተወሰነ ሰዓት በኋላ ተንኳኳ

- «አስቻለው የምትባለው አንተ ነህ?»
- «አዎ አስቻለው ማለት እኔ ነኝ»
- «ታዲያ አስቻለው እዚህ አይኖርም እያልክ የምታመላልሰን ለምንድነው?»
- «አሁን ይሄ መኖር ይባላል? /የሰበሰውንና የጎጃውን ጓዳ እያሳየ/»

* * * *

## ከተሰመደ አሰልቺ ምክር ለማምለጥ

እናት ለልጇ

- «ሚሚዬ! ከሴቶችም ውስጥ አጥሚት መጠጣት የማይወዱ እንዳሉ ታውቂያለሽ?»
- «አዎ እማዬ! የወላጆቻቸውን ምክር አልሰማ ብለው ጋጠወጥ በመሆን የዱቄት ፋብሪካ ሰራተኞች ሆነው የቀሩ ....»

* * * *

## አዲሱ ገበያተኛ

ማሙሽ ከአባቱ ቀድሞ ጫማ ሱቅ ይገባና: -

- ባለሱቅ! የጫማ ክር አለህ?
- ምን አይነት?
- የማራና የቀኝ!

* * * *

## ፒያኖ መጫወትስ

በቤት ሰራተኛነት ለመቀጠር ከተነጋገረች በኋላ:-



t.me/OLDBOOKSPDF

- እሜቴ እከፍልሻለሁ ባሉኝ ደሞዝ ተስማምቻለሁ፣ ስራዎቹንም በደንብ አድርጌ መስራቱን አውቅበታለሁ:: ግን ከወዲሁ የምነግርዎት ነገር ወለል ማጽዳትና መስታወት መወልወል ስለማልወድ እጆቿ እንዳይሉኝ ነው::
- ፒያኖ መጫወትስ ትችያለሽ?
- አልችልም:: ደሞ እሱን ለምን ጠየቁኝ? /በመገረም/
- አይ! እኔ ወለልና መስታወት ሳፀዳ አንቺ ፒያኖ እንድትመቺልኝ!

*　　*　　*　　*

## <u>የበቀል ጅማሬ</u>

ስራ አስኪያጁ ለሰራተኛው:-

- በግል ባጋጠመህ ችግር ቅሬታህን ልትነግረኝ እስከመጣህበት ቀን ድረስ ያን ያህል ብዙ ገንዘብ እንከፍልህ እንደነበር አላስተዋልኩም!

*　　*　　*　　*

## ቢሆንም አመስግናት

- እክስቴ! ስላደረግሽልኝ ስጦታ አመሰግናለሁ!::
- እረ ግዴለም ማሙሽዬ! ይሄ -እኮ ስጦታም አይባል ዝም ብሎ ነገር ነው::
- እማዬም ልክ እንዳንቺው ነው ያለችኝ ... ቢሆንም ግን አመስግናት ስላለችኝ ነው!

*　　*　　*　　*

## የገንዘብ ጣስ

ሞተው በሰማይ ቤት የተገናኙት አሜሪካዊ፣ ፈረንሳዊና ሩሲያዊ ስለ አመጣጣቸው በማውራት ላይ ናቸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

አሜሪካዊው: -

የእኔ አመጣጥ የሚያስገርም ነው በ«ፎርድ» መኪናዬ ከተወሰነው ፍጥነት በላይ በሰዓት 100 ኪ.ሜ እየነዳሁ እያለ በኋላ ማሳያ መስታወቱ ፖሊስ ሲከተለኝ አየሁና ፍጥነቱን ጨምሬ 150 ገባሁ አሁንም ላመልጠው ስላልቻልኩ 200 ገብቼ እየረገጥኩ በዛው እዚህ መጣሁ::

ፈረንሳዊው:-

የእኔ እንኳ ቀለል ይላል«ፔጆዬን» ይዤ ስሄድ የሆነች ቆንጆ ልጅ የስፖርት መኪና ይዛ ቀድማኝ በጎኔ ስታልፍ ተከተልኳትና ደርሼባት ከጎኗ እየበረርኩ እጄን በማወዛወዝ ሰላም አልኳት:: እሷ ደግሞ የምትገርም ነች ፍጥነቷን ሳትቀንስ ሁለት እጇን አውጥታ እያወዛወዘች የሰላምታ አፀፋዋን መለሰች:: እኔም ውበቷና ድርጊቷ ስለማረከኝና ስላስደነቀኝ መሪ ለቅቄ እንደሷ ሁለት እጆቼን በማወዛወዝ ሰላም እያልኳት በዛው እዚህ መጣሁ::

ሩሲያዊው:-

የኔስ ሰው ሬም አይመች! ከሚስቴ ጋር «ላዳ» መኪና ለመግዛት ወሰንና ገንዘብ ማጠራቀም ጀመርን:: አንድ ዓመት አጠራቀምን:: 2 ዓመት .... 3 ዓመት አጠራቀምን .... በዛው እዚህ መጣሁ::

* • • •

## ሆዷን የማታስቀድም ቂል!

ድመቱ አይጧን አፈፍ ካረጋት በኋላ: -

- አይጠ! መኖር ትፈልጊያለሽ?
- ከማን ጋር?
- አይዋት እቺ'ኮ ሆዷን የማታስቀድም ቂል::

• • • •



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጠጄ

ለማኑ መንገድ ዳር ተቀምጦ፡ -

- ደጎቼ! እባካችሁ ረሀቤን ማስታገሻ ወርውሩልኝ? ስለ መድኃኒዓለም ወገኖቼ! አትለፉኝ ! እያለ ይማፀናል፡፡

አንድ መንገደኛ ጠጋ ይለውና

- አጭበርባሪ ! ይሄኔ ለጠጅ መጠጫ ነው የምትለምነው!
- እረ በፍጹም ጌታዬ! ለሆዴ ነው፣ የጠጀማ ምልቶልኛል!

* * * *

## መብረቋ ሹፌር

ጓደኛሞች ስለሚስቶቻቸው በማውራት ላይ ናቸው፡-

- የኔ ሚስት መኪና ስትነዳ እንደ መብረቅ ነው!
- በጣም ትፈጥናለች?
- አይ...! ብዙውን ጊዜ የምትጋጨው ከዛፍ ጋር ነው፡፡

* * * *

## የመልስ ምት

የሚስትየዋን 50ኛ ዓመት የልደት በዓል እቤታቸው ሆነው እያከበሩ ነው

ባልየው ያደረገው ንግግር ፡-

.... በ20 ዓመትሽ ድንቡሼ ነበርሽ፣ በ30 ዓመትሽ ሻምፒዮን ሆንሽ፣ በ40 ዓመትሽ ወደ ኮኛክነት ተቀየርሽ ይኸው ዛሬ በ50ኛ ዓመትሽ ኮምጣጤ ሆንሽ!

የሚስት የመልስ ንግግር

እዎ! በ20 ዓመቴ ድንቡሼ ነበርኩ፡፡ የቀጠፍከኝ ግን አንተ አልነበርክም! አዎ! በ30 ዓመቴ ሻምፒዮን ነበርኩ፡፡ ላንተ የደረሰህ ግን ከተረፈው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሻምፒዮኝ ውስጥ ድንገት ካፍህ የገባው ብቻ ነው! እም በ40 ዓመቴ ኮፍኝ ነበርኩ፡፡ የጠጣኸው ግን ከሶስት ሰው ጋር ተካፍለህ ነው! እም! ዛሬ በ50ኛ አመቴ ከምጣጤ ሆኛለሁ፡፡ ከምጣጤዬን መቋቋሚያ ግን የለህም! ....

* * * *

## ሶስተኛው ልጄስ

የመኪናውን ቁልፍ በእጁ እያሽከረከረ ጎረቤቱ ጋ ሄዶ፡-

- ሁለቱ ልጆችሽ መኪናዬ ጎማ ስር ነው ያሉት!
- የፈጠረኝ አምላክ! 3ኛው ልጄስ የት ነው ያለው?

* * * *

## ተወዳዳሪም የለው!

- ኢልሳ! ባልሽ እንዴት ነው ቆንጆ ነው?
- ተወዳዳሪም የለው!.... ከእናቱ የወሰደው ተአምረኛ ሰማያዊ አይን ሲኖረው እንደ አባቱ ቆንጆ የእሽቅድምድም መኪና ይመስላል!

* * * *

## ከየት ነው የምትደውለው

መሴህ ዱብያ ጋዜጣ ከፍቶ ሲያነብ የራሱን መርዶ ተረዳና ሳይሞት ሞተ በመባሉ ተገርሞ ለጓደኛው ስልክ ይደውላል፡ -

- ፒየር! የዛሬውን ጋዜጣ አነበብክ?
- አንብቤዋለሁ ምስኪን ጓዴ! ለባለቤትህም የማጽናኛ ቴሌግራም ልኬላታለሁ፡፡ .... በነገራችን ላይ ከየት ነው እየደወልክ ያለኸው?

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## በስልጣን መባለግ

ሩሲያ ውስጥ አንድ ትራፊክ ፖሊስ ብቻ ባላት አነስተኛ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ዶክተርና ሚስቱ በመኪናቸው እየሄዱ ነው፡-

ሚስት - «እረ ቀስ በል! ..... ብቻ ያ እርጉም ትራፊክ ፖሊስ እንዳያየን እግዚአብሄር ይሁነን!»

ዶክተር - «አታስቢ ውዴ! ዛሬ ጠዋት የሚያደነዝዝ መርፌ ሰጥቼው የእልጋ እረፍት እንዲያደርግ ፍቃድ ጽፌለታለሁ።»

* * * *

## እንዳታሳዩብኝ

ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ፡-

- «ሚስቱ ስለጠፋችብኝ እርዳታ እንድታደርጉልኝ ብዬ ነው የመጣሁት»
- «እዚህ ቅጽ ላይ ስምና አድራሻዎን ይሙሉና ከታች ምን እንደምትመስል በዝርዝር ይፃፉ»
- «እሺ! እጽፋለሁ ጌታዬ! አደራ የምላችሁ ግን ካገኛችኋት የፃፍኩትን እንዳታሳዩብኝ ነው።»

* * * *

## አንድ አይነት ሞዴል

ዶክተሩ የተበላሸ መኪናውን ጋራዥ ወስዶ ካስጠገነ በኋላ ሂሳቡ ቀረበለት፡ -

ዶክተር - ለአንድ ሰዓት ስራ ይሄን ሁሉ ገንዘብ እንዴት ክፈል ትሉኛላችሁ?

የጋራዡ ባለቤት - ሰሙ ዶክተር! እናንተ ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የምትጠግኑት አንድ አይነት ሞዴል ነው። እኛ ግን በየጊዜው ሞዴል በተቀያየረ ቁጥር እንደገና ለማጥናት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንገደዳለን ለዚህም ጊዜና ገንዘባችንን እናጠፋለን። ስለዚህ ከፍያችን ......

* * * *

## ሱሰኛው

አንድ የማውቀው ሰው፤ ልጅ ሆኖ መርፌ ይፈራ ነበር። ነገር ግን ሳይታከት የመርፌ ፍርሃቱን ለማስወገድ ከመታገሉ የተነሳ ዛሬ በየቀኑ መርፌ ሳይወጋ መዋል አይችልም።

* * * *

## የሩሲያውያን የፊልም አመዳደብ

«ጥሩ ፊልም አለ፣ መጥፎ ፊልም አለ፣ የህንድም ፊልም አለ።»

* * * *

## ድንጋይን በድንጋይ

- ያንቺን ፍቅር ለማግኘት ያልሞከርኩት ነገር የለም። ይሄን ድንጋይ ልብሽን በምን ስርስሬ መግባት እንደምችል ግራ ገብቶኛል?
- በከበረ የዕንቁ ድንጋይ

* * * *

## «የዕረፍት ቀን»

- ስማ አስቲ! በእረፍት ጊዜህ ምንድነው የምትሰራው?
- ምንም ነገር አልሰራም
- እንዴት ምንም ነገር አትሰራም?
- የሆነ ነገር ከሰራሁማ ምኑን የእረፍት ቀኔ ሆነ?

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

አሽከርካሪው ከተወሰነው ፍጥነት በላይ ሲነዳ ፖሊስ ተከታትሎ አስቆመውና

- ለምን እንዳቆምኩህ ግልጽ ይመስለኛል!
- ጌታዬ! በሰዓት 100 ኪ.ሜ የነዳሁ መስሎ ታይቶህ ይሆናል እንጂ 80 ኪሎ ሜትርም አይሞላ፣ እረ እንዳውም 60 ኪሎ ሜትር አካባቢ ነው፤ ውነቱን ንገረኝ ካልክ ግን ስነዳ የነበረው 40 ኪሎ ሜትር........
- ስማ ሰውዬ! ከኋላህ ያቆምኩትን የፖሊስ መኪና ገጭተህ ሌላ ዕዳ ውስጥ መግባትህ ነው!

* * * *

## ሹፌርም ነው!

ሴትየዋ ከቤት ሰራተኛዋ ጋር የከረረ ፀብ ውስጥ ትገባና እየገፈታተረቻት፡ -

- አሁኑኑ እቃሽን ሰብስበሽ ከዚህ ቤት ውጭልኝ! የማትችል አስጠሊታ!
- ከኔና ከርስዎ ማን አስጠሊታ እንደሆነ ይታያ!
- እንዴት ባክሽ?
- በቁንጅና እንደምበልጥዎ ማንም ይመሰክራል! እረ ምን በቁንጅና ብቻ በሌላም ቢሆን ተመስክሮልኛል
- አሃ! ለዚህ ነዋ ጥጋብሽ ከልክ ያለፈው፡፡ ማነው መስካሪው ባሌ ነው?
- እረ እኔ እንደርስዎ ሰው ላይ ምን አድርሶኝ ሹፌርም ነው ...

* * * *

## የምን ድኖ መውጣት

ሆስፒታል ውስጥ ህክምና ላይ እያለ

- ዶክተር! ቢራ በጣም አሰኝቶኛልና ብጠጣ ምን ይለኛል?
- ጭንቅላት የለህም እንዴ? የምን ቢራ ነው የምታወራው?
- እሺ! ድኜ ስወጣስ መጠጣት እችላለሁ?
- ጭንቅላት የለህም እንዴ? የምን ድኖ መውጣት ነው የምታወራው?



t.me/OLDBOOKSPDF

## ደረሰኝ

ሰውየው መኪናውን መንገድ ዳር ካቆመ በኋላ ሌቦች እንዳይነካኩበት «መኪናዬ የቤንዚን ጋን ባዶ ነው፣ ሬድዮ ካሴት የለውም፣ ሞተሩም ተሰርቋል» የሚል ጽሁፍ ጽፎ መስታወቱ ላይ ለጥፎ ይሄዳል::

በነጋታው መኪናው ጋር ሲሄድ እሱ ከፃፈበትና ከለጠፈበት ጎን: -

«እንደዛ ከሆነ ጎማዎቹ አያስፈልጉህም ማለት ነው? የሚል ተለጥፏል»

* * * *

## ደህና ሲሆን

በዶክተር ምርመራ ክፍል ውስጥ: -

ዶክተር - በትክክል የህመምህን መንስኤ ለማግኘት ቸግሮኛል:: እንደምገምተው ግን ችግሩ ከስካር ጋር የተያያዘ ይመስለኛል::

ታካሚ - እኔም እንደዛ ነው የመሰለኝ:: እንግዲያውም ሌላ ጊዜ ደህና ሲሆኑ ተመልሼ እመጣለሁ::

* * * *

## አፐታይዘር

ሬስቶራንት ውስጥ: -

- የሚበላ ምን ምን አላችሁ?
- ቀይ ወጥ ብቻ ነው ያለን
- ታዲያ ይሄን ሁሉ የምግብ ዝርዝር ሜኑ ላይ ለምን ፃፋችሁ?
- የተመጋቢዎችን አፐታይት ለመክፈት!

* * * *

## ከማለቃቸው በፊት

ማስታወቂያ! በእኛ ካምፓኒ አይሮፕላኖች ይብረሩ! የቀሩን ትንሽ ስለሆኑ ተሽቀዳድመው ቲኬት ይግዙ!



t.me/OLDBOOKSPDF

## ታማኝ ጓደኛ

አባባል፡ - «እውነተኛ የወንድ ጓደኛ በችግር ጊዜ፣ የሴት ጓደኛ ደግሞ በመዝናኛ ቦታ ይለያል»

* * * *

## ብዙ የምትናገረው

- ማሙሽ! እናትህን ነው አባትህን በብዛት የምትሰማው?

- እናቴን!
- ለምን?
- ብዙ የምትናገረው እሷ ናታ!

* * * *

## ቴሌግራም አታድርግ

በስራ ምክንያት ራቅ ወዳለ ቦታ የሚሄድ ባል ሚስቱን እየተሰናበተ፡ -

- ውዴ የኔ! ምናልባት ስራው አላልቅ ብሎኝ ለዘመን መለወጫ በአል ካልደረስኩ ቀድሜ ቴሌግራም አረግልሻለሁ!
- ግዴለም አታርግ! ቴሌግራም ልታደርግ የፃፍከውን ልብስህን ሳዘጋጅ ካፖርትህ ኪስ ውስጥ አግኝቼ አንብቤዋለሁ።

* * * *

## ትዕዛዝ ፈጻሚው

አዲስ አስተናጋጅ ምን ጊዜም የደምበኞችን ፍላጎት እንዲያስቀድም ተነግሮታል፡ -

- ምን ልታዘዝ ጌታዬ?
- ከጎኔ ያለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠው ሰውዬ የሚበላውን !



t.me/OLDBOOKSPDF

- ጥሩ? ሰውየው ስልክ እንደሚፈልገው እነግረዋለሁ ከዛ በኋላ እንግዲህ እርስዎ ይወቁበት!

* * * *

## ምንህ ላይ

ዶክተር! ሄሞራይድ ይዞኛል
ምንህ ላይ?

* * * *

## የመጨረሻ ቃል

ሞቱ ሲቃረብ ውስጡ የቀረውን ኃይል አሰባስቦ፡ -

- ውድ ባለቤቴ! የመጨረሻ ጥያቄዬን ልታሟይልኝ ቃል ትገቢልኛለሽ?
- በደንብ ነዋ!
- ከሞትኩኝ በኋላ ጆንን እንድታገቢው እጠይቅሻለሁ!
- ምነው ጆንን በጣም ትጠላው አልነበር እንዴ?
- አሁንም እጠላዋለሁ!

* * * *

## እምርረህ አልቅስ!

ቤተሰቡ ውስጥ ያለመግባባት ተፈጥሮ ባል እየጮኸ

- የዚህ ቤት አዛዡ ማን እንደሆነ ሊለይ አልቻለም! እንዴት አድርጌ ነው? አባወራነቴን የማስከብረው! ምን ባደርግ ነው ያልኩት የሚፈፀመው?
- ሚስት - አባባ! ምርር ብለህ አልቅስ።

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## መጥታ ልትቀለብ

- ማሙሽ - እከስቴ! በእጅሽ መብላት አትችይበትም እንዴ?
- እከስት - እችላለሁ ማሙሽዬ! ምነው ለምን ጠየቅከኝ?
- ማሙሽ - በቀደም ስልክ ደውለሽ ለአንድ ሳምንት እናንተጋ መጥቼ አርፋለሁ ስትይ አባቴ ደግሞ «ሳምንት ሙሉ መጥታ ልትቀለብ ነው » ሲል ስለሰማሁ::

* * * *

## እንዴት አድርጌ ልስራው?

ባል - ውዴ! ዛሬ አራት የስራ ባልደረቦቼን እራት ጋብዣለሁና እስቲ የሆነ ነገር አዘጋጂ ....

ሚስት - እሺ የኔ ፍቅር! እራቱን ሴላ ቀንም ተመልሰው እንዲመጡ አይነት አርጌ ልስራው? ወይስ ሁለተኛ እዚች ቤት ድርሽ እንዳይሉ አድርጌ....

* * * *

## ግልባጭ

ፈረንሳዊው የስነ አይምሮ ምሁር የዛሬው ትውልድ ከእኛ ትውልድ በምንም አይለይም በማለት ማሳመኛ ማስረጃውን ይፋ አደረገ: - ምሁሩ;:

*«የአሁን ትውልድም ልክ እንደኛው ያድጋሉ፣ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፣ የመጀመሪያ ሲጋራቸውን ይቀምሳሉ፣ ከወላጆቻቸው ቤት ይወጣሉ፣ ሚስት ያገባሉ፣ ልጆች ይወልዳሉ»*

ካለ በኋላ

*«ልዩነታችን የዛሬው ትውልዶች እነዚህን ተግባሮች የሚፈጽሙበት ቅደም ተከተል በግልባጩ መሆኑ ብቻ ነው»*



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲል ማስረጃውን አጠቃሏል።

* * * *

## ወደምታይበት እንዳትሄድ!

ትራፊክ ፖሊስ ሰማይ ሰማይ እያየ የመኪና መንገድ ለሚያቋርጠው እግረኛ በጩኸት: -

- ሰውዬ! ወደምትሄድበት ካላየህ ወደምታይበት መሄድህ ነው!

* * * *

## በአደባባይ

የመዋኛ ቦታ ተቆጣጣሪው በጣም ተናዶ :-

- ከእንግዲህ ወዲህ ግን ሽንትህን መዋኛ ውስጥ ብትሸና ሁለተኛ እዚህ እንዳትደርስ አሳግድሃለሁ! ገባህ?
- እኔን ብቻ ነው ያየኸው? መአት ሰው ነው የሚሸናው!
  ከመዝለያው ላይ? /በመደነቅ/

* * * *

## ጉዳት

- ዶክተር በሽታዬ ለጉዳት የሚሰጥ አይነት ነው?
- ብዙም አይጎዳሽም አንድ አምስት ሺህ ቢያስወጣሽ ነው።

* * * *

## ምክንያት መች አጥታ

- ምነው ባክህ? በጣም ያዘንክ ትመስላለህ
- አባክህ! ሚስቴ «የምለብሰው ልብስ እንኳን አጣሁ» እያለች በየቀኑ ትጨቀጭቀኛለች



t.me/OLDBOOKSPDF

• ታዲያ ሙቀት አገር ሄደህ መኖር ነዋ መድሃኒቱ

እዛ ደግሞ «የማወልቀው ልብስ እንክዋን አጣሁ » ማለቷ አይቀርም

*    *    *    *

## ልዩነት

• በፍቅርና በጋብቻ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

• ፍቅር የህይወት መብራት ነው:: ጋብቻ ደግሞ ላበራኸው መብራት የምትከፍለው ሂሳብ ነው::

*    *    *    *

## የጥርስ ክሊኒክ

• አሁን ጥርስህን ላወልቀው ነውና ህመሙ እንዳይሰማህ ሌላ ሌላ ነገር አስብ

• ህክምናው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ ::

• ግሩም ነው! ለመሆኑ ስለምን? ብታስብ ነው እንደዚህ ህመምክን ቻል ያረከው

• በእኔ ቦታ ላይ አለቃዬን አስቀመጥኩታ!

*    *    *    *

## ሚስቴን

ዳኛው ፍርድ ቤት ተሰይመዋል: -

• ግጭቱ ከመጀመሩ በፊት ባለጋራህ በእጁ ቆመጥ ይዞ ነበር ነው ያልከኝ?

• አዎ! ጌታዬ

• አንተስ በእጅህ ምን ይዘህ ነበር

• ሚስቴን!

*    *    *    *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የስራ አጀማመር

ማቆሚያው ላይ አውርዶና ጭኖ በመነሳት ላይ ያለ የከተማ አውቶቡስ ላይ ለመድረስ ሴትየዋ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ: -

- እቁም በሉልኝ! እቁም በሉልኝ እባካችሁ! ስራ ማርፈዴ ነው! እቁም!
- ተሳፋሪዎቹም ስላዘኑላት ሹፌሩን «እባክህ አንድ ምስኪን በሩጫ እየመጣች ነው አቁምላት» ብለው ሲለምኑት አቆመ:: ሴትየዋም ቁና ቁና እየተነፈሰች: -
- ኡህ! እንደምንም ለስራዬ ደረስኩ! እሺ መንገደኞች ቲኬቶቻችሁን መቆጣጠር ልጀምር ነውና ሁላችሁም እያወጣችሁ አሳዩ! /በቁጣ/

* * * *

## አንተስ

ታክሲ ነጂውን ሁለት የገጠር ሰዎች ያስቆሙትና

- 3 ሰው አውቶቡስ ጣቢያ ትወስዳለህ?
- ሁለት አይደላችሁም እንዴ! የታለ ሶስተኛው ?
- ምነው አንተስ መሄድ አትፈልግም?

* * * *

## ተቃራኒ ቅጣት

የንግድ ተቆጣጣሪው ለባለ ምግብ ቤቱ:-

- ያለ ፈቃድ አልኮል በመሸጥህ 1500 ብር
- አልኮል ውስጥ ውሃ ደባልቀህ በመሸጥህ 500 .....

* * * *

## የሚያስፈልግ ነገር.....

ሩሲያዊቷ ሴትዮ ለባሏ ምግብ ካቀረበችለት በኋላ በንዴት እየተንገበገበች: -



t.me/OLDBOOKSPDF

- አየህ! ሳንቲም ሳይቀር እንጠፍጥፌ ገንዘብ ጨርሻለሁ:: ካሁን ጀምሮ ቀሰብህ እንደዚህ ላመል እንኳ ስጋ የሌለበት ባዶ ሾርባ ብቻ ነው!

ባል ፀጥ ብሎ የሾርባው ሳህን ላይ አይኑን ተከሏል

- የቤታችን ጣራ እላያችን ላይ ሊፈርስ ነው! አንተ ቮድካህን እየዞርክ ትግፋለህ:: የልጆቹ ልብስ እላያቸው ላይ አልቋል! ክረምት አፍንጫችን ስር ነው ለበረዶው የሚደራርቡት ልብስ ያስፈልጋቸዋል::

ባል ቀስ እያለ ከሾርባው ጋ ይታገላል

- በአል እየተቃረበ ነው ዶሮ መግዛት ያስፈልጋል ... ልጆቹም የበአል ኬክ ያምራቸዋል

ባል ቃል አልተነፈሰም

- ለበዓሉ ጠረጴዛችን ላይ ወይን ያስፈልገናል

ባል ድንገት ሳይታሰብ ከእጁ የያዘው የሾርባ ማንኪያ ወዲያ እስኪፈናጠር ዘሎ በመነሳት:-

- የሚያስፈልግ ነገርማ የግድ ያስፈልጋል!

* * * *

## ኩርፊያ

ከዘመዶቻቸው ደብዳቤ የደረሳቸው የመርከብ ላይ ሰራተኞች በሙሉ በትዝታ ተውጠው በማንበብ ላይ ናቸው:: አንዱ መርከበኛ ግን በፖስታ ውስጥ ምንም ነገር ያልተፃፈበት ንፁህ ወረቀት ስለደረሰው ደብዳቤውን በእጁ እንደያዘ በመስኮት ወደ ውጭ እያየ ይተክዛል:: ሁኔታውን ያስተዋለው ጓደኛው: -

- ማነው ምንም ያልተፃፈበት ደብዳቤ የላከልህ?
- ሚስቴ ናት
- እንዴት ታዲያ አንድም ቃል አልፃፈችልህም?
- ተኳርፈናል አንነጋገርም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለት ሰካራሞች መሬት ላይ ወድቆ መነሳት ያቃተውን ሶስተኛውን ሰካራም ጓደኛቸውን በመርዳት ላይ ናቸው:-

- ምናባቱ ነክቶት ነው በመከራ እያቆምነው እስር ጊዜ መልሶ የሚወድቀው?
- መቼም ጥለነው እንሄድ! ነግበኔ ነው ....ያዝ እስቲ እንዴ ደግሞ እንሞክር
- ድንገት በዛ የሚያልፉ ሴትዮ ሰካራሞቹን ያዩዋቸውና:-
- እረ እባካችሁ ሰዎች! በጭንቅላቱ ልታቆሙት ነው የምትታገሉት.....

*            *            *            *

## ከማንኛውም ደሮ....

ባል ለሚስቱ: -

- አንቺ ውዴ! በህይወትሽ ምንም መፅሐፍ ፅፈሽ የማታውቂ ሰው ስለሆንሽ የኔን አዲስ መፅሐፍ በትክክል ለመፍረድ በፍጹም አትችይም!
- ለምን ተብሎ?! በህይወቴ እንቁላል ጥዬ ባላውቅም ስለ እንቁላል እምሌት ከማንኛውም ደሮ የበለጠ አውቃለሁ

*            *            *            *

## ማንነቱን የሚያውቅ

የተንኳኳ በሯን ስትከፍት:-

ፖሊስ - ባለቤትዎን የቆሻሻ መድፊያ ላይ ወድቀው ማግኘታችንን ልንገልፅልዎ ነው የመጣነው

ሴትየዋ ትከሻዋን ነቅንቃ: -

- የማያገባችሁ ውስጥ ምነው ባትገቡ? እንደዛሽ የሆነው፤ ወደ ስራ ስወጣ በቤት ውስጥ ያለውን የማይጠቅም ነገር ሁሉ ጠራርገህ ቆሻሻ መድፊያ ወስደህ እንድትጥል ብዬ አስጠንቅቄው ስለነበር ነው........



t.me/OLDBOOKSPDF

### የዝምድና ማረጋገጫ

ሚስቱ ከስራ እንደተመለሰች :-

- ቅድም የሆነ ሰው መጥቶ «ያንች የቅርብ የስጋ ዘመድ ነኝ ይሄንንም በማስረጃ አረጋግጣለሁ» አለኝ
- ደደብ መሆን አለበት!
- ሳይሆን አይቀርም:: ነገር ግን ሌላም ተጨማሪ ማስረጃ እንዳለው ነው .......

*  *  *  *

### መውጫ ቀዳዳ

ለምን የመኪናዎን ግማሽ ጎን ቀይ ግማሹን አረንጓዴ አስቀቡት?

እግዜር አያምጣውና የሆነ ሰው ብገጭ የምስክሮች ቃል እንዲለያይ!

*  *  *  *

### ሚስቴ ጠፍታብኝ

ብዙ ሺህ ሽማች ህዝብ በሚተረማመስበት በአለም ላይ ካለ ትላልቅ ገበያዎች አንዱ በሆነው ሞስኮ በሚገኘው መደብር (ጉም) ውስጥ አንድ እንግሊዛዊ ቱሪስት ወደ መረጃ /ኢንፎርሚሽን / ስጭው ይጠጋና

- እባክህ! «ሚስቴ ጠፍታብኝ» ነው እንድትረዳኝ የመጣሁት
- ለቀብር የሚሆኑ ዕቃዎች 3ኛ ፎቅ ላይ ነው የሚሸጡት

*  *  *  *

### የደብዳቤ ልውውጥ

ሰላም! ቻርሊ ቻፕሊን !

ፊልምህ በምድራችን ላይ የታወቀ ስለሆነ ወደፊት ታዋቂ ታላቅ ሰው መሆንህ የማይቀር ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

## አልበርት አንስታይን

ሰላም! አልበርት አንስታይን!

የአንፃራዊነት ንድፈ ሃሳብህ በምድራችን ላይ አንድም ሰው እንኳን ሳያውቀውና ሳይገባው አንተም ታዋቂ ታላቅ ሰው ሆነሃል::

ቻርሊ ቻፕሊን

* * * *

## እኔስ ከዚህ የተለየ

ወደ ማርሴል በሚጓዘው ባቡር ላይ 6 ልጆች የያዙች ሴት እንደተሳፈረች ልጆቹ ይንጫጫሉ፣ ይታገላሉ፣ ይሯሯጣሉ:: ለ1 ደቂቃ ቦታቸው ሳይቀመጡ ተሳፋሪውን ህዝብ ክፉኛ በጠበጡት::

አንዱ ተሳፋሪ ብስጭቱን መቻል ስላቃተው :-

- ለእረፍት የሚጓዝ ሰው ቢያንስ ግማሾቹን ልጆቹን እቤቱ ሊተዋቸው ይገባል!
- እኔስ ከዚህ የተለየ ምን አደረግኩ? /በመበሳጨት/

* * * *

## ሁለት ማስታወሻዎች

በባቢሎን አካባቢ በተደረገው የከርሰ ምድር ቁፋሮ በግምት በ280 ዓ.ም የተጻፉ ሁለት ማስታወሻዎች የተገኙ ሲሆን የሚከተለው ተፅፎባቸዋል::

በአንደኛው ላይ «ሌላ ዘመን በመምጣት ላይ ነው»

በሁለተኛው ላይ «በቅርቡ አለማችን ያበቃላታል:: ልጆች ከእንግዲህ ለወላጆቻቸው አይታዘዙም፣ ሁሉም ሰው መፅሀፍ ሊጽፍ ይፈልጋል»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የውሳኔ ዕድሜ

- በተዋወቅን በ3ኛው ቀን ለትዳር የጠየቅከኝ ሰውዬ መኪና ለመግዛት ለመወሰን እንዴት 2 ወር ይወስድብሃል?
- ምነው ነፍሴ! መኪና መግዛት ማለት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር እንደሆነ እንዴት አይገባሽም?

* * * *

## እሾህን በእሾህ!

አንድ የፈረንሳይ ጋዜጣ የሚከተለውን ጠቃሚ ምክር በእትሙ ላይ በማውጣት ለታዳሚዎቹ እንደሚከተለው አስነብቧል: -

እንባቢ ሆይ! ፍቱን መድሃኒትነቱ በተግባር ተሞክሮ የተረጋገጠ ዘዴ ይሄውልዎ! ከመሽ በኋላ ጎረቤትዎ ሬድዮ እያስጮኸ እንቅልፍ ከነሳዎት ከንጋቱ 10 ሰዓት ላይ ተነስተው በሩን በማንኳኳት ይቀስቅሱትና ማታ ስላካፈልዎ ፕሮግራም አመስግኑት!

* * * *

## ልጅ አባቡ

ከጣሊያን ሃገር ጉብኝቱ በተመለሰ በወሩ ፀጉሩን ሊስተካከል ደምበኛው ጋር ሄዷል:: ፀጉር አስተካካዩም እያስተካከለው እያለ: -

- ልጅ አባቡ! ጣልያን ሃገር ሄደው ነበር የሚል ወሬ ሰማሁ!
- አዎ ሄጄ ነበር::
- ታዲያ እንዴት ነበር?
- ምንም አይልም ደህና ነበር
- የሮማውን ጳጳስ አዩአቸው?
- አዎ አየኋቸው ::
- እንዴት ነው? ምን ይመስላሉ?
- ያው እንደማንኛውም ጳጳስ ናቸው::
- እንዴት እነደዛ ይሆናል? የተለየ ነገር የላቸውም?



t.me/OLDBOOKSPDF

- ያው እንደማንኛውም ጳጳስ ሲመጡ ሁሉም ሰው ይነሳል::
- እርስዎስ?
- እኔ እዛው ቁጭ ያልኩበት ጎንበስ ብዬ እጅ ነሳሁ::
- እና ስላልተነሱ ምንም የመቀየም ስሜት አላዩባቸውም?
- ምንም? ብቻ ጠጋ አሉኝና «ልጅ አባቡ! የማን ልፋጭ ጭንቅላት ነው? ፀጉርህን እንደዚህ ያስተካከለህ!» አሉኝ

*    *    *    *

## ሽበቶዎች

ኢማኑኤል ካንት የተባለው የጀርመን ፈላስፋ ከቡኒ አይነትና ጥቁር ፀጉር ካላቸው ሴቶች ታማኞቹ የትኞቹ ናቸው ተብሎ ሲጠየቅ:-

- ሽበቶዎች! /ለስከንድ ሳያስብ/

*    *    *    *

## መፍትሔ

አንድ እዛውንት የከተማ አውቶቡስ ስምሪት ክፍል ኃላፊውን ገብተው: -

- አውቶቡሶች በሰአታቸው ስለማይመጡ ተገልጋዮች በጣም እየተንገላታን ነውና ለምን አንድ መፍትሄ አትፈልጉም?
- አባት! ለዚህ ችግርማ መፍትሄ ከሰጠን ቆየን እኮ! በየአውቶቡስ ማቆሚያው ተጨማሪ አግዳሚ ወንበር ማስራታችንን እንዴት? ልብ አላሉም::

*    *    *    *

## መጋለጥ

ሁለት ጓደኛሞች መጠጥ ላይ ጨዋታ ይዘዋል: -

- በህይወትህ የማይጠበቅ የደደብ ስህተት ሰርተህ ታውቃለህ?



t.me/OLDBOOKSPDF

- አንድ ጊዜ ብቻ! ... ትዝ ይለኛል ሚስቴን ለስራ ጉዳይ ክፍለ ሃገር ሄጄ እስክርማለሁ ብያት ከእኛ ሁለት ፎቅ ከፍ ብላ የምትኖር ሴት ጋር መሸግኩ::
- እናስ?
- እናማ በ3ኛው ቀን ቤት ውስጥ መታሸት ስለቸኘና በጣም ከመሸ በኋላ በዛውም ቆሻሻ ልድፋ ብዬ የሴትየዋን ፒጃማና ነጠላ ጫማ አድርጌ ወጣሁ::
- ከዛስ?
- ከዛማ ጭንቅላቴ የሆነ ሃሳብ ውስጥ ገብቶ ስመለስ ሁሌም እንደማደርገው ባሊዬን እንዳንጠለጠልኩ ወደ ቤቴ ውስጥ .......

*　　　*　　　*　　　*

## ከአንተም ጋር

እማች ውሻ ገዝተው በማስልጠን ላይ ናቸው :-

- እማት - ዝም ብለው ነው የሚለፉት አልሆነልዎትም::
- እማች - ከአንተም ጋር ስንጀምር ልክ እንደዚሁ ነበር ዋናው በትዕግስት ማለማመድ ነው::

*　　　*　　　*　　　*

## ባትሞት ኖሮ

ሰውዬው መቃብር ቦታ ሄዶ ሃውልት ላይ ተደፍቶ ምርር ብሎ እየተንሰቀሰቀ ያለቅሳል:: ሁኔታውን የተመለከተ ሰው ልቡ በሃዘን ይነካና ይጠጋዋል: -

ሃዘንተኛው - ምነው በጠዋቱ! ምነው ቸኩለህ ሄድክ? /እያለ በመደጋገም እዬዬውን.../

አዛኝ - የቅርብ ዘመድዎ ነበር? /ለማጽናናት በር መክፈቱ ነው/

ሃዘንተኛው - አይደለም:: የሚስቴ የመጀመሪያ ባሏ ነበር::



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፖስተኛው

ዶክተር በሽተኛውን ከመረመረ በኋላ ምክር መለገስ ጀመረ: -

ዶክተር - ችግርህ ዘመን ያመጣው ችግር ነው ማለት ይቻላል:: ማለትም ሳይንቀሳቀሱ ቁጭ ብሎ ከመዋል፣ ንፁህ አየር ካለማግኘት፣ የእግር እንቅስቃሴ ካለማድረግ የሚመጣ ነው:: ስለዚህ ለሶስት ሳምንት ያህል በቀን 5 ኪሎሜትር የእግር ጉዞ ብታደርግ ብዙ ለውጥ እንደምታመጣ እርግጠኛ ነኝ::

በሽተኛ - የእግር ጉዞውን ከስራ በፊት ላርገው ወይስ ከስራ በኋላ?

ዶክተር - ስራህ ምንድ ነው?

በሽተኛ - የእግር ፖስተኛ::

* * * *

## ነገር በምሳሌ

ማስት የቀረጥ ኃላፊ ባሏን እየጠየቀች ነው: -

- በቀጥተኛ እና በተዘዋዋሪ ቀረጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- እንዴት መሰለሽ! እንቅልፍ ሲወስደኝ ኪሴ ገብተሽ ብሬን ብትወስጂ ቀጥተኛ ቀረጥ ይባላል:: ለምግብ ከመደብነው በጀት ላይ ቀናንሰሽ ለራስሽ መኳኳያ ብትገዢ ተዘዋዋሪ ቀረጥ ይባላል::

* * * *

## ያኔም አሁንም

ባልና ሚስት ከተጋቡ ከ5 ዓመት በኋላ ፍቅር ጠፋ: -

- ከመጋባታችን በፊት ግን ለተወሰነች ደቂቃ ብታገኘኝ ደስተኛ ነበርክ:: አሁንም እንደዛው ነው!::

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ነፍስ ነገር

መስሪያ ቤት ውስጥ ጨዋታው ጦፏል፡ -

- የኔ ሚስትስ ነፍስ ነገር ነች!! ከስራ ስገባ በመሳም ትቀበለኛለች፣ ልብሴን ሳወልቅ ትረዳኛለች፣ ጫማዬን አውልቃ ነጠላ ጫማ ታቀርብልኛለች፣ የላስቲክ የእጅ ጓንት ታረግልኛለች
- ደግሞ ጓንቱ ምን የሚሉት ነው?
- ብረትድስት ሳጥብ እጄ እንዳይበላሽ .... አታይም እጄን! ይሄ አሁን ብረትድስት....

* * * *

## ከእንቅልፍ መቀስቀሻ

በጠዋት መነሳት የቸገረው ሰው መደብር ይገባና፡-

- እባክህ የኔ ወንድም ጥሩ የሆነ ከእንቅልፍ ማንቂያ ነገር ይኖራችኋል?
- በሚገባ! እራሱን የሚፈልጉትን አይነት አገኝልዎታለሁ ...... ይሄውልዎ! መጀመሪያ የስልክ ጥሪ ድምፅ ይሰጣል ... ካልተነሱ ድምፅን ወደ እሳት አደጋ መኪና ድምፅ ይቀይራል ... ካልተነሱ የመድፍ ድምፅ ማሰማት ይጀምራል .... ካልተነሱ ቀዝቃዛ ውሃ መርጨት ይጀምራል ... አሁንም ካልተነሱ ዋናው አለቃዎ ጋር ደውሎ መታመምዎን ይነግራል....

* * *

## ብልህ መልስ

ባሏን መምከር የምታበዛ ሴት ምክሯ የሰለቸውን ባሏን ለማሳመን እንዲረዳት ጥያቄ አቀረበችለት፡ -

- እግዚአብሄር በመጀመሪያ ወንድን ቀጥሎ ሴትን ለምን ፈጠረ?
- ወንድን በሚፈጥርበት ጊዜ የሴት ምክር ስላልፈለገ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

### ጋጠወጥ ሳውንደሪ

- ለምንድነው ካፓርቴ ላይ ሌላ አይነት ቁልፍ የተከላችሁት?
- ቁልፍህ ላይ ሌላ አይነት ካፖርት ብንተክልልህ ይሻል ነበር?

* * * *

### ከሚገርመኝ ነገር

- እያቴ በፈረስ መሄድ እንጂ በመኪና መሄድ ትፈራ ነበር ፡
- እናቴ በመኪና መሄድ ብትወድም በአይሮፕላን መሄድ ግን ትፈራለች ፡
- ልጄ በአይሮፕላን እንደመሄድ የሚያስደስታት ነገር የለም በፈረስ መሄድ ግን ትፈራለች፡፡

* * * *

### ስለ ሴት

ፓይለቶችና ሚስቶቻቸው መዝናኛ ቦታ ላይ ተቀምጠው ቡና እየጠጡ ያወራሉ፡፡ ባሎች በሙሉ ቢያወሩ ስለአውሮፕላን ሞተር፣ ቢያወሩ ስለ መገናኛ ሬድዮ፣ ቢያወሩ ስለ አይሮፕላን አነሳስና አስተራረፍ የሆነባት አንደኛዋ ሚስት ስላንገፈገፋት ወሬ እንዲቀይሩ ብላ፡-

- ስመሆኑ እዛ ስራ ቦታችሁ ስትገናኙ ምን ልታወሩ ነው?
- እዛማ ስለ ሴት ነዋ!

* * * *

### እንዴት አይገባህም„ „ „

ጫማ ሰፊ ቤት፡ -

- እንድትሰራልኝ የሰጠሁህ እኮ ሁለት እግር ጫማ ነው ለምንድነው አንድ እግር ብቻ የምትሰጠኝ?



t.me/OLDBOOKSPDF

- ይሄ በእጅህ የያዝከው ጫማ አንድ ቀን ሙሉ ነው የጨረሰብኝ፣ ጠቅላላ ተበትኖ ቆዳው ተጠጋግኖ ሶሉም ተደራርቦና ተገጣጥሞ መሰራት ነበረበት::
- በጣም አመሰግናለሁ! የታለ ሌላው እግር?
- ደግሞ ለዚህ ጫማ ከራሴ ቆዳ ልጠቀም!? አንድ ጫማ ሰፍቼ ብሸጥ ነው የሚያዋጣኝ::
- አልገባኝም!
- እንዴት አይገባህም አንደኛውን እግር እዚህ ላይ አብቃቃሁልሃ! /በንዴት/

* * * *

## ምን ላይ ልጫነው

ታክሲ ነጂው ሰው በሰው ላይ ጭኖ ሲሄድ ያስተዋለው እግረኛ ትራፊክ ፖሊስ እንዲያቆም ምልክት አሳየው:: ታክሲ ነጂው ግን እንደውም ፍጥነቱን ጨመረ: -

- ተሳፋሪ - ለምንድነው አቁም እያለህ የማታቆመው?
- ሹፌር - ምን ላይ እንድጭነው ፈለግክ?

* * * *

## <u>የጆርጅያውያን አባባል</u>

- ለ 1 ቀን ደስተኛ መሆን ካማረህ ስከር
- ለ1 ሳምንት ደስተኛ መሆን ካማረህ ታመም
- ለ1 ወር ደስተኛ መሆን ካማረህ ሚስት አግባ
- ለ1 ዓመት ደስተኛ መሆን ካማረህ ፍቅረኛ ያዝ
- እድሜህን በሙሉ ደስተኛ መሆን ካማረህ ጤነኛ ሁን!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የሰካር መስኪያ

የሰካራሙ ሚስትና ጎረቤቷ: -

- ጎረቤት - ሚስጥር ካልሆነ ለምንድነው? ለልጅሽ «ኮንስታንቲኖፕል» ብለሽ ረዥም ስም ያወጣሽለት::
- የሰካራም ሚስት - ባሌ ማታ ቤት ገብቶ ልጁን ሲጣራ ስንት እንደጠጣ ማወቅ እንድችል ብዬ::

* * * *

## የደሞዝ ቀን

ፖሊስ ጣቢያ ሄዳ: -

- እባክዎ ጌታዬ! በጣም የምወደውና ካለሱ መኖር የማይሆንልኝ ባሌ ጠፍቶብኛልና ካለበት ቦታ ፈልጋችሁ አምጡልኝ /በለቅሶ/
- ፓ/አዛዥ - ከመቼ ጀምሮ ነው የጠፋው?
- ይኸው ዛሬ 1 ሳምንት ሆነው!
- ፓ/አዛዥ - ታዲያ መጥፋቱን ለማመልከት ምን እስከዛሬ አስጠበቀሽ?
- የደሞዝ መቀበያ ቀኑ ዛሬ ነዋ!

* * * *

## የአለማወቅ ሦስት ማዕዘኖች

የአለማወቅ ሶስት ማዕዘኖች:-

ጉዳዩን ምንም ያለማወቅ

ጥሩ አርጎ ያለማወቅ

የማያስከትለውን ነገር ማወቅ?

* * * *

## ግንዛቤ

- ዶክተር - መጠጥ ብታቆም እድሜህ ይረዝማል!
- ስዚህ ነው ሳምንቱን ባልጠጣ አመት የመሰለኝ?

t.me/OLDBOOKSPDF

## የኋላ ማርሽ

- ስማ እንጂ! የምርጥ ቲያትሮችን የመግቢያ ቲኬት ለማግኘት ሰው ሁሉ ሲቸገር አንተ ሁሌም እየተሳካልህ የምትገባው እንዴት ነው?
- የምን ቲኬት አመጣህብኝ! በተቆጣጣሪዎቹ አጠገብ ፊቴን አዙሬ በጀርባዬ ወደ ኋላ ስገባ የምወጣ እየመሰላቸው ተናግረውኝም አያውቁ::

* * * *

## ስለወደፊት ሚስቶቹ

- ባለቤቴ ስራው በየቀኑ ስለድሮ ሚስቶቹ ማውራት ብቻ ስለሆነ ናላዬን እያዞረው ላብድ ትንሽ ነው የቀረኝ....
- አንቺስ እድለኛ ነሽ! እንደእኔ ባል ሌት ተቀን የሚያወራው ስለ ወደፊት ሚስቶቹ ቢሆን ኖሮ ምን ልትሆኚ ነበር?

* * * *

## ከአሁን ወዲህማ

ለብዙ ዓመታት በእጮኝነት ጎጆ ሳይመሰርቱ ቆዩ:: በመጨረሻም ሴቷ ድፍረት ገዝታ: -

- ስለ ጋብቻችን ማሰብና አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብናል!
- ከአሁን ወዲህማ አረጀን እኮ! የሚያገባን እናገኛለን ብለሽ ነው?

* * * *

## ጡት አልጣለም ነበር

የታሪክ ተመራማሪው ቱሪስት መናፈሻ ውስጥ የተቀመጡትን ሽማግሌ ስለ ታሪክ እንዲያወጉት ፈለገና ለመግባባት: -

- አባት! መቼም የዕድሜ ባለፀጋ መሆን አለብዎት?
- እግዚአብሄር ይመስገን 80 ዓመት ካለፈኝ ቆየሁ:: ሟቹ ታላቅ ወንድሜ በህይወት ቢኖር ኖሮ ልክ የዛሬ ሳምንት 90 ዓመቱን ይደፍን ነበር::



t.me/OLDBOOKSPDF

- ሰው ሆኖ ከሞት የሚቀር ማን አለ? ብለው ነው:: ካረፉ ቆዩ?
- አዬ እሱማ ቆየ እንደነገሩኝ ሲሞት የአናቱን ጡት እንኳን አልጣለም ነበር::

• • • •

አድሜዉ ገፋ ያደረገ ሰው ወደ ክሊኒክ ይሄድና: -

- ዶክተር! እኔና ሚስቴ ስራችን መነጫነጭ ከመሆኑ የተነሳ ሳንጣላ የዋልንበት ቀን የለም:: እባክዎን ምን እንደሚሻለኝ ይንገሩኝ::
- እንደሚመስለኝ የችግሩ መንስኤ የሁለታችሁ ጤና ከአካል ጥንካሬያችሁ ጋር ያለመመጣጠን ነው:: ስለዚህ የአካል እቅስቃሴ ማድረግ ሰውነታችሁን ከማጠንከሩም ሌላ አይምሯችሁን እንዲዝናና ያደርገዋልና እስቲ እርስዎ በቀን 10 ኪ.ሜ የእግር ጉዞ በማድረግ ይሞክሩ:: ለማንኛ ውም ከ2 ሳምንት በኋላ ለውጡን ደውለው ያሳውቁኝ::

ከ15 ቀን በኋላ ሰውየው ዶክተሩ ጋር ደውሎ በደስታ እየጮኸ: -

- አመሰግናለሁ ዶክተር! ሁሉም ነገር እጹብ ድንቅ ነው! ይሄውልዎ!
- ከባለቤትዎ ጋር የነበረው ፀብ ቆመ አይደል?
- ታዲያሳ! በምን ስንገናኝ?! አሁን እኮ እኔ የምገኘው ከቤቴ 150 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ነው::

• • • •

**ባልተነኳኩሰው ኖሮ**

እማዬ! ለምንድነው ባሌን በነገር የምትነካኪው?

እናትየው ወደ ልጃቸው ጆሮ ተጠግተው በሹክሹክታ: -

ምንጣፍ ለማጽዳት ሲልፈሰፈስ አገኘሁታ! ታዲያ በነገር ባልተነኳኩሰው ኖሮ እንደዚህ ጉልበት አግኝቶ ምንጣፉን ጥሩ አድርጎ በዱላ እየነረተ ይፀዳ ነበር?



t.me/OLDBOOKSPDF

## ከእኔና ከአንተ ሌላ

የፓርላማ ተወዳዳሪው ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ቤቱ ሲመለስ፡ -

- ሚስት - እሺ! እንዴት ነበር ምርጫው? ስንት ድምፅ አገኘህ?
- ተወዳዳሪ - ሶስት
- ሚስት - አትዋሽ! ውሽማ አለህ ማለት ነው!

* * * *

## ሞራል!

- አባት - በኢንተርኔት ወደፊት የኑሮ ጓደኛን ለመተዋወቅ መሞከር የሞራለ ቢሶች ተግባር ከመሆኑም ሌላ ግብረገብነት የጎደለው ነው።
- ልጅ - አንተ እንዴት ነው እናቴን ያገኘሃት?
- አባት - እኔ ያንተ አባት! ከሰው ላይ በቁማር በልቼ ነዋ!

## ተራ ያዝ

መጠጥ የተከለከለበት አገር ገጠር ውስጥ ለስራ የተላከ የአልኮል ሱሰኛ በድብቅ የሚሸጥ መጠጥ ለማግኘት እዛው ኗሪ የሆነ ሰውጋ ጠጋ ብሎ፡-

- እባክህ ውስኪ የማገኝበትን ቦታ ልትጠቁመኝ ትችላለህ?
- የኔ ወንድም በዚህ አገር አልኮል መጠጥ ክልክል ስለሆነ ውስኪ የሚሰጠው በእባብ ለተነደፈ ሰው ብቻ ነው። በመንደሩ ደግሞ ያለው እባብ አንድ ብቻ ነውና ከመድከሙ በፊት ቶሎ ሄደህ ተራ ያዝ!

* * * *

## እንደ አባትህ

- መቼ ነው እንደ እናቴ ጥሩ ምግብ የምታዘጋጂልኝ?
- እንደ አባትህ ደህና ገንዘብ መስራት ስትጀምር።



t.me/OLDBOOKSPDF

## እኛ ነበርን

ልጁ አልሰማ እያለ ያስቸገራት እናት በተረት አድርጋ እያስተማረችው ነው፡-

- እናት - አየህ ማሙሽዬ! የበግ ግልገሉ እናቱ የምትለውን ቢሰማ ኖሮ ተኩላው አይበላውም ነበር:: ገባህ?
- ማሙሽ - ገባኝ እማማ! እናቱ የምትለውን ቢሰማ ኖሮ እኛ ነበርን የምንበላው::

* * * *

## አዎ እማዬ

ማሙሽ በጊዜ አልተኛም ብሎ አባት በተረት አፍዝዞ ሊያስተኛው እየሞከረ ነው ሩብ ሰዓት አለፈ .... ግማሽ ሰዓት ... አንድ ሰዓት ... እናት ቀስ ብላ በሩን ከፍታ በሹክሹክታ፡-

- «ተኛልህ?»
- «አዎ እማዬ! .....»

* * * *

## ከእርስዎ ያለመሆኑ

ሰውየው የሚስቱን የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ለመስማት ክሊኒክ ሄዶ ወረቀት የሚያገላብጠውን ዶክተር በጉጉት እየጠበቀ ነው፡ -

- ስለ ባለቤትዎ የምርመራ ውጤት ጥሩም መጥፎም ዜና አለኝ:: የቱን ላስቀድም?
- መጥፎውን
- ባለቤትዎ የአባለዘር በሽታ ተገኝቶባቸዋል
- የዲማው ጊዮርጊስ! ... ጥሩው ወሬው ምን ሊሆን ነው?
- በሽታው የተጋባባቸው ከእርስዎ አለመሆኑ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ኖረው አልኖረው

ሰውየው ቡና ቤት ይገባና «ባለጌ ወንበር» ላይ ተፈናጦ፣ 4 እግር የሌለው «ድንክዬ» ውሻውን ባንኮኒው ላይ ፊት ለፊቱ አስቀምጦ መጠጥ ያዛል:: ባሬስታው የታዘዘውን መጠጥ ካቀረበለት በኋላ: -

- ጌታው! ይሄ የእርስዎ ውሻ ስሙ ማነው?
- ስም ኖረው አልኖረው ምን ያደርግለታል? ቢጠሩት አይመጣ!

*   *   *   *

## ሰይጣን ያልወሰደብንን

የገጠር ትምህርት ቤት 2ኛ ክፍል አስተማሪ: -

- ተማሪዎች በምድር ላይ ከሰይጣን የበለጠ መጥፎ ሰው ይኖራል?
- ይኖራል /አንዱ ተማሪ እጁን አውጥቶ/
- የሚገርም ነው! ማነው እሱ?
- ግብር ሰብሳቢው
- ለምን ግብር ሰብሳቢው ልትል ቻልክ? /በመገረም/
- እኛ ቤት ሁላችንንም ወተት እየሰጠች ያሳደገችና የምንወዳት አንድ ላም ነበረችን:: ይችን ላም አንዳንዴ እናቴ «ሰይጣን ይዞሽ ይሂድ» ብላ ብትረግማትም ሰይጣኑ አልወሰዳትም:: ግብር ሰብሳቢው ግን እዳ አለባችሁ ብሎ ላማችንን ይዟት ሄደ.....

*   *   *   *

## ቢቃኝ

- ስለ አልኮልና ሲጋራ ኒኮቲን በጣም ብዙ መጽሃፎች ስላነበብኩ ከአዲስ አመት ጀምሮ ለማቆም ወሰንኩ!
- ምኑን? መጠጡን ወይስ ሲጋራውን
- ማንበቡን!



t.me/OLDBOOKSPDF

## ወደታች የማያይ ዓለም

- ደሃ ዘመዶች አሉህ?
- እኔ እስከማውቀው ምንም ደሃ ዘመድ የለኝም
- ሃብታም ዘመድስ?
- ሁለት የናጠጡ ሃብታም ዘመዶች አሉኝ:: እነሱ ግን አያውቁኝም::

• • • •

## አባባል

«ሩቅ ምስራቅ ከሚኖር የቅርብ ዘመድ መካከለኛው ምስራቅ የሚኖር የሩቅ ዘመድ ይሻላል!»

• • • •

## ይብላኝላቸው!

የፖለቲካ ካድሬው የሴቶችን ማህበር አስተምሮ እንደጨረሰ አንዷን ወጣት ሴት ያስነሳና፡-

- በእኛ እድሜ ኮሙኒዝም የምንደርስ ይመስልሻል?
- እኛስ አንደርስም! ይብላኝ ለልጆቻችን ::

• • • •

## አንተ ነህ! .......

በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ ነው፡ -

- በሽንት ቤት ወረቀትና በካርቶን መካከል ያለውን ልዩነት ታውቃለህ?
- አላውቅም
- እሃ! አንተ ነህ ማለት ነው!

• • • •



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምን ያስከትለኛል?

ዶክተር በ80 ዓመቴ ሴቶች መከተል አበዛለሁ
ታዲያ ምናለ? ጥሩ ነዋ!
እኔኮ ያልገባኝ........ ምንድነው እነሱን የሚያስከትለኝ?

*　　　*　　　*　　　*

## አንተን እንድታፈቅር

ቄሱ ጋ ሄዶ: -

- እግዚአብሔር ለምንድነው ሚስቴን ቆንጆ አድርጎ የፈጠራት?
- አንተ እንድታፈቅራት ብሎ!
- ለምን አሳቢና ተንከባካቢ አደረጋት?
- አንተ እንድታፈቅራት ብሎ!
- እንደዛ ከሆነ ለምን ሞኝ አደረጋት?
- አንተን እንድታፈቅር ብሎ!

*　　　*　　　*　　　*

## ምስኪኖች ቤት

እናት　-　አንተ ልጅ! እረ በጣም ከሳህ ናና ይሄን አሹቅህን ጨርስ!

*　　　*　　　*　　　*

## ሊጠቀልል

የደሞዝ ቀን ደሞዙን ሊቀበል ሲገባ ከፋዩ አዲስ መሆኑን ሲያውቅ:-

- ደሞዝ ከፋይ　-　ስም ከነአባት?
- ደሞዝ ተቀባይ　-　ጠቅላላ ድምር!

*　　　*　　　*　　　*



t.me/OLDBOOKSPDF

## ስህተተኛ ግምት

ሰውየው በጫካ ውስጥ እያቆራረጠ ወደ አገሩ ሲሄድ አንበሳ ዋሻ መግቢያ ላይ በጣም ትንሽ የአንበሳ ግልገል ያጋጥመዋል፡ -

- የአንበሳ ግልገል! አባትህ አለ?
- የለም
- እናትህስ?
- እሷም የለችም
- በያዘው በትር የአንበሳውን ግልገል ቸብ ያደርገውና
- ዞር በል ከመንገዱ ላይ!
- እያቴ!!!!!!!! /ረዥም የዕርዳታ ጥሪ/

* * * *

## ፀረ ሴሜቲክ

ፀረ-አይሁድ የሆነ ሩሲያዊ ሰክሮ በመንገድ ላይ እየሄደ «አይሁዶችን ሁሉ መቃብር ክተቱ!» «አይሁዶችን ሁሉ መቃብር ክተቱ!» እያለ ሲጮህ ፖሊስ ያስቆመውና፡ -

- ትንሽ ስለምትናገረው አታፍርም? አይሁዶችም እኮ እንደኛው ናቸው። ጥሩ አይሁድ አለ። መጥፎ አይሁድ አለ።
- «እሺ ጌታዬ! ገብቶኛል! ሁሉም ነገር ግልጽ ነው ይቅርታ!»
- ከሰው በኋላ ሰካራሙ ከፖሊሱ እይታ ትንሽ ራቅ አለና፡-
- «ጥሩ አይሁዶችን ጥሩ መቃብር፤ መጥፎ አይሁዶችን መጥፎ መቃብር ክተቱ!» .....

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ለእኛ ለእኛ ሲሆን

ምስኮ ውስጥ:-

ሁለት አይሁዶች በመንገድ ላይ ሲሄዱ ወፍ በአንደኛው ጭንቅላት ላይ ኩሷን ማለችበት:-

- አየህ አሮን! ይች ወፍ የሰራችኝን? ለሩሲያኖች ሲሆን ይዘምራሉ፤ ለእኛ .....

*    *    *    *

## ማጽናኛ

- ዶክተር! እንዴት ነው በሽታዬ? የምተርፍ አይደለሁም ማለት ነው?
- ያን ያህልም አታክብደዋ! ... እንዴት መሰለህ.. እኔ አንተን ካዳንኩህ በአለም የታወቅኩ ዶክተር እሆናለሁ::

*    *    *    *

## «ምንጩን ማድረቅ»

ሚስቱን ከሌላ ወንድ ጋር ስትማግጥ አግኝቷት በመግደል ወንጀል ተከሶ ፍርዱ እየታየ ነው:: አቃቤ ህግ: -

- የራስህን ሚስት ገድለህ ፍቅረኛዋን ግን ምንም ሳትነካው የለቀቅክበትን ምክንያት ለክቡር ፍርድ ቤቱ ልታስረዳ ትችላለህ?
- ክቡር ሆይ! እኔ ሁኔታውን አውጥቼና አውርጄ በየሳምንቱ አማጋጮቿን ስገድል ከምኖር ለነገሩ እልባት ለማበጀት ራሷን ሴትየዋን መግደል አዋቂነት ነው ብዬ ስለወሰንኩ ነው!

*    *    *    *

## የሃብታም ባል አይነቶች

በዚህ አለም ላይ ሁለት አይነት ሃብታሞች ባሎች አሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

• የሚስታቸው ሃብት ሃብታም ያረጋቸው ባሎች
• ሃብታቸው ሚስት ያስገኘላቸው ባሎች

• • • •

## ብቸኛው ልዩነት

ጠርጣሪዋና ቀናተኛዋ ሚስት ስትጠየቅ: -

- በባልና በህፃን ልጅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ምንም አይነት ልዩነት የላቸውም! ልዩነት ካለ ህፃኑን ልጅ ለሞግዚት መተው መቻሉ ብቻ ነው::

• • • •

## በላሁዎት

በየቀኑ ምሳውን በአንድ ሆቴል የሚመገበው ሰው በቋሚነት ለሚያስተናግደው አስተናጋጅ ሁልግዜም ደህና ጉርሻ እንደሰጠው ነው::

እንደለመደው ምሳውን ለመብላት ሆቴሉ ገብቶ እንደተቀመጠ ሌላ አስተናጋጅ ሊያስተናግደው መጣ: -

- ምነው በደህና? ወጣቱ ቋሚ አስተናጋጅ የት ሄዶ ነው አንተ የምታስተናግደኝ?
- አይ እርስዎን በቁማር አሲዞ ስለበላሁት ከእንግዲህ ቋሚ አስተናጋጅዎ እኔ ነኝ::

• • • •

## ገና በጊዜ?

እንደማንኛውም ስካራም ሰካራሙ ሰው ሰዓት መንገደኛውን ጠየቀው: -

- የ...ኔ ወንድ...ም ሰ...አት ስንት ይ..ላል?
- 5 ጉዳይ ለ11
- ወየው ከችሳው! ገና ...በ6 ሰ...አት ተጨ..ናቀቅኩ ማ..ለት ነው? /ሰራሱ/



t.me/OLDBOOKSPDF

## ገበናችን

ሩሲያዊው ወዛደር በሩሲያዊው ጋዜጠኛ ቃለ መጠይቅ ቀረበለት፡ -

- አሜሪካኖች ላይ የምንደርስባቸው ይመስልሃል?
- በደንብ እርገን እንደርስባቸዋለን! ከኋላ የተቀደደው ሱሪያችን ገበናችንን ስለሚያሳይ አፍረን ነው እንጂ አልፈናቸው መሄድም አያቅተንም ነበር።

* * * *

## የእከክልኝ ልከክልህ ዓለም

የኮሎኔል ልጅ፡ -

- አባቴ ሳድግ ኮሎኔል መሆን እፈልጋለሁ!
- ጥሩ ሃሳብ ነው ልጄ፣ ትሆናለሃ ምናለ?
- ጄኔራል መሆንስ እችላለሁ?
- አትችልም!
- ለምን ?
- ጄኔራሎችም ልጆች አላቸዋ!

* * * *

## የበር ላይ ማስታወሻ

በጥገና ምክንያት በራችን ስለተዘጋ በስልክ ቁጥር 123456 ያንኳኩልን!

* * * *

## ገነት ምንሽር

በቀይ ሽብር ዘመን አብዮት ጥበቃው፡ -

- ቁሚ አንቺ! ስምሽ ማነው?

t.me/OLDBOOKSPDF

- ስሜ ጓድ ሌኒን አገራችን በሶሻሊዝም ጎዳና ሄዶ ምን እንደምትመስል ቃል የገቡልን ሲሆን የአባቴ ስም ደግሞ ጓድ ሊ/መንበር እኛን የሚመግቡበት ጡጦ ነው::
- ወ/ሪት ገነት ምንሽር ቅደሚ!

• • • •

<u>በዘር ሲፈረጅ</u>

በሶቪየት ህብረት ዘመን አንዱን የፋብሪካ ሠራተኛ የፓርቲ አባል እንዲሆን ቢጠይቁት ለመሆን ስላልፈለገ: -

- እኒማ ፓርቲ አባል መሆን አልችልም በጦርነቱ ጊዜ አባቴ ለጀርመኖች ያደረ ባንዳ ነበር::
- ታዲያ ምናለበት! እኛ ልጅን በአባቱ ጥፋት አንፈርጅም
- ስልህ! አባቴ ለጀርመኖች መስራት ብቻ ሳይሆን ገራፊ ክፍል ውስጥ ነው ያገለገለው
- ታዲያ ምናለበት! እኛ ልጅን በአባቱ ጥፋት አንፈርጅም
- አባቴ አንድ መንደር ህዝብ ከነነፍሱ እንዳለ በእሳት አጋይቷል፣ ህፃናትና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ረሽኗልና እንዴት የፓርቲ አባል ሁን ትለኛለህ?
- ነገርኩህ እኮ! 100 ጊዜ እደግምልሃለሁ! እኛ ልጅን በአባቱ ጥፋት አንፈርጅም
- ያልነገርኩህ ደግሞ እያቴ አይሁዳዊ ነበረች
- ቀላሉን ነገር! ያንተ አያት የፈለገችውን ብትሆን ምን አለበት? ካለ በኋላ ትንሽ እንደማሰብ ብሎ
- ግን እውነትህን ነው አባትህ ለጀርመኖች ስላገለገለ የፓርቲ አባል መሆንህ ላንተም ለፓርቲውም ጥሩ አይደለም::

• • • •



t.me/OLDBOOKSPDF

## የሬድዮ ጥያቄና መልስ

### የሬዲዮ ጥያቄና መልስ

- ለእኛ ሀገር ከአንድ የፓለቲካ ፓርቲ በላይ ያስፈልጋታል ወይ?
- አያስፈልጋትም! ህዝቧ አንዱንም ፓርቲ መቀለብ አቅቶታል?

* * * *

## የአይሁዶች በዓል

ሂትለር ጦርነቱ እልሆን እያለው ሽንፈት እየደረሰበት ሲመጣ አንድ የታወቀች በካርታ የምትጠነቁል ሴትን አስጠርቶ፡ -

- የወደፊት ህይወቴ ምን እንደሚመስል እስቲ ንገሪኝ?
- የሚታየኝ ነገር ሞትህ በአይሁዶች በአል ቀን እንደሚሆን ነው!
- በየትኛው በአላቸው?
- በየትኛውም ቀን ሙት ያ ቀን የአይሁዶች ታላቅ የበአል ቀን ይሆናል።

* * * *

## ምርጫ

ሆስተሷ ወደ መንገደኛው ቀርባ፡ -

- ምግብ ይፈልጋሉ?
- ያሉኝን ምርጫዎች ብትነግሪኝ
- እፈልጋለሁ ወይም አልፈልግም!

* * * *

## ይበዛበታል!

ከንምሩክ ኃላፊዎች ከሆኑት ለአንደኛው የልደት ቀኑን በማስመልከት ስጦታ ለመስጠት ሰራተኞች በሚስጥር ውይይት ይዘዋል፡ -

- አዲስ መርሴዲስ ገዝተን እንስጠው!



t.me/OLDBOOKSPDF

- መርሰዲስማ እምና ሰጥተነው የለም እንዴ? ሌላ ነገር አስቡ እስቲ! እንደኛው ሠራተኛ ያስብና: -
- በቃ 2 ወረፋ እንዲሰራ እድል እንስጠው
- አብደሃል እንዴ?..... ለየትኛው ውለታው ነው? እንዲህ ያለ ውድ ስጦታ የምንሰጠው!

* * * *

## ጥያቄና መልስ

- ከተሰጠዎት የዓመት እረፍት የበለጠ ፈጥና የሚያልቅ ምንድነው? ገንዘብ! /ወዲያው/

* * * *

## በእንስሳ ላይ

ሴትየዋ አብረዋቸው ከሚሰሩ ሰዎች ውስጥ አዋቂ ነው ብለው የሚገምቱት ሰው-ጋ ጠጋ ይሉና: -

- ስማኝኝ ወይ ጌታው! ይሄንን ሶሻሊዝምን የቀመሩት ፖለቲከኞች ናቸው ወይስ ሳይንቲስቶች?
- ምን ጥያቄ አለው! ፖለቲከኞች ናቸዋ!
- እኔም እንደዛ ነው ያሰብኩት! ቀማሪዎቹ ሳይንቲስቶች ቢሆኑ ኖሮ መጀመሪያ የሚሞክሩት በእንስሳ ላይ ነበር!

* * * *

## ውሳኔ!

ዶክተሩ ለሽማግሌው ታካሚ: -

- አባት! አሁኑኑ መጠጥ ካላቆሙ አይንዎ መታወሩ ነውና ምርጫዎን በፍጥነት ይወስኑ!



t.me/OLDBOOKSPDF

- ይሰሙኛል ዶክተር! እኔ እንደሆንኩ ከእንግዲህ ያላየሁት ነገር ይመጣል የሚል ግምት የለኝም .....

• • • •

## እንወራረድ!

ሽማግሌው አይሁድ ስራ ላይ እንዳለ ስለሞተ ሚስቱን ለመርዶ ለማዘጋጀት ሌላው ሽማግሌ አይሁድ የሟቹ አድራሻ ተሰጥቷቸው ተላኩ፡፡

- እባክዎ ባሏ የሞተባት ሴት /መበለት/ እዚህ ነው የምትኖረው?
- ይቅርታዎን! እኔ መበለት አይደለሁም
- እንወራረድ!

• • • •

## ምን እናንጠልጥል

ሽማግሌው በመንገድ ላይ ሲሄዱ ትልቅ ሰዓት ደጃፉ ላይ የተንጠለጠለበት ቤት ይገቡና፡-

- እባካችሁ ይችን ሰዓት ልትጠግኑልኝ ትችላላችሁ?
- አባት! ይሄ የሰዓት ማደሻ ቤት አይደለም፡፡
- ታዲያ የምን ቤት ነው?
- ይሄ የልጆች መግረዣ ክሊኒክ ነው ፡፡
- ታዲያ ለምን ይሄን የሚያክል ሰዓት በራችሁ ላይ አንጠለጠላችሁ?
- ታዲያ ምን እንድናንጠለጥል ፈለጋችሁ?

• • • •

## ሌላ ሰው

- ስማ ነፍሴ! ትላንትና በሳቅ ልሞት!



t.me/OLDBOOKSPDF

- ምን የሚያስቅ ነገር አገኘህ?
- ትላንት ማታ በቨሎዲያ ቤት አጠገብ ሳልፍ መስኮቱ ሙሉ ለሙሉ ስላልተዘጋ ራቁቱን ወደ ሚስቱ ሲሮጥ አይቼ በሳቅ ፈረስኩ ነው የምልህ! ቲ ቲ ቲ .....
- የበለጠ መሳቅ ትፈልጋለህ?
- እሺ!

- ቨሎዲያ ማታ ከኔጋ ስራ ነው ያደረው፣ ያየኸው ሌላ ሰው ነው ማለት ነው!

* * * *

## አበሻ

አንድ አበሻ የፖለቲካ ፈላስፋ ነው፣ ሁለት አበሻ - የፖለቲካ ፓርቲ ያቋቁማል፣ 3 አበሻ - የፖለቲካ ግምባር ይመሰርታል፣ 4 አበሻ የብሄር ንቅናቄ ያከሂዳል፣ 5 አበሻ እቁብ ይጠጣል፣ 6 አበሻ - እድርተኛ ይሆናል፤ 7 እማካይ የአበሻ የቤተሰብ ብዛት!

* * * *

## ግዛና አሳየኝ!

ሰውየው ከሆቴል ውስጥ ሲጋራ እያጨሰ ሲወጣ የመንገድ ላይ ኃይማኖት ሰባኪው ይቀርበውና: -

- ይቅርታ የኔ ወንድም! የምታጨሰው ሲጋራ ዋጋው ምን ያህል ነው?
- 40 ሳንቲም
- በቀን ስንት ሲጋራ ታጨሳለህ?
- 30 ሲጋራ



t.me/OLDBOOKSPDF

- ተመልከት በቀን 12 ብር ለነፋስ! .......ሲጋራ ብታቆም ግን በጥቂት አመታት ይህንን ሆቴል መግዛት እንደምትችል ታውቃለህ?
- አንተስ ሲጋራ አጭስህ ተውቃለህ?
- እረ በፍፁም!
- ታዲያ ይሄንን ሆቴል ለምን አትገዛውም? በነገራችን ላይ ሆቴሉ የኔ ነው!

*  *  *  *

## የዕድሜ ክልል

አውሮፕላኑ በውቅያኖስ ላይ ሲበር ወደቀና ተሳፋሪዎቹ ሁለት የተራራቁ ደሴቶች ላይ አረፉ:: ወንዶቹ በአንደኛው ደሴት ሴቶቹ ደግሞ በሌላኛው::

- ወንዶቹ ባረፉበት ደሴት ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ውይይት ጀመሩ:: 20 ዓመት እድሜ ያላቸው:-
- ምን እየጠበቅን ነው? እየዋኘን ወደ ሴቶቹ ጋር እንሂድ እንጂ! 30 ዓመት እድሜ ያላቸው:-
- ተረጋጉ! መንሳፈፊያ ጀልባ ነገር አሁኑኑ እንስራና በአንድ ላይ እንሻገራለን 50 ዓመት እድሜ ያላቸው:-
- አሁን ምን ያጨቃጭቀናል! ትንሽ ብንታገስ ሴቶቹ እራሳቸው ሲመጡ ታያላችሁ! 60 ዓመት እድሜ ያላቸው
- ጎበዝ! ምንድነው የምትንጫጩት? ከዚህ ሆኖ ሁሉም ነገር ቁልጭ ብሎ ይታይ የለም እንዴ?

*  *  *  *

## ድንቁም ባለ ፊት!

ስቃዩ የበዛበት በሽተኛ ዶክተሩጋ ሲሮጥ ሄዶ:-

- እረ ዶክተር! አይኔን ምን ነክቶኝ ነው? መጥፋቱ ነው!
- ቻል አድርገው እንጂ ምንድነው! ... ይሄማ ሄሞራይድ ነው!



t.me/OLDBOOKSPDF

- እንዴ! እንዴት ሂምራይድ እፊት ላይ ይወጣል?
- አሁን አንተም ፊት አለኝ ባይ ነህ?

* * * *

**ጥቅምት 10/98**

መስከረም 23/93 አንዲት ቆንጆ ልጃገረድ በወህኒ ቤት አጥር ጥግ ጥጉን ይዛ እየሄደች እያለ እስረኞች በመስኮት ቀዳዳ አይን ጥለውባታል። አንደኛው እስረኛ፡ -

- ቆንጆ ልጅ! ጥቅምት 10/98 ማታ ምንሰራ አለብሽ?

* * * *

**እንደለመደው!**

አብዮት ጥበቃው ሰክሮ ሰርዱን መክፈት ሲያቅተው፡-

- ክፈት! አብዮት ጥበቃዎች ነን።

* * * *

**ደግሞ ሌላ ስራ!**

የምርመራ ክፍል ኀላፊው ከጓደኛው ጋር ጨዋታ ይዘዋል፡ -

- ስመሆኑ ሚስትህን ደብድበህ ታውቃለህ?
- አብደሃል እንዴ! የራሴ የስራ ወረፋ መች አነሰኝ አልኩህ!

* * * *

**የችሎታው ሚስጥር**

- እንዴት ነው በ «ላምባዳ» ዳንስ እንደዚህ አሪፍ ልትሆን የቻልከው?
- መቀመጫዬ ላይ እርሳስ አስሬ 8 ቁጥር ለመፃፍ በመለማመድ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

**የመጽናኛ አባባል**

- ከዝንጀሮ ሻል የሚል መልክ ያለው ወንድ ሁሉ ቆንጆ ነው!

* * * *

**<u>የፓይለት ያለህ!</u>**

ሙሉ መንገደኞች ጭኖ በመብረር ላይ ባለው አይሮፕላን ውስጥ አስተናጋጇ የድምጽ ማጉያውን በመጠቀም: -

- ከቡራን መንገደኞቻችን ከመካከላችሁ ዶክተሮች ካላችሁ እባካችሁ ወደ ማብረሪያው ክፍል በአስቸኳይ ኑልን !
- አንድ ተሳፋሪ በፍጥነት ወደ ማብረሪያው ክፍል እየሮጠ ገባ:: ከትንሽ ደቂቃ በኋላ:
- ክቡራን መንገደኞቻችን ከመካከላችሁ ፓይለቶች ካላችሁ ወደ ማብረሪያው ክፍል በአስቸኳይ ኑልን!

* * * *

**<u>እንደው ቢገባህ!</u>**

ኢጣሊያዊው የሙዚቃ ቀማሪ ዲ.ጂ ቬርዲ 50 አመት እንደሞላው አድሚው 18 አመት ከሆነ ወጣት ሙዚቀኛ ጋር-ይገናኛል:: ወጣቱ ሙዚቀኛ ስለ ራሱና ስለ ሙዚቃው ብዙ አወራ:: ለፈለፈ:: ቬርዲም በትዕግስት ወሬውን ካስጨረሰው በኋላ እንዲህ አለው:-

- 18 ዓመት እንደሆነኝ ራሴን እንደታላቅ ሙዚቀኛ በመቁጠር ወሬዬ ሁሉ «እኔ» የሚል ብቻ ነበረ::
- 25 ዓመት ሲሞላኝ «እኔና ሞዛርት» ማለት ጀመርኩ::
- 40 አመቴ ላይ ስደርስ ወሬዬ «ሞዛርትና እኔ» በሚል ተቀየረ::
- አሁን ግን የማወራው «ሞዛርት» እያልኩ ብቻ ነው!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## «እግዚአብሔር ቅርባችን ስለሆነ»

የሮማው ጳጳስ አሜሪካንን በይፋ ለመጎብኘት ሄደው ሳለ ፕሬዝዳንት ኬኔዲ የኋይት ሃውስ ቢሮቸውን ሲያስጎበኟቸው ጠረጴዛቸው ላይ በዛ ያለ ስልክ ስላዩ:-

- ፕሬዚዳንት ኬኔዲ! ይሄ ሁሉ የስልክ መዓት ምን ያደርግልዎታል? በዚህ ዓይነት ከእግዚአብሄርም ጋር ግንኙነት ሳይኖርዎት አይቀርም ማለት ነው!
- አዎ ጳጳስ ሆይ! ግንኙነት አለን!
- ታዲያ ምናለ እኔንም አገናኙኝ?
- ይቻላል! ግን በደቂቃ 120 ሺህ ዶላር ያስከፍልዎታል .......

ከተወሰነ ግዜ በኋላ ጳጳሱ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጡና ጃንሆይ ቢሮም በብዛት ስልክ ስላዩ: -

- ጃንሆይ! ምንድነው ይሄ ሁሉ ስልክ እናንተም እንደ አሜሪካኖች ከእግዚአብሄር ጋር ትገናኛላችሁ ማለት ነው?
- ልክ ብለዋል ጳጳስ ሆይ እንገናኛለን!
- ታዲያ ለናንተ ዋጋው ውድ አይሆንባችሁም?
- ውድ አይደለም በደቂቃ 2 ብር ሂሳብ ነው
- እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ከአሜሪካ እንኳን አገናኙኝ ብላቸው በደቂቃ ከ100 ሺህ ዶላር በላይ ያስከፍልሃል ስላሉኝና አቅሜም ስላልፈቀደልኝ ነበር ሳልደውል የቀረሁት:: እንዴት እናንተ ጋር 2 ብር ብቻ ሆነ?
- ጳጳስ ሆይ! እኛጋ 2 ብር ብቻ የሆነው ከእኛ ጋር ጥሪው የአገር ውስጥ ስለሆነ ነው!

* * * *

## <u>ሳይደርስኝ</u>

በእብዶች ሆስፒታል ኮሪደር ውስጥ ታካሚው መስኮት ላይ አስደግፎ የሆነ ነገር ኤሮግራም ላይ ይጽፋል:: ዶክተሩ ምን እንደሚጽፍ ለማወቅ ይጓጓና: -



t.me/OLDBOOKSPDF

- ምን እየፃፍክ ነው?
- ደብዳቤ እየፃፍኩ ነው ዶክተር!
- ጎሽ! ግን ለማን ነው የምትጽፈው?
- ለራሴ!
- እስቲ ምን እያልክ እንደፃፍክ አንብብልኝ?
- አይ ዶክተር የምታስቅ ነህ! ሳይደርሰኝ ምኑን አውቄ ነው የማነብልህ?

* * * *

መንገደኛው በመንገደኛው ጋዜጠኛ ሲጠየቅ: -

- ሴቶች ሚስጢር ቀብረው መያዝ ይችላሉ?
- በሚገባ ይችላሉ! የሚችሉት ግን ከሚስጥሩ ጋር አብረው ከተቀበሩ በኋላ ነው::

* * * *

**ጥብሱ ቅቅሉን**

ሆቴል ቤት ገብቶ ዶሮ አሮስቶና አብሮ የሚቀርብ በቆሎ ቅቅል ያዛል::

- አስተናጋጁ በ2 ደቂቃ ውስጥ ምግቡን አቀረበለት: - ከ2 ደቂቃ በኋላ: -
- ስማ! አስተናጋጅ ይሄን ዶሮ ምናለ በደንብ ብትጠብሱት ኖሮ?
- ምነው ጌታዬ! ምን ተፈጠረ?
- ዶሮው በቆሎ ቅቅሉን እንዳለ ጨረሰው!

* * * *

**ክብርም ገንዘብም**

በፋብሪካ ውስጥ የስራ ምርታማነት ግምገማ ተደረገና 3 ኮከብ ሰራተኞች ተመረጡ:: የፋብሪካው ስራ አስኪያጅ አሸናፊዎቹን ለሰራተኛው ከማስተዋወቃቸውና ከመሸለማቸው በፊት ሶስቱንም ቢሯቸው ያስጠሩና እንኳን ደስ ያላችሁ ካሏቸው በኋላ አንደኛውን: -



t.me/OLDBOOKSPDF

- ሜዳሊያ እንሸልምህ ወይስ 10 ብር?
- የምን ሜዳሊያ ነው! ቢከፋም ቢለማም ገንዘብ ይሻለኛል 10 ብሩን ስጡኝ።
- አንተስ?
- አሁን 10 ብር ምን ላደርግበት ነው? ማስታወሻነቱና ኩራቱ ስለሚበልጥብኝ ሜዳሊያው ይሻለኛል።
- ለ3ኛውም ተመሳሳይ ጥያቄ ሲቀርብለት
- ጌታዬ! በመጀመሪያ ምርጫዬን ከመናገሬ በፊት የሜዳሊያው ዋጋ ይነገረኝ?
- የሜዳሊያው ዋጋ 1 ብር ነው
- እንግዲያውስ 1 ሜዳሊያና 9 ብር ይሰጠኝ!

* * * *

## ለምቾት

ሬሳ ሳጥን መሸጫ ሱቅ ውስጥ:-

- ይሄኛው ሳጥን 30 ብር ያኛው ሳጥን 60 ብር የሆነበት ምክንያቱ ምንድነው?
- ባለ 60 ብሩ መገለባበጥ ስለሚያስችል!

* * * *

## ወቅት ሲቀያየር

3 እስረኞች ተቀምጠው ሲያወሩ: -

- አንተ ለምን ታሰርክ?
- ታምራት ላይኔ ዐረ-ህዝብ ነው ብዬ
- አንተስ?
- ታምራት ላይኔ ዐረ-ህዝብ አይደለም ብዬ



t.me/OLDBOOKSPDF

• አንተስ?
• ታምራት ላይኔ ነኝ!

*          *          *          *

## የቮድካ አፍቃሪዎች መፈክር

«ቀይ ወይን ለጤንነት ይጠቅማል፣ ጤንነት ደግሞ ቮድካ ለመጠጣት!»

*          *          *          *

## እግረመንገድህን!

ሰውየውን ሚስቱ አትወደውም:: በቤቱ ውስጥ ጭቅጭቅ አሳበደው! ስለዚህም እራሱን ለማጥፋት ወሰነና ከሚኖርበት 7ኛ ፎቅ አፓርታማ ላይ ለመዝለል ሲዘጋጅ ሚስቱ አየችውና: -

• ቆይ! ቆይ! በዛውም ቆሻሻ ትደፋልኛለህ!

*          *          *          *

## ምርጫ

ሚስት ወደ ባሏ ቀርባ በንዴት: -

• አሁኑኑ ወስን! ከእኔና ከቮድካ ማንን ነው የምትመርጠው?
• ከስንት ቮድካ?

*          *          *          *

## በፕሬዚዳንት ምርጫ ሰሞን

ዶክተር እባክዎ! ድምጼ መዘጋቱ ነው!

• ሰሙ ወይ አባት! ይረጋጉ:: ድምፅዎን የማይሆን ሰው መርጠውበታል ማለት ነው እሱን ይጠይቁ!

*          *          *          *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ማን ፈለገኝ

- ቢን ላደን ማታ ወደ ቤቱ ሲገባ ለሚስቱ፡ -
- የፈለገኝ ሰው ነበር?

* * * *

## ጨዋ ሰው ግን...

- በፓሪስና በጨዋ ሰው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ፓሪስ ምንጊዜም ፓሪስ ነው።

* * * *

## የክፍለ ዘመኑ ክርክር

21ኛው ክፍለዘመን የሚጀምረው ከ2000 እ/ም ነው ወይስ ከ2001 እ/ም በማለት የአለም ታወቂ ሳይንቲስቶችና የኃይማኖት ጠበብቶች፤የታሪክ ሊቃውንት ታላቅ ክርክር ያደረጉበትንና በሃሳብ የተለያዩበትን ጉዳይ የአዲስ አበባው ምስኪን ሲጋራ አጫሪ፡ -

«የመጀመሪያው ፓኮ 20ኛው ሲጋራ ላይ ያልቅና፣ 2ኛው ፓኮ 21ኛው ሲጋራ ላይ ይጀምራል» በማለት በቀላሉ እቅጩን መልስ አስቀምጦታል!

* * * *

## ብቸኛው ልዩነት

ዊንስተን ቸርችል ለጋዜጠኛው፡ -

ስታሊንና ሂትለር በምንድነው የሚለያዩት?
በረዝ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ጉቶ ሆኜ

ልጁ ከጨዋታ መልስ እቤቱ ሲገባ እናቱ ታየውና፡-

- እንዴ! ምንድነው እንዲዚህ የበሰበሰከው?
- ከጓደኞቼ ጋር «ውሻ ውሻ» ስንጫወት
- የምን «ውሻ ውሻ» ነው የምትለው አልገባኝም?
- እነሱ ውሻ ሆነው እኔ ጉቶ ሆኜ ......

*　　　　*　　　　*　　　　*

## ፍርስራሹን መውደቂያ አሳጡት!

ሶቭየት ሕብረት ውስጥ አይሁዶች ተጨቁነውና ተጠልተው ይኖሩ ነበር:: አንዱ አይሁድ በመንገድ ላይ ሲሄድ ከፎቅ ቤት ላይ የወደቀ የሸክላ ፍርስራሽ እናቱን ይበረቅሰዋል:: ሰውየውም ንዴቱን መቆጣጠር ስላልቻለ በጩኸት ህዝብ እንዲሰማው፡ -

- ምን አይነት ጉድ ነው! በዚህ አገር የሸክላ ፍርስራሽ ሰው እናት ላይ እየወደቀ በመንገድ መሄድ እንኳን አልቻልንም!

ሁኔታውን ያስተዋለ መንገደኛ የተመታው አይሁድ መሆኑን ስላወቀ እሱም ህዝብ እንዲሰማው በጩኸት፡ -

- ተመልከቱ! በየቦታው የማይገቡበት የማይሄዱት ቦታ የለም የቤት ፍርስራሽ እንኳን መውደቂያ አጣ!

*　　　　*　　　　*　　　　*

## ያለ አንድ እንክን?

- ሚስት ለማግባት አስቤ ነበር!
- ጥሩ ነው አግባ!
- ግን ልጅቷ አይነስውር ሆነችብኝ
- ትሁና! ስከረህ ስትመጣ አታይህ! ገበናህ ሁሉ ይደበቅልሃል!



t.me/OLDBOOKSPDF

- እሱስ ልክ ነው! በዚህ ላይ ደንቆሮ ነች
- ምን ያህል እድለኛ መሆንህ አይገባህም ዛሬት ስላንተ አትሰማምና ስላም ይኖርሃል!
- እሱም ልክ ነው! ሌላው ደግሞ ዱዳ ነች
- ዝምተኛ ሚስትን የመሰለ ምን ነገር አለ
- ልክ ነው! ከዚህ በተጨማሪ ከጀርባዋ ትንሽ ጎበጥ ትላለች
- ምን ነካህ አንተ ሰው!? የምታገባት ሴት እንደው አንድም እንከን አይኑራት ነው የምትለው?

* * * *

## ቢጫና ቀይ ካርድ

የእግር ኳስ ጨዋታው እንደተጠናቀቀ መልበሻ ክፍል የሚሄደውን ታዋቂ ተጫዋች ጋዜጠኞች ከበቡትና፡ -

- እንዴት ነው በባላጋራህ ቡድን አደገኛ አጀማመር እንሸነፋለን ብለህ ተደናግጠህ ስለነበር ነው በፋውል መጫወት የጀመርከው?
- በፍጹም የደነገጥኩት ዳኛው ቢጫ ካርድ ሲያሳየኝ ነበር?
- ሰምን ደነገጥክ ቀይ አላሳየህ?
- ከካርዱጋ ከሚስቱ ጋር የተነሳሁትን ፎቶራፍ አብሮ ስላሳየኝ ነው!

* * * *

## <u>በጭራው ሲያስነቃ!</u>

እንግሊዛዊው ከውሻው ጋር ካርታ እየተጫወተ እያለ የሩት ወዳጁ ሊጠይቀው መጣ፡-

- የሚገርም ነው! ምን አይነት ብልጥ ውሻ ነው ያለህ? ካርታ መጫወት ሁሉ የሚችል! ይሄ የጉድ ነው!



t.me/OLDBOOKSPDF

- አንተ ደግሞ ዝም ብለህ ነው! ምኑ ነው ብልጥ! አታየውም ጭራውን እየቆላ ጥሩ ካርታ እንደደረሰው ሲያስነቃ!

*   *   *   *

## የአፋልጉን ማስታወቂያ

ውሻችንን አግኝቶ ላመጣልን ጥሩ አርገን ወሮታ እንከፍላለን !

| | |
|---|---|
| የመልኳ አይነት:- | ጥቁርና ነጭ |
| ልዩ ምልክት:- | ግራ አይኗ የጠፋ፣ የቀኝ የኋላ እግሯ ሰባራ፣ የጀርባዋ ፀጉር በፈላ ውሃ የተላጠ፣ ጭራዋ የተቆረጠ |
| መጠሪያ ስሟ:- | «እድላዊት!» |

*   *   *   *

## ቅንጣቢ ስለሚወድቅላት

ውሻዋ ከፀጉር አስተካካዩ እግር ስር ተኝታ ጭራዋን ትቆላላች:: ሁኔታዋ የገረመው ፀጉር አስተካካይ

- ለምንድነው ውሻህ እንደዚህ አፍጥጣ የምትመለከተኝ?
- ምን መሰለዎት! እንዳንዴ ወለል ላይ የጆሮ ቅንጣቢ ስለሚወድቅላት ነው! ለምን እንደሆን አላውቅም እንደ ጆሮ የሚጥማት ምግብ የለም!

*   *   *   *

## አባባል

- 100 ብር የባንክ ብድር ካለብህ እሱ ያንተ ችግር ነው
- 1 ሚሊዮን የባንክ ብድር ካለብህ ግን እሱ የባንኩ ችግር ነው!

*   *   *   *



t.me/OLDBOOKSPDF

## አንተ እሱን ትላለህ...

ሩሲያ ውስጥ ብዛት ያለው ሰው ቪዛ ለመግባት ወረፋ ይዞ ተሰልፏል:: ድንገት ከሰልፉ ውጭ አንድ ሰው ይመጣና: -

- ጎበዝ ይቅርታ! እንዴ ታሳልፉኝ? መኪና መንገድ ዳር ደርቤ አቁሜ ነው የመጣሁትና አባካችሁ ቅድሚያ ስጡኝ .....
- ወንድም! ትቀልዳለህ እንዴ? አንተ መኪና አቁሜ ነው? ትላለህ እኛ ፋብሪካ አቁመን ነው የመጣነው ....

## ድግሪ ከሌለህ

አውራ ዶሮው ሙዚቃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ይሄዳል መዝጋቢው:-

- አንተ ደግሞ ምን ትምህርት ያስፈልግሃል? በተፈጥሮ ሳትማር ጥሩ አርገህ ሙዚቃ መጫወት ትችል የለም እንዴ!
- ልክ ነህ አውቃለሁ! ግን ምን ታደርገዋለህ የዘመኑ ሴት ዶሮዎች ድግሪ ከሌለህ ዞር ብለውም አያዩህማ!......

* * * *

## ሲቆጭ!

- ከስ አወላቂው ሙዚቃ ሲያይ ገብቶ የኪቦርድ ተጫዋቹን እለንጋ ጣቶች እያየ በመቆጨት ....
- ያሳዝናል!.... አሁን ይህንን የመሰለ ጣት ለማይረባ ነገር ይጠቀምበት?

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሰመቼ ፈለግሽው

እንትናዬ! አትታዘቢኝና ትውውቃችን ከ12 ሰዓት በላይ ቢሆንም ለምን እንደሆነ አላውቅም ስምሽ ይጠፋብኛል ... ማን ነበር ያልሽኝ?

- ተጠያቂዋ ትንሽ ካሰበች በኋላ: -
- ስሜን የፈለግሽው ለመቼ ነው?

*   *   *   *

## ለዚህ ነዋ!....

ሁለት ሰካራም ባልና ሚስቶች መጠጫ ገንዘብ አጥሯቸው ተክዘዋል: -

- ሚስት - ልጆችህን በቢራ ለውጥ ብትባል ትለውጣለህ?
- ባል - በፍፁም! እንዴት ተደርጎ!
- ሚስት - እሃ! ለዚህ ነዋ ዶሮዎቻችን እንቁላል መጣል ያቆሙት!

*   *   *   *

## ግማሾቹ አባላት

የምክር ቤት ስብሰባ ላይ ተወካዩ በመናደድ ተነስቶ: -

- ግማሽ የሚሆኑት የምክር ቤት አባላት ብቃት የለሽና ጉብኞች ናቸው!
- አፈ ጉባኤው ወዲያው: -
- ይህ አባባልማ ክብረነክ ስለሆነ ምክር ቤቱን ይቅርታ ለመጠየቅ የተናገሩትን ቃል እንዲያስቡ አጥብቄ እጠይቃለሁ!

*   *   *   *

ከረዥም ፀጥታ በኋላ ተወካዩ ይነሳና: -

- ይቅርታ! ቃሌን አንስቻለሁ ግማሽ የሚሆኑት የምክር ቤት አባሎች ብቃት የለሽና ጉብኞች አይደሉም::



t.me/OLDBOOKSPDF

የተማሪዎች አጠቃላይ የህክምና ምርመራ ሲካሄድ የአንገት በላይ ሃኪሙ የ፲ኛ ክፍል ተማሪውን እየመረመረ ነው።

- ማሙሽ! ጆሮህና አፍንጫህን በተመለከተ የተቸገርክበት ነገር አለ?
- አለ! ሹራቤን ለመልበስ ሁልጊዜም እንዳስቸገሩኝ ነው!

•　　　•　　　•　　　•

<u>ምን የማያሟሟው አለ!</u>

አንድ ወጣት ቡና ቤት ገብቶ ሻይ አስቀርቦ ስኳሩን እያማሰለ ከአጠገቡ አልኮል መጠጥ ጨብጠው ከፊት የሚተከዙትን ሰውዬ፡ -

- አባት! አልኮል መጠጥ ስኳርን ያሟሟል?
- በደንብ ነዋ! ምን ስኳርን ብቻ ወርቅን፤ ድንጋይ ቤትን፣ መኪናን፣ ትዳርን፤ ፍቅርን፤ ደስታን ፤ ጤንነትን... ምን የማያሟሟው ነገረ አለ ብለህ ነው ?

•　　　•　　　•　　　•

<u>«ብር ቀስም»</u>

ስማ እስቲ! አንድ የማይገባኝን ነገር ልጠይቅህ። ወደ ደሃ ሰው ስትሄድ ይሽቆጠቁጥልሃል፤ በሚችለው ሁሉ ይረዳሃል። ወደ ሃብታም ሰው ስትሄድ ግን ሲያይህም አይፈልግም። እንደው ይሄ ብር የሚባል ነገር የሰውን ማንነት ይሄን ያህል የመለወጥ ኃይል አለው ማለት ነው?

•　　　•　　　•　　　•

**ተጠያቂው ማስረዳት ጀመረ፡ -**

- በመስታወት መስኮት ውስጥ ተመልከትና ምን እንዳየህ ንገረኝ
- ህፃን ያዘለች ሴትዮ የገበያ ዘንቢል ይዛ
- አሁን ደግሞ የቁም ሳጥኑን መስታወት እየውና ምን እንዳየህ ንገረኝ
- ከራሴው ምስል በቀር ምንም ነገር አይታየኝም



t.me/OLDBOOKSPDF

- ልዩነቱን አየኸው? ንፁሁን የመስታወት መስኮት ከጀርባው ብር ቀለም ብትቀባው ራስህን ብቻ ነው የምታየው!

* * * *

### ራሱን ነው!

ጠላ ቤት ገብቶ እንድጊዜ ፉት ካለ በኋላ ስላልጣመው: -

- እሜቴ! የዛሬ አስራ አምስት ቀን የሸጡልን ጠላ እንዴት ቆንጆ ነበር!
- እረ ወላዲትን! ዛሬም ቢሆን ራሱን ነው ያቀረብኩላችሁ!

* * * *

### ስዊዛዊ አትመስልም

ለንደን ውስጥ ስዊዛዊውና አሜሪካዊው ቱሪስት ይገናኛሉ:

- ከየት ሃገር ነህ?
- ከአለም ታላቋ ሃገር !
- የሃገር ልጆች ነና! እንግሊዝኛህ ግን ስዊዛዊ አይመስልም

* * * *

### መጽሐፉ ያዛላ!

- ወንድም! አልኮል መጠጥ የጤንነትህ ጠላት አይደለም ወይ?
- ጠላት ነው!
- ታዲያ ለምንድነው የምትጠጣው?
- ምን ታረገዋለህ? መጽሃፉ «ጠላትህን እንደራስህ አርገህ ውደድ» ይላላ!

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## ተሳካ!

በታወቀ ሬስቶራንት በር ላይ «ያዲስ ሩሲያዊ» ሞዴል 600 መርሰዲስ መኪና ቆሟል። ሹፌሩም መሪው ጋር ተቀምጦ እንቅልፍ ያዳፋዋል። ድንገት የሆነ ሰው ይቀሰቅሰውና የታሸገ ደብዳቤ በመስጠት «በአስቸኳይ ለአለቃህ እንዲደርስ አድርግ!» ብሎት ጥሎት ይሄዳል።

ሹፌሩም እንደተነገረው ወዲያው ደብዳቤውን ለአለቃው ለማድረስ ተጣድፎ ሬስቶራንት ውስጥ በመግባት ይሰጠዋል። አለቃውም በነገሩ ተገርሞ ደብዳቤውን ፈጥኖ ይከፍትና ሲያየው «ከተሳካ አሪፍ ነው! ካልተሳካ ምን ታደርገዋለህ!?» የሚል መልዕክት ተጽፎበታል።

አስተናጊው ግራ በመጋባት «ማን ነው የሰጠህ? ምን ለማለት ፈልጎ ነው?» ይልና ለሹፌሩ መልዕክቱን ቢያሳየውም ሹፌሩ የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

አለቃውም «ሂድ እስቲ ድንገት ሰውየውን ውጭ ካገኘኸው ጥራውና ማን እንደላከው ልጠይቀው» ይልና ሹፌሩን ያዘዋል።

ሹፌሩም ደቂቃ ሳይሞላ ተመልሶ፡ -

ተሳካ!

ምን ነው የተሳካው?

መኪናችን መሰረቁ!

*     *     *     *

## የመቅጠሪያ ቅፅ

ልጅቷ « አዲስ ሩሲያዊ» የከፈተው ካምፓኒ  ፐርሶናል ቢሮ ትገባና፡-

- ስራ ፍለጋ ነበር የመጣሁት
- ሰውየውም ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ጥሩ የሰውነት ቅርጽ ላላቸው ሴቶች የሚሆን የዋና ልብስ ከሳጥን ውስጥ አውጥቶ እያቀበላት፡ -
- መልካም! ይሄንን የአዲስ ተቀጣሪዎች ቅጽ ሙይና እምጪ....



t.me/OLDBOOKSPDF

## ዜና ጋብሮቭ

ሰሞኑን በጋብሮቮች ከተማ የአለም የስስታሞች ሻምፒዮና ውድድር ከተካሄደ በኋላ የውድድሩ አዘጋጅ ኮሚቴ ለአሸናፊዎች የተዘጋጀው የወርቅ፣ የብርና የነሃስ ሜዳሊያ ለማንም እንዳይሰጥ በአንድ ድምጽ ወሰነ!

* * * *

## በእግርህ አቆምሃለሁ!

- ዶክተሩ በ2 ሳምንት ጊዜ ውስጥ በእግርህ አቆምሃለሁ አለኝ
- እናሳ?
- እውነቱን ነበር! ለታከምኩበት ሂሳብ መኪናዬን ሸጬ ከፈልኩታ!

* * * *

## የምግብ ፕሮግራም ለውጥ

. በሂትለር ማጎሪያ ካምፕ ውስጥ ለታሰሩ እስረኞች የጥበቃው ኃላፊ ንግግር እያደረገ ነው፡ -

- ከዛሬዋ ቀን ጀምሮ የእስር ቤታችን እመጋገብ ተቀይሮ ምግብ የሚታደላችሁ 3 ጊዜ ይሆናል!
- ብራቮ! /የማያቋርጥ ጭብጨባና ፉጨት/
- ሰኞ፣ ረቡዕ እና አርብ!

* * * *

## የጥያቄ ለውጥ

ወንደላጤው ለጓደኛው

- አሁን ተኖረና አረጀሁ ማለት ነው?
- ደግሞ ከመቼ ወዲህ ነው እንደዚህ «ተስፋ ቢስና አረጀሁ ባይ» የሆንከው?



t.me/OLDBOOKSPDF

- ከሴቶች ጥያቄ.... ድሮ «ለምን አታገባም?» ይሉኝ የነበሩ ዛሬ ግን «እንዴት አላገባህም?» ብለው መጠየቅ ስለጀመሩ.....

•   •   •   •

## እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ...

በፈረንሳይ ሃገር ለደረሰው የውሃ መጥለቅለቅ ላስፈለገው አስቸኳይ እርዳታ አሜሪካ 3 ቢሊዮን፤ ጃፓን 5 ቢሊዮን ዶላር ሲረዱ፣ ሶቭየት ህብረት 10 ሚሊዮን የዋና ማስተማሪያ መጽሃፎች ላከች!

•   •   •   •

## በማርስም ላይ

የሬዲዮ ጥያቄ በኢትዮጵያ: -

- በማርስ ላይ ህይወት አለ?
- በማርስም ላይ ሕይወት የለም!

•   •   •   •

## <u>ቁጠባ!</u>

ጋብሮቮ ጓደኛውን ሊጠይቅ እቤቱ ሄዶ: -

- ምን እያደረክ ነው?
- የአይነ ስውራን ፊደል እያጠናሁ ነው።
- ምን ያደርግልሃል? ዶክተር ወደፊት አይንህ ይታወራል አለህ እንዴ?
- እረ በፍጹም! ማታ ማታ መጽሃፍ ለማንበብ ምን መብራት አስቃጠለኝ ብዬ....

•   •   •   •



t.me/OLDBOOKSPDF

## እሱም በተራው

ሰካራሙ ሰውዬ በራሱ ስህተት በእሳት ተቃጥሎ ሆስፒታል ገብቷል:: ዶክተሩም ባለቤቱን ያስጠራና: -

- ባለቤትዎ በከባድ ሁኔታ ቆዳው በእሳት ስለጋየ ከእርስዎ ቆዳ ለማስወት ካልተካንለት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው ያለው
- ዶክተር! ይሄ ሰው በትዳር ዘመናችን ሁሉ እያንገበገበኝና እያቃጠለኝ 3 ጊዜ መላ ቆዳዬን የላጠኝ ሲሆን በትዕግስትና አይቼ እንዳላየ በመሆን የተላጠ ቆዳዬን እየተካሁ ኖሬአለሁና ዛሬ እሱም በተራው የራሱን ቆዳ ያብቅል!

*　　*　　*　　*

## ከዘፈኑ አስቀድሙኝ

ሁለት ወንጀለኞች የሞት ቅጣት ሊፈፀምባቸው አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ቅጣቱን አስፈፃሚው ግለሰብ አንደኛውን: -

- ሊደረግልህ የምትፈልገውን የመጨረሻ ምኞት ተናገር!
- ሙዚቃ አፍቃሪ ስለሆንኩ ከመገደሌ በፊት የ__________ን (የማትወዱትን ዘፋኝ ስም ያስገቡ) ዘፈን እንዲዘፈንልኝ እጠይቃለሁ!
- ችግር የለም! የጠየቅከው ዘፋኝ ሙዚቃ ይደረግልሃል! አንተስ የመጨረሻ የምኞት ጥያቄህ ምንድ ነው?
- በጣም የምለምናችሁ ጓደኛዬ የጠየቀው ዘፋኝ ዘፈን ከመዘፈኑ በፊት ቀድማችሁ እንድትሰቅሉኝ ነው!

*　　*　　*　　*

## እንዳልሰማሁ ቁጠረው

- የሆነ የግል ሚስጥሬን ልነግርህ አስቤ ነበር
- ንገረኝ! ሚስጥርህን ከኔጋ ይገኘው መቃብሬ እገባለሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF

- ያልጠበኩት ከባድ ዕዳ ውስጥ ገብቼልሃለሁ:: በጣም በአስቸኳይ ገንዘብ ያስፈልገኛል
- ፈፅሞ አታስብ!... በቃ እኔ ምንም ነገር እንዳልሰማሁ ቁጠረው

* * * *

## ሰጥቶ መቀበል

በተባበሩት መንግስታት በዩጎዝላቪያው ጦርነት ተዋጊ አውሮፕላን አብራሪዎች ለመቅጠር የተቋቋመው ኮሚሽን አመልካቾችን በመገምገም ላይ ነው::

በመጀመሪያ ፈረንሳዊው ቀረበ: -

- ምን ያህል ጊዜ አብርረሃል?
- አንድ ሺህ ሰዓት
- በጣም ጥሩ! ምን ያህል እንዲከፈልህ ትፈልጋለህ?
- በሳምንት 3 ሺህ ዶላር
- ለምን 3ሺህ ዶላር?
- እንዴት ነው... 1 ሺህ ለራሴ፣ አንድ ሺህ ለቤተሰቤ፣ 1ሺህ ለፍቅረኛዬ

በመቀጠል ሩሲያዊዉ ቀረበ

- ምን ያል ጊዜ አብርረሃል?
- 2 ሺህ ሰዓት አብርሬአለሁ ለዚህም የተሸለምኩት ሊሻን አለኝ
- በጣም ጥሩ ምን ያህል እንዲከፈልህ ትፈልጋለህ?
- 6 ሺህ ዶላር በሳምንት
- እንዴት መሰላችሁ 2ሺህ ለራሴ፣ 2ሺህ ለቤተሰቤ፣ 2 ሺህ ለቮድካዬ

በመጨረሻም እንግሊዛዊው ቀረበ

- ምን ያህል አብርረሃል?
- የበረራ እንኳን ብዙ ልምድ የለኝም
- ምን ያህል እንዲከፈልህ ትፈልጋለህ?



t.me/OLDBOOKSPDF

- 9 ሺህ ዶላር በሳምንት
- ለምን?
- እንዴት መሰላችሁ ... 3ሺህ ለእናንተ፣ 3ሺህ ለእኔ፣ በተረፈው 3ሺህ ፈረንሳዊውን ፓይለት እቀጥራለሁ?

*　　　*　　　*　　　*

ጥያቄና መልስ

አሞሮች ለምንድነው የቀስት ቅርጽ በመስራት ወደ ደቡብ የሚበሩት?

- ከፊት ያለው ካርታና ኮምፓስ ስለያዘ ....

*　　　*　　　*　　　*

አባባል

በዚህ አለም ላይ ሰካራሞች ባይኖሩ ኖሮ መልከጥፉ ሰዎች አይኖሩም ነበር።

*　　　*　　　*　　　*

አለም የዕብዶች መኖሪያ!

የስነ አይምሮው ሃኪም ከ15 ዓመት ግልጋሎት በኋላ የደረሰበት እውነት:-

- በዚህ አለም ላይ በሽታው ተመርምሮ ያልታወቀለት እንጂ ጤነኛ ሰው የለም!

*　　　*　　　*　　　*

የመናጢው ልጅ

የታወቀው «አዲስ ሩሲያዊ» ሚሊየነር ከቤቱ ላደረሰው ባለታክሲ 10 ሩብል ጉርሻ ሲሰጠው ሹፌሩ በመቀየም :-

- «ትላንት ከቤቷ ያደረስኳቸው ልጅህ እንኳዋን 20 ሩብል ጉርሻ ስትሰጠኝ አንተ እንዴት 10 ሩብል ብቻ ትሰጠኛለህ?»
- «እሷ አባቷ ሚሊየነር ስለሆነ ነው ። እኔ የመናጢ ደሃ ልጅ ነኝ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

## አየር ባየር

- የ «አዲሶቹ ሩሲያውያን» ንግድ፡-
- «ስማ እንጂ! አንድ ፉርጎ ስኒከር ሚማ ልትወስድልኝ ትችላለህ? »
- «ምን ችግር አለው! ጠቅላላ ዋጋው የአንትፍ ምሬት ያህል ቀላል አይደለች እንዴ!»
- ከዛ በኋላ ይለያያሉ። አንዱ ስኒከር ሌላው ገንዘብ ፍለጋ!

*                    *                    *                    *

## ከ3-5 አመት

- «አዲሱ ሩሲያዊ» ያስደነቀውን ነገር ለጓደኛው ይዞ መጥቶ፡-
- «ስማ ! ለካስ የወለድኩት ተአምረኛ ልጅ ነው!»
- «ለምን እንደዚህ ልትል ቻልክ?»
- «ምን መሰለህ ለልደቱ ስጦታ ተገጣጣሚ ድልድይ ገዛሁለትና በሶስት ቀን ውስጥ ግጥምጥም አድርጎ ጨረሰው!»
- «ታዲያ ይሄ ምን ያስደንቃል?»
- «ስጦታው የታሸገበት ካርቶን ላይ የሚለው እኮ «ከ3-5 ዓመት» ነው»

*                    *                    *                    *

## <u>የኔን ደም</u>

ጋብሮቭ አገር ለጉብኝት የሄደው ሃብታም አሜሪካዊ ቱሪስት የመኪና አደጋ ያጋጥመውና ሆስፒታል ሲወስዱት ደም አስፈለገው። «ደም የሚለግስ» ጋብሮቭ ቢገኝም በቅድሚያ ገንዘብ ጠየቀ። ደም ተቀባዮቹም ጉዳተኛው ሚሊየነር አሜሪካዊ እንደሆነና ሲድን ደህና አድርጎ እንደሚከፍለው ገለፁለት።

ጋብሮቭ - «አይሆንም! አልፈልግም! ፈፅሞ አልስማማም!»

ደም ተቀባይ - «ለምን?»

ጋብሮቭ - «ደሙ በኔ ደም ከተቀየረ በኋላ እንደማይከፍለኝ አውቀዋለኋ!»



t.me/OLDBOOKSPDF

## የሚጥምህን እንዳላረግ

ሩሲያዊው ባል ሚስቱን :-

- «ይሄ አዲሱ ኮፍያሽ ምንም አልጣመኝም »
- «ውዴ! ምን ታደርገዋለህ? የቮድካ ጠርሙስ ኮፍያ አይሆን ! »

* * * *

## <u>200 ዶላር</u>

ቱሪስቱ « ሩሲያ ሆቴል » በር ላይ ያገኛትን ቆንጆ ልጅ :-

- « እንግሊዝኛ መናገር ትችያለሽ? »
- « በመጠኑ »
- « ምን ያህል ? »
- « 200 ዶላር »

* * * *

## <u>ቀበቶ እሰሩ.....</u>

የገጠር አከባቢው የምክር ቤት ተወካይ ለስብሰባ ወደ ዋና ከተማው መጥቶ ከአውሮፕላን እንደወረደ የሚቀበለው ሰው የተወካዩ ሱሪ ወደታች ወርዶ ስላየው:-

- «ምነው? ሱሪህ እኮ ጭራሽ ወደታች ከመውረዱ የተነሳ አደናቅፎ ሊጥልህ ነው»
- «ምን ላድርግ? እነዚህ አስተናጋጆቹ « እንዴ ቀበቶ እሰሩ ሲሉ እንዴ ፍቱ ሲሉን መልሰው እሰሩ ሲሉ .........»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የፍልውሃ ታክሲ

የሰፈሩን ልጅ መንገድ ላይ ታክሲ ስትጠብቅ ያገኛትና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ:-

- «ወደ ሰፈር ለመሄድ ታክሲ ልይዝ ነው እንቺም እንደዛው መሰለኝ»
- «አዎ እኔም ታክሲ ለመያዝ ነው የቆምኩት»

ከትንሽ ዝምታ በኋላ:-

- «ስሚ እንጂ ሮዛ! አንቺ እኮ በጣም አዋቂ ሰው ነሽ! መቼም የማታውቂው ነገር የለምና እስቲ ንገሪኝ! የግራ መዳፌን ዝም ብሎ ያሳክከኛል!»
- «ጥሩ ነገር ነው! ገንዘብ ልታገኝ ነው! »
- «የቀኝ መዳፌንም ያሳክከኛል!»
- «ጤንነት ነው!»
- «ሆዴንም እንደዛው ያስፎክተኛል!»

ነገሩ ቢገርማትም « ጥጋብ ነው! እንጀራ ይወጣልሃል!»

- «አንገትና ትከሻዬን የሚያሳክከኝስ ምንድነው?»
- «ስማኝ ክቡ! የሰፈር ታክሲው ቀርቶብህ የፍልውሃውን ታክሲ ይዘህ ገላህን ብትታጠብ አይሻልም?»

* * * *

## የጓደኛ መፈተኛ

ለወንዶች :-

- «ታማኝ የወንድ ጓደኛ በቀውጢ ቦታ፤ ታማኝ የሴት ጓደኛ ደግሞ በመዝናኛ ቦታ ላይ ይለያል!»

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

ሁለት ሴት ጓደኞች ስለወንዶች እያወሩ ነው ፡-

« መቼም ወንድ ሲባል ጠጪ ነው!»

« የኔ በእዛ ላይ መሶብ ገልባጭ ነው!»

* * * *

## ተጨማሪ

አባባል ፡-

- ወንድ ልጅ በመከራ ጊዜው አንድ ሴት ይፈልጋል፡፡ በደስታ ጊዜው ደግሞ ሌላ አንድ ሴት ይፈልጋል፡፡»

* * * *

## ፈውስ ተገኝቷል

የዛሬውን እያደርገውና ከዘመነ ኤድስ በፊት ነው ፡፡ ባሏ ለስራ ጉዳይ ወደ ዋና ከተማው ለመሄድ ሲነሳ፡-

- «ውዴ! እንግዲህ ከመሰነባበታችን በፊት ስራዬን ጨርሼ ስመለስ የማመጣልሽን ስጦታ ንገሪኝ! »
- «ደስ ያሰህን ይዘህ ና፤ ፈጣሪ ይመስገን! ባሁኑ ጊዜ ሁሉንም መፈወስ ተችሏል»

* * * *

## ባሏ የሞተባት ብቻ

የሩሲያውያን አባባል ፡-

- «ባሏ በትክክል የት እንዳለ የምታውቅ ሴት በሞት የተለያት ብቻ ነች »

* * * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## እሁንም ያው ነው !

ልጅ አባቱን ይጠይቃል ፦

- «አባቴ! በድሮ ጊዜ ባል ሚስቱን እስኪያገባት ድረስ አያውቃትም የሚባለው እውነት ነው?»
- «ልጄ! አሁንም እንደዛው ነው! እስኪያገባት ድረስ አያውቃትም!»

* * * *

## ሁለት ማስታወቂያዎች

የመቃብር ሃውልት ላይ ተፅፎ የተገኙ ሁለት ማስታወቂያዎች፦

- «እዚህ ቦታ ላይ የተቀበሩት የ105 አመት ሰድሚ የነበሩቸው አዛውንት ሙሉ ጥርሳቸው በጥሩ ሁኔታ እንዳለ ነበር! እርስዎም እንደሳቸው «ኮልጌትን» ይጠቀሙ!»
- «እዚህ ቦታ ማንም እንዳይቀበር የ«-------------» ኮንዶም ይጠቀሙ!»

* * * *

## ሚስቴ የምትበልጠኝ

ሰውዬው ለጓደኛው፦

- «የኔ ሚስት በትዳር አመራረጥ ብቻ ነው የምትበልጠኝ!»

* * * *

## እስካገኝ

የሚሊዮን ዶላር ሎተሪ ቢደርስህስ?

- «በመጀመሪያ እዳዬን እከፍላለሁ!»
- «የቀረውንስ?»
- «የቀረው ደግሞ ትንሽ ይጠብቅ»



t.me/OLDBOOKSPDF

## ክብሪት ላኪ አላለም

ሴትየዋ ባሏ ከሞተ ከተወሰነ ቀናት በኋላ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ « ሙታን አናጋሪ» ቤት ትሄዳለች። አስፈላጊውን ክፍያ ከፍላ «ሙታን አናጋሪው» የሚያጯጭሰውን አጭሶ አይኑን ጨፍኖ የሚያደርገውን አድርጎ ልክ ሲያበቃ:-

- «እንዴት ነው?»
- «ብዙም ጥሩ አይደለም ቢሆንም ደህና ነው»
- «ስለኔ ጠየቀህ?»
- «ጠይቆኛል!»
- «ስለ ልጆቹስ ጠየቀህ?
- «ጠይቆኛል!»
- «የላከው መልዕክት የለም?»
- «ምንም መልእክት አላከኝም»
- «ምንም ነገር አልጠየቀህም?»
- «ምንም! »
- «ሊሆን አይችልም የኔ ባል ሰው አግኝቶ አንድ ነገር መጠየቁ አይቀርም»
- «አሃ! አዎ ጠይቆኛል! አረስቼው ነው! ሲጋራ አስልክልኝ ብሎኝ ነበር»
- «አየህ ነገረከህ እኮ ባሌን መቼ አጣሁት! ታዲያ ሲጋራውን የት ነው የምልከው?»
- «ምን አውቃለሁ?»
- «እንዴት አታውቅም? አንተ የምር ሙታን አናጋሪ ነህ ወይስ አጭበርባሪ?»
- «ስሚ ሴትዮ! ይሄንን እራስሽ ማወቅ ሲገባሽ ለምን እኔን ትጠይቂኛለሽ?
- ባልሽ ሲጋራ ላኪልኝ እንጂ ክብሪት ላኪልኝ አላለም።»

*  *  *  *



t.me/OLDBOOKSPDF

### ቢዝነስ!

አረብ አገር ውስጥ ሁለት ሰዎች መንገድ ዳር ቁጭ ብለው ከመንገደኛው አርጥባን ይጠብቃሉ:: አንደኛው መስመኛ ካርቶኑ ላይ «አረብ» የሚል ፅሁፍ ፅፎበታል ። ሁለተኛው «አይሁድ» የሚል ፅፎበታል:: «አረብ» ለሚለው መንገደኛው በሙሉ ገንዘብ እየጣለለት ካርቶኑ በገንዘብ ሞልቷል:: «አይሁድ» የሚል ለፃፈው ግን ሳንቲም የወረወረለት አልነበረም:: ይህንን ሁኔታ በማየት ያዘኑ አንዲት አሮጊት ወደ አይሁዱ ጆሮ ጠጋ ይሉና:-

አሮጊቷ- «አንተም ከአጠገብህ እንደሚለምነው ሰውዬ እንድታገኝ ካርቶንህ ላይ «አረብ» ብለህ ፃፍበት» ብለው ሲሄዱ አይሁዱም አጠገቡ ለሚለምነው:-

ስማ አብርሃም! እነዚህ አረቦች ቢዝነስ ሊያስተምሩንም ይፈልጋሉ!

*                    *                    *                    *

### የምሬን ነው ....

ሁለት አዲስ ጓደኞች መንገድ ዳር ቆመው እያወሩ እያለ ድንገት አንደኛዋ:-

«ያንን መርሰዲስ የያዘውን «አዲስ ሩሲያዊ » ልብ ብለሽ እዩው!»

«አየሁት! ምንድነው?»

«እኔ ነኝ ሚሊየነር ያደረግኩት»

«የማይሆን ነገር ባታወሪ ምናለ!»

«የምሬን ነው ከኔጋ ስንገናኝ ቢሊየነር ነበር!»



t.me/OLDBOOKSPDF

# የአጫጭር ቀልዶቹ የትርጉም ምንጭ

- አኒክዶት 2000 ጎዳ ነ .ቪ. ቤሎቭ
  ሚኒስክ 2000

- አኒክዶት ትሬተቫ ትሲቺሌቲያ ነ .ቪ. ቤሎቭ
  ሚኒስክ 2001

- ኢንሳይክሎፒዲያ ሁሊጋንስትቩዩሺኽ …
  ዩሴፍ ራስኪን ምስክቫ 2003

- አኒክዶት ቭፑስክ ቮስሞይ ቪ.ኢ. ሃርኮቨር
  መስክቫ 1994

- ቭኖሽም ስቬቴ /የተለያዩ ቀናት ጋዜጦች/

t.me/OLDBOOKSPDF

To order the book
pls. contact as at
bmoges@aol.com
Tel# 314 363 4626
P.O.Box 28282
St. Lousi MO 63132
U.S.A

Or

fekadeyesus@yahoo.com
Tel. 51 07 34
09-65 08 19
09-68 30 24
Addis Ababa, ETHIOPIA

t.me/OLDBOOKSPDF

ያልፍልናል ብለው ከመላው ዓለም ወደ አሜሪካ የገቡ ዜጎች ህይወት በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ተካቷል:: እያዘንኩ፣ ከፋኝ እያሰብኩ አነበብኩት:: አይ የሰው ልጅ ህይወት! ..... አገኛለሁ ብለው ማጣት ያውም ህይወትን ... አይ የታክሲ ነጂዎች ኑሮ! ማንንም ሰው ቢያነበው ስለ «ምድራዊ ገነት» አሜሪካ ያለውን አመለካከትና ናፍቆት ቆም ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል... ቶንጆ ጽሑፍ... ትረካ... ዕውነት ...

ለሚያስቱ ነገሮች እጅግ ቅርብ ነኝ:: በተለይ በተለይ እንዲህ እንደ መጽሀፉ ተዘጋጅቶ ሲቀርብልኝማ ማንንም ባላናግር ደስታዬ ነው:: ይህን መጽሐፍ ሳነብ አላዋልኩ አላሳደርኩት! ብንያም ሙግጥ አድርጌ ጨረስኩት:: ኗናም ቀና ስል ለአንድ ዘመድ የሚሆን እንባ ፊቴ ላይ ይታይ ነበር ፓፓፓ ..... በጣም ሳቅሁ ::

ደረጀ ኃይሌ
(ኮሜዲያን)

. . . . . . .

ብርሃኑ ሞገስ በአሜሪካ የመጽሔታችን ተባባሪ ዘጋቢ በመሆን የላከልንን በርካታ ጽሑፎቹን ከአንባቢያን ጋር አጣጥመናል:: አሁን ደግሞ የአሜሪካ ታክሲ ነጂዎችን አስገራሚና አዝናኝ አልፎ አልፎም አሳዛኝ የሆነ የህይወት ገጠመኝ በተለመደው ብዕሩ አንካችሁ ብሎናል:: ይህንን አስገራሚ ታሪክ እኔ አንብቤ ሌሎች እንዲያነቡ ያለመንገር ራስ ወዳድነት መስሎኛልና አንብቡት...

ታምራት ኃይሉ
(የቀም ነገር መጽሔት ማኔጂንግ ኤዲተር)

ዋጋው ብር 22.00
t.me/OLDBOOKSPDF
በብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ